# በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጉዳዮች

በማስታወቂያ ሚኒስቴር
የኘሬስና ኦዶቪዥዋል መምሪያ

ግንቦት 1994 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ

ገፅ

## ክፍል አንድ
## ምን አይነት ዴሞክራሲ? ለምን?


1. ዴሞክራሲና የአገራችን ህልውና ..................................... .... 1
   1.1. ዴሞክራሲ ሰላምና የአገራችን ህልውና ...................... 2
   1.2. ዴሞክራሲ፣ ልማትና የአገራችን ህልውና................. 6
   1.3. ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የህልውና ጥያቄ ነው 11
2. የዴሞክራሲያችን መለያ ባህሪያት .................................... 13
   2.1. ዴሞክራሲያችንና የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ .............. 14
   2.2. ዴሞክራሲያችንና የህዝቦች መብት .......................... 23

3. የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን........................ 40


## ክልፍ ሁለት
## የግለሰብ መብቶችና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር


1. የግለሰቦች የጋራ መብቶች ................................................ 42
   1.1. የግለሰብና የጋራ መብቶች ትስስር............................ 42
   1.2. አገራዊ የጋራ አመለካከት መፍጠርና ዴሞክራሲ............ 45

2. የህዝብ ምክር ቤቶችና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ............. 58




ገፅ


   2.1. ምክር ቤቶች በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ
        ያላቸው ሚና .........................................................58
   2.2. በምክር ቤቶች አካባቢ የሚታዩ ጉድለቶች................. 61

3. የህግ አስፈፃሚው አካልና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ........ 69
   3.1. ህግ አስፈፃሚው በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ
        ያለው ሚና ........................................................ 69
   3.2. የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ በዴሞክራሲያዊ
        ስርአት ግንባታ......................................................... 71
   3.3. ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር............................... 82

4. የዳኝነት ስርአትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ................ 87
   4.1. የዳኝነት ስርአቱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ
        ላይ ያለው ሚና..................................................... 87
   4.2. የዳኝነት ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት..................... 89
   4.3. የዳኝነት ስርአቱን የመገንባት ትግል......................... 96

5. የህዝብ ማህበራት የህዝብ ተቋሞችና የዴሞክራሲ
   ስርአት ግንባታ......................................................... 98
   5.1. የፖለቲካ -ርቲዎችና የዴሞክራሲያዊ ስርአት
        ግንባታችን ........................................................ 99
   5.2. ሚድያና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን.........109

ገፅ

5.3. የብዙሃንና የሙያ ማህበራት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ 127

6. የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎና ያልተማከለ አስተዳደር................. 138
6.1. ያልተማከለ አስተዳደር አስፈላጊነት ............................ 138
6.2. የዝቅተኛ አስተዳደር እርከኖች ብቃትና የህዝብ ተሳትፎ. 141
6.3. ያልተማከለ አስተዳደርና አገራዊ መመሪያዎች............. 144

## ክፍል ሶስት
## የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና ዴሞክራሲ

1. የጋራ አላማዎች፣ የጋራ እሴቶችና የብሄር/ብሄረሰቦች መብት 149

2. እኩልነት፣ እኩል ተጠቃሚነት የብሄር/ብሄረሰቦች መብት... 151
2.1. የህዝቦች የእኩልነት መብት...................................... 151
2.2. የህዝቦች እኩል ተጠቃሚነት መብት........................... 165
2.3. የህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያጋጥሙ ችግሮች ................................ 175

3. የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ ............................................................. 180
3.1. አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች..................................................................... 180
3.2. አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና ሲቪል ሰርቪስ ............... 185



ገፅ

3.3. አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና የህግ-አስከባሪ ሃይሎች....... 192

4. የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ.....................................................................200
4.1. አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማና መሰረታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች .......................................... 201
4.2. የካፒታል ነፃ ዝውውርና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ........................................................... 206
4.3. የጉልበት ነፃ ዝውውርና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ ......................................................... 213

# በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጉዳዮች

# ክፍል አንድ

# ምን አይነት ዴሞክራሲ? ለምን?

## 1. ዴሞክራሲና የአገራችን ህልውና፣

የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማየት መላው ህዝባችን ተመኝቷል፣ ታግሏል፣ ብዙዎችም ለዚሁ አላማ መስዋዕት ሆነዋል። በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአትን የመገንባት አላማ የትውልዶች ምኞት፣ ህልምና የትግል አላማ ሆኖ ቆይቷል። ዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው የሚከበርበት ሁኔታ እንዲፈጠር መመኘታቸውም ሆነ ለዚህ የተቀደሰ አላማ መታገላቸው የሚገርም አይደለም። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የህዝብን መብትና ጥቅም ለማስከበር የግድ መሟላት ያለበት ራሱን የቻለ ትልቅ አላማ ነውና። ነገር ግን ዴሞክራሲ በአገራችን ተፈላጊና አማራጭ የሌለው የሚሆነው ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ራሳቸውን የቻሉ ጠቃሚና ተፈላጊ ነገሮች ስለሆኑ ብቻ አይደለም። የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጉዳይ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የህልውና ጉዳይ ስለሆነም ጭምር ነው።



### 1.1. ዴሞክራሲ ሰላምና የአገራችን ህልውና፣

አገራችን ለረጅም ጊዜ በፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ስትማቅቅ የነበረች አገር ነች። ዜጎች መብታቸውንና ጥቅማቸውን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ማስጠበቅ የሚችሉበት ዕድል ተነፍጓቸው የነበሩባት አገር ነች። አንድም የጭቆናውን ቀንበር ተሸክመው መኖር አለያም ቀንበሩን አሽቀንጥሮ ለመጣል ሲሉ ለማመፅ የሚገደዱበት ሁኔታ የተፈጠረባት አገር ነበረች። በአንድ በኩል የጭቆናው ቀንበር በላይ በላዩ እየተከማመረ ዜጎች ተሸክመውት መቆየት የማይችሉበት ደረጃ ላይ የደረሱበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሌላው አለም የተሳካ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስርአት ግንባታ ያካሄዱ አገሮች ያገኙትን ጥቅም በማየት ልባቸው እየማለለ ለስርአቱ ያላቸው ፍላጎትና ጉጉት እየጨመረ ሄዶ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን መሆን ለመዋደቅ ዝግጁ የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። የደርግ አገዛዝ መውደቅ የዚህ ውጤትና መገለጫ ነው።

በደርግ መንግስት ውድቀት ማግስት ለኢትዮጵያ ህዝብ የነበሩት አማራጮች ሁለት ናቸው። የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ተከብሮ፣ ዜጎች ጥቅማቸውንና መብታቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ በማራመድ፣ ጥቅሞቻቸውንና መብቶቻቸውን ለማቻቻል፣ የመደማመጥ፣ የጋራ ጥቅምን የማስቀደምና ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ለመፍጠር የሚያስችል ስርአት መገንባት አንደኛው አማራጭ ነበር። ይህ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርአት

ግንባታ አማራጭ ተግባራዊ ከሆነ በአገራችን አስተማማኝ ሰላም ሊሰፍን የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ አገራችን በማያባራ ቀውስና አለመረጋጋት ውስጥ ልትዘፈቅ የምትችልበት ሁኔታ በቁጥጥር ስር ይገባል፡፡

በደርግ መንግስት ውድቀት ማግስት የነበረው ሌላው አማራጭ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዙን በአንድ ወይም በሌላ መልክ የማስቀጠል አማራጭ ነበር፡፡ ለዘመናት በተከማቸ ጭቆናና በደል እጅግ የተመረረው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የሌሎች አገሮችን ልምድ በማየት ዴሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ለነገ ሳይሆን ለዛሬ ሲመኝ የኖረው ህዝብ ግን ይህንን አማራጭ ሊሸከመው የሚችል አልነበረም፡፡ በደርግ ዘመን በከፍተኛ ደረጃ የተቀጣጠለው አመፅና ጦርነት ቀጥሎና ተባብሶ አገሪቱ ለአጠቃላይ ብተና የምትዳረግበትን ሁኔታ የሚፈጥር አማራጭ ነበር፡፡ በመሆኑም የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር አማራጭ የሰላም፣ አገሪቱን ከማያባራ ጦርነትና ቀውስ የማዳንና ህልውናዋን የማረጋገጥ አማራጭ ሲሆን የፀረ-ዴሞክራሲ አማራጭ ግን ማለቂያ የሌለው ደም መፋሰስና ፍፁም የመበታተን አማራጭ ነው፡፡ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታ ጉዳይ ሰላምን ብሎም የአገራችንን ህልውና የማረጋገጥ ጉዳይ ነው የምንልበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መታፈናቸው በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከብሄር/ብሄረሰቦች መብት መታፈን ጋር በቅርብ የተሳሰረ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ለዘመናት



በተንሰራፋው የፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ሂደት በጭቁን ብሄሮችና ብሄረሰቦች ላይ ይደርስ የነበረው ጭቆናና አድልዎ እየተባባሰ ሄዶ ህዝቦቹ ሊሸከሙት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ ከሌሎች የዴሞክራሲ መብቶች መታፈንና ከሚዘገንን ድህነት ጋር ተደማምሮ የብሄር ቅራኔን እጅግ በጣም ወደተካረረበት ደረጃ ላይ አድርሶት ነበር፡፡ በደርግ መንግስት ውድቀት ዋዜማ ከ17 በላይ የታጠቁ የብሄረሰብ ተቃዋሚ ድርጅቶች በትጥቅ ትግል የሚፋለሙበት ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር፡፡ አገሪቱ ከዳር-ዳር በቅራኔውና ቅራኔው በፈጠረው ጦርነት የምትታመስበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በዚህ ሂደት በአንድ በኩል የህዝቦችን መነጣጠል የሚሰብክ ጠባብነት በሌላ በኩል ጭቆናውና አድልዎው በአንድ ወይም በሌላ መልኩ እንዲቀጥል የሚሻ ትምክህተኛ አስተሳሰብ ስር እየሰደዱና ችግሩን እያባባሱ የመጡበት ሁኔታ ነበር፡፡ ከዚህም አኳያ ሲታይ በደርግ መንግስት ውድቀት ማግስት በጦርነት እጅግ የማቀቀችውና የማሰነችው አገራችን ሁለት አማራጮች ነበሯት፡፡

አንደኛው አማራጭ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታ አማራጭ ነበር፡፡ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማስከበር ላይ የተመሰረተ የህዝቦች እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የማረጋገጥ አማራጭ ነበር፡፡ ህዝቦች የእኩልነት መብታቸውን የሚያስከብሩበት፣ የብሄረሰብ እሴቶቻቸው የሚታወቁበትና የሚከበሩበት፣ በነፃ ፍላጎታቸው በመፈቃቀድና በወንድማማችነት በጋራ የሚኖሩበት፣ ይህ ሳይሆን ሲቀር ሳይናቆሩ፣ ሳይጫረሱ በሰላም የሚለያዩበት የሰላምና

የአንድነት አማራጭ ነበር፡፡ የህዝቦችን እኩልነትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የሚያስከብርና በተሟላ አኳኋን እውን እንዲሆን የሚያደርግ ብሎም አገሪቱን ከጦርነትና ከአጠቃላይ ብተና ለመታደግ የሚያስችል አማራጭ ነበር፡፡

ሁለተኛው አማራጭ የነበረውን የጭቆና ስርአት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ጠጋግኖ የማስቀጠል አማራጭ ነበር፡፡ ብሄረሰቦች ለመብታቸው ትጥቅ አንስተው ይፋለሙ በነበሩባት አገር፣ በጦርነት ማቃና ማስና በነበረች አገር ይህን አማራጭ መከተል ማለት ጦርነቱና ቀውሱ እንዲቀጥል ማድረግና ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ አገሪቱ ለአጠቃላይ ብተናና እጅግ ዘግናኝ ለሆነ የርስ-በርስ እልቂት እንድትዳረግ ማድረግ ማለት ነበር፡፡ የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያና የሶማሊያ እጣ ፈንታ በአገራችን እጅግ በከፋ መልኩ እንዲደገም ማድረግ ማለት ነበር፡፡

በአጠቃላይ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርአት በአገራችን መገንባት ማለት በፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ምክንያት እጅግ በጣም የሰላ ደረጃ ላይ ደርሰው የነበሩትን የተለያዩ ቅራኔዎች በተለይም የብሄር ቅራኔን ማርገብ፣ በሂደትም መፍታት ማለት ነው፡፡ አገራችንን ከቀጣይ እልቂትና ጠቅላላ ብተና መታደግ ማለት ነው፡፡ በአገራችን ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ መፍጠር ማለት ነው፡፡ የአገራችንን ህልውና የማረጋገጥና የማስቀጠል ጉዳይ ነው፡፡



## 1.2. ዴሞክራሲ፣ ልማትና የአገራችን ህልውና፣

አገራችን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዙ በፈጠራቸውና ባባባሳቸው ቅራኔዎች ለረጅም ጊዜ በጦርነትና በተለያዩ የፖለቲካ ቀውሶች ስትታመስ የነበረች በመሆኗ ህዝቧን ከአስከፊ ድህነትና ኋላ-ቀርነት ለማላቀቅ የሚያስችል ስራ መስራት የቻለች አልነበረችም፡፡ ጦርነት እጅግ አውዳሚ የሆነ ክስተት እንደመሆኑ መጠን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የአገራችንን ድህነትና ኋላ ቀርነት በከፍተኛ ደረጃ ሲያባብስ ቆይቷል፡፡ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር በመጥፋቱ አገራችንን ከድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ የሚያስችል የተስተካከለ ፖሊሲ ሊቀረፅና ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም፡፡ ስለሆነም ድህነታችን ከአመት አመት እየተባባሰና እጅግ ውስብስብ እየሆነ ሊሄድ ችሏል፡፡

እጅግ ስር የሰደደና ውስብስብ ምክንያቶች ያሉት የዚሁ ድህነታችን አንዱ መገለጫ የምግብ ዋስትናችን ከጊዜ ጊዜ እየተዳከመ መምጣቱ ነው፡፡ የሰላም፣ የመልካም አስተዳደርና ፖሊሲ እጦት እጅግ ኋላቀር ከሆነ የአስተራረስ ዘይቤና ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዘው ህዝባችን ከአመት አመት በይበልጥ በርሃብ አረንቋ ውስጥ እየሰመጠ እንዲሄድ አድርገዋል፡፡ በኋላ ቀር የአስተራረስ ዘይቤና በህዝቡ ቁጥር መጨመር ሳቢያ አፈራችን ከአመት አመት በከፍተኛ ደረጃ እየተሸረሸረ፣ ደኖች እየተመነጠሩና መታረስ የማይገባቸው መሬቶች ታርሰው ከጥቅም ውጭ እየሆኑ፣ መሬቱ ቁጥሩ እየጨመረ የመጣውን ዜጋ ለማስተናገድ በከፍተኛ ደረጃ እየተሸነሸነና እየተበጣጠሰ ሄዶ

አገሪቱ ዜጎችዋን ለመመገብ ያላት ብቃት ክፉኛ እያሽቆለቆለ ሄዷል፡፡ ከዝናብ መቆራረጥና እጦት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የድርቅ አመታት ለረሃብ የሚጋለጠው የህዝብ መጠን ከአመት አመት እየጨመረ ሄዶ ከአስር ሚሊዮን የማያንስ የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ አንዳንድ ትንበያዎች እንደሚያመለክቱት መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ስራ ካልተሰራ በስተቀር በሚቀጥሉት አስርና ሃያ አመታት ውስጥ ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ ይህ አገራችን መውጫ ወደሌለው የድህነት አዙሪት እየገባች የነበረች መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ሌሎችም በርካታ መገለጫዎች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

አንድ አገር መውጫ ወደሌለው የድህነት አዙሪት ሲገባ፣ ህብረተሰቡ ከዛሬ ነገ ኑሮዬ ይሻሻላል፣ በልቼ የማድርበት ሁኔታ ይፈጠራል ብሎ ተስፋ ማድረጉን ሲያቋርጥ፣ በመቶ ሺዎችና በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በረሃብ እየተገረፉ መጪው ዕድላቸው ሁሉ ጨለማ ሆኖ ሲታያቸው፣ በተስፋ መቁረጥ ላይ ወደተመሰረተ መፍትሄና ፋይዳ ወደሌለው ትርምስና ደም መፋሰስ መግባታቸው አይቀሬ ነው፡፡ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የታዩት ትርጉም የለሽ እልቂቶች አንድ መነሻ የህዝቡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ መሰረት ተንዶ፣ ተስፋ ቆራጭነትና ጨለምተኝነት በህዝቡ ውስጥ መስፈኑ ነው፡፡ ከገባንበት የድህነት አዙሪት በአፋጣኝ መውጣት ካልጀመርን፣ ነገ ከዛሬ እንደሚሻል በተጨባጭ ለማሳየት ካልቻልን፣ ተስፋ ቆራጭነትና ጨለምተኝነት የሚወገዱበት ሁኔታ ካልፈጠርን እኛም



ወደተመሳሳይ ትርጉም የለሽ ትርምስና እልቂት የመግባታችን ጉዳይ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የማይቀር ነው፡፡ እንዲዚህ አይነቱ በጨለምተኝነት ላይ የተመሰረተ የትርጉም አልባ እልቂት እሳት በሚቀጣጠልበት ወቅት የአገራችን ህልውናም አብሮ እንደሚያከትም መገመት አያዳግትም፡፡

ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ብቻውን አገራችንን ከድህነት አዙሪት አውጥቶ በልማት ጎዳና እንድትራመድ ማድረግ አይችልም፡፡ ለዚህ የሰለጠነ የሰው ሃይል፣ ካፒታል፣ ተጨባጭ የልማት እንቅስቃሴና የመሳሰሉት ነገሮችም መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁንና ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር በሌሉበት ሌሎቹ ለልማት ተፈላጊ የሆኑ ነገሮችም አይኖሩም፣ ቢኖሩም አገሪቱን ከድህነት አዙሪት ለማላቀቅ የሚችሉ አይሆኑም፡፡ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አገራችንን ከድህነትና ድህነት ከሚፈጥረው ትርጉም የለሽ ደም መፋሰስና እልቂት ለማላቀቅ፣ በዚሁ ሳቢያ ሊከሰት ከሚችለው አጠቃላይ ብተና ለማዳንና የአገራችንን ህልውና ለማረጋገጥ እጅግ ተፈላጊ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የዜጎችና የህዝቦች መብትና እኩልነትን በማረጋገጥ በአገራችን አስተማማኝ ሰላም ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም መኖሩ አገሪቱን ከድህነት አዙሪት ውስጥ ለማውጣት ተቀዳሚ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የጦርነትና እልቂት ፖለቲካዊ

ምንጮችን በማድረቅ በሰላማዊ ሁኔታ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታን ይፈጥራል:: ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አገራችን ልትለማ የምትችልበትን የተስተካከለ ፖሊሲ ለመቅረፅ ያስችላል:: የህዝቡ ፍላጎት ልማትን ማረጋገጥ በመሆኑ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ሁሉም -ርቲዎች ለልማት ይበጃል ብለው የሚያስቡትን -ሊሲ ለማቅረብ ይገደዳሉ:: ህዝቡም ከሚቀርበው አማራጭ የተሻለ ነው ብሎ የሚያምንበትን ሊመርጥ ይችላል:: በዚህም ዴሞክራሲ በአገራችን ለልማት የሚበጅ ፖሊሲ ሊቀረፅ የሚችልበትን የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል::

የተስተካከሉ የልማት ፖሊሲዎች መቀረፃቸው ለልማት እጅግ ተፈላጊ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ እነዚህን የተስተካከሉ የልማት ፖሊሲዎች ተግባራዊ ማድረጉ ነው:: መላው ህዝብ ከዳር-ዳር ለልማት የሚነሳሳበትና የየበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያበረክትበት አፈፃፀም መኖሩ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሌላ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: ድህነታችንና ኋላቀርነታችን እጅግ በጣም ጥልቅ ነው:: የልማት እንቅስቃሴያችን እጅግ ጥልቅ ከሆነና በየቀኑ ይበልጥ እየተደረመሰ ከሚሄድ ጉድጓድ የመውጣት ያህል እጅግ ከባድ ርብርብ የሚጠይቅ እንቅስቃሴ ነው:: እንኳንስና የመላው ህብረተሰብ ርብርብ ሳይታከልበት፣ መላው ህዝብ በላቀ ደረጃ ተሳትፎበትም ቢሆን በቀላሉ የሚሳካ ነገር አይደለም:: የድህነታችን ምንጮች እጅግ የተወሳሰቡና የተጠላለፉ በየጊዜውም በይበልጥ የሚወሳሰቡ በመሆናቸው የልማት ስራችን የመላው ህዝብ የላቀ ተሳትፎ ሳይታከልበት



በምንም መልክ ሊሳካ አይችልም:: የልማት እንቅስቃሴያችን አፈፃፀም የተሳካ ሊሆን የሚችለው መላው ህብረተሰብ በመሰረታዊ የልማት ጉዳዮችና አላማዎች ላይ አንድ የጋራ አቋምና አመለካከት ኖሮት (ናሽናል ኮንሰንሰስ ተፈጥሮ) በዚሁ ዙሪያ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ድርሻ በብቃት መወጣት ሲችል ነው:: እንደዚህ አይነቱ ተሳትፎ ባለበትም ወቅት የልማት ትግሉ አስቸጋሪና ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ አይቀርም::

የዴሞክራሲ ስርአት በመሰረታዊ የልማት ጉዳዮች ላይ በሰፊው ለመወያየት፣ ለመከራከርና ጠቃሚውን ከጎጂው ለማንገዋለል የሚያስችለን ፖለቲካዊ ሁኔታ ይፈጥርልናል:: ተጨባጭ የልማት ስራዎቻችንን ግልፅና ገንቢ በሆነ አኳኋን ለመገምገም፣ ከልምዳችን ተምረን ጠቃሚውን ለማጎልበትና ጎጂውን ለማስወገድ ሰፊ ዕድል ይሰጠናል:: በምንከተላቸው የልማት ፖሊሲዎች ዙሪያ በሚካሄድ ክርክርና ውይይት፣ የፖሊሲዎችን አፈፃፀም መሰረት በማድረግ በሚካሄድ ልምድ የመቀመር ስራ አማካኝነት አንድ የጋራ አመለካከትና እምነት ለመያዝ ያስችለናል:: በዚህ የጋራ እምነትና አመለካከት ዙሪያ እያንዳንዱ ሰው የበኩሉን አስተያየት ለመሰንዘር፣ የበኩሉን የስራ ድርሻ እንዲፈፅም ለማድረግ የሚያመች ሁኔታ ይፈጥራል:: የልማት ስራችን ከየአቅጣጫው የሚሰባሰቡ ገባር ወንዞች አጠናክረውት ትልቅ ጎርፍ እንደሚሆን ወንዝ ይሆናል:: ሁላችንም በአንድ በመሰረታዊ የልማት አላማ ዙሪያ ተሰባስበን ድርሻችንን ለመፈፀም የምንችልበት አገር አቀፍ የልማት ጎርፍ መፍጠር ያስችለናል::

በመሆኑም የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርአት መኖሩ የጦርነትና የብተና ፖለቲካዊ ምንጮችን በማድረቅ፣ ለሰላምና ልማት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር፣ ለልማት የሚበጁ የተስተካከሉ ፖሊሲዎች ሊቀረፁ የሚችሉበት ሰፊ በር በመክፈት፣ ህብረተሰቡ በተስተካከሉ የልማት ፖሊሲዎች ዙሪያ አንድ አይነት የጋራ አመለካከትና እምነት እንዲይዝ፣ ህብረተሰቡ ከዳር-ዳር እንዲነሳሳ ስለሆነም የልማት ትግሉ አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን በማድረግ አገራችን ከድህነት አዙሪት የምትወጣበትን ቅድመ-ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ መውጫ በሌለው የድህነት አዙሪት ውስጥ በመግባት የሚፈጠረው ተስፋ ቆራጭነትና ጨለምተኛነት የሚያስከትሉትን የፋይዳ የለሽ ጦርነትና እልቂት አደጋ ብሎም የአገራችንን ጠቅላላ የመበታተን አደጋ ለመከላከል ያስችላል፡፡ በዚህም መልኩ ሲታይ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጉዳይ የአገራችን የህልውና ጉዳይም ጭምር ይሆናል፡፡

## 1.3. ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የህልውና ጥያቄ ነው፡፡

በደርግ መንግስት ውድቀት ማግስትና በዋዜማው አገራችን ለማያባራ ጦርነት እልቂትና ጠቅላላ ብተና የተመቻቸች ነበረች፡፡ ብዙ ታዛቢዎች የቀድሞዋን ዩጎዝላቪያ ሁኔታ እያዩና ሂደቱን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያያያዙ በማየት ከቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ እጅግ የባሰ ደም መፋሰስና ጠቅላላ መበታተን በኢትዮጵያ ውስጥ ይከሰታል ብለው ተንብየው ነበር፡፡ አገራችን በዜጎችና ህዝቦች መብት መታፈን በተፈጠረውና በተባባሰው ቅራኔ ምክንያት አገራችን በአስከፊ ጦርነት ውስጥ



ተዘፍቃ ክፉኛ የማሰነችበት ሁኔታ ውስጥ ባለችበት ወቅት የቀረበ ትንበያ ስለነበር ይህን ያህል መስመር የለቀቀ ትንበያ ነበር ማለትም አይቻልም፡፡ ለዘመናት ስር እየሰደደና እየተወሳሰበ የመጣው ድህነት ከጦርነቱ ጋር እየተመጋገበ አገራችንን ወደመጨረሻው የጥፋት ጠርዝ ላይ ባደረሰበት ወቅት የተደረገ ትንበያ ስለነበር ይህን ያህል ዕንፈኛ ትንበያ ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በመገንባት የጦርነቱን ፖለቲካዊ ምንጭ ማድረቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ካልተቻለ እውን መሆኑ በፍፁም የማይቀር ትንበያ ነው የነበረው፡፡ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጉዳይ በአገራችን የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ህዝቡን ከአስከፊ እልቂት፣ አገሪቱን ከጠቅላላ ብተና የመታደግ ጉዳይም ጭምር መሆኑን የሚያረጋግጥ አጋጣሚ ነበር፡፡

በእርግጥ ጉዳዩ የምርጫ ጉዳይ ብቻም ቢሆን ኖሮ ምልአተ-ህዝቡ ከፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ይልቅ ዴሞክራሲን እንደሚመርጥ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለውም፡፡ ምርጫውን ለረጅም ጊዜ ዴሞክራሲን ለማስፈን ባደረገው መራራ ትግል አረጋግጧልና፡፡ ይሁንና በአገራችን ሁኔታ የዴሞክራሲ ስርአት የምርጫ ጉዳይ ብቻም አይደለም፡፡ የህልውና ጉዳይም ጭምር ነው፡፡ አንድም የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስርአት እንገነባለን፣ የእልቂት ፖለቲካዊ ምንጮችን በማድረቅና የእልቂት ኢኮኖሚያዊ ምንጭን ለማድረቅ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር በመቻል ህዝባችንን ከእልቂት፣ አገራችንን ከጠቅላላ ብተና ለመታደግ እንዲሁም፣ ህልውናችንን ለማረጋገጥ ዕድል

ይኖረናል፡፡ አለያም የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርአት መገንባት ተስኖን እጅግ ዘግናኝ በሆነ እልቂት ተንጠን ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ እንበታተናለን፡፡ ህልውናችንን ለማረጋገጥ ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ ውጭ አማራጭ የለንም፡፡ በዚህ አላማ ላይ መንሸራተትን፣ ወደኋላ መመለስን፣ ሽንፈትን መቀበል አይቻልም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሽንፈት ማለት እንኳንስ ለመሸከም ለማሰብም የሚከብድ ጥፋት የሚያስከትል ነገር ማለት ነውና፡፡

በመሆኑም እኛ ከማንም በላይ ለህልውናችን ስንል፣ ከጠቅላላ ጥፋት ለመዳን ስንል ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ መዋደቅ አለብን፡፡ እኛ ከማንም በላይ የዴሞክራሲ ባህልና ተቋሞች ባልነበሩበት፣ ከዴሞክራሲ አኳያ ምድረ-በዳ በሆነችው አገራችን የዴሞክራሲን ስርአት ለመዝራት፣ ለማብቀልና ፍሬውንም ለመሰብሰብ የሚያስችለን በጥንቃቄ የተመረጠና ትክክለኛ አቅጣጫ መቀየስ መቻል አለብን፡፡ እኛ ከማንም በላይ ለህልውናችን ስንል የተስተካከለ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታ አቅጣጫ ቀይሰን በዙሪያው ተሰባስበን ለተግባራዊነቱ እንደ አንድ ሰው ተባብረን መቆም አለብን፡፡ በዚህ የህልውና ጉዳይ ላይ ሽንፈትን መቀበል አንችልምና፡፡

## 2. የዴሞክራሲያችን መለያ ባህሪያት፣

በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት ማዕቀፍ ውስጥ የሚገነቡት



የዴሞክራሲ አገዛዞች በመሰረታዊ ባህሪያቸውና ይዘታቸው አንድ ናቸው፡፡ እኛም የምንገነባው የዴሞክራሲ ስርአት በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት ማዕቀፍ ውስጥ የሚገነባ በመሆኑ በመሰረታዊ ይዘቱና ባህሪው ከሌሎች መሰል ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች የሚለይ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ህገ-መንግስታችንን ያነበበ ማንኛውም ሰው እጅግ የሚበዙት የህገ-መንግስቱ አንቀፆች ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስታት አንቀፆች ጋር አንድና ያው መሆናቸውን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህ መሰረታዊ ሃቅ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ አገር የሚገነባውን የዴሞክራሲ ስርአት፣ ከአገሩ የልማት ደረጃና ታሪክ፣ ከህብረተሰቡ አኗኗርና አደረጃጀት ጋር ማጣጣም ይኖርበታል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ወቅትም የሚገነባው የዴሞክራሲ ስርአት የራሱ የሆኑ ልዩ ባህሪያት መያዙ የማይቀር ይሆናል፡፡ በመሆኑም እኛ የምንገነባው የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርአት በመሰረታዊ ይዘቱ ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ጋር አንድ የሆነ ነገር ግን ከአገራችን ልዩ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ምክንያት የራሱ የሆኑ ልዩ ባህሪያትም ያሉት መሆኑ አይቀርም፡፡ ማንኛውም ህገ-መንስታችንን ያነበበ ሰው የምንገነባው የዴሞክራሲ ስርአት ሁለት መለያ ባህሪያት እንዳሉት መገንዘብ ይችላል፡፡

### 2.1. ዴሞክራሲያችንና የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ፣

የአገራችን ህገ-መንግስት የህዝብ ሉአላዊነትን መርህ በሚያብራራበት አንቀፅ 8 ላይ በሶስተኛው ንኡስ አንቀፁ የሚከተለውን ያስቀምጣል፡፡ “ሉአላዊነታቸውም የሚገለፀው በዚህ

ህገ-መንግስት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል፡፡” ህገ-መንግስታችን እንደሌሎች ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስቶች ሁሉ ህዝቡ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆኑን፣ ሉአላዊነት ሲባል የጋራ ሸንተረሩ፣ የወንዙ ወዘተ. ሉአላዊነት ሳይሆን የህዝብ ሉአላዊነት መሆኑን ይገልፃል፡፡ እንደሌሎች ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስቶች ሁሉ የኛም ህገ-መንግስት የህዝብ ሉአላዊነት በዴሞክራሲያዊ አኳኋን በሚመርጣቸው ተወካዮች አማካኝነት እንደሚገለፅ ያስቀምጣል፡፡ ዴሞክራሲያችን በህዝብ ተወካዮች ላይ የሚመሰረት የዴሞክራሲያዊ ውክልና (ሬፕሬዜንታቲቭ ዴሞክራሲ) ስርአት መሆኑን ያሰምርበታል፡፡ ይሁንና ህገ-መንግስታችን ከብዙዎቹ ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስቶች በተለየ አኳኋን በውክልና ዴሞክራሲ ላይ ብቻ ሳይወሰን የህዝብ ሉአላዊነት በቀጥታ በሚያደርገው ተሳትፎም መገለፅ እንዳለበት ያሰምርበታል፡፡ ዴሞክራሲያችን የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ መሰረት ያደረገ (ዳይሬክት ዴሞክራሲ) እንደሆነም፣ ሁለቱን ባህሪያት አጣምሮ የያዘ መሆን እንዳለበትም ያስቀምጣል፡፡

በርግጥ ህዝቡ ተወካዮቹን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን በመምረጥ የሚፈለገውን መንግስት ሹሞ የማይፈልገውን መሻር እስከቻለ ድረስ ሉአላዊነቱና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎው ተረጋግጧል ሊባል ይችላል፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት በተራዘመ ታሪካዊ ሂደት በተገነባባቸው አገሮች የውክልናው ጉዳይም ቢሆን ደረጃ በደረጃ የተፈፀመ ጉዳይ ነው የነበረው፡፡ በፆታ፣ በንብረት፣ በትምህርት ወዘተ. ምክንያት አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል



ከመመረጥ ወይም ከመምረጥና መመረጥ መብት ተገልሎ ለረጅም ጊዜ የሚቆይበት፣ ውክልናው በተግባር ብቻ ሳይሆን በህግም የጥቂቶች ሆኖ የሚቆይበት ሂደት ነው የነበረው፡፡ ስለሆነም ይህን ሂደት አሳጥሮ ሁሉም ህዝብ መምረጥም መመረጥም ይችላል ማለቱ ራሱ ትልቅ ርምጃ ነው፡፡ መላው ህዝብ መምረጥና መመረጥ ይችላል በተባለበት ወቅትም ቢሆን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የህዝቡ ክፍል ከፖለቲካ ተገልሎ በምርጫዎች ላይ ሳይሳተፍ የሚቀርበት ሁኔታ እያለ ውክልናውን ከማጠናከር አልፎ ስለቀጥተኛ ተሳትፎ ማሰብ ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር ማንሳት ይቻላል፡፡ የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ብሎ ነገር ለማለቱ ያህል የሚቀርብና ተግባራዊ የማይሆን ነገር ተደርጎም ሊወሰድ ይችላል፡፡

ህገ-መንግስታችን ህዝቡ በቀጥታም መሳተፍ አለበት ሲል መላው ህዝብ በውክልና የሚያደርገው ተሳትፎ ያለውን ዴሞክራሲያዊ ፋይዳ አሳንሶ በማየት፣ ወይም ይህንኑ የማጠናከርና ስር እንዲሰድ የማድረግ አስፈላጊነትን በመካድ አይደለም፡፡ የውክልና ዴሞክራሲ አንዱ የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫና ቁልፍ የአፈፃፀም ገፅታው እንደሆነና መሆንም እንደሚገባው እሙን ነው፡፡ በውክልና የሚያደርገው ተሳትፎ እንዲጠናከርና ስር እንዲሰድ የማድረጉ ስራ እራሱ ከባድና ጊዜ የሚጠይቅ፣ ውስብስብ ትግል የሚካሄድበት ከፍተኛ ስራ መሆኑም አያጠያይቅም፡፡ ህገ-መንግስታችንም ይህንን በመገንዘቡ ነው ቀጥተኛ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲ አንዱ የህዝቡ የሉአላዊነት መገለጫ ነው ይላል፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የዴሞክራሲ ስርአትን

እውን ለማድረግ፣ የውክልናውን ስርአት እውን ከማድረግና ከማጠናከር ጎን ለጎን ህዝቡ በቀጥታም ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ እጅግ ተፈላጊ ነው ብሎ ስላመነ ነው የቀጥተኛ ተሳትፎን ጉዳይ አበክሮ ያነሳው፡፡

ህገ-መንግስቱ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ጉዳይ አበክሮ ያነሳው ለህዝቡን ተግባራዊ ሊሆን የማይችል የህልም እንጀራ ለመመገብም አይደለም፣ በስርአታችን አወቃቀርና አሰራር ላይ ተጨባጭ ተፅእኖ የሚያስቀምጥ አቅጣጫን ለመቀየስ እንጂ፡፡ ህገ-መንግስቱ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ጉዳይ አበክሮ ያነሳው አንዳንዶቹ ለድሃው ህብረተሰብ ካላቸው ወገንተኝነት በመነሳት ነው ስላሉት ብቻም አይደለም፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ዴሞክራሲ የእልቂት ፖለቲካዊ ምንጮችን በማድረቅና የእልቂት ኢኮኖሚያዊ ምንጮች የሚደርቁበት የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር ለአገራችን ህልውና መረጋገጥ መጫወት የሚገባውን ሚና ሊጫወት የሚችለው፣ ስርአቱ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ባካተተ መልኩ ሲገነባ መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡ ይህ የሚሆንባቸው በርካታ ተጨባጭነት ያላቸው ምክንያቶች እንዳሉ በመገንዘቡ ነው፡፡

የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርአት በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ የሚሆነው ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ተቋሞችና ድርጅቶች በተፈጠሩበትና በተጠናከሩበት፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የዴሞክራሲ አስተሳሰብና ባህል በዳበረበት ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም በብዙዎቹ



የዳበረ የዴሞክራሲ ስርአት ባላቸው አገሮች በተራዘመ የታሪክ ሂደት እንደዚህ አይነቱን ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡ በተራዘመው ሂደት መጀመሪያ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባለው የህብረተሰብ ክፍል፣ ቀጥሎ ደረጃ በደረጃ ወደህዝቡ የወረደ፣ በብዙ ውጣ ውረድ የተፈጠረ የዴሞክራሲ ባህል እውን ሆኗል፡፡ አገሮች በሚመሩባቸው መሰረታዊ መርሆዎች በህገ-መንግስታዊ ስርአቱ ላይ እጅግ የሚበዛው ህዝብ አንድ አይነት የጋራ አቋም ለመያዝ ችሏል፡፡ ልዩነቶችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ፣ በውይይት፣ በህዝብ ውሳኔ፣ በምርጫ መንገዶች ብቻ የመፍታት ባህል ዳብሯል፡፡ እንደዚህ አይነቱ መሰረታዊ የአመለካከት፣ የእምነትና የባህል አንድነት መሰረት በጣለበት ሁኔታ የሚፈጠሩት ልዩነቶች መለስተኛና በዴሞክራሲያዊ አኳኋንና በመቻቻል የሚፈቱ፣ ስርአቱን ለቀውስና ለአደጋ የማያጋልጡ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ በተመሳሳይ  መልክ በተራዘመ የታሪክ ሂደት የተፈጠሩ የመንግስት ተቋሞች -ርቲዎች፣ ማህበራት፣ ሚድያ ወዘተ. የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም በዳበረ አኳኋን ማራመድ የሚችሉ፣ በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ አንድ አይነት አመለካከትና እምነት ያላቸው፣ በዚህ ላይ ተመስርተው በጋራ የሚሰሩና መለስተኛ ልዩነቶቻቸውን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ለመፍታት የሚችሉ ሊሆኑ ሆነዋል፡፡

በአገራችንም የዴሞክራሲ ስርአት ስር ሊሰድና ሊዳብር የሚችለው በተመሳሳይ መልኩ በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ ህብረተሰቡ አንድ አይነት የጋራ እምነት የሚይዝበት፣ በዚህ ላይ ተመስርቶ በጋራ እምነቶቹ ዙሪያ አብሮ የሚሰራበት፣

መለስተኛ ልዩነቶች ስርአቱን ለቀውስና ለአደጋ ሳያጋልጡ በዴሞክራሲያዊ አኳኋንና በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ብቻ የሚፈቱበት ባህል የሚዳብርበት፣ የዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ተቋሞችና ድርጅቶች በዚሁ መንፈስ የሚዳብሩበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው:: ነገር ግን አገራችን ይህን ሁኔታ እጅግ በተራዘመ ሂደት ለመፍጠርም በተመቻቸና በቀለለ ሁኔታ ላይ አይደለችም:: የዴሞክራሲ ጉዳይ በአገራችን የነብስ አድን እንቅስቃሴ ጉዳይም ጭምር ስለሆነ በተፋጠነ ሂደት መጠናቀቅ አለበት፣ አለበለዚያ አገራችን ከጥፋት መዳን አትችልም::

የዴሞክራሲ አገዛዝ በአፋጣኝ ስር እንዲሰድ፣ እምነቱና ተቋሞቹ እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ከተፈለገ መላው ህብረተሰብ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴው ውስጥ በስፋትና በቀጥታ መሳተፍ አለበት:: በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ የጋራ እምነት ለመፍጠር የሚነሱ ተቋሞችና ስልቶችን በሙሉ በማቀናጀት ከመጠቀም በተጨማሪ በዚህ ጉዳይ ላይ መላው ህዝብ በየደረጃው ተሳታፊ እየሆነ ከዴሞክራሲው በቀጥታ መጠቀምና መቋደስ መቻል አለበት:: የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባት በሚደረገው የለት-ተዕለት ትግል በቀጥታ ተሳታፊ እየሆነ ከልምዱ መማር፣ ጉድለቶችን እያስተካከለ ጠንካራ ጎኖችን እያጎለበተ ከስርአቱ በቀጥታ ተጠቃሚ መሆን አለበት:: በዚሁ ሂደት መላው ህዝብ በተፋጠነ ሂደት ዴሞክራሲ ከሚያስገኝለት መብትና ጥቅም ተቋዳሽ እየሆነ፣ ከልምዱ፣ ከውይይቱና ከክርክሩ እየተማረና የዴሞክራሲ ባህሉን እያጠናከረ ለዴሞክራሲ የተመቻቸ ሁኔታ በአፋጣኝ ሊፈጠር ይችላል:: የዴሞክራሲ



ተጠቃሚ፣ ጠበቃና ጠባቂ የሆነ ሰፊ ህብረተሰባዊ ሃይል በመፍጠር ታዳጊው ስርአት በእንጭጩ እንዳይቀጭና የአገራችንም ህልውና አብሮ እንዳያከትም ለማድረግ ይቻላል::

በአገራችን የሚገነባው የዴሞክራሲ ስርአት በመሰረቱ በዋና ከተማ ላይና ከፍተኛ ቦታ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የታጠረ ከሆነ በእንጭጩ እንደሚቀጭ ምንም ጥርጥር የለውም:: እነዚህ ክፍሎች በሚያደርጉት የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል ያልገራው ሽኩቻ የሩቅ ተመልካች የሆነው ህዝብ ግፋ ቢል ታዛቢ የሚሆንበት አለያም የአንዱ ወይም የሌላው ቡድን መሳሪያ በመሆን ተገድቦ አገሪቱ በቀጣይ ቀውስ መናጧ የማይቀር ይሆናል:: ዴሞክራሲ በአገራችን እየወደቀ እየተነሳ ያድጋል እንዳይባል አንዴ በእንጭጩ ከተቀጨና ውድቀትና ሽንፈት ካጋጠመው ተመልሶ የመነሳት ዕድል የሌለው ይሆናል:: ሽንፈት ማለት በተጨባጭ እልቂትና ብተና ማለት ነውና:: ስለሆነም ህዝቡ በሰፊውና በቀጥታ እንዲሳተፍ ማድረጉ ራሱን ችሎ የሚቆም ተፈላጊ አላማ ቢሆንም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ዴሞክራሲያችን በእንጭጩ እንዳይቀጭ፣ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲዳብርና ስር እንዲሰድ ለማድረግም እጅግ ተፈላጊ ነው::

እንደሚታወቀው ሁሉ የአገራችን ድህነትና ኋላ ቀርነት እጅግ የከፋ ስር የሰደደና የተወሳሰቡ ምንጮች ያሉት ነው:: የተስተካከለ የልማት አቅጣጫ ተይዞ መላው ህብረተሰብ ድህነትን ለመዋጋት ከዳር-ዳር በሚነቃነቅበትም ወቅት ቢሆን ከፍተኛ ትግልና ጊዜ የሚጠይቅ ስራ መሆኑ የማይቀር ነው:: ይህ በሌለበት

ሁኔታ ከአዙሪቱ መውጣት አይቻልም፣ ህዝባችን ለከፍተኛ አደጋ መጋለጡ አይቀርም። ምልአተ-ህዝቡ በልማት ተግባር ላይ ከዳር-ዳር እንዲንቀሳቀስ ከተፈለገ ከሚገኘው ልማት በቀጥታ ተጠቃሚ መሆን አለበት። ፖሊሲዎችን ለመቀየስ በሚደረገው ውይይት ክርክር በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ጥቅሙን የሚያስጠብቁለት ፖሊሲዎች እንዲቀረፁ ማድረግ መቻል አለበት። በአፈፃፀም ሂደቱም ከልምዱ እየተማረ ማስተካከል መቻል አለበት። በውይይትና በተግባር ፖሊሲዎቹ በርግጥም የሚጠቅሙት መሆናቸውን መገንዘብና ማመን አለበት። ይህ ሳይሆን በሙሉ ልብ በልማት ተግባር ላይ በመሳተፍ አገሪቱንና ራሱን ማዳን አይችልም። በሌላ አነጋገር በዴሞክራሲያዊ ሂደት በቀጥታና በሰፊው ተሳታፊ ካልሆነ በስተቀር በልማቱ መስክ እንዲጫወት የሚፈለገውን ሚና መጫወት አይችልም። በአገራችን ዴሞክራሲ አንድ ተጨባጭ የልማት ሃይል በመሆን ማገልገል አለበት ያልነው ጉዳይ በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ መሆን አይችልም። ስለሆነም የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ካለው አጠቃላይ ተፈላጊነት በተጨማሪ የድህነትና ኋላ-ቀርነት አዙሪትን በመበጠስ ህዝባችንን ከጥፋት ለመታደግ የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያችን መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

የበለፀገ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚና የዳበረ ዴሞክራሲ ባለበት አገር የፖለቲካ -ርቲዎች የአንድ ወይም የሌላውን የህብረተሰብ ክፍል መብትና ጥቅም ወክለው ይቆማሉ። በሚነሱት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ለቆሙለት የህብረተሰብ ክፍል ይጠቅማል ብለው የሚያስቡትን ሃሳብ በአግባቡ ተንትነው አጥብቀው



ይከራከራሉ። በተጨባጭ የዚያ ክፍል ተወካዮች ይሆናሉ። በ-ርቲዎች መካከል የሚደረግ ትግልና ድርድር በርግጥም ከ-ርቲዎች በስተጀርባ ያሉ ሃይሎች የሚያደርጉት ትግልና ድርድር ነው ሊባል ይችላል። ከዚህም አኳያ የግለሰብ ዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ይህን ያህል ወሳኝ ነው ላይባል ይችላል።

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከህዝቡ ወደ 85% የሚሆነው አርሶ አደር ነው። በአርሶ አደሩ መካከል በአሁኑ ወቅት ይህ ነው የሚባል የጥቅምም ሆነ የመብት ግጭትና ልዩነት የለም። አንድ ድርጅት የአርሶ አደሩን መብትና ጥቅም ማስጠበቅን በዋነኛ አላማነት ይዞ ከተነሳና በአርሶ አደሩም ተቀባይነት ካገኘ በፖለቲካ ሂደቱ ላይ ወሳኝ ተፅእኖ ማሳረፍ የሚችል ይሆናል። ከዚህ ውጭ ያለው የ-ርቲዎች ቦታ እጅግ ጠባብና የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ በቂ ዕድል የማይከፍት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ብዙዎቹ -ርቲዎች አዳዲስ በመሆናቸውና የየትኛውንም የህብረተሰብ ክፍል መብትና ጥቅም በብቃት መወከል ያልቻሉ፣ በግለሰቦች ዙሪያ ወይም በጋራ ቅሬታ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሆነው ይገኛሉ። የፖለቲካ ድርጅቶች በዚህ መልኩ እጅግ ደካማ በሆኑበት ወቅት ከነሱ ባሻገር ሄዶ እያንዳንዱን የህብረተሰብ ክፍልና ዜጋ በብቃት ማሳተፍ አማራጭ የሌለው ይሆናል። የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ እጅግ በጣም ተፈላጊ የሚሆንበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው።

ዴሞክራሲያችን የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት ማለት ብቻውን በቂ ሊሆን አይችልም።

ይህ በስርአቱ አደረጃጀትና አሰራር ላይ ተጨባጭ የሆነ ተፅእኖ እንዲያሳርፍ ካልተደረገ በስተቀር ባዶ ቃላት ከመሆን አይዘልም:: ህገ-መንግስታችን ይህንኑ በመገንዘብ ይህ መርህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልባቸውን መሰረታዊ አቅጣጫዎች ጠቁሟል:: በዚህ ፅሁፍ ተከታይ ክፍሎች የመርሁን አፈፃፀም የምንመለከትበት ይሆናል:: እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ ዴሞክራሲያችን በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ የፖለቲካ ድርጅቶች ከራሳቸው አመለካከት በመነሳት ተፈላጊ ነው ከሚሉበት ምክንያት ባሻገር ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች በሚመነጩ መሰረታዊ ምክንያቶችም እጅግ ተፈላጊ ጉዳይና አንድ የዴሞክራሲያችን መለያ ባህሪ መሆኑ ነው::

## 2.2. ዴሞክራሲያችንና የህዝቦች መብት፣

ህገ-መንግስታችን ካስቀመጣቸው መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ የህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ጉዳይ ነው:: ህገ-መንግስታችንን የሚቃወሙት ወገኖች የሚያተኩሩት ይህንን መብት በሚዘረዝረው የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 39 ላይ ነው:: ህገ-መንግስቱን ከሚቃወሙትም ሆነ ከሚደግፉት የዚሁ መርህ መሰረታዊ ይዘትና ህገ-መንግስታችን ከዚህ አኳያ የሚያስቀምጣቸው ነጥቦችን በተሟላ መልኩ ያልተገነዘቡ ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል:: ህገ-መንግስቱን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያያያዙ ለመገንዘብ የሚቸገሩ ሰዎች እንዳሉም እሙን ነው:: ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ ህገ-



መንግስታችን የሚያስቀምጠውን መሰረታዊ አቅጣጫ በይበልጥ ለመረዳት የጉዳዩን ታሪካዊ አመጣጥ በአጭሩ መቃኘት ያስፈልጋል::

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄር/ብሄረሰቦች አገር ሆና ለብዙ ዘመናት ቆይታለች:: በብሄር-ብሄረሰቦቹ መካከል የሚፈጠረው አስተዳደራዊ ግንኙነት በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ የመጣ ቢሆንም በመሰረታዊ ይዘቱ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ነው የነበረው:: ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ትስስሮች በይበልጥ እየጠበቁ በሄዱ ቁጥር የህዝቦቹ ትስስር ኢ-ዴሞክራሲያዊ ገፅታም እየተጠናከረ ነው የሄደው:: ህዝቦች አንድነታቸውና ወንድማማችነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የየራሳቸው ቋንቋ ባህል፣ ታሪክ ወዘተ. የሚታወቅበትና የሚከበርበት ዕድል ተነፍጓቸው ነው የነበረው:: የተለያየ ባህል ቋንቋ ወዘተ. ያላቸው ህዝቦች መኖራቸው የህዝባዊ አንድነታችን ጥንካሬ ምንጭ ሳይሆን የአንድነታችን ፀር ተደርጎ ሲወሰድ ኖሯል:: ስለሆነም ህዝቦች በቋንቋቸው በባህላቸው ወዘተ. እንዳይጠቀሙ፣ በዚሁ እንዳይኮሩ ለማፈንና በአስተዳደራዊ መንገድ ብሄረሰባዊ እሴቶቻቸውን እንዲያጡ ለማድረግ ነው የተሞከረው:: የአገራችን ባህል ቋንቋ ወዘተ. እነዚህን ብሄረሰባዊ እሴቶች በሙሉ ያጣመረ እጅግ የበለፀገ ሊሆን ሲችል ያ ሁሉ ጠፍቶ በአስተዳደራዊ መንገድ አንድ ቋንቋ፣ ባህል ወዘተ. እንዲኖረን ለማድረግ ነበር የተጣረው:: አንድነታችን ህዝቦች ባላቸው የጋራ አላማና ጥቅም፣ ባላቸው የወንድማማችነት መንፈስ ላይ ሳይሆን፣ ነባራዊ ህልውና ያላቸውን ብሄር/ብሄረሰቦች እንደሌሉ በመቁጠር ወይም እንዳይኖሩ በማድረግ ላይ

መመስረት እንዳለበት ነበር የታመነው::

የዜጎችን መብትና እኩልነት ያፈኑ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዞች የህዝቦችን መብትና እኩልነት ሊያከብሩ አይችሉምና፣ ህዝቦች እኩልነታችን ይከበር፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ይኑረን ሲሉ ያለፉት ገዥዎች ግን በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲያቸው አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች አድርገው ለማቅረብ ነበር የሞከሩት:: በርግጥ ማንኛውም ህዝብ በተግባር የበላይ የሆነበት ሁኔታ አልነበረም፣ ሊኖርም አይችልም:: ሁሉም ህዝቦች በተለያየ መልክ ሲጨቆኑና ሲመዘበሩ የነበሩ ናቸው:: በተጨባጭ የበላይ የነበሩት በህዝቦች ስም የሚነግዱት ጥቂት ገዥዎች ነበሩ:: ይሁንና ህዝቦች በብሄረሰብ እሴቶቻቸው እኩል እንዳይጠቀሙ መደረጉ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አንድነት እንዳይኖር አድርጓል:: በአገራችን የብሄር/ብሄረሰብ ቅራኔ እንዲፈጠር ያደረገው መሰረታዊ ነገር ይህ የጭቆና የአድልዎና የፀረ-ዴሞክራሲ አቅጣጫ ነው::

የአገራችን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ የፈጠረውን የብሄር ቅራኔ የህዝቦችን የተናጠልና የጋራ ጥቅም በሚያስጠብቅ ዴሞክራሲያዊ አኳኋን ከመፍታት ይልቅ በተሳሳተ አቅጣጫ ለመፍታት ጥረት ያደረጉ የተለያዩ ሃይሎች ቅራኔውን ባይፈጥሩትም እንዲባባስ በማድረግ ላይ የበኩላቸውን ሚና እንደተጫወቱም ግልፅ ነው:: በአንድ በኩል በጭቁን ብሄረሰቦች ላይ የሚደርሰውን በደል እናስወግዳለን ብለው ከተነሱ ወገኖች ጠባብ አስተሳሰብ የነበራቸው ክፍሎች የቅራኔውን አመጣጥና



ትክክለኛ አፈታት ስተው በህዝቦች መካከል መቃቃርን ሊፈጥሩ የሚችሉ ስራዎች ሰርተዋል:: ችግሩ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዳይፈታና ህዝቦች በነፃ ፍላጎታቸው በመፈቃቀድ አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ጥረት አድርገዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ለህዝቦች አንድነት ቆመናል ከሚሉት ወገኖች ትምክህተኛ አስተሳሰብ የነበራቸው ክፍሎች አንድነቱን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የህዝቦችን ብሄረሰባዊ እሴቶች በማክበርና እኩልነትን በማስፈን ሳይሆን እነዚህን በአስተዳደራዊ መንገድ በማጥፋት ለመፍጠር ጥረዋል:: በዚህም ጭቁን ብሄሮችን አርቀዋል፣ አስከፍተዋል፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነታችንንም ሸርሽረዋል::

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት፣ የብሄር/ብሄረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ብቅ ያለው ህገ-መንግስታችን ሲፀድቅ አይደለም:: በንጉሱ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ተነስቶ፣ በደርግ አገዛዝ ወቅት እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ፣ በደርግ መንግስት ውድቀት ዋዜማ ላይ ቢያንስ 17 የታጠቁ የብሄረሰብ ድርጅቶች የነበሩበትና የራሱ ረጅም ታሪካዊ አመጣጥ ያለው ነው:: ይህን ጥያቄ የፈጠረው የህገ-መንግስታችን አንቀፅ 39 አይደለም፣ ነባራዊ ጭቆናውና አድልዎው ነው:: ጥያቄውን ወደከፍተኛ ደረጃ ያደረሰውም ህገ-መንግስቱ ሳይሆን ነባራዊ ጭቆናውና በዚህ ላይ ተመስርተው እየተስፋፉ የመጡት ጠባብና ትምክህተኛ ሃይሎች ናቸው:: ህገ-መንግስቱ ከላይ በተገለፀው መልኩ እጅግ ተባብሶ ሊፈነዳ የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰውን ይህን ቅራኔ፣ አገራችንን ለጠቅላላ ብተና ሊዳርግ የሚችልበት

ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረውን ይህን ቅራኔ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ ነበር የቀየሰው።

ህገ-መንግስታችን ህዝቦች እኩልነታቸው መከበር እንዳለበት፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን የመጠቀምና የማዳበር መብት እንዳላቸው፣ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር እንዳለባቸው አስቀምጧል። እነዚህ መብቶች መከበራቸው የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ከማስጠበቅ አኳያ ያለውን ትልቅ ፋይዳ ቀጥለን የምንመለስበት ጉዳይ ነው። እነዚህ መብቶች መከበራቸው ለግለሰቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርም እጅግ መሰረታዊ የሆነ ተፈላጊነት አለው። ዴሞክራሲያችን መላው ህዝብ በቀጥታ የሚሳተፍበት መሆን አለበት ብለናል። ህዝቡ በራሱ ቋንቋ መጠቀም ካልቻለ በአስተርጓሚ የነቃና ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊያደርግ አይችልም። ህዝቡ በየአካባቢው በየቋንቋው እየተጠቀመ የአካባቢውን ጉዳዮች መወሰን ካልቻለ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊኖረው አይችልም። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የህዝቦች መብትና የዜግነት መብቶች ተነጣጥለው ሊከበሩ አይችሉም።

ዜጎች በቋንቋችን እንናገር፣ ባህላችን ይከበር፣ ታሪካችን ይህ ነው ብለው መፃፍና መናገር ካልቻሉ የመናገርና የመፃፍ መብታቸው ሊከበር አይችልም። ከዚያም አልፈው መገንጠል ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ይህንኑ እምነታቸውን የሌላን መብት ሳይነኩ በሰላማዊ መንገድ እንዲያቀርቡ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር የእምነት ነፃነታቸው ሊረጋገጥ አይችልም።



ዴሞክራሲያዊ ስርአት በዜጎች የመናገር የመፃፍ የእምነት ወዘተ. ነፃነት ላይ ሊጥለው የሚችለው ገደብ የሌላን መብት እንዳይነካ፣ ጦርነትን እንዳይሰብክ በማድረግ መልኩ ብቻ ነው። ከዚህ አልፎ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደዚህ አይነት ሃሳብ መያዝና ሃሳብህን መግለፅ አትችልም ብሎ ገደብ ከጣለ ዞሮ ዞሮ መብቶቹ ተገፈፉ፣ ዴሞክራሲ ጠፋ ማለት ነው። በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ጠባብና ትምክህተኛ አመለካከቶችን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ እንዳይቀርቡ ማገድ አይገባም። እነዚህን በህግ እናግዳለን ማለት ዞሮ ዞሮ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ሁሉ ማገድን ያስከትላል። በዴሞክራሲያዊ ስርአት ሁሉም ሃሳቦች ከላይ የተጠቀሱት ጠባብነትንና ትምክህትን የሚያንፀባርቁ የተሳሳቱ ሃሳቦችም ጭምር የሌላን መብት ሳይደፍሩ፣ ጦርነት ሳይቀሰቅሱ እንዲቀርቡ መፍቀድ፣ እነዚህን የተሳሳቱ አመለካከቶች በተስተካከሉ አመለካከቶች በሰላማዊ መንገድ ማጋለጥ ማፍረስና ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው ተገቢ የሚሆነው።

የብሄር ቅራኔ እጅግ የሰላ ደረጃ ላይ በደረሰባት አገራችን፣ በርካታ ጠባብና ትምክህተኛ አመለካከት ያላቸው ድርጅቶችና ቡድኖች በነበሩባትና ባሉባት አገራችን እነዚህ ሃይሎች ሃሳባቸውን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ እንዲያቀርቡ ከመፍቀድ ውጭ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበት ስርአት ሊታሰብ የሚችል አልነበረም። እነዚህ ክፍሎች ሃሳባቸውን በነፃና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዲያቀርቡ ፈቅዶ በተመሳሳይ ዴሞክራሲያዊ አኳኋን ሃሳባቸው በህብረተሰቡ ተቀባይነት እንዳይኖረው ማድረግ ነበር ብቸኛው ዴሞክራሲያዊ

አማራጭ፡፡ ሃሳባቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖረው ሊያደርጉ የሚችሉትን የብሄር/ብሄረሰብ ተገቢ ጥያቄዎችን በመፍታት አስተሳሰባቸውን ከምንጩ ለማድረቅ መታገል ነው ብቸኛው ዴሞክራሲያዊ አማራጭ፡፡ ህገ-መንግስታችን በአንድ በኩል የብሄር/ብሄረሰቦችን ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በመመለስ ለአንድነታችን ፀር የሆኑ አስተሳሰቦችን በዴሞክራሲያዊና አስተማማኝ አኳኋን ለማምከን የሚያስችል በር ሲከፍት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች የሌላን መብት ሲደፍሩና ሰላምን ሲያደፈርሱ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ገደብ ሳይጣልባቸው ሃሳባቸውን እንዲገልፁ በማድረግ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊከበሩ የሚችሉበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡

ህገ-መንግስታችን የብሄር/ብሄረሰቦችን መብት ከማስከበር አኳያ ያስቀመጣቸውን አንቀፆች ከሚቃወሙት ወገኖች ውስጥ ለግለሰቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ቆመናል የሚሉ አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሁለቱ ተነጣጥለው ሊሄዱ እንደማይችሉ የተገነዘቡ አይመስሉም፡፡ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት አፍኖ፣ በብሄረሰቦች መካከል የሚነሱ ቅራኔዎችን ምንጭ ሳያደርቁ፣ ትምክህተኛና ጠባብ አስተሳሰቦችን ማድረቅ አይቻልም፡፡ እነዚህን መብቶች አፍኖ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማስከበር አይቻልም፡፡ የብሄር/ብሄረሰቦች መብቶች ታፍነው ጠባብና ትምክህተኛ አስተሳሰቦች በነፃ ይንሸራሸሩ ከተባለ ጠባብነትና ትምክህት በህዝቦች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አግኝተው ህገ-መንግስቱ መገንጠልን ቢፈቅድም ባይፈቅድም ህዝቡ ወደ ቀጣይ እልቂት ገብቶ መበታተኑ



አይቀርም፡፡ የብሄሮችን መብት በህግ አረጋግጦ፣ የጠባቦችና ትምክህተኞችን አስተሳሰብ ከምንጩ ለማድረቅ የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር፣ ሃሳባቸውን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዲያቀርቡ ፈቅዶ በዴሞክራሲያዊ የሃሳብ ትግል ከማምከን ውጭ በአገራችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያስከብር ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት ሊታሰብ የሚችል አይደለም፡፡ ህገ-መንግስታችን የህዝቦችን መብት የሚያስከብርበት አንዱ ዋነኛ ምክንያት የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማክበር በአገራችን ያለው ብቸኛ አማራጭ ይኸው ስለሆነ ነው፡፡ የህገ-መንግስቱን አንቀፅ 39 ከሚደግፉትም ሆነ ከሚቃወሙት ወገኖች ይህንን መሰረታዊ ነጥብ የማያስተውሉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

ህገ-መንግስታችን የህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መከበር አለበት የሚለው በህዝቦች መካከል ቀጣይ ልዩነትና ቁርሾ እንዲኖር ለማድረግ አይደለም፡፡ የህገ-መንግስቱ መነሻ ሃሳብ መለያየትና መነጣጠል አይደለም፡፡ የህገ-መንግስቱ መነሻ ሃሳብ በህዝቦች መካከል በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ አንድነትን መፍጠር ነው፡፡ አንድነታችን ብሄረሰባዊ እሴቶችን በአስተዳደራዊ መንገድ በማጥፋት ሊገነባ እንደማይችል ተግባር ያረጋገጠው ሃቅ በመሆኑ በዚህ ምትክ የጠንካራ ህዝባዊ አንድነት መሰረቶችን ለመጣልና ለማጠናከር ነው ህገ-መንግስታችን የተነደፈው፡፡ ይህን መሰረታዊ ሃቅ ከራሱ ከህገ-መንግስቱ መግቢያ በላይ በጣም ግልፅ በሆነ መልክ ያስቀመጠ ሰነድ ስለሌለ የህገ-መንግስቱን መግቢያ እንዳለ መጥቀስ

ተገቢ ነው።

**የህገ-መንግስታችን መግቢያ እንደሚከተለው ይላል፡፡**

- ♦ **እኛ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ህዝቦች፡-**

በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነፃ ፍላጎታችን በህግ የበላይነትና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፣

ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ የግለሰብና የብሄር/ብሄረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ፅኑ እምነታችን በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ አገራችን የየራሳችን አኩሪ ባህል ያለን፣ የየራሳችን መልክአ-ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት አገር በመሆኗ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፣

መጭው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን



በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፣

ጥቅማችንን መብታችንና ነፃነታችን በጋራና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባትን አስፈላጊነት በማመን፣

በትግላችንና በከፈልነው መስዋእትነት የተገኘውን ዴሞክራሲና ሰላም ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ፣

ይህ ህገ-መንግስት ከዚህ በላይ ለገለፅናቸው አላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆነን እንዲወክሉን መርጠን በላክናቸው ተወካዮቻችን አማካይነት በህገ-መንግስት ጉባኤ ዛሬ ህዳር 29 ቀን 1987 አፅድቀናል፡

በመግቢያው የመጀመሪያዎቹ ቃላት ግልፅ እንደሆነው ህገ-መንግስቱ የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የጋራ ሰነድ፣ የጋራ ቃልኪዳን ነው። ዜጎች በተናጠል የወሰኑበት ሳይሆን ብሄር/ብሄረሰቦች እንደብሄር ብሄረሰቦች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የጋራ አላማዎቻቸውና እምነቶቻቸው ማስፈፀሚያ ይሆናል ብለው ያፀደቁት የቃል ኪዳን ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ የኢትዮጵያ ብሄር-ብሄረሰቦች በጋራ በአንድነት ለመኖር በነፃ ፍላጎታቸው የወሰኑ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ይህን አንድነት ለምን እንደሚፈልጉትና እንዴትም መመስረት እንዳለበት በግልፅ ሳያስቀምጡ አስተዳደራዊ ትስስር ይኑረን ያሉበት ሰነድ

አልነበረም፡፡

በመግቢያው የመጀመሪያ -ራግራፍ ላይ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር ቆርጠን ተነስተናል ይላሉ፡፡ የተለያዩ የፖለቲካ ማህበረሰቦች በሆነ አስተዳደራዊ ገመድ ይተሳሰሩ ሳይሆን አንድ አገር፣ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ይኑረን ነው የሚሉት፡፡ ይህን የሚሉበትን ምክንያት በራሱ በመጀመሪያው -ራግራፍና በሶስተኛው -ራግራፍ ላይ ገልፀዋል፡፡ ዘላቂ ሰላም ለማግኘት አንድ የ-ለቲካ ማህበረሰብ ያስፈልገናል፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ ለማስፈን አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ያስፈልገናል፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችንን ለማፋጠን አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ያስፈልገናል ነው የሚሉት፡፡ የእያንዳንዱን ዜጋ፣ የእያንዳንዱን ብሄር/ብሄረሰብ የሰላም ፍላጎት፣ የዴሞክራሲ ጥማት፣ የፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ምኞት ለማሳካት የምንችለው ተነጣጥለን ሳይሆን አንድ የ-ለቲካ ማህበረሰብ በመፍጠር፣ በፖለቲካዊ አንድነት ነው ብለው ማመናቸውን ነው የገለፁት፡፡ በድፍኑ ስለአንድነት አስፈላጊነት፣ ስለአስተዳደራዊ አንድነት ሳይሆን የተናጠልና የጋራ ጥቅማችንና መብታችንን ለማሳካት ብቸኛ አማራጭ ስለሆነው የፖለቲካ አንድነታችን ነው ውሳኔያቸውን ያስተላለፉት፡፡

በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝቦች ፖለቲካዊ አንድነት ለወደፊት በምንመኘውና የጋራ አላማችን በሆነው የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ጉዳይ ላይ ብቻ አይደለም የሚመሰረተው፡፡ ስለቀጣይ ፖለቲካዊ አንድነታችን ስናቅድ ዋናው መሰረቱ የጋራ



አላማችንና ራዕያችን፣ የአገራችን ቀጣይ ጉዞና ዕጣ ፈንታ በሚወስነው የጋራ አላማና ራዕይ ላይ መመስረት ይኖርበታል፡፡ ህገ-መንግስቱም ይህንኑ አስምሮበታል፡፡ ይሁንና የአገራችንና የህዝባችን አንድነት በመጪው ጉዞ ላይ ብቻ ሳይሆን ባለፈው ጉዟችንም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የህገ-መንግስቱ መግቢያ ሶስተኛው -ራግራፍ እንደሚያስቀምጠው የየራሳችን ብሄረሰባዊ እሴቶች ያሉን ህዝቦች ብንሆንም ባለፈው ታሪካችን ሂደት ለአንድነታችን መሰረት የሚሆኑ የጋራ ጥቅሞችና አመለካከቶች አፍርተናል፡፡ እነዚህም ታሪካዊ እሴቶች የፖለቲካዊ አንድነታችን መሰረቶች ናቸው፡፡ ይሁንና የህገ-መንግስቱ መግቢያ አራተኛው -ራግራፍ እንደሚያስቀምጠው በታሪካችን የተዛቡ ግንኙነቶችም ስለነበሩ ታሪካችን የፖለቲካዊ አንድነታችን መሰረት የሚሆነው እነዚህን የተዛቡ ግንኙነቶችን እንዳሉ በመውረስ ሳይሆን እነዚህን በማስተካከል ነው፡፡

ስለሆነም ህገ-መንግስታችን የኢትዮጵያ ህዝቦች የሰላም፣ የዴሞክራሲ የልማት አላማቸውንና ፍላጎታቸውን ለማሳካት፣ ባለፈው ታሪካቸው ሂደት ያፈሯቸውን የጋራ እሴቶች መሰረት በማድረግና የተዛቡትንም በማስተካከል አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ፣ አንድ የተከበረ አገር ለመፍጠር በነፃ ፍላጎታቸው መርጠው መወሰናቸውን የሚያበስር፣ የዚሁ የጋራና ነፃ ውሳኔ መሰረት ምን እንደሆነ የሚያስቀምጥ ነው፡፡

ህገ-መንግስታችን በመግቢያው ሁለተኛ -ራግራፍ ላይ እንደሚያስቀምጠው ይህንን አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመፍጠር

አላማ ከግብ ለማድረስ የሚቻለው የግለሰቦችና የብሄር ብሄረሰብ መሰረታዊ መብቶች ሲከበሩ ብቻ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱ ሁለቱን አይነጣጥልም፡፡ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማችን የሚሳካው የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ የህዝቦች መብቶች በጣምራ ሲከበሩና ሲረጋገጡ እንደሆነ ያሰምራል፡፡ ህገ-መንግስቱ ሁለቱ በጣምራ መከበር እንዳለባቸው ከማስቀመጡም ባሻገር የብሄር/ብሄረሰብ መብቶች መከበር አለባቸው የሚልበት መሰረታዊ ምክንያት ምን እንደሆነ በማያሻማ አኳኋን አስቀምጧል፡፡ ‹‹ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ፡ ይለዋል፣ ማለትም በመጀመሪያው -ራግራፍ የተቀመጠውን በህዝቦች ነፃ ፍላጎት አንድ የ-ለቲካ ማህበረሰብ የመገንባት አላማን ከግብ ለማድረስ ነው መብቱ መከበር ያለበት፡፡ በህዝቦች መካከል ዘላቂ ልዩነት፣ ቁርሾና መነጣጠል ለመፍጠር ሳይሆን በህዝቦች ነፃ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መፍጠርን ነው ህገ-መንግስቱ ያፀደቀው፡፡

ህገ-መንግስቱ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ ብቻ ሳይሆን አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠርም አላማ አለው፡፡ ህገ-መንግስቱ አንድ አገራዊ ኢኮኖሚ፣ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እንዲኖረን ፍላጎት ያለን መሆኑን አስፍሯል፡፡ አንድ የጋራ ኢኮኖሚ በመፍጠር ነው የጋራና የእያንዳንዳችንን ጥቅም ማስጠበቅ የምንችለው፡፡ የህገ-መንግስቱ አላማ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ ይህን ለመፍጠር የዜጎችና የህዝቦችን መብቶች ማክበርና ካለፈው ታሪካችን የተወረሱ የተዛቡ ግንኙነቶችን አስተካክሎ



አንድነታችንን በታሪክ ሂደት ባዳበርናቸው የጋራ እሴቶችም ላይ እንዲመሰረት ማድረግ፣ በዋነኛነት ደግሞ በሰላም፣ በዴሞክራሲና በልማት የጋራ አላማችንና ትግላችን ላይ እንዲመሰረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ነው ህገ-መንግስቱ የሚያስቀምጠው፡፡

በመጨረሻም የህገ-መንግስቱ መግቢያ ህገ-መንግስቱ የፀደቀው ከላይ ለተዘረዘሩት አላማዎችና እምነቶች ማሰሪያና መቋጫ እንዲሆን ስለተፈለገ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ህገ-መንግስቱ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ አንድነት አላማን ያነገበ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አንድነቱ ለምን እንደሚያስፈልገንና እንዴትስ መገንባት እንዳለበት በግልፅ ያስቀመጠ በህዝቦች ነፃ ውሳኔ የፀደቀ ሰነድ ብቻ አይደለም፡፡ የነዚህ አላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ መቋጫም ጭምር ነው፡፡ ሁሉም ዜጎች ብሄር/ብሄረሰቦች የሚመሩበት በጥብቅ ተግባራዊ የሚያደርጉት የጋራ መመሪያ ነው፡፡ የጋራ ቃል ኪዳን፣ የጋራ ቻርተር ነው፡፡ ህገ-መንግስቱን መናድ ማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ መመሪያችን፣ ቃል ኪዳናችንና ነፃ ውሳኔያችን ነው ያሉትን ሰነድ መናድ ማለት ነው፡፡

ህገ-መንግስታችን የፖለቲካና ኢኮኖሚ አንድነት አላማን ሲያራምድ በጋራ አላማዎች፣ በጋራ እምነቶች፣ በጋራ እሴቶች፣ በጋራ ጥቅሞች ላይ የተመሰረተ አንድነትን በማሰብ ነው፡፡ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች መኖር ስላለበት ተራ አስተዳደራዊ ትስስር ሳይሆን በግልፅ ተለይተው በተቀመጡ፣ በህገ-መንግስቱ

ላይ በሰፈሩ የጋራ ጥቅሞችና እምነቶች፣ በመፈቃቀድ ላይ በተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መቆሙን ነው የሚያበስረው:: ህገ-መንግስታችን የእንደዚህ አይነቱ አንድነት መመሪያ፣ አቅጣጫ ቀያሽና መሰረትም የሆነ ሰነድ ነው::

የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 39 መታየት ያለበት በመግቢያው ላይ ከተገለፀው የህገ-መንግስቱ አላማ አኳያ ነው:: አንቀፅ 39 ህዝቦች እኩልነታቸው እንዲጠበቅ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ በጋራ አስተዳደራዊ መዋቅሮች ውስጥ በእኩልነትና ሚዛናዊ በሆነ አኳኋን እንዲወከሉ፣ ብሄረሰባዊ እሴቶቻቸውን እንዲያዳብሩ ይፈቅዳል:: እነዚህ መብቶች በተከበሩበት ወቅት ህዝቦች በፈቃዳቸው ከላይ ለተገለፁት አላማዎች ሲሉ በጋራ መኖርን እንደሚመርጡ ምንም ጥርጥር የለውም:: በርግጥ ከዚህ የተለየ ሃሳብ ያላቸው ቡድኖችና ድርጅቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: የነዚህን ሃሳብ የህዝቦችን የእኩልነት መብት በማክበር ከምንጩ ማድረቅ፣ በዴሞክራሲያዊ የሃሳብ ትግል ማምከን ይቻላል:: በእኩልነትና በዴሞክራሲ ላይ በመመስረት የኢትዮጵያን ጠንካራ አንድነት መመስረት ይቻላል:: ብሄረሰባዊ እሴቶች የኢትዮጵያዊነት እሴቶች መሰረት እንጂ የኢትዮጵያዊነት እሴቶች ተፃራሪ እንዳይሆኑ ማድረግ የሚቻለው በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ነው::

ይሁንና ህገ-መንግስታችን አንቀፅ 39 የብሄር/ብሄረሰቦችን የመገንጠል መብት በማያሻማ መልኩ ከማስቀመጥ ባሻገር ተግባራዊ የሚሆንበትንም መንገድ በዝርዝር ያስቀምጣል::



የፖለቲካና የኢኮኖሚ አንድነት አላማን በግልፅ አስቀምጦ የተነሳ ህገ-መንግስት የመገንጠልን መብት በተመሳሳይ አኳኋን በግልፅ ማስቀመጡና መቀበሉ እርስ በርሱ የሚጋጭ ሊመስል ይችላል:: ግን የሚጋጭ አይደለም::

ይህንን መሰረታዊ ነጥብ በይበልጥ ለመረዳት ህገ-መንግስቱ ይህንን መብት ባይቀበልስ የሚለውን አማራጭ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል:: ህገ-መንግስቱ ይህንን መብት ሳይቀበል ህዝቦች በእኩልነትና በመፈቃቀድ እንዲኖሩ ሊያስተምር ይችላል:: ይህንን ሃሳብ የሚፃረሩ ወገኖችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኙ ለማድረግ ይቻላል:: ይህ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ጥረት ከተሳካ የህዝቦች አንድነት በህዝቡ ጠንካራ ድጋፍ ላይ የተመሰረተና አስተማማኝ ሆኖ ይቀጥላል:: በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ የመገንጠል መብትን የተቀበለውና ያልተቀበለው ህገ-መንግስት ውጤታቸው አንድና ያው ይሆናል:: ልዩነቱ የሚከሰተው የአንድ ብሄር/ብሄረሰብ ህዝብ በሆነ አጋጣሚ አንድነትን የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ ነው:: ህዝቡ ስለአንድነት የተስተካከለ ግንዛቤ እንዲይዝ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ጥረት ተደርጎ ሳይሳካ ቢቀር የሚኖሩት አማራጮች ሁለት ናቸው:: አንደኛው አማራጭ አብሮ መኖር ያልፈለገውን ህዝብ በሰላም መሸኘት ነው:: ሁለተኛው አማራጭ አብሮ መኖር ያልፈለገውን ህዝብ በጉልበት፣ በሃይል ለማስቀረት መሞከር ነው:: በጉልበት ለማስቀረት የሚደረገው ሙከራ ወደከፍተኛ ጦርነት እንደሚያመራ ጥርጥር የለውም:: አንድን ህዝብ ያለፍላጎቱ አስሮ ማኖር ስለማይቻል በመጨረሻ በጉልበት

አብሮ እንዲኖር የማስገደዱ አላማ እንደሚከሽፍም ጥርጥር የለውም:: በጉልበት አንድነትን ለማስጠበቅ የሚደረግ ሙከራ ዞሮ ዞሮ መክሸፉ ላይቀር ነገር እስኪከሽፍ ድረስ ግን አገሪቱ በአስከፊ ጦርነት እንድትናጥ፣ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ አላማዎች ለከፍተኛ አደጋ እንዲጋለጡ ያደርጋል::

የመገንጠል መብትን በህገ-መንግስቱ ላይ ማስፈር አብሮ ለመኖር ያልፈለገን ህዝብ በጉልበት አስሮ የማኖሩ ሙከራ የሚያስከትለውን ጥፋት ያስወግዳል:: ይህንን መብት የሚቃወም ህገ-መንግስት አብሮ ለመኖር ያልፈለገን ህዝብ በሃይል አስሮ ለማቆየት ሙከራ እንዲደረግ የሚያስገድድ ይሆናል:: ይህ ሙከራ ሄዶ-ሄዶ መክሸፉ የማይቀር ቢሆንም ሙከራው ተንኮታኩቶ እስኪወድቅ ድረስ አገሪቱን በመላ ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ ይሆናል:: ልዩነቱ ያለውም እዚህ ላይ ነው:: ህገ-መንግስታችን አንድነታችን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ ተመስርቶ በአስተማማኝ መልኩ ሊረጋገጥ ይችላል ብሎ ያምናል:: ህገ-መንግስታችን ከዚህም አልፎ አንድነታችንን ለማረጋገጥ ያለው ብቸኛው አማራጭ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ነው ብሎ ያምናል:: ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ አንድነታችንን ለማረጋገጥ መሞከር የማይሳካ ነገር ብቻ ሳይሆን አገራችንን ለከፋ አደጋ ያጋልጣል የሚል መነሻ አለው:: ስለሆነም አንድነታችንን በብቸኛው የዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ አማራጭ ለማስከበር፣ በአንድነት ለመኖር ያልፈለገ ህዝብ በፍላጎቱ የሚለቅበትን የመገንጠል መብት ያስከብራል:: ህገ-መንግስታችን የመገንጠል መብትን በማያሻማ መልኩ ማረጋገጡ መገነጣጠልን



ማራመዱ ወይም መስበኩ ሳይሆን ብቸኛውን የሰላምና የአንድነት አማራጭ መምረጡ ነው::

## 3. የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን፣

በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአትን ለመገንባት ህዝቦቻችን ለዘመናት የታገሉለትን አላማ እውን ለማድረግ የሚያስችል ህገ-መንግስት አፅድቀን የግንባታ ስራውን ጀምረናል:: ዴሞክራሲያችን በነፃ ገበያ ኢኮኖሚያዊ ስርአት ማዕቀፍ ውስጥ የሚገነባ ዴሞክራሲ በመሆኑ በመሰረታዊ ይዘቱ ከሌሎች መሰል ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ጋር አንድ አይነትና ተመሳሳይ ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚመነጩ ሁለት መለያ ባህሪያት አሉት:: ዴሞክራሲያችን በዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይም መመስረት እንዳለበት መቀመጡ አንዱ መለያ ባህሪው ነው:: በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ ብቻ ለተመሰረተ አንድነት መቆሙና ከዚህም አኳያ ብሄር/ብሄረሰቦች እስከመገንጠል ድረስ ያሉት መብቶቻቸው እንዲከበሩ ማድረጉ ሌላው መለያ ባህሪው ነው::

የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ትግላችን የዴሞክራሲ ምድረ በዳ ሆና በነበረች አገራችን የሚካሄድ በመሆኑ ሰፊ ርብርብና ትግል የሚጠይቅ እንደሆነ እሙን ነው:: የዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ተቋማትና ድርጅቶችን መፍጠርና ማጠናከርን የሚያክል ግዙፍና አስቸጋሪ ስራ መስራትን ይጠይቃል:: የዴሞክራሲ አስተሳሰብና ባህልን በህዝባችን ስነ-ልቦና ውስጥ መቅረፅን የሚያክል ውስብስብ ትግል ይጠይቃል:: በነዚህ ሁለት ዋነኛ ስራዎች ላይ በማተኮር ሌት ተቀን

መረባረብን ይጠይቃል፡፡ የዴሞክራሲያችን አድማሳዊ ባህሪያትንም ሆነ መለያ ባህሪያትን አስተሳስሮ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ትክክለኛ አቅጣጫ መቀየስን ይጠይቃል፡፡ የዚህ ፅሁፍ ቀጣይ ክፍሎችም በነዚህ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ፡፡



# ክፍል ሁለት

# የግለሰብ መብቶችና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር

## 1. የግለሰብና የጋራ መብቶች፣

የግለሰቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በህገ-መንግስታችን ሙሉ ጥበቃ ተደርጎላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ህገ-መንግስታችን ለብሄር/ብሄረሰቦች የጋራ መብቶችም የተሟላ ጥበቃ አድርጓል፡፡ ህገ-መንግስቱ ሁለቱን መብቶች ነጣጥሎ ሳይሆን አጣምሮ ነው የሚያያቸው፡፡ ይሁንና በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች መሰንዘራቸው አልቀረም፡፡ በአንድ በኩል ከግለሰብና ከጋራ መብቶች የበላይነት የሚሰጠው የቱ ነው በሚል መልክ የሚነሳ ክርክር አለ፡፡ ይህ ክርክር ራሱ በግለሰብ መብቶችና በጋራ መብቶች መካከል ቅራኔ እንደሚኖር ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት የጋራ መብቶች ተብለው የተቀመጡት የግለሰቦችን መብት ለመርገጥ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ በሚል መልክ የሚቀርብ ክርክር አለ፡፡

### 1.1. የግለሰብና የጋራ መብቶች ትስስር፣

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የግለሰብ መብቶችና የጋራ መብቶች ተነጣጥለው ሊሄዱ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ከላይ

እንደተገለፀው የብሄር/ብሄረሰቦችን መብት በተሟላ መልኩ ማስከበር ተፈላጊ የሚሆንበት አንድ መሰረታዊ ምክንያት ይህንን ከማድረግ ውጭ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የግለሰቦችን መብት ማስከበር ስለማይቻል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሰዎች ሃሳባቸውን በነፃ እንዳይገልፁ፣ በመሰላቸው አኳኋን እንዳይደራጁ ወዘተ. በተከለከሉበት ወቅት የብሄሮች/ብሄረሰቦች መብት ሊከበር አይችልም፡፡ በየብሄር/ብሄረሰቡ ያሉት ሰዎች ሁሉ መብታቸው ስለሚታፈን ብሄር/ብሄረሰቦቹም በጋራ መብታቸው የተረገጠ ይሆናል፡፡ በሌላ አገላለፅ የጋራ መብቶቹ መሰረታቸው የግለሰብ መብት ይሆናል፡፡ ሁለቱ ተሳስረው አንዱ ለሌላው መከበር መሰረት ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ህገ-መንግስታችን የግለሰቦችን መብት በማስከበር ሽፋን የብሄር-ብሄረሰቦች መብት መረገጥን እንደማይቀበል ሁሉ በብሄር/ ብሄረሰቦች መብት መከበር ሽፋን የግለሰቦች መብት መታፈንን አይቀበልም፡፡ የጋራ መብቶች ለግለሰብ መብቶች መታፈን መሳሪያ ይሆናሉ የሚለው አባባል ምንም አይነት ህገ-መንግስታዊ መሰረት የሌለው ነገር ነው፡፡ የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 25 ይህንን በተመለከተ ‹‹ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፣ በመካከላቸውም ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሄር፣ ብሄረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሃብት በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡፡ ይላል፡፡ ህገ-መንግስታችን



በጋራ መብቶች ሽፋን የግለሰብን መብት መርገጥ የተከለከለ መሆኑን በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

በርግጥ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በግለሰቦች መብትና በጋራ መብቶች መካከል በአፈፃፀም ላይ ግጭት ሊያጋጥም እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ እንደዚህ አይነቱ ግጭት በግልና በጋራ መብቶች መካከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የግለሰብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መካከልም ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እንደዚህ አይነት ግጭት በሚያጋጥምበትም ወቅት አንዱ ከሌላው የበላይ ነው ብሎ በመፈረጅ አንደኛውን ረግጦ ሌላኛውን በማክበር መልክ መፍታት አይቻልም፡፡ እንደዚህ አይነቱ አካሄድ ዞሮ ዞሮ የሁሉንም መብቶች መሸርሸርና መታፈንን ከማስከተል በስተቀር መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው እንደዚህ አይነቱ ግጭት በሚያጋጥምበት ወቅት የተጋጩትን መብቶች በማጣጣምና በማቻቻል የሁሉንም መብቶች መሰረታዊ ባህሪና ይዘት በሚያስጠብቅ አኳኋን መፍታት ነው፡፡ መብቶቹ በባህሪያቸው ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ በመሆናቸው ይህንን ለማድረግ የማይቻልበት አንዳች ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡

የግለሰብና የጋራ የዴሞክራሲ መብቶች የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው በመሆናቸው በህገ-መንግስታችን ተለያይተው ቀርበዋል፣ በዚህ ፅሁፍም የህገ-መንግስቱን ፈለግ በመከተል ተለያይተው ይቀርባሉ፡፡ ይሁንና ህገ-መንግስቱም ሆነ ይህ ፅሁፍ ሁለቱ መብቶች በፍፁም ተነጣጥለው ሊሄዱ እንደማይችሉ በጥብቅ ያምኑበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ ክፍል ሁለት ላይ ስለግለሰቦች

መብት መከበር የሚቀርበው ሃተታ በሙሉ እንድምታው በግለሰቦች መብት መከበር ላይ የታጠረ አይሆንም። ለብሄር/ብሄረሰቦች መብት መከበርም የሚያገለግል ነው። በተመሳሳይ መልክ በፅሁፉ ክፍል ሶስት ላይ ስለብሄር/ብሄረሰቦች መብት መከበር የሚቀርበው ሃተታ ለግለሰብ መብቶች መከበርም የሚያገለግል ነው። በተለያዩ ክፍሎች ተነጣጥሎ መቅረቡ መብቶቹ የተነጣጠሉ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

## 1.2. አገራዊ የጋራ አመለካከት መፍጠርና ዴሞክራሲ፣

በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአት እንዲያብብ ለማድረግ የዴሞክራሲ ተቋሞችና ድርጅቶች መፍጠር መጠናከርና ማበብ እንዳለባቸው፣ የዴሞክራሲ አስተሳሰብና ባህል መዳበር እንዳለበት፣ በነዚህ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሰፊ ርብርብ መደረግ እንዳለበት በተደጋጋሚ ተገልጿል። የዳበረ የዴሞክራሲ ስርአት የገነቡት ብዙዎቹ አገሮች በረጅም የታሪክ ሂደት እየወደቁ እየተነሱ እንደዚህ አይነቶቹን ተቋሞችና ባህል መፍጠር እንደቻሉ፣ በኛ ሁኔታ ግን ይህ ሂደት እጅግ የተፋጠነ መሆን እንዳለበትና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጥረታችን ከከሸፈ ጠቅላላ ጥፋትን የሚያስከትል በመሆኑ እየወደቁ መነሳት እንደአማራጭ ለኛ ክፍት አለመሆኑ ተሰምሮበታል።

የዴሞክራሲ ባህልና አስተሳሰብ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ስር ሰዷል ሊባል የሚችለው ህብረተሰቡ በሚመራባቸው መሰረታዊ



መርሆዎች ላይ አንድ አይነት የጋራ አመለካከት፣ የጋራ እምነት ሲፈጠር ነው። ይህ ሲባል ሁሉም ሰው በሁሉም ጉዳዮች ላይ አንድ አይነት አመለካከትና እምነት ይኖረዋል ማለት አይደለም። በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ የጋራ አቋም ተይዞ ከዚያ በመለስ ባሉ ጥያቄዎች ላይ በጣም የተለያዩ ብዙ አመለካከቶችና እምነቶች መኖራቸው በፍፁም የማይቀር ነው። ይልቁንም ዴሞክራሲ እነዚህን ልዩነቶች ለማቻቻልና ለመፍታት ተብሎ የሚፈጠር ስርአት ነው። ህብረተሰቡ በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ የጋራ አቋም መያዝ አለበት ሲባል ሁሉም ዜጎች በመሰረታዊ መርሆዎችም ላይ አንድ አቋም ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል ባላቸው አገሮችም ቢሆን ህብረተሰቡ በሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች ላይ እጅግ የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ይኖራሉ። የጋራ አገራዊ አመለካከት (ናሽናል ኮንሰንሰስ) ተፈጥሯል የሚባለው ሁሉም ዜጋ በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ አንድ አቋም ሲይዝ ሳይሆን እጅግ የሚበዛው ዜጋ የጋራ አቋም ሲይዝ ነው። እጅግ የሚበዛው ዜጋ እንደዚህ አይነት አቋም ሲይዝ፣ ከዚህ የተለየ አቋም ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ቢኖሩም በስርአቱ ህልውናና ጤንነት ላይ የሚያስከትሉት አደጋ አይኖርም።

በዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠረው የጋራ አቋም በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ መመስረት አለበት። የዜጎችን መብት በማክበር፣ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ፣ ዜጎች መብትና ጥቅማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ አኳኋንና በዚህ መንገድ ብቻ የማስጠበቅ እምነት እንዲይዙ በማድረግ ላይ መመስረት

አለበት፡፡ ልዩነቶችን በውይይት፣ በክርክር በመጨረሻም በህዝቡ ዴሞክራሲያዊ ምርጫና ውሳኔ የመፍታት ጠንካራ እምነት በመያዝ ላይ መመስረት አለበት፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስቶች የሚሰፍሩ በመሆናቸው የጋራ እምነቱና አመለካከቱ በህገ-መንግስቱ ዙሪያ መፈጠር ያለበት ይሆናል፡፡ ልዩነቶችን በውይይት፣ በክርክርና በህዝቡ ምርጫ ለመፍታት ዝግጁነቱ ከሌለ፣ ሁሉም የየራሱ አቋም እስካልተፈፀመለት ድረስ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ ውሳኔ ለመርገጥ ዝግጁ እስከሆነ ድረስ ቀጣይነት ያለው የዴሞክራሲ ስርአት ሊኖር አይችልም፡፡ በግጭቶችና ጦርነቶች መካከል የሚኖር የተኩስ አቁም ስምምነት ከመሆን የዘለለ ስርአት ሊሆን አይችልም፡፡ ሁሉም ሰው የህግ የበላይነትን ተቀብሎ ለመሄድ ዝግጁ እስካልሆነ ድረስ ሁሉም የየራሱን አቋም ከህግ በላይ አድርጎ ባመቸው መንገድ ለማስፈፀም እስከተንቀሳቀሰ ድረስ የዴሞክራሲ ስርአት ብሎ ነገር ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም የዴሞክራሲ ስርአት እንዲኖር ከተፈለገ እጅግ የሚበዛው ህዝብ በግልና በማህበራዊ ኑሮው ልዩነቶችን በውይይትና በመጨረሻም በህዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የመፍታትን አቅጣጫ እንደብቸኛ አማራጭ ሊይዝ ይገባል፡፡ እጅግ የሚበዛው ህዝብ መብትና ጥቅሙን በህግ የበላይነት ማዕቀፍ በሰላማዊና ህጋዊ አኳኋንና በዚህ አኳኋን ብቻ የማራመድ ጠንካራ እምነት መያዝ አለበት፡፡ እነዚህን እምነቶች በያዘው ህገ-መንግስት ዙሪያ አንድ አገራዊ የጋራ አመለካከት መያዝ አለበት፡፡

ከላይ በተጠቀሱትና በመሳሰሉት የዴሞክራሲ መርሆዎች



ላይ አንድ አገራዊ የጋራ አቋም ባልተያዘበት ወይም ይህ የጋራ አቋም በተለያየ ምክንያት በተሸረሸረበት አገር ዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት የዳበረ ዴሞክራሲ አላቸው በሚባሉ አገሮች ውስጥ እንደዚህ አይነቱ የጋራ አቋም ባልተያዘበት የመጀመሪያው ምዕራፍ ዴሞክራሲያዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ መንግስታት እየተገላበጡ ስልጣን ሲይዙ፣ ዴሞክራሲያዊ መንግስታት የሚባሉትም በርግጥ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሌላቸው ሲሆኑ ታይተዋል፡፡ የጋራ አቋም ከተያዘ በኋላ በሂደት በተሸረሸረባቸው አገሮችም ተመሳሳይ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ቀውሶች ታይተዋል፡፡ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት በበርካታ ዴሞክራሲያዊ አገሮች ፋሽዝም የመንገሱ ክስተት በተለያዩ ምክንያቶች ህብረተሰቡ የነበረው የጋራ ዴሞክራሲያዊ እምነትና አመለካከት ከመሸርሸሩ ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ያላቸው አገሮች በነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች ላይ፣ ህብረተሰቡ፣ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ወዘተ. አንድ አይነት የጋራ እምነትና አመለካከት ያላቸው በመሆኑ ዴሞክራሲው በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እየሆነ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በነፃ ገበያ ኢኮኖሚያዊ ስርአት ማዕቀፍ የሚገነባው የዴሞክራሲ ስርአት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ በዴሞክራሲው መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የጋራ አቋም መያዙ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ በኢኮኖሚያዊ ስርአቱ በራሱ ላይ መሰረታዊ መግባባት መያዝ አለበት፡፡ ሁሉም የየግሉን ጥቅም ማራመዱ የማይቀር ቢሆንም፣ ሁሉም ኢኮኖሚው የራሱን ጥቅም

በይበልጥ በሚያስጠብቅ አኳኋን እንዲመራ የሚያደርግ የፖሊሲ አማራጭ ማቅረቡ የማይቀር ቢሆንም፣ ጥቅሙን በስርአቱ ክልል ሆኖ ለማራመድ ዝግጁ መሆን አለበት፡፡ እጅግ የሚበዛው ህዝብ ይህን የመሰለ የጋራ እምነትና አመለካከት ባልያዘበት፣ በኢኮኖሚያዊ ስርአቱ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ጥቅሙን ማስጠበቅ እንደማይችል ሲገነዘብና ጥቅሙን ከስርአቱ ባሻገር ሄዶ ለማስጠበቅ በሚወስንበት ወቅት ዴሞክራሲው ለቀውስ መዳረጉ የማይቀር ነው፡፡ በተለያዩ ወቅቶች ጥቅማቸውን ከስርአቱ ባሻገር ሄደው ለማስጠበቅ በሚሹ ክፍሎች የተቀሰቀሱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ወደአመፅና ብጥብጥ ከዚህም አልፎ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ላይ የተመሰረቱ ዴሞክራሲያዊ ስርአቶችን ወደማክሰም ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ በተለያዩ የበለፀጉ አገሮች በተለያዩ ወቅቶች የተከሰተውም ይኸው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የገነቡ አገሮች በኢኮኖሚያዊ ስርአቱ መሰረታዊ መርሆዎች ላይ አንድ አይነት አገራዊ የጋራ እምነትና አመለካከት የያዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም የዳበረና የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚፈጠረው በዴሞክራሲው መሰረታዊ መርሆዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚው መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የጋራ እምነትና አመለካከት ሲያዝ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የዳበረ ዴሞክራሲ ያላቸው አገሮች ከዚህም ያለፈ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት ለመፍጠር ችለዋል፡፡ የተለያዩ -ርቲዎች በተለያዩ ወቅቶች በምርጫ እያሸነፉ ስልጣን ቢይዙም መንግስታቱ በሚከተሉዋቸው ፖሊሲዎች ላይ ይህ



ነው የሚባል ለውጥ የማይታይበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የግል ሚዲያዎችም በተመሳሳይ መልኩ በርካታና የተለያዩ ቢሆኑም በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የሚያራምዷቸው አቋሞች የረባ ልዩነት የማይታይባቸው ናቸው፡፡ ልዩነቶቹ እጅግ ውሱን በመሆናቸው የነዚህ አገር ብዙ ዜጎች የትኛውም -ርቲ ቢመረጥ ለውጥ አያመጣም ብለው በማመን በምርጫዎች ላይ ሳይሳተፉ የሚቀሩበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ የአመለካከት ልዩነቶች እየጠበቡ፣ የጋራ እምነቶችና አመለካከቶች አድማስ እየሰፋ ሄዶ የተለያዩ -ርቲዎች በመሰረታዊ ፖሊሲዎቻቸው አንድና ተመሳሳይ የሚሆኑበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡

አገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታን ስራ የተያያዘችው የዳበረና የተረጋጋ ዴሞክራሲ የሚጠይቀው አገራዊ የጋራ አመለካከትና እምነት ባልተፈጠረበት ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም እንደዚህ አይነቱን የጋራ እምነት ለመፍጠር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ ይጠይቃል፡፡ በዴሞክራሲያችን መሰረታዊ መርሆዎች ላይ የጋራ አመለካከት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በመሰረታዊ የልማት አቅጣጫዎቻችንና በብሄራዊ ጥቅሞቻችን ወዘተ. ጉዳዮች ላይ አንድ አይነት የጋራ አቋም መያዝ አለብን፡፡ ከዚህ ውጭ በየትኛውም አገር የዳበረና የተረጋጋ ዴሞክራሲ አልተፈጠረም፣ በኛም አገር ሊፈጠር አይችልም፡፡ ይልቁንም በኛ አገር የተያዘው የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ በይዘቱ አገራዊ ህልውናን የማረጋገጥ ባህሪ ያለው በመሆኑ፣ ሽንፈትን ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባት እንቅስቃሴውን መጓተትም ሊሸከም አይችልም፡፡ ስለሆነም

ለዴሞክራሲ ስርአት ማበብ መሰረት የሆነው ይህ የጋራ እምነትና አመለካከት በአፋጣኝና በተሳካ ሁኔታ መፈጠሩን የማረጋገጥ ጉዳይ በተዘዋዋሪ መንገድ አገራችንን ከጠቅላላ ጥፋት የመታደግ ጉዳይም ነው።

እንደሌሎች አገሮች ሁሉ ይህንኑ የጋራ እምነት ለመፍጠር ዋነኛ መነሻ የሚሆነን ሰነድ ህገ-መንግስታችን ነው። ህገ-መንግስታችን እንደሌሎች መሰል ህገ-መንግስቶች ሁሉ የዴሞክራሲያችን መሰረታዊ መርሆዎችና የነፃ ገበያ ኢኮኖሚያችን መሰረታዊ ባህሪን ይዘረዝራል። በነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች ዙሪያ የጋራ አቋም ለመያዝ የሚያስችል ባህሪ አለው። ህገ-መንግስታችን ከብዙ ሌሎች ህገ-መንግስቶች በተለየ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት አላማዎችንና የውጭ ግንኙነታችን የሚመራባቸውን መርሆዎች ያስቀምጣል። በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያም የጋራ አቋም ለመያዝ መሰረት ሊሆን ይችላል። በህገ-መንግስቱ ላይ በመመስረት መንግስት የሚቀይሳቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎችም የጋራ አቋሙ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ዋናው ጉዳይ የጋራ አቋም የመፍጠሩን አስፈላጊነት ተገንዝቦ ይህን በአፋጣኝ ተግባራዊ ለማድረግ መረባረብ ነው።

የዳበሩ አገሮች የተረጋጋና የበለፀገ ዴሞክራሲ ለመፍጠር የቻሉት የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠቀም የጋራ እምነቶች እንዲሰርፁና ተቀባይነት እንዲያገኙ ማድረግ በመቻላቸው ነው። ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምረው እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ያሉትን የትምህርት ተቋማት ለዚሁ አላማ ተጠቅመዋል።



የተለያዩ የምርምርና ጥናት ተቋማት፣ የተለያዩ ማህበራትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ለዚሁ አላማ የላቀ አስተዋፅኦ አድርገዋል። የፖለቲካ ድርጅቶችና ሚድያ ወዘተም ለዚሁ አላማ በከፍተኛ ደረጃ ተሰልፈዋል። አስተሳሰብ ለማስረፅ ሊያገለግሉ የሚችሉ መሳሪያዎችን በሙሉ በሰፊውና በቅንጅት ተጠቅመውባቸዋል። እኛም የተለየ አማራጭ የለንም። ይልቁንም እኛ ስራውን በአፋጣኝ ለመፈፀም ሁሉንም መሳሪያዎች በተሻለ ቅንጅትና ውጤታማነት ለመጠቀም መቻል ይኖርብናል።

ይሁንና የጋራ አቋምና አመለካከት የመፍጠር ጉዳይ የማስተማር፣ የቅስቀሳና ስብከት ጉዳይ ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። በመሰረታዊ መርሆዎች ላይ ሰፊ የትምህርትና ቅስቀሳ ስራ መሰራት ያለበት ቢሆንም ይህ ስራ ዘላቂ ውጤት ሊኖረው የሚችለው ህብረተሰቡ በአጠቃላይ በነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በሰፊው መወያየትና መከራከር ሲችል ነው። አንድ አስተሳሰብ የበላይነት ሊያገኝና በህብረተሰቡ ዘንድ ሊሰርፅ የሚችለው አማራጭ አስተሳሰቦችን በመድፈቅ ሳይሆን አማራጭ አስተሳሰቦችን በማሸነፍና የተሻለ ሃሳብ መሆኑን በማሳመን ነው። በመሆኑም ሁሉም አማራጮች ለህዝቡ በሰፊው ቀርበው ህዝቡ የተሻለውን የሚመርጥበትና በዚህ ዙሪያ የጋራ እምነት የሚፈጥርበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት።

በዚህ ረገድ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተሰሩ በርካታ ስራዎች ቢኖሩም ቀላል ግምት የማይሰጣቸው እጥረቶችም አሉ። በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ

አይነት የጋራ እምነትና አመለካከት የመፍጠር አስፈላጊነትና ይህን የመሰለው የጋራ አገራዊ አቋም ለልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን መሳካት ያለው ወሳኝ አስተዋፅኦ በቂ ግንዛቤ የተያዘበት ጉዳይ አልነበረም:: በመሆኑም እንደዚህ አይነቱን የጋራ እምነት በአፋጣኝ ለመፍጠር መንግስት መስራት የሚገባውን ስራ ሁሉ ሰርቷል ሊባል አይቻልም:: የትምህርት ተቋሞች የጋራ እምነቱን በመፍጠር ረገድ ያላቸውን ቁልፍ ሚና በተሳካ ሁኔታ እንዲፈፅሙ ለማድረግ አጥጋቢ ስራ አልተሰራም:: የመንግስት ሚድያ በዚህ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለማበርከት ሲችልና ሲገባው ተልእኮውን በሚገባ ሳይወጣ ቀርቷል:: በህገ-መንግስትና በዚሁ ላይ በመመስረት መንግስት በሚነድፋቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ መላውን ህብረተሰብ ያሳተፈ ውይይት በሚፈለገው ደረጃ የተካሄደ አልነበረም:: ከመንግስት ውጭ ያሉ ተቋሞች ለዚሁ አገራዊ ተልእኮ የየበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ በቂ ጥረት አልተደረገም::

መንግስት በአሁኑ ወቅት እነዚህን ጉድለቶች ተገንዝቦ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን በይበልጥ የተሳካና የተቀላጠፈ እንዲሆን ለማድረግ የተስተካከሉ አቅጣጫዎችን ቀይሷል:: በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ የጋራ አገራዊ እምነት መቅረፅ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታውም ሆነ ለልማቱ ወሳኝ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳለው በማመን በዚሁ ስራ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ ጀምሯል:: የትምህርት ተቋማት ለዚህ ስራ በቂ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ የማስተካከያ ርምጃዎችን መውሰድ ጀምሯል:: የመንግስት ሚድያም ድርሻውን እንዲወጣ



ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው:: ህገ-መንግስቱን መሰረት በማድረግ የሚወጡ የመንግስት መሰረታዊ አቅጣጫዎች እየተዘረዘሩ ለህዝቡ እንዲሰራጩና ውይይት እንዲደረግባቸው የማድረግ ስራም ተጀምሯል:: ከመንግስት ውጭ ያሉትንና ለዚሁ ስራ በጎ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ አካላትን ለማሳተፍም ሙከራ እየተደረገ ነው:: የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ስራችን በነዚህ ጥረቶች መሳካት ላይ የተንጠለጠለ ነው:: ስለሆነም በዚህ መልክ የተጀመረውን ስራ አጠናክሮ መቀጠልና ከሚገኘው ልምድ በመነሳት በቀጣይነት ማሻሻል በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአትን የመገንባት ትግላችን አንድ ወሳኝ ገፅታ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል::

ሰፊ የማስተማርና ቅስቀሳ ስራ መላውን ህዝብ የሚያሳትፉ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ በሚካሄድ በሳልና ዴሞክራሲያዊ ውይይት ታጅቦ ሲፈፀም ለዴሞክራሲያችን ማበብ መሰረት የሚሆነውን አንድ አገራዊ እምነት፣ የዴሞክራሲ አመለካከትና ባህል በመፍጠር ረገድ ረጅም ርቀት የሚወስደን ቢሆንም ብቻውን ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝልን የሚችል አይሆንም:: ዞሮ ዞሮ ህዝቡ እምነቱን የሚመሰርተው ከተጨባጭ ተግባርና ልምዱ በመነሳት ነው:: ከተግባር ጋር ያልተያያዘ፣ በተግባር ያልተደገፈ ትምህርትና ውይይት የጠንካራ እምነት መሰረት ሊሆን አይችልም:: ስለሆነም ስለ ዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና ስለልማት የምናስቀምጣቸውን መሰረታዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ በዚሁ የአፈፃፀም ሂደት ህዝቡን በሰፊው ለማሳተፍ ይህንን የተግባር እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ ህዝቡ

የአቅጣጫዎቹን ትክክለኛነት በይበልጥ እንዲገነዘብና አቅጣጫዎቹን ራሳቸውን እንዲያጎለብታቸው ማድረግ አለብን፡፡ የቀየስናቸው አቅጣጫዎች ለሰፊ ተግባራዊ ርብርብ፣ ተግባራዊ ርብርቡ ደግሞ የተቀየሱትን አቅጣጫዎች ለማስረፅና ለማዳበር መነሻ እንዲሆኑ ሁለቱም በቅርብ ተሳስረውና ተመጋግበው እንዲፈፀሙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ህዝቡ በየዕለቱ በረሃብና በበሽታ በሚገረፍባት አገር ተሯሩጦ ወደተግባር መግባት እንጂ ይህን ያህል ትምህርትና ቅስቀሳ፣ ይህን ያህል ስብሰባና ውይይት ለምን ያስፈልጋል፣ ጊዜን በከንቱ ማባከን አይሆንም ወይ የሚል ሃሳብ ይነሳል፡፡ በርግጥ ድህነትን በውይይት ሳይሆን በተጨባጭ የልማት ተግባር ነው የምናስወግደው፡፡ ስለሆነም ለተግባራዊ ርብርብ የሚሆን በቂ ጊዜ ሊኖረን ይገባል፡፡ ውይይቶችን ውጤታማ በሚሆኑበት አኳኋን ማቀድ፣ ማስፈፀምና በተቻለ መጠን እንዲያጥሩ ማድረግ አለብን፡፡ ነገር ግን ይህ የጋራ አመለካከትና እምነትን ለመፍጠር የሚደረገውን የትምህርትና የውይይት ስራ በከንቱ ጊዜ ማጥፋትና ስራን አለመስራት ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ የልማት ስራችን የተሳካ ሊሆን የሚችለው የተስተካከለ የልማት አቅጣጫ ሳንይዝ የእውር ድንበራችንን ስለተወራጨን አይደለም፡፡ የተስተካከለ የልማት አቅጣጫ ይዘን፣ ሁሉም ይህን አቅጣጫ አውቆ የየድርሻውን ለማበርከት በሰፊውና በተደራጀ አኳኋን ሲንቀሳቀስና የተገኘውን ልምድ እየቀመረ ሲያሻሽል ነው፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን የሚሳካውም ተመሳሳይ ስራ ሲሰራ ነው፡፡ በመሆኑም ትምህርቱ፣ ቅስቀሳው፣ ውይይቱ ተጨባጩን



የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራ በብቃት ለመፈፀም የሚከናወን፣ የተግባሩ አመራርና የተግባሩ አካል የሆነ ስራ እንጂ ከዚሁ የተነጠለ የጊዜ ማባከኛ አይደለም፡፡

ይሁንና ትምህርቱና ውይይቱ በርግጥም የተግባራዊ ርብርቡ አካል ሊሆን የሚችለው የተፈለገውን አመለካከት በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያሰፍን፣ ያልተንዛዛና ውጤታማ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ውጤት አልባና የተንዛዛ ስብሰባ የተግባራዊ ርብርባችን አካል ሳይሆን በርግጥም ወርቃማ ጊዜያችንን ማባከኛ ከመሆን ሊዘል አይችልም፡፡ ከዚያም በላይ ትምህርቱና ውይይቱ ወደተጨባጭ ተግባር የሚያሸጋግረን፣ ተጨባጭ ተግባራችንን በተሻለ አኳኋን ለመፈፀም የሚያስችለን መሆን አለበት፡፡ በቀጥታ በተሻለ የተግባር ርብርብ የማይመነዘር ውይይት ከንቱ ስራና ወርቃማ ጊዜያችንን ማባከኛ ከመሆን አያልፍም፡፡ ትምህርትና ውይይቶች በቀጥታ በተስተካከለ አቅጣጫና አፈፃፀም በሚመራ ተግባር ከመመንዘር፣ ይህንን ከመምራት አልፈው ከእያንዳንዱ ተጨባጭ ተግባር የላቀ ትምህርት የምንወስድባቸው፣ ልምዶችን ቀምረን ስራችንን የምናሻሽልባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ በሌላ አገላለፅ ትምህርትና ውይይቶቹ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራችን የማይነጠሉ አካላት የሚሆኑት ተግባርን አጅበውና ማዕከል አድርገው በብቃትና በሚፈለገው ፍጥነት እስከተፈፀሙ ድረስ ነው፡፡ ውይይትና ትምህርቶቹ የተግባር መነሻ ይሆናሉ፣ አላማና ግባቸውም የላቀ ውጤት የሚያስገኝ ተግባር እንዲኖር ማድረግ ይሆናል፡፡ ውይይትና ትምህርቶቹ ከተጨባጭ ተግባር በመነሳት ትምህርትና ልምድ የምንቀስምባቸው ይሆናሉ፡፡

የውይይትና ትምህርቶቹ መነሻና መድረሻ ተጨባጭ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ስራ ይሆናል፡፡ እነዚህን በጥብቅ በማቀናጀትና በብቃት በመፈፀም የዴሞክራሲያዊ ስርአታችን አንዱ መሰረት የሆነውን የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት፣ የጋራ የዴሞክራሲ አስተሳሰብና ባህል መፍጠር እንችላለን፡፡

የዴሞክራሲ ስርአትን በአገራችን ለመገንባት ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ የዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ተቋሞችና ድርጅቶች የመፍጠሩና የማጠናከሩ ስራ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ተጨባጭ የአፈፃፀም ተግባሮች መከናወን የሚችሉት በነዚህ ተቋሞችና ድርጅቶች አማካኝነት ስለሆነ እነዚህ በሌሉበትና ባልተጠናከሩበት ምንም አይነት አስተሳሰብ ቢኖር ዴሞክራሲ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የአፈፃፀሙ መቋጫ እነዚህን ድርጅቶች የመፍጠርና የማጠናከር ስራ ነው፡፡ የዴሞክራሲ አስተሳሰቡና ባህሉ ራሱ በተናጠል በሚካሄድ ንድፈ-ሃሳባዊ ውይይት ሳይሆን በተግባርም መደገፍ ያለበት በመሆኑና እነዚህ ድርጅቶችና ተቋሞች ተግባሩ የሚከናወንባቸው መድረኮች ስለሆኑ አስተሳሰቡን በመቅረፅ ረገድም የላቀ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አስተሳሰቡ መጎልበቱ ለነዚህ ድርጅቶች መጠናከር መሰረት ይሆናል፡፡ ስለሆነም አስተሳሰቡን ለመቅረፅ የሚሰራው ስራና የዴሞክራሲ ተቋማትና ድርጅቶችን ለመፍጠርና ለማጠናከር የሚሰራው ስራ የተሳሰሩና ተመጋጋቢ ናቸው፡፡

አስተሳሰቡን ለመቅረፅ ምን አይነት ስራ መሰራት እንዳለበት ከላይ በአጭሩ አስቀምጠናል፡፡ በሌሎች ፅሁፎችም



ይበልጥ ዘርዘር ባለ አኳኋን ተገልጿል፡፡ በትምህርት ቤቶች የዴሞክራሲ አስተሳሰብና ባህል ለመቅረፅ መሰራት የሚገባውን ስራ በተመለከተ ቀደም ብሎ በተዘጋጀ ፅሁፍ የቀረበው በምሳሌነት ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ፅሁፍ ላይ በዋነኛነት የሚተኮረው የዴሞክራሲ ተቋሞችና ድርጅቶችን በመፍጠርና በማጠናከር ረገድ መሰራት በሚገባው ስራ ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ መሰራት ያለባቸው ዋና ዋና ስራዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 2. የህዝብ ምክር ቤቶችና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣

### 2.1. ምክር ቤቶች በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ ያላቸው ሚና፣

ህገ-መንግስታችን ሉአላዊነት ሲባል የህዝብ ሉአላዊነት ማለት እንደሆነ፣ ይህ የህዝብ ሉአላዊነት ከሚገለፅባቸው መሰረታዊ መልኮች አንዱና ዋነኛውም ህዝቡ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን በሚመርጣቸው ተወካዮች አማካኝነት እንደሆነ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ በመነሳት በየደረጃው በህዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስለሚቋቋሙት ምክር ቤቶች ስልጣንና ሃላፊነትም ይደነግጋል፡፡ ምክር ቤቶች የህዝቡ ሉአላዊነት መገለጫ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እምብርትና የዴሞክራሲያዊ አገዛዝ አውራ ተቋሞች ናቸው፡፡ ሌሎቹ የዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ተቋሞችና ድርጅቶች የሚመሰረቱት በምክር ቤቶቹና ምክር ቤቶቹ በሚሰሯቸው ስራዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የነዚህ ምክር ቤቶች

መቋቋምና መጠናከር ለዴሞክራሲያዊ ስርአታችን መጠናከር ወሳኝ ነው።

ምክር ቤቶች በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ተወያይተው የአገሪቱ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና የልማት ስራዎች የሚከናወኑባቸው ህጎች ያወጣሉ፣ ስራዎችን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ በጀት ያፀድቃሉ። የህግ አስፈፃሚው አካል ስራውን የሚያከናውነው በምክር ቤት የተሰጠውን በጀት በመጠቀም በምክር ቤት የፀደቁትን ህጎች በማስፈፀም ነው። ከዚህ ውጭ አንድ ጋት መንቀሳቀስ አይችልም፣ አይገባውምም። በተመሳሳይ መልኩ የዳኝነት ስርአቱ ስራውን የሚሰራው ምክር ቤቶቹ ባፀደቁለት በጀትና ምክር ቤቶቹ ያወጡትን ህግ በመተርጎም ነው። ከዚህ ውጭ አንድ ጋት መንቀሳቀስ አይችልም፣ አይገባውምም። ህዝቡም ቢሆን በተደራጀም ሆነ ባልተደራጀ አኳኋን የሚያከናውናቸው ተግባራት ምክር ቤቶቹ ባወጧቸው አዋጆችና እነዚህን መሰረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ነው።

የዴሞክራሲ ስርአት በህግ የበላይነት መርህ ላይ የሚመሰረት ስርአት ስለሆነ፣ የበጀት አዋጆችን ጨምሮ ሁሉም አዋጆች የሚወጡት በምክር ቤቶች በመሆኑና ሌሎቹ የህዝብና የመንግስት አካላት በነዚህ የሚመሩና የሚገዙ በመሆናቸው ምክር ቤቶቹ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታችን ሂደት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ይሆናሉ። በመሆኑም ምክር ቤቶች የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎቻችን የሚመሩባቸው



የተስተካከሉ ውጤታማና ዴሞክራሲያዊ ህጎችን ለማውጣት የሚያስችል ብቃትና ጥንካሬ ሊኖራቸው ይገባል። ዴሞክራሲያችን በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ መሆን ስላለበት ህጎች በማውጣት ሂደት ህዝቡ በየደረጃው ተሳታፊ የሚሆንበት፣ ከወጡ በኋላም ህዝቡ ስለህጎቹና ከህጎቹ በስተጀርባ ስላሉ መሰረታዊ የልማትና የዴሞክራሲ አቅጣጫዎች የተሟላ ግንዛቤ እንዲይዝ የማድረግ አሰራርና ብቃት ሊኖራቸው ይገባል።

በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች አዋጆችን ከማውጣት ባሻገር የህግ አስፈፃሚውን አካል የሚሾሙና የሚሽሩ ናቸው። ዳኞችም የሚሾሙትና በመጨረሻም የሚሻሩት በምክር ቤቶች ነው። በሌላ አነጋገር ሌሎቹን የመንግስት አካላት የመሾምና የመሻር ስልጣን የምክር ቤቶች በመሆኑ ከሁሉም የበላይና የህዝቡ ሉአላዊነት መገለጫ ይሆናሉ። ከዚህ በመነሳት ምክር ቤቶች ህግ አስፈፃሚው አካል ስራውን በአግባቡና ምክር ቤቱ ባፀደቃቸው ህጎች፣ ምክር ቤቱ ባፀደቀው በጀት እየፈፀመ መሆኑን በቅርብ የመከታተልና አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች እንዲደረጉ የማዘዝ ስልጣን አላቸው። ምክር ቤቶች በዚህ አኳኋን ስራቸውን ሲያከናውኑ የህግ አስፈፃሚው አካል ስራውን በብቃት የማይፈፅም ሆኖ ሲያገኙት የመሻር መብትም ይኖራቸዋል። የዳኝነት አካሉ ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቶች ዳኞች ስራቸውን በህጉ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን የመከታተል መብት አላቸው። በዳኞች አስተዳደር ጉባኤዎች አማካኝነት በመከታተልና በሚቀርቡላቸው ሪፖርት ላይ በመመስረት በህጉ መሰረት ለመስራት ብቃቱ ወይም ፍላጎቱ የሚጎድላቸው ዳኞች እንዲሻሩ

የማድረግ መብት አላቸው። ምክር ቤቶች የህግ አስፈፃሚውንና የዳኝነት አካሉን በብቃት የመከታተልና የመቆጣጠር ስራቸውን መፈፀም ሲችሉ ነው የዴሞክራሲ ስርአቱ በአጠቃላይ ሊጎለብትና ሊዳብር የሚችለው።

## 2.2. በምክር ቤቶች አካባቢ የሚታዩ ጉድለቶች፣

የህዝቡ ሉአላዊነት መገለጫ በመሆንና ብሄር/ብሄረሰቦች የየራሳቸውን አካባቢ ራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውን መሰረት በማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ተቋቁመዋል። በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ምክር ቤት ሲሆን በየክልሉና በየወረዳው ወዘተ. የተቋቋሙት ምክር ቤቶች ግን ቋሚ አይደሉም። በየደረጃው ያሉት እነዚህ ምክር ቤቶች ስራቸውን በብቃት ለመፈፀም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚያጋጥሟቸው በርካታ እንቅፋቶች አሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ መቀመጥ ያለበት ችግር የአባላቱ ብቃት ነው። የምክር ቤቶቹ ስልጣንና ተግባር ምን ያህል ሰፊና ወሳኝ እንደሆነ፣ ምክር ቤቶቹ ሃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸው ለዴሞክራሲያዊ ስርአታችን ማበብ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ በመገንዘብ ረገድ በምክር ቤት አባላትም ሆነ በሌላው የህብረተሰብ ክፍል፣ በየደረጃው ባሉ የህግ አስፈፃሚ አካላት ወዘተ. በቂ ግንዛቤ የተያዘበት ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም ምክር ቤቶቹ ሃላፊነታቸውን በሚገባ እንዲወጡ



የማብቃቱ ስራ በቂ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም። የምክር ቤት አባላትና መላው ህብረተሰብ የምክር ቤቶችን ሚናና ሃላፊነት በሚገባ እንዲገነዘብና ምክር ቤቶቹን እንደሉአላዊነቱ መገለጫዎች በአግባቡ እንዲገለገልባቸው ማድረግ ያስፈልጋል። የምክር ቤት አባላት ከዚሁ አጠቃላይ ግንዛቤ ባሻገር ስራቸውን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችላቸው ትምህርትና ስልጠና በተከታታይነት ማግኘት ይገባቸዋል።

ቋሚም ሆኑ ቋሚ ያልሆኑ ምክር ቤቶች ስራቸውን በአግባቡ ለመምራት በተገቢው መንገድ መደራጀት አለባቸው። የምክር ቤቶች ኮሚቴዎች ከዚህ አኳያ የላቀ ሚና መጫወት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም። በየስራ መስኩ የተደራጁ ጠንካራ ኮሚቴዎች በሚኖሩበት ወቅት በየስራ መስካቸው እየተፈፀሙ ያሉትን የመንግስት ስራዎች ይከታተላሉ። በዚህ ረገድ በህዝቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና መረጃዎችን ያዳምጣሉ፣ ያጣራሉ። እንደአስፈላጊነቱ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት እየጠሩ ያነጋግራሉ፣ ሪፖርት ያዳምጣሉ። በስራ መስካቸው ጠቃሚ ሃሳብና አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ ብለው የሚያስቧቸውን ግለሰቦችና የተለያዩ ማህበራት መሪዎች እየጠሩ ያነጋግራሉ፣ አስተያየት ያዳምጣሉ። በነዚህ ላይ በመመስረት አዋጆች እንዲቀረፁ የተቀረፁትም እንዲስተካከሉ ያደርጋሉ፣ መስተካከል የሚገባቸውን ነገሮች በሚመለከት አስተያየታቸውን ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ። የህግ ረቂቆች በሚቀርቡበት ወቅት ጉዳዩን በዝርዝር አጥንተው ምክር ቤቱ እንዲወስንባቸው ያደርጋሉ። እንደዚህ አይነቶቹ ጠንካራ ኮሚቴዎች

አለመቋቋማቸው ምክር ቤቶቹ ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር በመሆኑ በየደረጃው ኮሚቴዎች እንዲፈጠሩ፣ ስራቸውን በሚመለከት በቂ ስልጠናና ትምህርት እንዲሰጣቸውና በአጠቃላይም በቀጣይነት እንዲጠናከሩ ማድረግ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው::

እንደኛ ባለው -ርላማዊ ስርአት ለምክር ቤቶች የሚቀርቡት ረቂቅ አዋጆችና የበጀት ረቂቅ ሃሳቦች በወሳኝ መልኩ የሚረቀቁት በህግ አስፈፃሚው ነው:: በመሆኑም ህግ አስፈፃሚው እነዚህን ረቂቆች በበቂ ጥናትና የሙያተኛ ምክር ላይ ተመስርቶ ማዘጋጀት መቻል አለበት:: ዴሞክራሲያችን በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ መመስረት ስላለበት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ህዝብ እንዲመክርበትና አስተያየትም እንዲሰጥበት ማድረግ አለበት:: ረቂቅ ሃሳቦቹ ወደምክር ቤቶች በሚቀርቡበት ወቅት ከበስተጀርባቸው ያለውን መሰረታዊ አቅጣጫ በአግባቡ ለማሳየት በሚያስችል አኳኋን በቂ ማብራሪያ መስጠት መቻል አለበት:: እነዚህ ስራዎች በብቃት በሚፈፀሙበት ወቅት ምክር ቤቶች ስራቸውን በአግባቡ ለመፈፀም የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል:: ይሁንና ምክር ቤቶች በዚህ ላይ ብቻ መታጠር የለባቸውም:: ስራቸውን ለመስራት የሚረዳቸው የራሳቸው የድጋፍና ምክር አገልግሎት ሰጭ አቅም ሊኖራቸው ይገባል:: ይህ በተለይም ቁልፍ ሚና በሚጫወተውና ቋሚ በሆነው የፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ደረጃ የማይታለፍ ስራ ነው::



የበለፀገ የዴሞክራሲ ባህል ባላቸው -ርላማዊ ስርአቶች በምክር ቤቶች ውስጥ የተለያየ አመለካከት ያላቸው -ርቲዎች ይወከላሉ:: -ርቲዎቹ በሁሉም መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የየራሳቸው የተተነተነ አማራጭ ይኖራቸዋል:: በመሆኑም ገዥው -ርቲ አንድ ሃሳብ በሚያቀርብበት ወቅት ተቃዋሚ -ርቲዎች የሚደግፉትን ደግፈው የሚቃወሙትንም ለምን እንደሚቃወሙት አብራርተው ያስረዳሉ፣ የተሻለና ተኪ አማራጭ ነው ብለው የሚያስቡትንም ሃሳብ ያቀርባሉ:: በዚሁ አኳኋን በ-ርላማ መድረኮች በተለያዩ አማራጭ ሃሳቦች ዙሪያ በሳልና ገንቢ ውይይት ይካሄዳል:: በዚሁ ሂደት ሃሳቦቹ በሚገባ ተብላልተው በጥልቀት የታየና የተተነተነ ውሳኔ ሊወሰን የሚችልበት ዕድል ይፈጠራል:: ህዝቡም ውይይቶቹን ለመከታተል ዕድል ተሰጥቶት በጉዳዮቹ ላይ የተሟላ ግንዛቤ ሊይዝ ይችላል::

በአገራችን በተቋቋሙት ምክር ቤቶችም፣ በተለይም በፌዴራል ደረጃ በተቋቋመው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተቃዋሚ ድርጅቶች ተወካዮች ይገኛሉ:: ይሁንና በዳበረ የ-ርላማ ስርአት እንደሚታየው በ-ርቲዎች መካከል በመሰረተ ሃሳቦች ዙሪያ በሳል ክርክር ሲካሄድ አይታይም:: ገዥው -ርቲ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የፖሊሲ አቅጣጫዎቹን ለምክር ቤቱ ተንትኖ በማቅረብ፣ አዋጆች ረቂቅ ሃሳቦች በሚቀርቡበትም ወቅት ከአዋጆቹ በስተጀርባ ያሉትን መሰረታዊ የአቅጣጫ ጥያቄዎች በሚያካትት አኳኋን በማብራራት ለበሳል ውይይትና ክርክር መነሻ የሚሆን አቀራረብ ያልነበረው መሆኑ ለዚህ ችግር አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ነው:: በዚህ ረገድ እየታዩ ያሉ

መሻሻሎች ለወደፊቱም ተጠናክረው መቀጠል የሚገባቸው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በምክር ቤቶች የተወከሉት የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት በዚህ መልኩ በሳል ውይይት ለማድረግ በቂ ዝግጅት፣ አቅምና አልፎ አልፎም ፍላጎቱ የሚጎድላቸው መሆኑ ሌላው መሰረታዊ ምክንያት ነው፡፡ የድርጅቶቹ ዝግጅትና አቅም እየተሻሻለ ሲሄድ ችግሩ አብሮ እንደሚቀረፍ ለመገመት ይቻላል፡፡

ይህ እስኪሆን ድረስ ግን ምክር ቤቶቹ የተለያዩ -ርቲዎች በመሰረተ-ሃሳቦች ዙሪያ በሚፈለገው መጠንና ጥልቀት በብቃት የሚከራከሩባቸው መድረኮች አይሆኑም፡፡ ይህም ምክር ቤቶቻችን ተልእኳቸውን በአግባቡ እንዳይፈፅሙ በማድረግ ረገድ የማይናቅ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡ ይህንን ችግር ለማስወገድ በአንድ በኩል ገዥው -ርቲ የጀመረውን -ሊሲዎቹን ዘርዝሮ ለምክር ቤቶች የማቅረብ አሰራር በሁሉም ደረጃዎች ተጠናክሮ ሊቀጥል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ -ርቲዎች በተመሳሳይ መልክ ሃሳባቸውን ለማቅረብ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የምክር ቤት አባላት ባይሆኑም የተለያዩ አማራጮችን ተንትነው ማቅረብ የሚፈልጉና የሚችሉ ግለሰቦችና የተለያዩ ማህበራት ተወካዮች መኖራቸው ስለማይቀር ለነዚህ ዕድል የሚሰጥበት አማራጭ መፈለግ ይኖርበታል፡፡ ቢያንስ ኮሚቴዎች በሚጠሯቸው መድረኮች ላይ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህ አሰራር -ርቲዎች ደካማ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ ተግባራዊ የሚሆን አሰራር አይደለም፡፡ ዴሞክራሲያችን በህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ መመስረት ያለበት በመሆኑም ጭምር እንጂ፡፡



በ-ርላማዊ ስርአት የፖለቲካ ስልጣን የሚይዘው በምክር ቤት አብላጫ ድምፅ ያለው -ርቲ ነው፡፡ በምክር ቤቱ ያሉ የገዥው -ርቲ አባላት የ-ርቲያቸውን -ሊሲና መስመር የምክር ቤት መድረኮችን ጨምሮ በየትኛውም መድረክ የመደገፍ መብትና ግዴታ አለባቸው፡፡ የ-ርቲውን -ሊሲ የማይደግፉ -ርቲውን ወክለው መቀመጥ አይችሉምና፡፡ ስለሆነም በምክር ቤቶች በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ክርክር የሚካሄደው በአንድ -ርቲ አባላት መካከል ሳይሆን በተለያዩ -ርቲዎች መካከል ነው፡፡ ይሁንና የገዥው -ርቲ አባላትም ቢሆኑ በስራ አፈፃፀምና ክትትል ጉዳዮች ላይ ስራ አስፈፃሚውን በቅርብ ሲቆጣጠሩ፣ ስህተቶችን ሲያጋልጡና እንዲስተካከሉ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ ይህም የ-ርቲያቸው -ሊሲ በአግባቡ መፈፀሙን ከመቆጣጠር ተለይቶ የማይታይና የ-ርቲ ግዴታቸውም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በተለያዩ ምክር ቤቶች የገዥው -ርቲ አባላትና ደጋፊዎች ብቻ አባላት የሚሆኑበት አጋጣሚ ይከሰታል፡፡ ስለሆነም በመሰረታዊ -ሊሲዎች ላይ እስከ መጨረሻው የሚገፉበት ክርክር ሊካሄድ የሚችልበት መሰረት አይኖርም፡፡ በዚህ ላይ የገዥው -ርቲ አባላት ፖሊሲዎች በትክክል እየተፈፀሙ መሆናቸውን በመቆጣጠር ረገድ ጠንካራ ሚና መጫወት እንዳለባቸው በቅጡ ያልተገነዘቡበት ሁኔታ ይታያል፡፡ የዚሁ ድምር ውጤት ምክር ቤቶች ስራቸውን በአግባቡ ሊወጡ የማይችሉ እንዲሆኑ ማድረግ ይሆናል፡፡ በምክር ቤት -ርቲዎችን ወክለው የሚሳተፉ ሰዎች የ-ርቲያቸውን -ሊሲ የመደገፍ ግዴታ ቢኖርባቸውም፣ የ-ርቲውን መሰረታዊ -ሊሲ

መደገፍ ከህሊናቸው ጋር የሚጋጭ ሲሆን -ርቲውን የመልቀቅ አማራጭ ብቻ ያላቸው ቢሆንም፣ የሚቀርቡት የፖሊሲ ሃሳቦች በሚገባ ተብላልተው ውይይት እንዲደረግባቸው በተለያየ መንገድ ጥረት ማድረግ እንደሚችሉና እንደሚገባቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚያም በላይ በፖሊሲ አፈፃፀም ላይ ህግ አስፈፃሚውን በጥብቅ የመቆጣጠር ግዴታና መብት እንዳላቸው ተገንዝበው በብቃት እንዲፈፅሙት ሁኔታው ሊመቻችላቸው ይገባል። በመጨረሻም የተለያዩ አስተያየቶች ያሏቸው የምክር ቤት አባላት ያልሆኑ ግለሰቦችና የማህበራት መሪዎች ሃሳባቸውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ የሚችሉበት ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። ይህ የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ከማረጋገጥ አላማም አኳያ መደረግ ያለበት ነው።

በክልልና ከዚያ በታች ያሉት ምክር ቤቶች የተወካዮች ምክር ቤቶችና የህግ አስፈፃሚው አካል በውል ተለይተው ሳይደራጁ መቆየታቸው፣ ምክር ቤቶች የህግ አስፈፃሚውን አካል በብቃት ለመቆጣጠርና ስራቸውን በአግባቡ ለመፈፀም እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። ይህ ጉድለት በበርካታዎቹ ክልሎች የተስተካከለ ሲሆን በሌሎችም በቀጣይ ጉዞ መስተካከል ያለበት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መታየት ያለበት ጉዳይ ምክር ቤቶች በህዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መቋቋም ያለባቸው ቢሆኑም በሁሉም አካባቢዎች የግድ አንድ አይነት ባህሪ ሊኖራቸው ይገባል ማለት እንዳልሆነ ነው። ለምሳሌ ከአርብቶ አደሩ አካባቢ ካለው የህብረተሰብ የጎሳ አወቃቀርና አደረጃጀት ጋር ተያይዞ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ የህዝቡን ተሳትፎ ይበልጥ ለማረጋገጥ በሚያስችል



አኳኋን ለመጠቀም የተለያዩ ስልቶች ሊቀየሱ ይችላሉ። የህዝብ ዴሞክራሲያዊ ውክልናን መርህ እስካልተፃረሩ ድረስ የተለያዩ አማራጮችን በመዳሰስ ምክር ቤቶችን ማዋቀር ህገ-መንግስታችንን ከየአካባቢው ልዩ ሁኔታ ጋር እያጣጣሙ መተግበር እንጂ ህገ-መንግስቱን መፃረር አይሆንም።

ምክር ቤቶች በተለይም ከፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በታች ያሉት ምክር ቤቶች ቋሚ ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞ ስብሰባዎቻቸውን በተመደበው ጊዜና በብቃት እንዲፈፀም ያለማድረግ ችግር አለባቸው። ምክር ቤቶቹ መደበኛ ስብሰባቸውን በወቅቱ የማካሄዳቸው ጉዳይ በጥብቅ መፈፀም ያለበት ጉዳይ ነው። ይህ በማይሆንበት ወቅት የዴሞክራሲያዊ ስርአታችን እምብርት የሆኑት ምክር ቤቶች ሽባ የመሆንና የስርአቱን ዴሞክራሲያዊ ባህሪ በአጠቃላይ አደጋ ላይ የመጣል ሁኔታን ሊያስከትል ይችላል። ስብሰባዎች በመደበኛ ጊዜያቸው እንዲፈፀሙ ከማድረግ በተጨማሪ ስብሰባዎቹ በቂ ዝግጅት የተደረገባቸውና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ የምክር ቤት አባላት የፖሊሲዎችን አፈፃፀም በሚመለከት የራሳቸውንና የህዝቡን ትዝብት አጠናቅረውና አጣርተው መቅረብ መቻል ይኖርባቸዋል። በተቻለ መጠንም የስብሰባዎቹ አጀንዳዎች አስቀድመው ለአባላት ሊገለፁና ሊዘጋጁባቸው ይገባል። ህግ አስፈፃሚ አካላት ዝርዝርና የተሟሉ ሪፖርቶችንና በአግባቡ የተተነተኑ የውሳኔ ሀሳቦችን ለምክር ቤቱ ማቅረብ መቻል አለባቸው። የምክር ቤት አባላት እነዚህን በሚገባ ለማጥናትና በነሱ ላይ ለመወያየት በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው

ይገባል። ቋሚ ባልሆኑ ምክር ቤቶችም ኮሚቴዎች ተደራጅተው የምክር ቤቶቹን ውይይቶች ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ስራ እንዲሰሩ መደረግ አለበት።

## 3. የህግ አስፈፃሚው አካልና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣

### 3.1. ህግ አስፈፃሚው በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ላይ ያለው ሚና፣

ከላይ እንደተጠቀሰው የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫ የሆነውና የዴሞክራሲያዊ ስርአታችን እምብርት የሆነው ተቋም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። ይሁንና ህግ አስፈፃሚውም አካል በዚህ ተግባር ላይ ቁልፍ ሚና አለው። በመሆኑም በአገራችን ብዙውን ጊዜ መንግስት እየተባለ የሚጠራው ህግ አውጭውን፣ ህግ አስፈፃሚውንና ህግ ተርጓሚውን (ምክር ቤቶች፣ መስተዳድሩና የዳኝነት ስርአቱን) በሙሉ ያጣመረው ሳይሆን ህግ አስፈፃሚው (መስተዳድሩ) ብቻ ነው።

ምክር ቤቶች ህግ ያወጣሉ፣ በጀት ያፀድቃሉ፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራሉ እንጂ ራሳቸው ፈፃሚዎች አይደሉም። በመሆኑም ምክር ቤቶቹ ለዴሞክራሲያዊ ስርአታችን ግንባታና ለልማታችን የሚበጁ ምርጥ ፖሊሲዎችና ማስፈፀሚያ ህጎች ቢያወጡ፣ ትክክለኛ በጀት ቢያፀድቁ ወዘተ. በሚፈለገው መልክ የሚፈፅማቸውና ተግባራዊ የሚያደርጋቸው አካል ከሌለ የወረቀት ላይ ጌጥ ሆነው መቅረታቸው የግድ ነው። የልማቱና



የዴሞክራሲያዊ ስርአቱ ግንባታ ስራውን የሚያከናውነው፣ ተግባራዊ የሚያደርገው የህግ አስፈፃሚው አካል ስለሆነ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ልዩ ግምት የሚሰጠው ሚና ይጫወታል። ይህንኑ ስራ በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል ብቃትና እምነት ያለው የህግ አስፈፃሚ አካል ሲኖር የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እቅዶች ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ። የህግ አስፈፃሚው አካል የህግ የበላይነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እንደ ፖሊሲና የመከላከያ ሃይል ያሉ ተቋሞችን የሚቆጣጠር በመሆኑ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታው ታማኝ ካልሆነ የዴሞክራሲ ተቋሞችን አፈራርሶ ስርአቱን ለአደጋ ሊያጋልጠው ይችላል። በተግባርም የዴሞክራሲ ስርአትን የመፈታተን አደጋ የሚመነጨው በአብዛኛው ከህግ አስፈፃሚው አካል ነው። በመሆኑም የህግ አስፈፃሚውን ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋም እንዲሆን አድርጎ መቅረፅና ይህንኑ መቆጣጠር ልዩ ግምት የሚሰጠው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ተግባር ይሆናል።

የህግ አስፈፃሚው አካል ሚና በምክር ቤቶች የሚፀድቁ ፖሊሲዎችንና ህጎችን የማስፈፀም ስራ ብቻ አይደለም። ዋናው ስራው ይኸው ቢሆንም ምክር ቤቶች ለሚወስኗቸው ውሳኔዎች ለሚያፀድቋቸው ህጎች ወዘተ. መነሻ የሚሆኑ ረቂቅ ሃሳቦች የማቅረብ ሃላፊነትም አለበት። በመሆኑም በምክር ቤቶቹ በራሳቸው የሚወጡት አዋጆችና የሚወሰኑት ውሳኔዎች በርግጥም ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የሚበጁ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከዚያም ባሻገር በምክር ቤቱ የሚወጡ

አዋጆችንና መሰረታዊ አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ ህግና ፖሊሲ የማውጣት ሚናም አለው፡፡ በዚሁ መሰረት ህገ-መንግስታችንና ብዙዎቹ በምክር ቤት የሚወጡ አዋጆች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብና መመሪያ እንደሚያወጣ ይደነግጋሉ፡፡ በሌላ አነጋገር በተወሰነ መልኩ ህግ የማውጣት ሚናም ይኖረዋል፡፡ ፖሊሲዎችን ማውጣት በተመለከተም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰፊ ሚና እንዳለው ህገ-መንግስቱ ይደነግጋል፡፡

የህግ አስፈፃሚው አካል የሚወጡትን ህጎችና መሰረታዊ አቅጣጫዎች የማስፈፀም ቁልፍ ሚና ያለውና እንደፖሊስና የመከላከያ ሃይል የመሳሰሉትን የህግ አስከባሪ ሃይሎችን የሚቆጣጠር በመሆኑ ህግና ፖሊሲ በማውጣት ረገድም በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፣ የዴሞክራሲ ስርአቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ፣ ይልቁንም ለዴሞክራሲ ስርአቱ መጠናከር ግንባር ቀደም ተዋናይ እንዲሆን አድርጎ የመቅረፁ ስራ ለግንባታው ስኬታማነት የላቀ ሚና የሚጫወት ስራ ይሆናል፡፡

## 3.2. የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ፣

የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆዎች በሁሉም አካላትና የስራ መስኮች መተግበራቸው ለዴሞክራሲ ስርአቱ መጠናከር ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ህገ-መንግስታችን በአንቀፅ 12 ላይ



የሚከተለውን ይደነግጋል፡፡

“ 1. የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡”

“ 2. ማንኛውም ሃላፊና የህዝብ ተመራጭ ሃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡”

ህዝቡ በመንግስት ውሳኔዎች ላይ በብቃት መሳተፍ የሚችለው ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት ሲችል ነው፡፡ ህዝቡ የመረጠው መንግስት በትክክል መስራቱን ለመቆጣጠር የሚችለው የመንግስት እቅዶችን፣ የእቅዶች አፈፃፀምን፣ የተገኙ ውጤቶችንና ያጋጠሙ ችግሮችን በሚመለከት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ሲያገኝ ነው፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻለ ነገሩ ሁሉ ግልፅ በመሆኑ ብቻ የአስተዳደር በደልና ብልሹነትን ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፡፡ ግልፅነቱ ራሱ በቀጥታ ከሚያስከትለው መሻሻል በላይ ህብረተሰቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በማግኘት ጉድለቶችን ለማስተካከል ርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ይችላል፡፡ ማን በምን አይነት መልክ ምን አይነት መንግስታዊ አገልግሎት እንደሚያገኝ በግልፅ በመቀመጡ ተጠቃሚው መብቱንና ግዴታውን አውቆ ለማስከበር የተሻለ ሁኔታ ያገኛል፡፡ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ በሁሉም የመንግስት አካላት ላይ (በምክር ቤቶች፣ መስተዳድሮችና የዳኝነት አካል) የሚሰራና መሰራትም ያለበት ሲሆን ከሁሉም በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የህግ አስፈፃሚው አካል

በነዚህ መርሆዎች መሰረት መስራቱን የማረጋገጡ ጉዳይ ነው፡፡

ህግ አስፈፃሚው አካል (መስተዳድሩ) የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ የሚያቀርባቸው የህግ ረቂቆች ወዘተ. ህብረተሰቡ በሚገባ የሚያውቃቸውና የተገነዘባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚያም አልፎ መሰረታዊ በሆኑት ላይ ህብረተሰቡ አስቀድሞ የተወያየባቸውና አስተያየት የሰጠባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ የግልፅነት መርህ በእነዚህ ወሳኝ በሆኑት የአቅጣጫ ጉዳዮች ላይ መጀመር አለበት፡፡ ነገር ግን መርሁ ከዚያም ባሻገር በመሄድ መፈፀም ያለበት ነው፡፡ እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን አይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ መውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ መንግስት የሚያወጣቸው እቅዶችና አፈፃፀማቸው፣ በዚሁ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና ውጤቶች ለህብረተሰቡ ትክክለኛና ወቅታዊ በሆነ አኳኋን መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

በአገራችን በተንሰራፋው ፀረ-ዴሞክራሲ ባህልና አሰራር ምክንያት የመንግስት አሰራር በግልፅነት መርህ የሚመራ ነበር ማለት አይቻልም፡፡ ከግልፅነት ይልቅ ድብቅነት እንደመርህ ተወስዶ ሲሰራበት ነበር ማለትም ይቻላል፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ከተጀመረና የግልፅነት መርህ የመንግስት መመሪያ መሆን እንዳለበት በህገ-መንግስታችን ከተደነገገ ወዲህም ቢሆን ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው መሻሻሎች ቢኖሩም መርሁ



በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ ሆኗል ማለት አይቻልም፡፡ በመሰረታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ህዝቡ ግልፅነት እንዲኖረው የተያዘው ጅማሮ መልካም ቢሆንም ይህ ወደፊት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው፡፡ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀጥታ የሚነኩ አዋጆች በሚወጡበት ወቅት ክፍሎቹን የሚወክሉ ወገኖች አስተያየት እንዲሰጡበት የማድረግ አሰራር ቋሚና በተደራጀ አኳኋን የሚፈፀም መሆን ይኖርበታል፡፡ እስካሁን የወጡ ፖሊሲዎችንና መሰረታዊ አዋጆችን ህዝቡ እንዲያውቃቸው ማድረግም ተፈላጊ ነው፡፡

የመንግስት እቅዶች ይዘትና የአፈፃፀማቸው መረጃም ቀጣይነት ባለው አኳኋን የሚቀርብ አልነበረም፡፡ የሚቀርበውም ቢሆን ወቅታዊነቱን የጠበቀ፣ ስለእቅዱና ስለአፈፃፀሙ የተሟላ ስእል ለማስጨበጥ የሚያስችል አልነበረም፡፡ ከዚህም አኳያ ምክር ቤቶች በእቅድ ውይይት መድረክነት፣ በእቅድ ሪፖርት ማቅረቢያና ግምገማ መድረክነት በሰፊው ማገልገል ሲችሉ ይህ አሰራር በሁሉም እርከኖች ቀጣይነት ባለው አኳኋን የሚፈፀም አልነበረም፡፡ ህዝቡ ስለእቅዶችና አፈፃፀማቸው መረጃ የማግኘት መብት ብቻ ሳይሆን በእቅድ አወጣጡና በአፈፃፀም ግምገማውም ላይ በቀጥታ ተሳታፊ የመሆን መብት አለው፡፡ በዚህ ረገድ ምንም እንኳ እቅዶቹ በምክር ቤቶች በሚፀድቁበትና በሚገመገሙበት ወቅት ህዝቡ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ቢሆንም በተለይም በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ በግልና በተለያዩ ማህበራቱ አማካኝነት ተሳታፊ መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚህ ረገድ የነበሩትን ጉድለቶች ለማስተካከል በየደረጃው ያሉ የመስተዳድር አካላት እቅዶቻቸውንና የአፈፃፀም ግምገማቸውን ለምክር ቤቶች የሚያቀርቡበት፣ በምክር ቤቶች በዝርዝር የሚፈተሹበትና ይኸው ሪፖርት ለህብረተሰቡ የሚቀርብበት መደበኛ አሰራር ሊኖርና በጥብቅ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል። የምክር ቤት ኮሚቴዎች የህግ-አስፈፃሚ አካላትን እየጠሩ የሚያካሂዷቸው መድረኮችም እቅዶችንና አፈፃፀማቸውን በዝርዝር ለማየትና፣ ይህንኑ ለህዝብ ለማሳወቅ የሚረዱ መሆን አለባቸው። የህግ አስፈፃሚው አካላት በመደበኛ አኳኋን ስለእቅዳቸውና ስለእቅድ አፈፃፀም ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ለህዝቡ በመገናኛ ብዙሃን እንዲቀርብ ማድረግም ይኖርባቸዋል። ህዝቡ በተለያዩ ማህበራቱ አማካኝነት በእቅድ አወጣጥና ግምገማ ስራ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን፣ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ህዝቡ በቀጥታ ተሳታፊ ሊሆን የሚችልባቸው በርካታ ዕድሎች ስላሉ እነዚህን በመደበኛ አሰራር መልክ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ስራ መስራት ይኖርበታል።

በየደረጃው ያሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለህብረተሰቡ የሚሰጡትን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ዝርዝርና ግልፅ መመሪያ በሚፈለገው መልኩ ቀርፀው የሚንቀሳቀሱ አይደሉም። ከዚያም በላይ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ምን አይነት አገልግሎት ከየት እንደሚያገኝና ይህን አገልግሎት ለማግኘት ምን ማሟላት እንዳለበት፣ ምን አይነት ስርአት መከተል እንዳለበት በይፋ እንዲያውቅ አይደረግም። በመሆኑም ተገልጋዩ መብቱንና ግዴታውን አውቆ መብቱ በትክክለኛ አኳኋን እንዲከበርለት



ለማድረግ አይችልም። ባልተሟላ መመሪያ ወይም በድብቅ በተያዘ ሽፋን የመንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ አካላት እንደመሰላቸው ለመስራት የሚያስችላቸው ሁኔታ ተፈጥሮ ቆይቷል። በዚህ ረገድም በሲቪል ሰርቪሱ አሰራር የግልፅነት መርህ በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ እጅግ ተፈላጊ ይሆናል።

የተጀመረው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጥርልናል። በፕሮግራሙ ውስጥ ከታቀፉት ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ሁሉም የመንግስት አካላት የሚሰጡትን መንግስታዊ አገልግሎት በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ እንዲያወጡና ይህንኑ መመሪያ ለተጠቃሚው እንዲያሳውቁ የማድረግ አሰራር ነው። ከዚያም ባሻገር መስሪያ ቤቶቹ ተጠቃሚውን የህብረተሰብ ክፍል በይበልጥ ለማገልገል በሚያስችል አኳኋን ራሳቸውን እንዲያደራጁ፣ ተጠቃሚው በህጉና በመመሪያው መሰረት በቂ አገልግሎት ሳያገኝ ሲቀር ቅሬታውን ሊያቀርብ የሚችልበት ቀልጣፋ ስርአት እንዲፈጥሩ ለማድረግ ታቅዷል። ይህን የለውጥ ርምጃ ከመንግስታዊ አገልግሎት ቅልጥፍና አኳያና የዴሞክራሲያዊ ስርአታችን መሰረታዊ መርህ የሆነውን ግልፅነትን ከማስፈን አኳያ ታይቶ በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ እጅግ ተፈላጊ ነው።

እንደኛ ባሉት -ርላማዊ የዴሞክራሲ ስርአቶች የህግ አስፈፃሚውን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚቻለው ስራ አስፈፃሚው ለምክር ቤቱ ካለው ተጠሪነት ጋር አያይዞ በማየት ነው። በ-ርላማ ስርአት የህዝብ የሉአላዊነት መገለጫዎች ምክር ቤቶች ናቸው።

ምክር ቤቶች በዚሁ መብታቸው የሚያስቀምጧቸውን መሰረታዊ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች እንዲያስፈፅሙላቸው የህግ አስፈፃሚው አካል ከፍተኛ የፖለቲካ ሃላፊዎችን ማለትም ሚኒስትሮችን ይሾማሉ:: በብዙ የ-ርላማ ስርአቶች ሚኒስትር ሆነው መሾም የሚችሉት የምክር ቤት አባላት ብቻ ናቸው:: በዚሁ አኳኋን ምክር ቤቱ ከራሱ አባላት የተወሰኑትን የዕለት ተዕለት አፈፃፀም የሚያስኬዱበት የህግ-አስፈፃሚው አካል የበላይ የፖለቲካ ሃላፊዎች ሹሞ በነዚህ አማካኝነት የህግ-አስፈፃሚውን በአጠቃላይ ይቆጣጠራል:: በኛ ሁኔታ ምንም እንኳ የምክር ቤት አባላት ያልሆኑም በሚኒስትርነት የሚሾሙ ቢሆኑም ዞሮ ዞሮ ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ የፖለቲካ ሹመኞች መሆናቸው አልቀረም::

ህግ-አስፈፃሚው የፖለቲካ ተሿሚዎችን ብቻ ያቀፈ አይደለም:: ይልቁንም በዋነኛነት በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ የሙያተኛ የሰው ሃይል ስብስብ ያለበት አካል ነው:: ሲቪል ሰርቪሱን በዋነኛነት የያዘ ሃይል ነው:: የተለያዩ የህግ አስከባሪ ክፍሎችንም ይይዛል:: እነዚህ ክፍሎች ቋሚ ሰራተኞችና ተቀጣሪዎች ቢሆኑም ዞሮ ዞሮ ተጠሪነታቸው በህዝብ ለተመረጠውና የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫ ለሆነው ምክር ቤት ነው:: ምክር ቤቱ ይህንን ለማድረግ ብዙውን ጊዜ ከራሱ አባላት ውስጥ ሚኒስትሮችን ይሾማል፣ በነዚህም አማካኝነት ህግ-አስፈፃሚው ህዝብ የመረጣቸውን ፖሊሲዎችና አዋጆችን በትክክል ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ይቆጣጠራል::

በዚሁም አኳኋን በህግ-አስፈፃሚው አካል ውስጥ ያሉት



የፖለቲካ ተሿሚዎች ስራቸው ምክር ቤቱ ያወጣቸውን -ሊሲዎችና አዋጆችን ሲቪል ሰርቪሱ በአግባቡ ተረድቶ በትክክል ተግባራዊ እንዲያደርግ መምራትና ይህንኑ በጥብቅ መቆጣጠር ነው:: ከዚሁ በተጨማሪ ምክር ቤቱ ለሚወስናቸው ውሳኔዎች በቂ የሙያተኛ የጥናትና ምክር አገልግሎት እየተገኘ መሆኑን ማረጋገጥ ነው:: እነዚህን መሰረት በማድረግ በምክር ቤቱ የወጡ መሰረታዊ አዋጆችና አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦች መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎችና እቅዶች ማዘጋጀት በትክክል መፈፃማቸውን ማረጋገጥ ነው:: ይህንን ስራ በትክክል ለመፈፀማቸው በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብም ይጠበቅባቸዋል:: ምክር ቤቱ ከተቀመጠው አቅጣጫ ውጭ የተሰራ ነገር ሲኖር፣ ወይም የተቀመጠው አቅጣጫ በትክክልና በብቃት ሳይፈፀም ቢቀር እንዲስተካከል የማድረግ፣ ከዚያም አልፎ የሚኒስትሮች ካቤኔውን እስከመሻር የሚሄድ ስልጣን አለው:: ምክር ቤቱ በመስተዳድሩ ላይ የሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር ብቃት ያለው መሆኑ መስተዳድሩ በተጠያቂነት መርህ የሚመራ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ቁልፍ ሚና የሚኖረውም በዚሁ ምክንያት ነው::

የፖለቲካ ተሿሚዎቹ በፈንታቸው ቋሚ የመንግስት ሰራተኞችና ሲቪል ሰርቪሱ በአጠቃላይ በምክር ቤቱ የተቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችና እነዚህን ለማስፈፀም የሚወጡ እቅዶች ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል መፈፀማቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል:: ሲቪል ሰርቪሱ ስራውና አላማው በህዝብ የተመረጠው መንግስት የሚያወጣቸውን እቅዶች፣ ፖሊሲዎችና

ህጎችን በብቃት ማስፈፀም፣ በዚህ ዙሪያ የምክርና የጥናት አገልግሎትን ማበርከት እንደሆነ እንዲገነዘብ ማድረግ ይገባቸዋል። በዚህ ላይ ተመስርተው ለሲቪል ሰርቪሱ የፖለቲካ አመራር መስጠትና መቆጣጠር ይገባቸዋል።

ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ሲቪል ሰርቪሱ ለፖለቲካ ተሿሚዎች፣ የፖለቲካ ተሿሚዎች ለምክር ቤቶች ተጠሪና ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ መስተዳድሩ በአጠቃላይ በተጠያቂነት መርህ የሚመራና ዞሮ ዞሮ ለህዝቡና ለህዝቡ ቀጥተኛ ተጠሪዎች ተጠያቂ እንዲሆን የማድረግ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻላል። ምክር ቤቶች የህግ አስፈፃሚው አካልን በመቆጣጠር ረገድ የነበራቸው ከላይ የተገለፀው ድክመት በአፋጣኝ መስተካከሉ የህግ አስፈፃሚው በተጠያቂነት መርህ እንዲሰራ ከማድረግም አንፃር ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ሊሰመርበት ይገባል።

በአገራችን ተንሰራፍቶ በነበረው ፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ምክንያት አንድ ጊዜ በእግዚአብሄር ሌላ ጊዜ በታሪክ የተሰየምን ነን የሚሉ መንግስታት ስለነበሩ የመንግስት ከፍተኛ የፖለቲካ ሃላፊዎች ለህዝብ ተጠያቂነት የነበራቸው አልነበሩም። በህዝብ የመገልገልና ህዝብን የማዘዝ ፖለቲካ እንጂ ህዝብን የማገልገል፣ የተጠያቂነት ፖለቲካ የነበራቸው አይደሉም። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እነዚህ ከፍተኛ የፖለቲካ ሃላፊዎች የሚያንቀሳቅሱት ሲቪል ሰርቪስም ህዝብን የመቆጣጠርና የማዘዝ እንጂ የህዝብ ተቀጣሪና አገልጋይ የመሆን አመለካከት አልነበረውም። ተቀጣሪና



አገልጋይ ነኝ ብሎ ሲያምንም በዋነኛነት ለፖለቲካ ሃላፊዎች ነበር። በፖለቲካ ሃላፊዎችና በሲቪል ሰርቪሱ መካከል በተጠያቂነት መርህ ላይ የተመሰረተ ግልፅ የስራ ክፍፍልና የእዝ ሰንሰለት አልነበረም። ይህ የአመለካከትና የአሰራር መዘበራረቅ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ በሰፊው በተያያዝንበት በአሁኑ ወቅትም ተቀርፏል ማለት አይቻልም።

በቅርቡ በህግ አስፈፃሚው አካል ውስጥ በፖለቲካ ሃላፊዎችና በሲቪል ሰርቪሱ መካከል በተጠያቂነት መርህ ላይ የተመሰረተ ግልፅና ያልተዘበራረቀ የስራ ክፍፍል እንዲኖር ለማድረግ የተጀመረው ስራ ችግሩን ለመቅረፍ በጎ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው መገመት ይቻላል። በተመሳሳይ መንገድ ምክር ቤቶች መስተዳድሩን በቅርብ የሚከታተሉበትንና የሚቆጣጠሩበትን ስርአት ለማጠናከር የተጀመረው ስራ በጎ ጅማሮ መሆኑ አያጠራጥርም። የተጠያቂነትን መርህ በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህ የተጀመሩት ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ሲቪል ሰርቪሱ አላማውንና ተልእኮውን እንዲገነዘብ፣ የዴሞክራሲ ስርአት የሚጠይቀውን አስተሳሰብና ባህል እንዲይዝ ለማድረግ ከሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር በማያያዝ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የግልፅነት መርህን ተግባራዊ ለማድረግ መወሰድ አለባቸው ተብለው የተቀመጡት መፍትሄዎች ጉድለት ሲገኝ ለመጠየቅና ለማረምም የሚረዱ ስለሆኑ የተጠያቂነትን መርህ ተግባራዊ ለማድረግም እጅግ ተፈላጊ ይሆናሉ። በአጠቃላይም ተጠያቂነትና ግልፅነት እርስ በርሳቸው

የተሳሰሩና ተመጋጋቢ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በተቀናጀ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

የህግ አስፈፃሚው አካል በተጠያቂነት መርህ እንዲሰራ ከማድረግ አኳያ የዳኝነት አካሉና የከፊል ዳኝነት አካላት ተብለው የሚታወቁት ተቋሞች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ መስተዳድሩ ከህግ ውጭ የዜጎችን መብትና ጥቅም በሚጥስበት ወቅት ዜጎች መንግስትን በፍርድ ቤት ከሰው መብትና ጥቅማቸውን ማስከበር ይችላሉ፡፡ ይህ መብት መረጋገጡ ራሱ መንግስት ስራውን በጥንቃቄና ህጋዊ በሆነ አኳኋን ብቻ እንዲያካሂድ ሊያስገድደው ይችላል፡፡ ዜጎችና ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ተገንዝበው የህግ የበላይነትን በማንኛውም ሁኔታ ለማስከበር በተሰጣቸው መብትና ስልጣን ዙሪያ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረጋቸውም ይህንኑ በይበልጥ እንደሚያጠናክረው አያጠራጥርም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፊል ዳኝነት አካላት የሚባሉት እንደ እንባ ጥበቃ ኮሚሽን፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የመሳሰሉት ተቋማት የሰብአዊ መብቶች መጣስንና አስተዳደራዊ በደሎችን በመከታተል እንዲስተካከሉ ለማድረግ ይችላሉ፡፡ በዚህም መልክ የዳኝነትና የከፊል ዳኝነት አካላት የተጠያቂነት መርህ በመስተዳድሩ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡



## 3.3. ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር፣

በአንድ አገር ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲኖር የዴሞክራሲ ስርአት መኖር ይገባዋል፡፡ ይሁንና የዴሞክራሲ ስርአት ባለበት ሁሉ መልካም አስተዳደር ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ባለበት አገር ሁሉ ቀልጣፋ የመንግስት አሰራር ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ ባለበት ሁሉ ከሙስና የፀዳ መንግስት ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ ባለበት ሁሉ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ቀልጣፋ የመንግስት አሰራር፣ ከሙስና የፀዳና ሙስና በቁጥጥር ስር የገባበት፣ ለፈጣን እድገት የተመቻቸ ሁኔታን የሚፈጥር መንግስት ባለበት ብቻ ነው መልካም አስተዳደር ሊኖር የሚችለው፡፡ በአገራችን ሁለቱም በጣምራ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ሁለቱም በጣምራ ካልተገኙ ዴሞክራሲ አገራችንን ከጠቅላላ ጥፋት ለመታደግ የሚያስችል መሳሪያ ሊሆን አይችልም፡፡

ሙስና በየትኛውም አገር ቢሆን መቶ በመቶ የተወገደበት ሁኔታ የለም፡፡ ይሁንና በቁጥጥር ስር ሲገባ በዝቅተኛ ደረጃና መጠን አልፎ አልፎ የሚከሰት ችግር ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ በኛ አገር ሁኔታ ሙስና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ወደምርትና ልማት ከማተኮር ይልቅ ወደማጭበርበርና የአየር-በአየር ንግድ እንዲያዘነብል በማድረግ ልማታችንን ክፉኛ ሊጎዳ ይችላል፡፡ የመንግስት አሰራር በአድልዎና ጉቦ ተጨማልቆ፣ መንግስት በልማት ተግባር ላይ በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ ተስኖት የልማት

ችግራችን የመፍትሄ አካል መሆኑ ቀርቶ ዋነኛው ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ መንግስት ህዝባዊ አገልግሎት የሚበረከትበት ሳይሆን ዝርፍያ የሚከናወንበት መድረክ ይሆንና የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ፉክክር በዘራፊዎች መካከል የሚደረግ የሞት ሽረት ትግል እንዲሆን፣ ስለሆነም ዴሞክራሲ ከስረ መሰረቱ እንዲናድ በር ሊከፍት ይችላል፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ሁሉ ሙስና ልማታችንን አደናቅፎ፣ የዴሞክራሲ ስርአታችንን ከውስጡ እንዲበሰብስ አድርጎ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ተስፋችን እንዲጨልም ማድረግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሙስናን በሰፊውና በብቃት የመዋጋት ስራ አንድ አስነዋሪ ስራን የማውገዝና የመቃወም ስራ ብቻ አይደለም፡፡ በአገራችን መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና የልማት ራዕያችን እውን እንዲሆን የማድረግ ጉዳይም ጭምር ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ሰፋ ያለ ፕሮግራም ቀርፆ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህንን በተለያዩ ፅሁፎች የተዘረዘረውን ፕሮግራም በተሳካ ሁኔታ መፈፀም በአገራችን ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ትርጉም እንዳለው ሊሰመርበት ይገባል፡፡

መንግስት አገልግሎቱን ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን እንዲሰጥ ማድረጉ ወይም አለማድረጉ ባለንበት አለም በኢኮኖሚ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ወይም ለመሸነፍ ምክንያት ከሚሆኑት ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ እንደኛ ባለው በከፋ የድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ በሚገኝ አገር መንግስት በሌሎች አገሮች ከሚጫወተው በላይ



የላቀ ልማታዊ ሚና መጫወት አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱን ሚና ለመጫወት የሚችለው ከሁሉም ነገር በፊትና ከሁሉም ነገር በላይ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ሲችል ነው፡፡ በየትኛውም አገር ቢሆን ዴሞክራሲ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው፣ መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አስተዋፅኦው ባሻገር ራሱን እንደቻለ አላማ ይወሰዳል፣ ህዝቦችም ራሱን እንደቻለ አላማ ይወስዱታል፡፡ ይሁንና በተለይም እንደኛ ባሉ አገሮች ህዝቡ ዴሞክራሲን የሚመኝበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ፍትሃዊና ቀልጣፋ የመንግስት አገልግሎትን ለማግኘት ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱን አገልግሎት ካላገኘ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ላይ ያለው እምነት በከፍተኛ ፍጥነትና ደረጃ ሊሸረሸር እንደሚችል የበርካታ አገሮች ልምድ ያረጋገጠው ነው፡፡ በመሆኑም ፍትሃዊና ቀልጣፋ መንግስታዊ አገልግሎት በማቅረብ መልካም አስተዳደርን ማስፈን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ራዕያችንን እውን ለማድረግ እጅግ ተፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

ይህንኑ በመገንዘብ መንግስት ከላይ እስከታች የመንግስታዊ አገልግሎቶችን ፍትሃዊነትና ቀልጣፋነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ርምጃዎች በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚሁ አኳያ ልዩ ትርጉም የሚሰጠው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራማችን ነው፡፡ የዚሁ ፕሮግራም አንድ መሰረታዊ አላማ የመንግስታዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋነትና ፍትሃዊነትን ማሻሻል በመሆኑ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተግባራዊነቱ መረባረብ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በአገራችን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተስተካከሉ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፖሊሲዎችን መቀየስና በብቃት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ህዝብ የመንግስትን ስልጣን መሰረታዊ ችግሮቹን ለመፍታትና ፍላጎቶቹን ለማሟላት እንደ መሳሪያ ሊጠቀምበት ይፈልጋል፡፡ መንግስት እንደዚህ አይነቱ ብቃት ያለው መሳሪያ ሊሆን የሚችለው የህዝቡን ችግሮች ለመፍታት፣ ፍላጎቶቹን ለማሟላት የሚያስችል የተስተካከለ -ሊሲ ሲኖረውና ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ሲኖረው ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ነው የተስተካከለ ፖሊሲና ይህንኑ የማስፈፀም ብቃት የመልካም አስተዳደር አንድ መሰረታዊ ባህሪ ነው የሚባለው፡፡

መንግስት ይህንኑ በመገንዘብ የተስተካከሉ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅና በቀጣይነትም ለማሻሻል ሰፊ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ፖሊሲዎቹ የህዝብን ችግር የሚፈቱ፣ ፍላጎቶቹን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በፖሊሲ ቀረፃው ላይ ህዝቡ በሰፊው እንዲሳተፍ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ የእቅዶች አፈፃፀምን በየጊዜው በመገምገም ከልምዱ በመማር ለማስተካከል እየተረባረበ ነው፡፡ ፖሊሲዎቹን በብቃት ለማስፈፀም እንዲቻል ሰፊ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራም ቀርፆና የእንቅስቃሴዎቹ ሁሉ ማዕከል እንዲሆን አድርጎ እየተረባረበ ነው፡፡ እነዚህ ስራዎች በአገራችን መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያም ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው በመሆኑ ለተግባራዊነታቸው ሌት ተቀን መረባረብ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡



ከላይ እንደተዘረዘረው መልካም አስተዳደር በአገራችን ፈጣን ልማት ለማረጋገጥና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታን እውን ለማድረግ እጅግ ተፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዴሞክራሲ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሙስናን በቁጥጥር ስር አድርጎ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ህብረተሰቡን በሰፊው ማንቀሳቀስ፣ በመንግስት አሰራር ውስጥ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡ ዴሞክራሲ በሌለበት ህዝቡ ደፍሮ ሙስናን በህጋዊ መንገድ መታገልና ማጋለጥ አይችልም፡፡ ዴሞክራሲ በሌለበት ግልፅነትና ተጠያቂነት የመንግስት አሰራር መሰረታዊ መርሆዎች ሆነው በጥብቅ ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የመንግስት አሰራር ቀልጣፋና ፍትሃዊ እንዲሆን ለማድረግ ህዝቡ ለዚሁ አላማ እንዲሰለፍ መብትና ግዴታውን አውቆ መብቱን ለማስጠበቅና ግዴታውን ለመወጣት በብቃት መንቀሳቀስ አለበት፡፡ ይህ ዴሞክራሲ በሌለበት ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ቀልጣፋና ፍትሃዊ መንግስታዊ አገልግሎትን ለማረጋገጥ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ ተግባራዊ መሆን ይገባዋል፡፡ ይህ ግን ዴሞክራሲ በሌለበት የሚሆን ነገር አይደለም፡፡ የህዝቡን ችግሮች ለመፍታትና ፍላጎቶቹን ለማሟላት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን በብቃት ለመቀየስና ለመፈፀም የህዝቡን ተሳትፎ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ዴሞክራሲ በሌለበት ፋይዳ ያለው የህዝብ ተሳትፎ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር በጥብቅ የተሳሰሩ ጉዳዮች መሆናቸውን ተገንዝቦ በተቀናጀ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## 4. የዳኝነት ስርአትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣

### 4.1. የዳኝነት ስርአቱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ላይ ያለው ሚና፣

የዳኝነት ስርአቱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ እንደ ሶስተኛው የመንግስት ክፍል ተደርጎ ይወሰዳል:: በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: የህግ የበላይነት የዴሞክራሲያዊ ስርአት አንድ መሰረት ነው:: የህግ የበላይነት እንደመርህና እንደተግባር ሙሉ በሙሉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም:: በአንድ አገር ውስጥ የህግ የበላይነት በተሟላ ሁኔታ ሊረጋገጥ የሚችለው መንግስትና ህዝቡ በመርሁ ላይ የተሟላ እምነት ኖሯቸው በዚሁ ሲመሩ ነው:: ሰዎች ከህግ ውጭ የሆነን ስራ መስራት ሲያቆሙ፣ ከዚያም አልፈው ከህግ ውጭ የሆነ ስራ በማንኛውም አካል በሚሰራበት ወቅት አጥብቀው ሲቃወሙ ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከህግ ውጭ የሆኑ ሰዎችንና አካላትን ተከትሎ ማስተካከልና መቅጣት የህግ የበላይነት በማረጋገጥ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል::

መንግስት በተለይም መስተዳድሩ ከህግ ውጭ የሆነ ስራ በሚሰራበት ወቅት ዜጎች ወደዳኝነት ስርአቱ በመሄድ መፍትሄ ማግኘት ሲችሉ የዴሞክራሲ መብቶች በይበልጥ ዋስትና ያገኛሉ፣ የህግ የበላይነት ይጠናከራል:: የህዝቡን ሰላምና መረጋጋት የሚያደፈርሱ ሰዎች ጥብቅ የህግ ክትትል ተደርጎባቸው ሲስተካከሉና ሲቀጡ የህግ የበላይነትና ሰላም



በይበልጥ ይጠበቃል:: አንዱ ዜጋ በሌላው ላይ በደል ሲያደርስ ግላዊ መፍትሄ ከመሻት ይልቅ በህግ ፊት በዳኝነት ስርአቱ መፍትሄ ሲገኝ የህግ የበላይነትና ሰላም ይረጋገጣል:: በሌላ አገላለፅ ሁሉም በተናጠልና እንደአቅሙ ራሱን ለመጠበቅ በሚንቀሳቀስበት ስርአት ሰላምም ሆነ ዴሞክራሲ ሲኖር ስለማይችል ሁሉንም ወገኖች በእኩልነት በህጉ መሰረትና በህጉ መሰረት ብቻ የሚዳኝ ስርአት መኖሩ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን፣ ሁሉም ዜጋና የህብረተሰቡ አካላት ስራቸውን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ብቻ የሚያከናውኑበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር ቁልፍ ሚና ይጫወታል::

ከህግ ውጭ የሆነውን ማንኛውንም ግለሰብ ወይም አካል በጥብቅ ተከታትሎ፣ ህጉ በሚያዘውና ህጉ በሚያዘው መሰረት ብቻ የማስተካከያ ርምጃ የሚወስድ ቀልጣፋና ፍትሃዊ የዳኝነት ስርአት መኖሩ፣ ሰላም የህግ የበላይነትን ለማስፈን እጅግ አስፈላጊ መሆኑ፣ የዳኝነት ስርአቱ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ላይ ያለውን ቁልፍ ሚና የሚያመለክት ነው::

የነፃ ገበያ ስርአት በኮንትራቶች ላይ የተመሰረተ ስርአት ነው:: የነፃ ገበያ ስርአት በግል ንብረት ላይ የተመሰረተ ስርአትም ነው:: ነፃ የገበያ ኢኮኖሚያዊ ስርአት በግል ጥቅምና በጋራ ጥቅም መካከል ቀጣይ ቅራኔ የሚታይበትና ይህንኑ ለማጣጣም የሚያስችል ስርአት በመንግስት አማካኝነት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግን የሚጠይቅ ስርአት ነው:: እነዚህ ነገሮች አዋጅ ደንብና መመሪያን የሚጠይቁ፣ እነዚህን ህጎችና መመሪያዎች ቅልጥፍና

ባለውና ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ተግባር ላይ ማዋልን የሚጠይቁ ናቸው:: ከህጎቹና ከመመሪያዎቹ ውጭ የሚንቀሳቀስ ግለሰብ ወይም አካል ሲኖር በአፋጣኝና በህጉ መሰረት ማረም መቅጣትን የሚጠይቅ ነው:: ቀልጣፋና ፍትሃዊ የዳኝነት ስርአት መኖር በነፃ ገበያ ኢኮኖሚያዊ ማዕቀፍ ውስጥ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገትን ለማረጋገጥ እጅግ በጣም ተፈላጊ ነው:: በመሆኑም የዳኝነት ስርአቱ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ራዕያችንንም ሆነ የልማት ግባችንን ለማሳካት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ስርአት ነው:: ቀልጣፋና ፍትሃዊ የዳኝነት ስርአትን ለመገንባት መረባረብ እጅግ አስፈላጊ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው::

## 4.2. የዳኝነት ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት፣

ቀልጣፋና ፍትሃዊ የዳኝነት ስርአት ሊኖር የሚችለው ዳኞች ያለአንዳች ተፅእኖ የሚቀርብባቸውን ጉዳይ በህጉ መሰረት መፈፀም ሲችሉ ነው:: በመሆኑም ዳኞች ተልእኳቸውን በአግባቡ በመፈፀም ከማንኛውም ተፅእኖ፣ በተለይም ከመስተዳድሩ ተፅእኖ ነፃ መሆን አለባቸው:: ይህንን በተመለከተ በአንቀፅ 79 ላይ የሚከተለውን ተቀምጧል::

"1. በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው::"

"2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ አካል ከማንኛውም የመንግስት አካል፣ ከማንኛውም ባለስልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅእኖ ነፃ ነው::"



"3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ በነፃነት ያከናውናሉ:: ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም::"

ከህገ-መንግስቱ መረዳት እንደሚቻለው በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የዳኝነት ነፃነትን የማረጋገጥ መርህ ሁለት የተሳሰሩና መሰረታዊ ገፅታዎች ያሉት ነገር ነው:: በአንድ በኩል የዳኝነት ስራ የፍርድ ቤቶች ብቻ እንዲሆንና ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ስራ በሚሰሩበት ወቅት ከማንኛውም ተፅእኖ በተለይም ከመንግስት ጣልቃ ገብነትና ተፅእኖ ነፃ እንዲሆኑ የማድረግ ጉዳይ ነው:: የውጭ ጣልቃ ገብነትና ተፅእኖን ማስወገድ፣ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የመንግስት አካላት አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖር ማድረግ የዳኝነት ነፃነት መርህ አንድ መሰረታዊ ገፅታ ነው:: የመርሁ ሌላ ገፅታ ዳኞች ከውጭ ተፅእኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ በሚሆኑበት ማዕቀፍ ውስጥ መመሪያቸው ህጉና ህጉ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ነው:: በህገ-መንግስቱ አገላለፅ ዳኞች ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ እንዳይመሩ ማድረግ ነው:: ዳኞች በህጉ በመመራት ህጉንና ከህጉ በስተጀርባ ያሉ ህብረተሰባዊ አላማዎችን ጠንቅቀው እንዲያውቁ፣ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል፣ በተለያዩ ስሜቶች በመገፋፋት ከህጉ ውጭ እንዳይሰሩ ማድረግ ከዳኝነት ነፃነት መርህ የማይነጠል ገፅታ ነው:: ሁለቱን ያላጣመረ የዳኝነት ነፃነት በርግጥም ነፃነት ሊሆን አይችልም::

ግልፅነትና ተጠያቂነት የዴሞክራሲያዊ ስርአት መሰረታዊ መርሆዎች ናቸው:: ምንም እንኳ መርሆዎቹን

ተግባራዊ ማድረግ እጅግ በጣም ተፈላጊ የሚሆነው በህግ አስፈፃሚው (በመስተዳድሩ) ውስጥ ቢሆንም በሌሎቹም የመንግስት አካላት መርሁን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ምክር ቤቶች ስራቸውን በግልፅነት መርህ እንዲፈፅሙ ማድረግ ፍፁም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል ለመረጠው ህዝብ ተጠያቂ እንዲሆን የማድረጉ መርህም እጅግ በጣም ተፈላጊ ነው:: ህገ-መንግስታችን ይህንኑ በመገንዘብ ህዝቡ በተወካዩ ላይ እምነት ባጣበት በማንኛውም ወቅት ተወካዮቹን መተካት እንደሚችል ያስቀምጣል:: የዳኝነት ስርአቱ ነፃነት መጠበቅ እንዳለበት ሊሰመርበት የሚገባ ቢሆንም ይህ መሆኑ ስርአቱን ከተጠያቂነትና ከግልፅነት መርህ ነፃ እንዲሆን አያደርገውም::

በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ዞሮ ዞሮ የሉአላዊነቱ ባለቤት ህዝቡ ነው:: ህዝቡ ሰላምና የህግ የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ ለመተዳደር በመፈለጉ ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉትን ህጎች በተወካዮቹ አማካኝነት ያወጣል:: የህጎቹ አላማ የህዝቡን መብትና ፍላጎት ማሟላት ነው:: የህጎቹም ባለቤት ህዝቡ ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ህዝቡ ህጎቹን በትክክል የሚተረጉምለት፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ዳኝነት መኖሩን የሚያረጋግጥለት የዳኝነት ስርአት ይፈጥራል:: የዚሁ ስርአት አላማ የህዝቡን መብትና ፍላጎት ህጎቹን በትክክል በመተርጎም ማሟላት ነው:: ዞሮ ዞሮ የህዝቡ አገልጋይና ለህዝቡ ተጠሪ የሆነ ስርአት ነው:: የዳኝነት ነፃነቱ የሚፈለገው ህጉን በትክክል በመተርጎም የህዝቡን ፍላጎትና መብት ለማሟላት እንጂ ከህዝብ በላይ ለመሆን፣ ከተጠያቂነት



ነፃ ለመሆን አይደለም:: ህዝቡ ያስፈልገኛል ብሎ የፈጠረው የዳኝነት ስርአት መብቱንና ፍላጎቱን በትክክል እያሟላ መሆኑን የማረጋገጥ የመቆጣጠር መብትና ግዴታ አለበት::

የዳኝነት ስርአቱ ግልፅነት በተላበሰ አኳኋን ስራውን ካልሰራ ህዝቡ በሉአላዊ መብቱ የፈረጠውን የዳኝነት ስርአት መከታተልና መቆጣጠር አይችልም:: በዳኝነት ስርአቱ የሚከናወኑትን ስነ-ስርአቶች፣ የሚሰጡትን ብይኖች ወዘተ. በማወቅ እያንዳንዱ ዳኛ ህጉን በትክክል እየተረጎመው መሆን አለመሆኑን፣ ስራውን በቅልጥፍና እየፈፀመ መሆን አለመሆኑን ማየት፣ መታዘብና ማረጋገጥ መቻል አለበት:: ፍርድ ቤቶች በልዩ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በግልፅ ችሎት እንዲያስችሉ የሚደነገገውም የዳኝነት ስርአቱ ስራውን በግልፅነት መርህ መሰረት እንዲፈፅም ለማድረግ ነው:: በርግጥ ህዝቡ በየችሎቱ እየተገኘ ስራውን መከታተል ቢችልም አብዛኛው ህዝብ ይህን ለማድረግ የሚመቸው አይሆንም:: ስለሆነም የዳኝነት ስርአቱ ህዝቡ የስርአቱን ፍትሃዊነትና ቀልጣፋነት ለመከታተል የሚያስችለው ትክክለኛና የተሟላ መረጃ እንዲያገኝ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል:: ዳኞች ስራቸውን ያለአንዳች ጣልቃ ገብነት የመስራት እንጂ ስራቸውን ከህዝብ የመደበቅ፣ የግልፅነትን መርህ የመጣስ መብት እንደሌላቸው ተገንዝበው መርሁን በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ማድረግ መቻል አለባቸው::

ዳኞች ነፃ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ነፃነታቸው በስራቸው ላይ ጣልቃ መግባትን ለመከልከል እንጂ ከተጠያቂነት

ነፃ እንዲሆኑ ለማድረግ አይደለም፡፡ የዳኝነት ነፃነቱ አንድ ገፅታ ዳኞች ከህጉ በስተቀር በሌላ ሁኔታ እንዳይሰሩ መከልከሉ ነው፡፡ ዳኞች ህጉን በትክክል ባለማወቅ የህጉን አላማና ግብ ባለመረዳት፣ በችሎታ ማነስ ምክንያት በህጉ መሰረት ሳይወስኑ ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ ዳኛ ነፃ ነው በሚል ሰበብ ችሎታው የሌላቸው ሰዎች ህጉን እንዲያመሰቃቅሉት መፍቀድ አይቻልም፣ አይገባምም፡፡ የችሎታ ችግር ሳይኖርባቸው በግል ጥቅም በመደለል፣ ወይም በተለያዩ የግል ስሜቶች በመነዳት፣ ህጉን ከይዘቱና ከአላማው ውጭ የሚተረጉሙ ዳኞችም ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ዳኞች ነፃ ናቸው በሚል ሰበብ ግለሰቦች እንዳሻቸው ህጉን ሲያተራምሱ ዝም ብሎ ማየት አይቻልም፡፡ የዳኝነት ነፃነት አንዱ መሰረታዊ ገፅታ ዳኞች በህጉና በህጉ መሰረት ብቻ መስራት እንዳለባቸው ማስገንዘብ ስለሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ከህግ ውጭ ሲሄዱ ተጠያቂ የሚሆኑበትና የሚስተካከሉበት ስርአት መኖሩ የዳኝነት ነፃነትን ራሱን ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

የዳኞች ነፃነት የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆዎች እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው መሄድ የሚችሉና የሚገባቸው በመሆናቸው ዳኞች የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ነፃነታቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ ህዝቡ ስለዳኝነት ስርአቱ ብይኖችና የስራ ውጤት የተሟላ መረጃ ሲያገኝ አንድ በፍርድ ቤት ላይ ያለን ነገር በህዝብ አስተያየትና ተፅእኖ ለማስወሰን ሊጠቀምበት አይገባም፡፡ ይህ ዳኞች ነፃ



ሆነው የሚወስኑት እንጂ በህዝብ አስተያየት የሚያልቅ ነገር አይደለም፣ መሆንም የለበትም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መረጃውን መሰረት በማድረግ በዳኝነት ስርአቱ ፍትሃዊነትና ቅልጥፍና ጉዳይ ላይ ህዝቡ በሰፊውና በነፃ መወያየትና መከራከር መቻል አለበት፡፡ በተጨማሪ መረጃ ላይ ተመስርቶ ገንቢ ሂስ የመስጠትና የማሻሻያ ሃሳቦችን የማቅረብ መብትም አለው፡፡ ይህ የዳኝነት ስርአቱን በአጠቃላይ ፍትሃዊና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል እንጂ በተናጠል የዳኝነት ጉዳዮች ላይ ተፅእኖ ለማሳረፍ የሚካሄድ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የተጠያቂነትም ጉዳይ በመጀመሪያ የሙያና የስነ-ምግባር ብቃት ያላቸውን ሰዎች ብቻ መርጦ በዳኝነት ለመሾም፣ ከተሾሙም በኋላ በችሎታ ችግር ወይም በስነ-ምግባር ችግር የሚያተራምሱትን ለማረምና ለማስወገድ የሚያስችል እንጂ በተናጠል ጉዳዮች ጣልቃ የሚያስገባ መሆን የለበትም፡፡ በአጠቃላይ የዳኝነት ነፃነትን ከግልፅነትና ከተጠያቂነት መርህ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ማድረግ ዴሞክራሲያዊ የዳኝነት ስርአትን ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በሌሎች የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎችም እንደሚያጋጥመው ቀልጣፋና ፍትሃዊ የዳኝነት ስርአት በመገንባት ረገድ የሚያጋጥመው ዋነኛው ችግር የአመለካከት ችግር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ የዳኝነት ነፃነትን በሚመለከት መርሁ ምን ማለት እንደሆነና ምንስ ማለት እንዳልሆነ በሚገባ ያለመገንዘብ ችግር ጎልቶ ይታያል፡፡ ከለመድነው ፀረ-ዴሞክራሲ ባህል በመነሳት በየደረጃው ካሉት ባለስልጣኖች ዳኞች

በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በባለስልጣኖቹ ተቀባይነት ያለው ውሳኔ እንዲወሰኑ ተፅእኖ የማሳረፍ መብትና ግዴታ ያላቸው የሚመስላቸው ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ለርሱ ያልተበየነለት ተከራካሪም ብይኑም ምንም ይሁን ምን ለማስገልበጥ በዳኞች ላይ በተቻለው መንገድ ሁሉ ተፅእኖ ከማሳረፍ ወደኋላ የማይልበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች የዳኝነት ስርአቱን ነፃነት በመፃረርና በማደናቀፍ በራሳቸው የዴሞክራሲ መብት መከበርና በአገሪቱ ህልውና መረጋገጥ ላይ እያስከተሉት ያሉትን መዘዝ በትክክል የተገነዘቡ አይደሉም፡፡ ስለሆነም በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የዳኝነት ስርአቱ ምን አይነት ሚና እንደሚጫወትና፣ ምን አይነት ባህሪ መያዝ እንዳለበት መላው ህብረተሰብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው፣ በዚህም ጉዳይ ላይ እንደሌሎቹ መሰረታዊ ጉዳዮች ሁሉ አንድ አይነት የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት እንዲፈጠር መታገል ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የዳኝነት ነፃነት ሲባል ዳኞች እንዳሻቸው የሚሆኑበት ስርአት መፍጠር፣ ከተጠያቂነት መርህ ውጭ እንደሆኑ አድርጎ የማየት አዝማሚያ ይታያል፡፡ የሙያ ችሎታ ሲያንሳቸው በግል ጥቅም ወይም በግል ስሜት በመነዳት ህጉን አውገርግረው ሲተረጉሙት ጉዳዩ ተጣርቶ መታረምና እንደሁኔታውም መቀጣትና ከስራቸው መባረር እንዳለባቸው የማይገነዘቡ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ዳኞች የህዝብ የበላይና ተቆጣጣሪ ሳይሆኑ የህዝብ አገልጋይና ተቀጣሪ መሆናቸውን የማያስተውሉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ስለብይናቸውና ስለስራ እንቅስቃሴያቸው ለህዝቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መግለጫ እንዲሰጡ



ማድረግ፣ በዚህ ላይ ተመስርቶ ህዝቡ በነፃና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን አስተያየቱን እንዲሰጥ ማድረግ የዳኞችን ክብር መድፈር ወይም የዳኝነት ነፃነትን ለአደጋ ማጋለጥ መስሎ የሚታያቸው፣ ከፊውዳላዊ አስተሳሰብ መላቀቅ የሚያስቸግራቸውም ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ህጎች በራሳቸው ምንም አይነት ህልውናና ፋይዳ የሌላቸው መሆናቸውን፣ የህዝቡን መብትና ፍላጎት ለማርካት የሚቀረፁና ይህንን በሚያረጋግጥ አኳኋን መተርጎም እንዳለባቸው የማይረዱ፣ ህጉን ከዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አላማ ውጭ በሆነ መንገድ የሚገነዘቡና የሚተረጉሙም ጥቂቶች አይደሉም፡፡ እነዚህን የተሳሳቱ አመለካከቶች ለህግ ሙያተኞች በሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም ባሻገር በነዚህ ጉዳዮች ላይ መላው ህብረተሰብ አንድ አይነት የጋራ አመለካከትና እምነት ይዞ ለተግባራዊነታቸው መታገል መቻል አለበት፡፡

## 4.3. የዳኝነት ስርአቱን የመገንባት ትግል፣

የዳኝነት ስርአቱ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና ለልማት ማበርከት የሚገባውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ለማድረግ በአዲስና ጠንካራ መሰረት ላይ በአፋጣኝ መገንባት አለበት፡፡ የህዝቡን መብትና ፍላጎት ለማርካት የሚያስችሉ ለአፈፃፀምና አተረጓጎም የተመቹ ህጎች መውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ሁሉም ህጎቻችን በዚህ መልክ የተቃኙ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በቂና በአግባቡ የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች፣ ማፍራትና በመስኩ እንዲሰማሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የዳኝነት

ስርአቱን አወቃቀርና አሰራር ቅልጥፍናና ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን መቅረፅ ያስፈልጋል። በጉዳዩ ላይ ህብረተሰቡ አንድ ትክክለኛና የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት እንዲይዝ ማድረግ ያስፈልጋል።

መንግስት የዚህን ስራ ፋይዳ በትክክል በመረዳት ተልእኮውን በትክክል ለመወጣት የሚችል የዳኝነት ስርአትን ለመገንባት ሰፊ የዳኝነት ስርአት የማስፈፀም አቅም ግንባታና ማሻሻያ ፕሮግራም በመንደፍ ለተግባራዊነቱ በመረባረብ ላይ ይገኛል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ከዚህ አኳያ የሚኖረው ዋናው ስራ ይህንኑ ፕሮግራም በተቻለ ፍጥነትና በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ማድረግ፣ በዚሁ ሂደት የሚገኙ ልምዶችን እየቀመሩ ፕሮግራሙንና አፈፃፀሙን በቀጣይነት ማሻሻል ነው።

የዳኝነት ስርአቱ አካል ባይሆኑም ከፊል የዳኝነት ተቋማት ተደርገው የሚወሰዱ ሌሎች ተቋማትም ይኖራሉ። ህገ-መንግስታችን ይህንኑ ተገንዝቦ የእንባ ጠባቂ ተቋምና የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እንዲቋቋሙ ይደነግጋል። እነዚህ ተቋሞች አስተዳደራዊ በደሎችን በማጣራት የሚወገዱበትን መፍትሄ በመሻት፣ በሰብአዊ መብቶች መከበር ዙሪያ የሚያጋጥሙ ጉድለቶችን በማጥናትና በማጣራት መብቶቹ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ በጣም ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይገባል። እስካሁን ድረስ በዚህ ረገድ የተሰራው ስራ በአብዛኛው የቅድመ ዝግጅት የሌሎች አገሮች ልምድን የመቀመርና ተቋሞቹን መስርቶ ስራቸውን በአግባቡ



የሚሰሩበት የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠር ስራ ነው። ይህ ስራ በርግጥም መሰራት የነበረበትና የራሱ ጊዜም የሚጠይቅ እንደሆነ እሙን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ተቋሞቹ ከሚጫወቱት ከፍተኛ ሚና አኳያ ሲታይ የማቋቋሙ ስራ መፋጠን እንደሚኖርበት ግልፅ ነው።

ተቋሞችን በተቻለ ፍጥነት ማቋቋምና ማደራጀት ትልቅ ክብደት የሚሰጠው ስራ ቢሆንም ከዚያም በላይ ተፈላጊ የሚሆነው ከተቋቋሙ በኋላ ስራቸውን በአግባቡ ሊሰሩ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። በዚህ ረገድ ህብረተሰቡ ስለተቋሞቹ ተልእኮና አሰራር የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖረው የማድረግ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ይሆናል። በዚህ ላይ በመመስረትም የተቋሞቹን ሃላፊዎችና ሰራተኞችን መቅጠርና ስራቸውን በተመለከተ የተሟላ እውቀት እንዲያገኙ፣ ሃላፊነታቸውን በብቃት የሚወጡ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 5. የህዝብ ማህበራት፣ የህዝብ ተቋማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣

የዴሞክራሲ ስርአትን በአገራችን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት በዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዲሰራና እንዲደራጅ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ሶስቱ የመንግስት አካላት፣ ማለትም ህግ አውጭው፣ ህግ አስፈፃሚውና ህግ ተርጓሚው በስርአቱ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና ለይቶ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል ስራ መስራት አስፈላጊ ነው። ይሁንና ዴሞክራሲ በመንግስት ተቋማት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም።

በተለይም የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ማረጋገጥ እንደ አንድ መሰረታዊ መርሆ በተወሰደበት በኛ አገር የህዝብ ማህበራትና ተቋማት በስርአቱ ውስጥ ተገቢ ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው:: በዚህ ረገድ የፖለቲካ -ርቲዎችና ድርጅቶች፣ ሚድያ፣ የሙያና የብዙሃን ማህበራት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ:: በመሆኑም የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማችንን ለማሳካት ተቋማዊ መሰረቱን ለማስፋትና የጋራ ዴሞክራሲያዊ አመለካከትና እምነትን ለመፍጠር የተጠቀሱትን ድርጅቶችና ተቋማት መፍጠር፣ ማጠናከርና ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲፈፅሙ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል::

## 5.1. የፖለቲካ -ርቲዎችና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታችን፣

የፖለቲካ -ርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የላቀ ሚና ይጫወታሉ፣ መጫወትም ይገባቸዋል:: የአንድን የህብረተሰብ ክፍል መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ አማራጭ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ እነዚህ ሃሳቦች በህብረተሰብ ክፍሉም ሆነ በአጠቃላይ በህዝቡ ተቀባይነት እንዲያገኙ በመጣር፣ ሃሳቦቹ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆኑ በመታገል ከፍተኛ የአመራር ሚና ይጫወታሉ:: የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደዚህ አይነት ብቃት ያለው አመራር አግኝተው መብትና ጥቅማቸውን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ለማስጠበቅ የሚችሉበትን ሁኔታ ይፈጥራሉ:: ዜጎች በሚገባ የተተነተኑ ሃሳቦችን ይዘው በዴሞክራሲያዊ ስርአቱ ውስጥ የሚያደርጉት ቀጥተኛና ሰፊ ተሳትፎ የነቃ ተሳትፎ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታን



ይፈጥራሉ:: በዚህ መልኩ የተደራጀ አመራር ሰጥተው የህዝቡን ድጋፍ ካገኙ የመንግስት ስልጣንን ይዘው ሃሳባቸውን ተግባራዊ በማድረግ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ::

-ርቲዎች ለቆሙለት አላማና የህብረተሰብ ክፍል በዴሞክራሲያዊ አኳኋን በመታገል ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ባሻገር አላማቸውን ማራመድ የሚችሉት የዴሞክራሲ ስርአት ሲገነባ መሆኑን በመገንዘብ የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ፣ የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል:: በአጠቃላይም የዴሞክራሲ ስርአቱ ግንባታ መምህራንና ግንባር ቀደም ተዋናዮች ሆነው ይሰለፋሉ::

-ርቲዎች በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ ከላይ የተጠቀሰውን የአመራር ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል ባህሪ ሲኖራቸው ነው:: በመሆኑም ከሁሉ በፊት -ርቲዎች በርግጥም የፖለቲካ -ርቲዎች መሆን አለባቸው:: ማለትም አንድ የፖለቲካ አላማን ለማራመድ፣ በዚህ የፖለቲካ አላማ ለመሰባሰብ የሚፈልጉትን ዜጎች በሙሉ ለማሰባሰብ የሚጥሩና መነሻና መድረሻቸው ይኸው የፖለቲካ አላማ የሆኑ ድርጅቶች መሆን አለባቸው:: -ርቲዎች የፖለቲካ አላማቸውን ለማራመድ አላማውን ራሱን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆን እንዳለባቸው ሳይታለም የተፈታ ነው:: ከዚህም ባሻገር አላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮችን ለመተንተን፣ ለማቀናበርና ለህዝብ የማቅረብ አቅም ሊኖራቸው

ይገባል፡፡ እንደዚህ አይነቱን የፖለቲካ አመራር ለመስጠት የማይችል -ርቲ አንድም የ-ለቲካ -ርቲ አይደለም፣ አለያም ተልዕኮውን በአግባቡ ሊወጣ የሚችል -ርቲ አይደለም፡፡

-ርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመጫወት እንዲችሉ አመለካከታቸው፣ እምነታቸውና አሰራራቸው ዴሞክራሲያዊ መሆን አለበት፡፡ የውስጥ አሰራሩ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ -ርቲ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባትና ማበብ ፋይዳ ያለው አስተዋፅኦ ማበርከት አይችልም፡፡ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ በተጀመረበት ሁኔታ አላማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለማራመድ የማይፈልጉ፣ የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብና የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲጠናከሩ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ዝግጁ ያልሆኑ -ርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ፋይዳ ያለው አስተዋፅኦ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ በመሰረታዊ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አቅጣጫዎችና በህገ-መንግስቱ ዙሪያ አንድ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት መፈጠሩ -ርቲዎች በመካከላቸው ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸውና ለስርአቱ መጠናከር በጎ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ በጣም ተፈላጊ ነው፡፡

በዳበረ የዴሞክራሲ ስርአት ገዥ የነበረ -ርቲ ተቃዋሚ፣ ተቃዋሚ የነበረውም ገዥ የመሆኑ ጉዳይ የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስልጣን ሽግግር ያለአንዳች ችግርና ቀውስ በሰላማዊ መንገድ የሚፈፀም ከመሆኑም ባሻገር ህብረተሰቡ



በሚመራባቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥን የሚያስከትል አይሆንም፡፡ ተቃዋሚ -ርቲዎች ታማኝ ተቃዋሚ (ሎያል ኦፖዚሽን) በሚል ስያሜ የሚታወቁ የራሳቸው የተለየ -ሊሲ ከማቅረብ ባሻገር ስርአቱን የሚንድ ሃሳብና ተግባር የሌላቸው ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ ሊሆን የሚችለው በህብረተሰቡ ውስጥ በመሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ አንድ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት በመያዙ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን የመሰለው የጋራ እምነትና አመለካከት መኖር -ርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መጫወት የሚገባቸውን የላቀ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ እጅግ ተፈላጊ ነው፡፡

በአገራችን ከላይ የተጠቀሰውን ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ጠንካራ -ርቲዎች እንዳይፈጠሩ እንቅፋት የሚሆኑ ከኋላ ቀርነታችን ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ የህብረተሰቡ አወቃቀር ራሱ የሚፈጥረው ተፅእኖ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ ህብረተሰባችን የአርሶ አደር ህብረተሰብ ነው፡፡ ከ85% የማያንሰው የህብረተሰብ ክፍል ይኸው ክፍል ነው፡፡ አርሶ አደሩ በቂ ትምህርት የሌለው፣ በተበታተነ አኳኋን የሚኖር የህብረተሰብ ክፍል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የሚመነጩና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መጫወት በሚገባው ሚና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ችግሮች መኖራቸው አንድ መዋቅራዊ ችግር ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዚህ የህብረተሰብ ክፍል ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ ድርጅት ጠንካራ ተፎካካሪ የሚሆን ሌላ ድርጅት ሊያጋጥመው የማይችል፣ የዚህን የህብረተሰብ ክፍል ድጋፍ በማግኘቱ ብቻ ለረጅም ጊዜ በስርአቱ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይዞ

ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑም ሌላው አደጋ ነው:: በአርሶ አደሩ ሰፊ ድጋፍ ላይ የተመሰረተው ይህ ድርጅት ለዴሞክራሲ ጠንካራ ታማኝነት ከሌለውም አደጋው የላቀ ይሆናል:: በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎቹ ድርጅቶች በጠባብ የህብረተሰብ ክፍል የታጠሩና ደካማም የሚሆኑበት ዕድል የሰፋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል::

በተበተነና ኋላ ቀር የአስተራረስ ዘይቤ ላይ የተመሰረተ ኑሮ ባለው የአርሶ አደር ህብረተሰብ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በመገንባት ላይ የሚያጋጥሙት እነዚህ መዋቅራዊ ችግሮች በብዙ አገሮች በተለያየ አጋጣሚና መልክ የተከሰቱ ሲሆኑ በተለይ በአርብቶ አደሩ ህብረተሰብ ዘንድ ደግሞ ባህርያቸው በከፋ መልኩ የሚገለፅ ይሆናል:: የአርብቶ አደሩ ህብረተሰብ ማህበራዊ አወቃቀር በደም ትስስርና በጎሳ ላይ የሚያጠነጥን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በእነዚህ አካባቢዎች ሰዎች በ-ለቲካ አመለካከት ዙሪያ የተለያዩ -ርቲዎችን የማቋቋም ዕድላቸው ጠባብ ሆኖ ይገኛል:: የሚቋቋሙት ስብስቦች በመሰረቱ የጎሳና የቤተሰብ ስብስብ በመሆናቸው የፖለቲካ -ርቲ ወይም ድርጅት ሊያስብላቸው የሚችል ባህሪ የሌላቸው የመሆን ዕድላቸው የሰፋ ይሆናል:: ይህም በነዚህ አካባቢዎች ጠንካራ የፖለቲካ -ርቲዎችን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት በርካታ ችግሮች የሚያጋጥሙት እንዲሆን ያደርጋል::

በብዙዎቹ ኋላ ቀር አገሮች፣ በተለይም በአፍሪካ ከፍተኛ ድህነት ያለ በመሆኑና የግል ባለሃብቶችም ደካማ በመሆናቸው



መንግስት በኢኮኖሚው ላይ በሰፊው ጣልቃ ለመግባት ይገደዳል:: እጅግ ኋላቀር በሆነ ሁኔታ ውስጥ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን አምርቶ ተወዳድሮ ለማሸነፍና በዚሁ ለመክበር ያለው ዕድልም ሰፊ ሆኖ አይታይም:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለመክበር የቀለለውና አቋራጭ መንገድ ከመንግስት ጋር በሚፈጠር ሽርክና በሙስናና በህገ-ወጥ ንግድ መክበር ይሆናል:: የመንግስት ጣልቃ ገብነትና ከአምራችነት ይልቅ ለጥገኝነት የተመቸ ሁኔታ መኖሩ ተደማምረው የመንግስት ስልጣንን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መቆጣጠር ሃብት የማካበት ዋነኛው አማራጭ ተደርጎ የሚወሰድበትን ሁኔታ ይፈጠራል::

በዚህም ምክንያት በዳበሩት አገሮች ሃብት ለማካበት የሚመኝ ሰው ፖለቲካውን ትቶ ወደንግድ ስራ ሲሰማራ እንደ አፍሪካ ባሉት አካባቢዎች ግን ሃብት ለማካበት የሚፈልግ ሰው የመጀመሪያ ምርጫው -ለቲካ ሆኖ ይገኛል:: በዚህ ምክንያት በስመ የፖለቲካ ድርጅት የሚቋቋሙት ድርጅቶች በመሰረቱ የግል ጥቅም ማራመጃ ለየት ያሉ ኩባንያዎች ይሆናሉ:: በነዚህ መካከል የሚደረገው ‹የፖለቲካ ውድድርም፡ በአማራጭ -ሊሲዎች ዙሪያ የሚደረግ ሰላማዊና የሰለጠነ የፖለቲካ ትግል መሆኑ ቀርቶ በተለያዩ የዘራፊ ቡድኖች መካከል የሚደረግ የሞት ሽረት ፍልሚያ ይሆናል:: ይህም ለጠንካራ የፖለቲካ -ርቲዎች መፈጠርና ለዴሞክራሲ ማበብ ከፍተኛ እንቅፋት ይሆናል::

በመሰረቱ በአገር ግንባታና በአስተዳደር ጉዳዮች ላይ አንድ የጋራ አመለካከትና እምነት መፈጠሩ ለዴሞክራሲ ስርአት ማበብ መሰረታዊ ተፈላጊነት ያለው ጉዳይ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ በአገራችንም በሌሎች በርካታ የአፍሪካ አገሮች እንደዚህ አይነቱ የጋራ አመለካከትና እምነት አለመፈጠሩ በመካከላቸው ጤናማ ግንኙነት ያላቸው ጠንካራ የፖለቲካ -ርቲዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በዚህ ላይ በህብረተሰቡ ውስጥ የተንሰራፋው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህል ታክሎበት በ-ርቲዎች መካከል የሚደረግ ትግል ስርአቱን ለአደጋ እስከሚያጋልጥበት ደረጃ የሚደርስበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ታማኝ ተቃዋሚ የሚባል ነገር የማይኖርበትና ተቃዋሚ መሆን ማለት መናድ፣ ማፍረስ፣ በተገኘው አጋጣሚና ባመቸ ስልት በመጠቀም ማደናቀፍ ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ነባራዊ ችግሮች እንደኛ ባሉ አገሮች ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊኖሩ እንደማይችሉ ወይም የዴሞክራሲ ስርአት ሊገነባ እንደማይችል የሚያመለክቱ አይደሉም፡፡ ፀረ-ዴሞክራሲ ሃይሎች እነዚህን ነባራዊ ችግሮች በዋቢነት በመጥቀስ እንደኛ ባሉ አገሮች ዴሞክራሲ ብሎ ነገር ልማትን የሚያጓትትና ከንቱ ንትርክን የሚያባብስ ነገር ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ፍፁም የተሳሳተ እንደሆነ የበርካታ አገሮችን ልምድ በመጥቀስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የነዚህ ነባራዊ ችግሮች መኖር የሚያረጋግጠው እንደኛ ባሉ አገሮች ጠንካራ የፖለቲካ -ርቲዎችን ለመፍጠርና የዴሞክራሲ ስርአትን



ለመገንባት ከፍተኛ ትግልና ጥረት፣ ከፍተኛ ጥንቃቄና ብቃት ያለው የአፈፃፀም ስልት የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ነባራዊ ችግሮች የሚፈጥሩብንን ችግር በብቃት ለመቋቋም የመጀመሪያውና ቁልፉ ጉዳይ ችግሮቹን በሚገባ የመረዳት ጉዳይ ነው፡፡ በአንድ በኩል «እነዚህ ችግሮች ስላሉ ዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም» የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ማስተካከል በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ችግሮች እንደሌሉ በመቁጠር ወይም ተጨባጭ እንድምታቸው ምን እንደሆነ ባለመገንዘብ የዳበሩ አገሮችን ልምድና አሰራር እንዳለ ለመኮረጅ የሚመኘውንና ዴሞክራሲን ለከፍተኛ አደጋ የሚያጋልጠውን አመለካከት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ የችግሮቹን መሰረታዊ ባህሪና እንድምታ በትክክል ተገንዝቦ የሚፈጥሩትን አደጋ ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል ተጨባጭና ትክክለኛ ስልት መቀየስ በዚሁ ላይ ህዝቡ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ችግሮቹን ከምንጫቸው ማድረቅ ዋነኛው መፍትሄ ቢሆንም ይህ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈፀም ስራ አይደለም፡፡ አርብቶ አደሩ ሰፍሮ፣ አርሶ አደሩ ወደዘመናዊ አርሶ አደርነትና ወደከተማ ነዋሪነት ተሸጋግሮ የህብረተሰቡ አወቃቀር ሊቀየር የሚችለው በልማት ሂደት ብቻ ነው፡፡ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ሸቀጥና ምርት አምርቶ የመክበር ጉዳይ ሰፊ ዕድል ያለው ስራ የሚሆነው በተሳካ የልማት እንቅስቃሴ ሂደት ነው፡፡ ሃብት ለማካበት የሚፈልገው ወደ ንግድ ስራው፣ ለአንድ የፖለቲካ

አላማ መኖርና መታገልን የሚመኘው ደግሞ ወደፖለቲካ የሚሰማሩበት የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጠረው በዚሁ የተሳካ የልማት ሂደት ነው:: ይህን መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ስራ የልማት ሰራ ውጤት በመሆኑ ጊዜ መጠየቁ የማይቀር ቢሆንም ዴሞክራሲ በአስተማማኝ መሰረት ላይ ሊገነባ የሚችለው ይኸው ሁኔታ ሲፈጠር ነው:: ስለሆነም ከወዲሁ ይህ ሁኔታ በተቻለ ፍጥነት እንዲፈጠር ለማድረግ ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ ሌት-ተቀን መረባረብ ያስፈልጋል:: ከዚህ አኳያ ሲታይ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት የማረጋገጥ ስራ ዴሞክራሲያችንን በአስተማማኝ መሰረት ላይ የመገንባት ስራም ጭምር ይሆናል::

ምንም እንኳ የዴሞክራሲያችንን መዋቅራዊ ችግሮች በመሰረቱ አስወግዶ ዴሞክራሲያችንን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለመገንባት፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ ርብርቡ ከወዲሁ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም ይህ የራሱ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ እስከዚያው ድረስ አደጋውን ለመቀነስ የሚያስችሉ ርምጃዎች መወሰድ አለባቸው:: ጠንካራ -ርቲዎች የመፈጠራቸው ዕድል ሰፊ ባልሆነበት ወቅት ህብረተሰቡ በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆንባቸውን የተለያዩ አማራጮች መዳሰስ ከሌላውም ጊዜና ቦታ በላይ በኛ ሁኔታ በጣም አስፈላጊ ይሆናል:: በዚህ ረገድ የህዝቡን የሙያና የብዙሃን ማህበራት ማጠናከርና በሰፊው ማሳተፍ፣ ህዝቡ በነዚህ አማካኝነት ብቻ ሳይሆን በግልም የሚሳተፍበትን ዕድል ማመቻቸት ያስፈልጋል::



የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያረጋግጡ የተለያዩ አማራጮችን መዳሰስና ተግባራዊ ማድረግ በአንድ በኩል ብቃት ያለው የፖለቲካ አመራር ለመስጠት የሚችሉ -ርቲዎች ባለመፈጠራቸው የሚፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ያስችላል:: ብቃት ያለው አመራርም ባይገኝ ህዝቡ በቀጥታ ተሳታፊ መሆንና የዴሞክራሲ ስርአቱን ማጎልበት የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል:: በሌላ በኩል ደግሞ በአርሶ አደሩ ተቀባይነት አግኝተው ወሳኝ ሚና መጫወት የሚችሉ ድርጅቶች ሲኖሩ ህዝቡ እነዚህን በቀጥታ ለመከታተልና ለመግራት የሚችልበት ዕድል ይሰፋል:: እንደዚህ አይነቱ ድርጅት ለዴሞክራሲ ታማኝነት ያለው ሲሆን ከነባራዊ ሁኔታው የሚመነጩ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌዎችን ለመመከት የተሻለ ዕድል ያገኛል::

ሙስናና ጥገኝነትን መዋጋትም እንደ አንድ መሰረታዊ መፍትሄ ሊወሰድ ይገባዋል:: መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ጣልቃ ገብነት ለልማት የግድ ተፈላጊ ከሆነው በላይ እንዳይሆን ማድረግ ልማቱን ለማቀላጠፍ ሲባል መደረግ ያለበት ቢሆንም፣ የመንግስትን ሚና በመገደብ ሙስናና ጥገኝነትን ማስወገድ አይቻልም:: የመንግስት ሚና ምንም ያህል ቢገደብ መንግስት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን ገንዘብ ማንቀሳቀሱ ስለማይቀር ሙስናና ጥገኝነቱ በዚህ ላይ ተመስርቶ ሊቀጥል ይችላል:: መደረግ ያለበትና መደረግም የሚችለው የመንግስት አሰራር ለሙስናና ለጥገኝነት የተመቻቸ እንዳይሆን አሰራሩን ማስተካከል ነው:: ህዝቡ በሙስናና በጥገኝነት ላይ በቀጣይነት ሊዘምት የሚችልበት አመለካከት እንዲኖረውና

ይህንኑ ተሳትፎ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ሙስናንና ጥገኝነትን በህጋዊ መንገድ ለመዋጋት የሚያስችል የተመቻቸ ህጋዊ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርትና ሸቀጥ በማምረት ለመክበር ለሚፈልጉት ዜጎች የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር መንግስት በአጋርነት ተሰልፎ ተፈላጊና ጠቃሚ ሆኖ በተገኘው መንገድ ሁሉ እንዲረባረብ ማድረግ ነው፡፡

መንግስት እነዚህን መሰረታዊ አቅጣጫዎች ተከትሎ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታውን በጥንቃቄና በተስተካከለ አቅጣጫ ለመምራት በመረባረብ ላይ ይገኛል፡፡ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ ዴሞክራሲያችንን በአስተማማኝ መሰረት ላይ በመገንባት ረገድም ያለውን ሚና በመገንዘብ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ በመረባረብ ላይ ይገኛል፡፡ ህዝቡ በቀጥታ እንዲሳተፍ ማድረግ ለስርአቱ ጤናማ እድገት ያለውን ተፈላጊነት በሚገባ በመገንዘብ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ ሙስናና ጥገኝነትን በብቃት ለመዋጋትም ያለማሰለስ እየታገለ ይገኛል፡፡ ከዚሁ አኳያ ዋናው ጉዳይ ህብረተሰቡ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተሟላ እውቀት እንዲኖረው ማድረግና ለተቀመጠው አቅጣጫ ተግባራዊነት ሁሉም በየፊናው እንዲረባረብ ማድረግ ነው፡፡

## 5.2. ሚድያና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን፣

ሚድያ የዴሞክራሲ ስርአትን ለመገንባትና ዴሞክራሲን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ለዴሞክራሲ



ስርአት መዳበር እጅግ በጣም ተፈላጊ የሆነውን የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት በመፍጠር ረገድ ሚድያ የላቀ ታሪካዊ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ በተለይም እንደኛ ባሉ ኋላቀር አገሮች ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ተልእኮ ነው፡፡ ሚዲያ ህዝቡ ለልማትና ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንዲነሳሳ፣ በዚሁ ተግባር ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ልማትና ዴሞክራሲ አገራችንን ከጠቅላላ ጥፋት የመታደግ ጉዳዮችም ስለሆኑ ሚድያ በዚህ ረገድ የሚጫወተው ሚና ልዩ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ህዝቡ በልማትና በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጉዳይ ላይ በሰፊው ይሳተፍ ዘንድ ይህንኑ የሚመለከት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት አለበት፡፡ ሚድያ እንደዚህ አይነቱን መረጃ በማቅረብ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ያግዛል፡፡

ሚድያ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት መሰረታዊ ተልዕኮዎች ለማሳካት የወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ምንጭ፣ የውይይትና ክርክር መድረክ ሆኖ ማገልገል አለበት፡፡ አገሪቱ በምትከተላቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ተከታታይ ትንተናዎችና በተለያዩ ወገኖች የሚቀርቡ የተለያዩ አማራጭ ሃሳቦችን እያቀረበ የውይይትና የክርክር መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሚድያ ይህን የመሰለ በሳል የፖለቲካ ውይይትና ክርክር መድረክ ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ሃሳቦችን በነፃ በማንሸራሸር የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ ሊረዳ ይችላል፡፡ በውይይቶቹና ክርክሮቹም ሂደት ተፈላጊው የጋራ እምነትና አመለካከት እንዲፈጠር በር ይከፍታል፡፡

ሚድያ አገሪቱ በምትከተላቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች መሰረት የሚከናወኑትን ተግባራት እየተከታተለ ለህዝብ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ይሰጣል። የተሰሩት የተሳኩ ስራዎች ምን እንደሆኑ ለምን እንደተሳኩ ተንትኖ ያስረዳል። በዚሁ ሂደት የታዩ ድክመቶችንና የተሰሩ ስህተቶችንም ሳያጋንን ወይም ሳይሸፋፍን ለህዝብ ያቀርባል። ስህተቶቹና ድክመቶቹ ለምን እንደተፈፀሙ፣ እነዚህን ለማስተካከል ያሉትን አማራጮች ያቀርባል። በዚሁ ሂደት ህዝቡ ከልምዱ እየተማረ የዴሞክራሲና የልማት አቅጣጫዎቻችንን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ ማድረግ ይቻላል። ህዝቡ በዚህ ላይ ተመስርቶ ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ ለማዳበር ስህተቶችንና ጉድለቶችን ለማስተካከል በሰፊው የሚነሳሳበት ሁኔታ እንዲፈጠርም ያስችላል።

በሚዲያ መቅረብ ያለበት መረጃ አገሪቱ በምትከተላቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ዙሪያ የሚፈፀሙትን ተግባራት የሚመለከት ብቻ መሆን የለበትም። በርግጥ ዋናው ጉዳይ ህዝቡ የራሱን ህይወት ለመምራት፣ በአገሩ ጉዳይ ላይ በብቃት ለመሳተፍ የሚያስችለው መረጃ የማግኘቱ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ዋናው ለህዝብ መቅረብ ያለበት መረጃ የአገሪቱንና የህዝቡን ዕድል በሚወስኑት የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ህይወቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚነኩ የውጭ ዜናዎችን፣ መረጃዎችንና ሌሎችንም መረጃዎች ማግኘት መቻል አለበት። ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ያለው ዜጋ



የዴሞክራሲ ትልቅ እሴት ነውና ሚድያ እንደዚህ አይነት ዜጋ እንዲኖር በማድረግ ረገድ የላቀ ሚና መጫወት ይገባዋል።

ሚድያ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከላይ እንደተጠቀሰው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ የተለያዩ አካላት በስራው ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ። መንግስት በሚድያ ስራ አንዱ ትልቁ ተዋናይ ነው። በዳበሩት አገሮችም ቢሆን መንግስት በሚድያ ስራ፣ በተለይም በኤሌክትሮኒክስ ሚድያ ስራ በሰፊው ተሳታፊ ይሆናል። ሌሎቹ የሚድያ አይነቶች የሚድያን ተልእኮ በብቃት የሚወጡበት ሁኔታ እየተፈጠረ በሄደ ቁጥር የመንግስት ሚና እየተሸረሸረ የመጣ ቢሆንም በበርካታ የዳበሩ አገሮች የላቀ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። በዚህ ረገድ በምሳሌነት የሚጠቀሰው ታዋቂው የእንግሊዝ መንግስት ንብረት የሆነው ቢቢሲ ነው።

እንደኛ ባሉት አገሮች ሌሎቹ የሚድያ አካላት የተለያዩ ውሱንነቶች እንደሚኖሩባቸው የታወቀ ጉዳይ ነው። በመሆኑም መንግስት በሚድያው ስራ ላይ በሰፊው መሳተፉ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። የመንግስት ሚና እዚህም ላይ በዳበሩት አገሮች ከሚታየው የላቀ እንጂ ያነሰ ሊሆን አይችልም። በርግጥ መንግስት የራሱ ጠንካራ ሚድያ መፍጠሩ ለበጎም ለመጥፎም ስራ ሊውል ይችላል። የመንግስት ሚድያ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ምን እንደሚሆን የሚወስነው የመንግስት ሚድያነቱ ሳይሆን፣ መንግስት የሚመራበት አላማ ነው። መንግስት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ቆርጦ የተነሳ

ከሆነ የመንግስት ሚድያም ትልቅ የዴሞክራሲ መሳሪያ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ በምሳሌነት የሚጠቀሰው አሁንም ቢቢሲ የተባለው የመንግስት ሚድያ ነው፡፡ የመንግስት አላማ ዴሞክራሲን ማፈን ከሆነ የመንግስት ሚድያም አንድ የአፈና መሳሪያ ሆኖ ማገልገሉ አይቀርም፡፡

በአገራችን መንግስት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው ትግል መሪና አስተባባሪ ነው፣ መሆንም ይኖርበታል፡፡ በአገራችን ከመንግስት ሚድያ ውጭ ያሉት ሚድያዎች የራሳቸው መዋቅራዊ ችግር ያለባቸው በመሆናቸው ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ማበርከት የሚችሉትን አስተዋፅኦ እያበረከቱ የሚገኙ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የመንግስት ሚድያ ጥራቱ ተጠብቆና በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ ሚድያ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ማበርከት የሚገባውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት መደረግ አለበት፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትንና ሚድያው ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አስተዋፅኦ ለማድረግ ሊከተላቸው የሚገቡትን አቅጣጫዎች በብቃት በመከተል ጥራቱን በየጊዜው እያሻሻለ በአገራችን ዋነኛ የሚድያ ሃይል ሆኖ እንዲቀጥል መደረግ አለበት፡፡

የፖለቲካ -ርቲዎችም በሚድያ ስራ ላይ በሰፊው መሳተፍ ይችላሉ፣ በተግባርም ይሳተፋሉ፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች መስመሮቻቸውንና አማራጭ ሃሳቦቻቸውን ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ ለማስረዳት ሚድያን በሰፊው ይጠቀማሉ፣ መጠቀምም ይገባቸዋል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች በውስጣቸው ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚያደርጉት በፖሊሲና



በአቅጣጫ ጉዳዮች ላይ የሚያካሂዱዋቸውን ክርክሮችም በሚድያቸው ያቀርባሉ፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች ሚድያ የድርጅቱን እንቅስቃሴ በሚመለከት ዜናዎችን በማቅረብ፣ በአገር ውስጥና በውጭ ዜናዎች ላይ የተመሰረቱ የፖርቲውን አቋም የሚያንፀባርቁ የዜና ትንታኔዎችን በማቅረብም ይሰራሉ፡፡ የፖለቲካ -ርቲዎች ሚድያ በዚሁ መልክ የድርጅቶቹን አቋም ከማስረዳት ባሻገር ለአገራዊው የጋራ አመለካከትና እምነት መፈጠርና መዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላል፡፡

በበለፀጉት አገሮች የ-ርቲዎች ሚድያ በሂደት እየተሸረሸረና እየከሰመ መጥቷል፡፡ ይህን የመሰለው ሚድያ ሰፊ ልምድ የነበራቸው የዳበሩ የአውሮ- አገሮችም ቢሆን ይህ ሚድያ እየከሰመ በግል ሚድያ እየተተካ መጥቷል፡፡ የግል ሚድያው የአንድ ወይም የሌላ የፖለቲካ አዝማሚያን የሚደግፍ በመሆኑ በተዘዋዋሪ መንገድ የ-ርቲዎችን አቋም ያራምዳል ቢባልም የድርጅት ልሳን በመሆን የሚታወቁ ሚድያዎች በጣም ጥቂት እየሆኑ መጥተዋል፡፡

በአገራችን በርካታ የድርጅት ልሳኖችና ሚድያዎች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ በግልፅና በይፋ የድርጅት ሚድያነታቸውን አሳውቀው የሚሰሩ ሲሆኑ ሌሎቹ የድርጅት ሚድያነታቸውን ለመደበቅ የሚሞክሩ ናቸው፡፡ በግል ሚድያ ስም የሚንቀሳቀሱ በተግባር ግን የህገ-ወጥ -ርቲዎችና ድርጅቶች ልሳኖች የሆኑ በርካታ ጋዜጦች በአገራችን ይዘጋጃሉ፣ ይሰራጫሉ፡፡ የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ያሉባቸው መዋቅራዊ ችግሮች ምን እንደሆኑ ከላይ

ተገልፀዋል፡፡ በ-ርቲዎቹ የሚዘጋጁ ልሳኖችም ከነዚህ ችግሮች ነፃ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በተለይም አላማቸውን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ የማራመድን አቅጣጫ ረግጠው ስርአቱን በሃይል ለመናድ እየተንቀሳቀሱ ያሉ የህገ-ወጥ ድርጅቶች ልሳኖች ለዴሞክራሲ ስርአት ይህ ነው የሚባል በጎ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ አይደሉም፡፡ አላማቸውም የተያዘውን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማ ማጠናከር፣ ማሻሻልና ማበልፀግ ሳይሆን ይህንኑ መናድ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ድርጅቶች ሚድያ በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፡፡ በአገራችን ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና ለልማት በፅናት የቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች በልሳኖቻቸው አማካኝነትና ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ከፍተኛና አዎንታዊ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደቱ እየተበራከቱና እየጎለበቱ ሲሄዱ የሚኖራቸው በጎ አስተዋፅኦም አብሮ እያደገ እንደሚሄድ ይገመታል፡፡

የብዙሃንና የሙያ ማህበራትም፣ በተለይ የሙያ ማህበራት በሚድያ ስራ ላይ ሊሳተፉና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ የሙያ ማህበራት በሙያ መስካቸው ያሉ አዳዲስ ግኝቶችን ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ በሚድያቸው አማካኝነት በማሳወቅ ለሳይንስ እውቀት መዳበርና መስፋፋት የላቀ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡ በሙያተኞች መካከል በተለያዩ ሙያ ነክ ጉዳዮች፣ በተለይም ከአገሪቱ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት



ግንባታ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ጥልቀት ያለው ውይይትና ክርክር እንዲካሄድ በመድረክነት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ በሙያ መስኩ የተደረጉ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ በሚድያቸው ማሳወቅ ይችላሉ፡፡ የብዙሃን ማህበራትም የስራ እንቅስቃሴያቸውን በሚመለከት ለህዝቡና ለአባሎቻቸው መረጃ የሚሰጡበት፣ የአባላቱን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አቋሞቻቸውን የሚያሳውቁበትና የሚከራከሩበት ሚድያ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ትግል ውስጥ የሙያና የብዙሃን ማህበራት የላቀና ለየት ያለ ሚና መጫወት እንደሚገባቸው ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡ የሙያና የብዙሃን ማህበራት ሚድያዎች ከዚሁ ጋር በተያያዘ የላቀ ሚና መጫወት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ ይሁንና ይህ ጉዳይ ከማህበራቱ አለመጠናከር ጋር በተያያዘ ምክንያት እስካሁን ድረስ አጥጋቢ ስራ የተሰራበት አይደለም፡፡ ለወደፊቱ የብዙሃንና የሙያ ማህበራትን ለማጠናከርና በልማትና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ላይ በቂ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚካሄደው ጥረት የነዚህን ድርጅቶች ሚድያ የመፍጠርና የማጠናከር ገፅታም ሊኖረው ይገባል፡፡

በብዙዎቹ የዳበሩ አገሮች ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የግል ሚድያ ነው፡፡ የግል ሚድያ በአንድ በኩል ከሆቴል ወይም ከፋብሪካ ባልተለየ መልኩ ትርፍ ለማግኘት ተብሎ የሚሰራ የንግድ ስራ ነው፡፡ የንግድ ተቋሞችን የሚመለከቱ ህግና ስርአቶችን በመከተል የሚሰራ ስራ ነው፡፡ ይልቁንም በአሁኑ

ወቅት በአለም እጅግ ግዙፍ ተብለው ከሚታወቁት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች መካከል የሚድያ ኩባንያዎች በቀደምትነት የሚጠቀሱ ሆነዋል፡፡ የግሉ ሚድያ በመሰረታዊ ባህሪው የንግድ ስራ ነው ቢባልም በአገሮች የፖለቲካ ህይወት ውስጥ የላቀ ሚና የሚጫወት ስራም ጭምር ነው፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ገፅታውን የሚገዙ ህጎች ይኖራሉ፡፡ በዚህ መሰረት ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት እየተሸረሸረ ያለ ቢሆንም የውጭ ኩባንያዎችን ሚና የሚገድብ አሰራር በበለፀጉት አገሮችም የተለመደ አሰራር ነበር፡፡ በሚድያ የሚደረግ ስም የማጥፋት ስራን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርአትም ይኖራል፡፡

በበለፀጉት አገሮች ያሉ የግል ሚድያዎች በጥራታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ህጉን ተከትለው የሚሰሩ ቢሆኑም በይዘታቸው ብስለት የሚጎድላቸውና የዘቀጡ ናቸው፡፡ በተለምዶ የዘቀጠ ፕሬስ (ጋተር ፕሬስ) ተብለው የሚገለፁም ናቸው፡፡ እንደነዚህ አይነቶቹ ሚድያዎች በበለፀጉት አገሮች ይህን ያህል ተሰሚነት የሌላቸው ናቸው፡፡ ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው የግል ሚድያዎች ከፍተኛ ብስለትና የሃላፊነት ስሜት ያላቸው በሳል ሚድያዎች ናቸው፡፡ ትርፍ ለማግኘት የተቋቋሙ በመሆናቸው ትርፍ የማግኘቱ አላማ ከሚድያው ስራ ጥራትና ብስለት ጋር የሚጋጭበት አጋጣሚ ቢኖርም በአጠቃላይ ሲታይ ግን እነዚህ ሚዲያዎች  የዴሞክራሲና የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ዋነኛ ጠበቆችና አቀንቃኞች ሆነው ይሰለፋሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የግል ሚድያዎች የአገሪቱን የንግድና



ሌሎች ህጎች አክብረው ይንቀሳቀሳሉ፣ ይህን ባያደርጉ በህግ እንደሚጠየቁም ያውቃሉ፡፡ ስለሆነም ህጉን የሚጥስ ስራ የሚሰሩበት አጋጣሚ ከቁጥር የማይገባ ሆኖ ይታያል፡፡ እነዚህ ሚድያዎች ሚድያ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መስራት የሚገባውን ስራ ከሞላ ጎደል በብቃት የሚፈፅሙት በየዕለቱ የሚቆጣጠራቸው የህግ አስከባሪ አካል በመኖሩ አይደለም፡፡ ስላመኑበት ጭምር ነው፡፡ የኩባንያዎቹ ባለቤቶች የዴሞክራሲ ስርአት ማበብና የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መጠናከር የህልውናቸው ጉዳይ እንደሆነ በሚገባ ያውቃሉ፡፡ ስለሆነም ስርአቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ምንም አይነት ስራ አይሰሩም፡፡ ይልቁንም ሚድያቸው የስርአቱ ዋነኛ ጠበቃ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ይህ ማለት ሁልግዜም በስልጣን ላይ ያለ መንግስትን ይደግፋሉ ማለት አይደለም፡፡ የተሳሳቱ ፖሊሲዎችን በበቂ ትንተና ያጋልጣሉ፣ የተፈፀሙ ጉድለቶችና ስህተቶችን ሳይሸፋፍኑ፣ ሳያጋንኑ ያጋልጣሉ፡፡ የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም ይጠቁማሉ፡፡ ይህን በማድረግ ጥራት ያለው የመንግስት ሚድያ ሊሰራው የሚገባውንም ስራ ይሰራሉ፡፡ ይህን በማድረግ በትክክለኛው መንገድ የስርአቱ ዋነኛ ጠበቆች ይሆናሉ፡፡

የሚድያዎች ባለቤቶች ብዙውን ጊዜ በሚድያው የዕለት ተዕለት ስራ ላይ ባይሳተፉም፣ ዋነኛ አዘጋጆችንና ኤዲተሮችን ይመርጣሉ፡፡ በዚህም አማካኝነት ሚድያቸውን ይቆጣጠራሉ፣ መሰረታዊ አቅጣጫውን ይወስናሉ፡፡ በመሆኑም ቀኝ ዘመም ባለቤቶች ያሏቸው የሚድያ ኩባንያዎች ቀኝ ዘመም አመለካከት ሲያንፀባርቁ፣ ግራ ዘመም ባለቤቶች ያሏቸው የሚድያ

ኩባንያዎችም ግራ ዘመምነቱን ያንፀባርቃሉ። ይሁንና የግል ሚድያ የተባለውን ሚና የሚጫወተው ባለቤቶቹ ስለተቆጣጠሩት ብቻ አይደለም። በሚድያው ስራ ላይ የተሰማሩ ጋዜጠኞችም የስርአቱ መናድ የህልውናቸው ማብቂያ መሆኑን አምነው ስለሚንቀሳቀሱ ጭምር ነው። ጋዜጠኞቹ የዴሞክራሲና የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአቱ ከተናደ የነሱም ህልውና አብሮ እንደሚያከትም ያውቃሉ ስለሆነም ለህልውናቸው ሲሉ ስርአቱን ለአደጋ በሚያጋልጥ ተግባር ላይ አይሰማሩም።

በበለፀጉት አገሮች ያሉት ዋና ዋና የግል ሚድያዎች እንደቢቢሲ ያሉ ጥራት ያላቸው የመንግስት ሚድያዎች ከሚሰሩት ስራ ባልተለየ አኳኋን በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና የለት ተለት እንቅስቃሴ ላይ ገንቢ ሚና የሚጫወቱት ከዚህ ውጭ መስራት የባለ ንብረቶቹንና የሰራተኞቹን ጥቅምና ህልውና ለአደጋ ስለሚያጋልጥ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ከዚሁ አኳያ የላቀ ሚና የሚጫወተው ጉዳይ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ በስርአቱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ የጋራ አመለካከትና እምነት የመያዙ ጉዳይ ነው። የሚድያ ባለንብረቶችና ሰራተኞችን ጨምሮ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ይህንን የጋራ አመለካከትና እምነት የሚጋሩ በመሆናቸው በነፃ ፍላጎታቸው የሚሰሩት ስራ ገንቢ ሊሆን ይችላል። የጋዜጠኛ ስነ-ምግባርና ሙያም ይህንኑ የጋራ እምነትና አመለካከት መሰረት ያደረገና የሚያጠናክር ይሆናል።

በኛ አገር ሁኔታ የግል ሚድያው መሰረታዊ መዋቅራዊ ችግሮች ያሉበት ነው። የሚድያውን የንግድ ስራ ገፅታ በምናይበት



ወቅት በሌላው የንግድ ስራ ከሚታየው የጥገኝነትና የአየር በአየር ንግድ ባህሪያት ነፃ ሊሆን አይችልም። በጥራቱና በዋጋው ተወዳዳሪ የሆነ አገልግሎት በማቅረብ ማትረፍን፣ ገቢና ወጪውን በትክክል ማሳወቅን፣ የመንግስትን ግብር በትክክል መክፈልን ያልለመደና ያልተቀበለ ጥገኛ የግል ባለሃብት የተሻለ ዕድል ባገኘበት ሁኔታ ውስጥ የሚሰሩ የሚድያ ኩባንያዎች በመሆናቸው ከነዚህ ስህተቶች የፀዱ አይደሉም። በህገ-ወጥ መንገድ ገቢን ማሰባሰብና መክበር እንደ ባህል በተወሰደበት ሁኔታ ውስጥ የሚሰሩ በመሆናቸው የዚሁ ባህል ሰለባ ከመሆን አይድኑም። ኩባንያዎቹን የተለያዩ ገንዘብ ያላቸው ሃይሎች በህገ-ወጥ መንገድ ፋይናንስ እያደረጉ እንደመሰላቸው ሊያሽከረክሩዋቸው የሚችሉበት ዕድል ሰፊ ሆኖ ይታያል። ሌላው ቀርቶ አክራሪዎችና ሽብር ፈጣሪዎች ፋይናንስ የሚያደርጓቸውና እንደመሰላቸው የሚያንቀሳቅሷቸው ሚድያዎች በአገራችን ብቅ እያሉ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ነገሮች አሉ። ይህ ችግር የሚድያ ኩባንያዎች የተናጠል ችግር ስላልሆነ በተናጠል ሊፈታ የሚችል አይደለም። በንግዱ ህብረተሰብ ውስጥ የጥገኝነትና የአየር በአየር አሰራርን ለማስወገድና ለማክሰም ከሚደረገው ትግል ጋር አብሮ መፈታት የሚችልና የሚገባውም ጉዳይ ነው።

የግል ሚድያ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መጫወት የሚገባውን ገንቢ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ከሚፈለጉት መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱ በመሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ አገራዊ የጋራ አመለካከትና እምነት መያዝ በመሆኑና በአገራችን በአሁኑ ወቅት ይህ ጉዳይ ተሟልቶ የማይገኝ በመሆኑ ለአገራችን የግል

ሚድያ መዳከም አንድ መሰረታዊ ምክንያት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ብዙዎቹ የግል ሚድያዎች ስርአቱን የመናድ፣ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ አላማውንና የልማት እቅዱን የማደናቀፍ ተልእኮ ተሸክመው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ሆነዋል። ይህ በግል ሚድያ ሽፋን የህገ-ወጥ የፖለቲካ ድርጅቶች ልሳን በመሆን የሚያገለግሉትን ብቻ ሳይሆን ከዚህ ውጭ ያሉትን በርከት ያሉ የግል ሚዲያዎች የሚመለከት ነው። የበሳል የፖሊሲና የአቅጣጫ ውይይትና ክርክር መድረክ መሆን አልቻሉም። የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ትግላችንን በሚመለከት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ከማቅረብ ይልቅ የሌሉ ስህተቶችን ፈጥሮ ያሉትን መልክና ይዘታቸውን በሚቀይር አኳኋን አዛብቶ በማቅረብ ላይ ያተኮሩ ሆነዋል። ከፍተኛ የጋዜጠኛ ስነ-ምግባርና የሙያ ችግርም የሚታይባቸው ናቸው።

መንግስት የግል ሚድያን በተመለከተ የተከተለው አቅጣጫም ለዚሁ ችግር መባባስ የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል። የችግሩ መሰረታዊ መዋቅራዊ ምንጮች ምን እንደሆኑ በመገንዘብ ችግሩን ከመሰረቱ ለማስወገድ የሚያስችል የረጅም ጊዜ እቅድና እይታ ያለው ስራ አልተሰራም። ችግሩ አገራዊ የጋራ እምነትና አመለካከት ካለመፈጠሩ፣ በንግዱ ህብረተሰብ ዘንድ ካለው ጥገኝነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስር-ነቀል መፍትሄ ማግኘት እንደማይቻል ሊሰመርበት ይገባ ነበር። ከዚህ አኳያ ችግሩ በልማቱ ሂደት ጥገኝነትን ከማክሰም ትግል ጋር ተያይዞ መታየትና በዚሁ ክልል እንዲፈታ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ሊሰመርበት በተገባ ነበር። ችግሩ የጋራ አመለካከትና



እምነት ከመፍጠር ጋር የተያያዘ በመሆኑ በህብረተሰቡ በአጠቃላይ ይህንኑ የጋራ እምነትና አመለካከት ለመፍጠር ከሚሰራው ስራ ጋር አብሮ እንዲታይና እንዲፈታ መደረግ እንዳለበት ሊጨበጥ ይገባ ነበር። ይህ እስከሆነ ድረስ በግል ሚድያው አካባቢ የሚታዩ ችግሮችን ለመቀነስ ጥረት ከማድረግ ጎን ለጎን ክፍተቱን ጥራት ባላቸው የመንግስት፣ የሙያና የብዙሃን ማህበራት ሚድያዎች ለመሸፈን ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ እንደሚገባ ሊታወቅ ይገባ ነበር።

ለወደፊቱም ቢሆን ሚድያ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታና በልማት አላማችን መሳካት ላይ ሊጫወት የሚገባውን ገንቢና የላቀ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ በትክክለኛ ትንተና ላይ የተመሰረተ የተቀናጀ ስራ መሰራት አለበት። ስለሆነም ከረጅም ጊዜ አኳያ ዋናው ጉዳይ የጋራ እምነትና አመለካከት የመፍጠርና በንግዱ ህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ጥገኝነት የማክሰም ጉዳይ ስለሆነ ይህንን ለማሟላት የሚካሄደው ስራና ትግል ሚድያንም በሚሸፍን አኳኋን እንዲፈፀም ማድረግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል። ከዚሁ ጎን ለጎን ክፍተቱን በከፊልም ቢሆን ሊሸፍኑ የሚችሉ የመንግስት፣ የሙያና የብዙሃን ማህበራት ሚድያዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መጫወት የሚገባቸውን ሚና በብቃት ለመጫወት የሚያስችል ይዘትና አቀራረብ እንዲኖራቸውና ይህንን መሰረት በማድረግ እንዲጠናከሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

የግሉ ሚድያ ከአጭር ጊዜም አኳያ ያሉበትን ችግሮች

ለመቀነስ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። መንግስት በዚህ ረገድ በዋነኛነት ሚድያው አፍራሽ ሚና እየተጫወተ ነው ከሚል እምነት በመነሳት ሚድያውን የማግለልና በከፉ መልኩ የሚገለፁ ህግን የመጣስ ስራዎችን በፍርድ ቤት የማቅረብ አካሄድ ነበር የተከተለው። ህጉ በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ የህግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት በመፍጠር ረገድ እጅግ ተፈላጊ ቢሆንም መንግስት በዚህ ረገድ ያከናወነው ስራም ህግን የመጣስ ስራዎችን ለማስቀምና ለመቀነስ የሚያስችል ይዘትና አፈፃፀም የነበረው አይደለም። ሚድያውን የማግለል አሰራርም ከግሉ ሚድያ ውስጥ በጎ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉትን ወይም ለወደፊቱ በዚህ አቅጣጫ ሊሰሩ የሚችሉትን የማያደፋፍር፣ አንድ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ሚድያውን እንዲያካትት ለማድረግ የማያስችል ነበር። በመሆኑም የአጭር ጊዜ ተግባሩም በተስተካከለ የረጅም ጊዜ ቅኝት ያልተመራ ከአጭር ጊዜ አኳያም የሚድያውን ችግር ለመቀነስ የማያስችል ነበር።

መንግስት የግል ሚድያውን ችግር ለመቅረፍ በሚያስብበት ወቅት የግሉ ሚድያ ያሉበትን መዋቅራዊ ችግሮች በአጭር ጊዜ ማስወገድ እንደማይችል፣ በመሆኑም ዘለቄታዊ መፍትሄ ለማምጣት የሚሰሩ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው እስከዚያው ድረስ ክፍተቱን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሊሸፍኑ የሚችሉ አማራጮችን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት። የሚቀመጠው የአጭር ጊዜ መፍትሄ ከረጅሙ ጊዜ አንፃርም ገንቢና ጠንካራ የግል ሚድያ ለመፍጠር የሚያስችል



መሆን አለበት። ከአጭር ጊዜ አኳያ የሚወሰዱት ርምጃዎች ከአጭር ጊዜ ጠቀሜታቸው አኳያ ብቻ ሳይሆን ከረጅም ጊዜ ጠቀሜታቸው አኳያ፣ በተራዘመ ሂደት ጠንካራ የግል ሚድያን በመፍጠር ረገድ ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ አኳያ መታየት አለባቸው። የግል ሚድያ በአገራችን አዲስ ተክል እንደመሆኑ መጠን በዚያው ቀጭጮ እንዳይቀር ወይም ከአበቃቀሉ ተጣሞ መቼም ቢሆን ተልእኮውን የማይፈፅም እንዳይሆን በተቃና አኳኋን የሚያድግበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆን አለበት።

በዚህ መሰረት ለምሳሌ በህግ የበላይነት የሚመራ ፕሬስ ከሌለ ከጅምሩ ይህንን መርህ በመጣስ ላይ የተመሰረተ ሚድያ ከሆነ ለወደፊቱም በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የሚጠበቅበትን ሚና የሚጫወት ሚድያ ሊኖረን አይችልም። የህግ የበላይነትን የተቀበለ ፕሬስ ከመፍጠር አኳያ መተኮር ያለበት ግን ለዘለቄታው ወሳኝነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ መሆን ይገባዋል። ከዚህ አኳያ ሚድያው እንደንግድ ተቋም ከጥገኛነትና ከአየር በአየር አሰራር ውጭ የሚሆንበትን ሁኔታ መፍጠር፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ወይም አገልግሎት በማቅረብ መክበርን እንደመርህ የወሰዱ የሚድያ ድርጅቶች እንዲሆኑ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። በአየር ባየር ንግድ ስሌት የሚሰሩ የሚድያ ድርጅቶች ምንም ቢሆን ወደጠንካራ የዴሞክራሲ ስርአት ሚድያ ሊያድጉ አይችሉም። በልማታዊ ባለሃብት ንግድ ስሌት የሚሰሩ የሚድያ ድርጅቶች ግን ከአጭር ጊዜ አኳያ አፍራሽ ሚና ቢጫወቱም በሂደት እየተሻሻሉና እየጎለበቱ መሄዳቸው የማይቀር ነው። ስለሆነም ገና ከጅምሩ የስንዴና የእንክርዳድ ዘርን ለመለየት

በሚያስችል አኳኋን የንግድ ድርጅት ገፅታቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስተካከልና ይኸው ስራ በኢኮኖሚው በአጠቃላይ የአየር በአየር ንግድን ለማክሰም ከሚደረገው ትግል ጋር ተቀናጅቶ እንዲፈፀም ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የግል ሚድያዎች ከአጭር ጊዜ አኳያ ገንቢ ሚና በመጫወት ረገድ ያለባቸውን ችግር ለመቀነስ ዋናው ጉዳይ ሰዶ ማሳደድ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት ለመፍጠር የሚደረገው ትግል ነው። መንግስት ይህ ትግል ሚድያንም በሚሸፍን አኳኋን በብቃት እንዲፈፀም የማድረግ ሃላፊነት አለበት። በዚህ መሰረት ለምሳሌ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የግል ሚዲያ ሚና ምን እንደሆነ፣ የሚዲያ ስነ-ምግባርና የሙያ ደረጃ ምን መምሰል እንዳለበት በመስኩ በተሰማሩ ሰዎች አካባቢ ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡ በአጠቃላይም እንዲታወቅ መደረግ አለበት። በስራው ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሙያ ብቃታቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረት መንግስት መደገፍ አለበት። በነዚህ ጉዳዮች ላይ መንግስት ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆን አለበት። ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ለህብረተሰቡ ማቅረብ ለሚፈልጉትና ለሚችሉት መንግስት መረጃውን መስጠት መጀመር አለበት።

መንግስት እነዚህን ርምጃዎች ሲወስድ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያሉ የግል ሚዲያዎች ሁሉ ጤናማ አቅጣጫን ይይዛሉ ተብሎ ሊታሰብ የሚችል አይደለም። የሰላምና የዴሞክራሲ ግንባታ አላማን ለማክሸፍ ሆን ብለው የተነሱ የውስጥና የውጭ



ሃይሎች የሚያሽከረክሩዋቸው ተቋሞች ስላሉ እነዚህ ምንም ቢሆን እንክርዳድነታቸውን መቀየር የሚቻል አይሆንም። ይሁንና ካሉት ውስጥ ጥራት ያለው የስንዴ ዘር መሆን የሚችሉ እንደሚኖሩና አዳዲስም ሊፈጠሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። ዋናው ጉዳይ ስንዴውን ከእንክርዳዱ በብቃት ለማንገዋለል የሚያስችል ሁኔታ የመፍጠርና በገንቢ አቅጣጫ ሊያድጉ ለሚችሉት ለእድገታቸው የተመቸ ሁኔታ የመፍጠር ጉዳይ ነው። ዋናው ነገር በስራው ላይ የተሰማሩት ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ ህብረተሰቡም ገንቢ ሚና የሚጫወቱትን ከሌሎቹ ማንገዋለል የሚችልበት ሁኔታ መፍጠር ነው። የመንግስት ዋነኛ ትኩረት በዚህና የሚዲያውን የንግድ ገፅታ ከአየር በአየር ንግድ ስሌት በማላቀቅ ተግባር ላይ መሆን ይኖርበታል።

ይህ ሲባል መንግስት የአገሪቱን ህጎች በግልፅ ከመጣስ ስም በማጥፋት ህውከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር በመስበክ ስራ ላይ የተሰማሩትን ሚዲያዎች እያየ እንዳላየ ማለፍ አለበት ማለት አይደለም። የህግ የበላይነት ሲረገጥ አይኑን በመጨፈን በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ የዴሞክራሲ ስርአት መገንባት አይቻልም። በመሆኑም ዋናው ትኩረት ከላይ በተገለፁት ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ እንጂ ሰዶ በማሳደድ ላይ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚወሰዱ የህግ ርምጃዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህም እንደ እስካሁኑ የከንቱ ሰዶ ማሳደድ ባህሪ የያዙ መሆን የለባቸውም። በዚህ ረገድ ያሉት አዋጆችና አሰራሮች ተፈትሸው፣ የሌሎች አገሮች ልምድም ተቀምሮ ህጉን አክብሮ የሚሰራውን የማይነካ ከህግ ውጭ የሆነውን በአስተማማኝ አኳኋን የሚያስወግድ

ይዘት ያለው ስራ መሆን አለበት:: የተመረጠ፣ ስንዴውን ከእንክርዳዱ በብቃት በመለየት ላይ የተመሰረተ አስተማማኝ ውጤት ያለው የህግ ርምጃ መሆን አለበት::

## 5.3. የብዙሃንና የሙያ ማህበራት በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣

የብዙሃንና የሙያ ማህበራት በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ስርአት ቢሆን እጅግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: በመሆኑም የዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ጥንካሬ ከሚመዘንባቸው መስፈርቶች አንዱ በስርአቱ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉ ተቋማት መጠንና ጥንካሬ ነው:: በኛ አገር ሁኔታ የነዚህ ድርጅቶች ሚና ከዚህም የላቀ መሆን ይኖርበታል:: በኛ ሁኔታ የፖለቲካ -ርቲዎች ብቃት ያለው የፖለቲካ አመራር በመስጠት ረገድ ምን አይነት ችግር እንዳለባቸውና ይህንኑ በከፊልም ቢሆን በማካካስ ረገድ የሙያና የብዙሃን ማህበሮች ተጨማሪ ሃላፊነት መሸከም እንዳለባቸው ከፍ ሲል ተገልጿል:: የግል ሚድያ ያለበትን ችግር በከፊል በማካካስ ረገድም ተጨማሪ ሃላፊነት መሸከም አለባቸው:: ዴሞክራሲያችን በህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ መሆን ስላለበትና ህዝቡ ብቃት ያለው ተሳትፎ ለማድረግ መደራጀት ስላለበት የሙያና የብዙሃን ማህበራት በዚህ ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል:: በነዚህና በመሰል ምክንያቶች የሙያና የብዙሃን ማህበሮች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን ውስጥ ልዩና የላቀ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ይሆናል::



የሙያና የብዙሃን ማህበራት ከላይ የተጠቀሰውን ሚና ለመጫወት የሚችሉት በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ መያዝ የሚገባቸውን ባህሪ ይዘው ሲገኙ ነው:: በዚህም መሰረት የሙያ ማህበሮች በግልፅ በሚቀመጥ መስፈርት መሰረት መስፈርቱን የሚያሟላ ዜጋን በሙሉ ለማሳተፍ ክፍት የሆኑና ሁሉንም ለማሰባሰብ በቂ ጥረት የሚያደርጉ መሆን ይኖርባቸዋል:: ግልፅ የአባልነት መስፈርት የሌላቸው፣ ወይም የአባልነት መስፈርት የማያሟላውን ሰው የሚያሰባስቡ፣ የሚያሟላውን ደግሞ የሚያገልሉ የብዙሃንና የሙያ ማህበራት ሊኖሩም አይገባም፣ የዚህ አይነት ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ስርአቱ ውስጥ ገንቢ ሚና ሊጫወቱ አይችሉም:: ማህበራቱ የጥቂት ሰዎች ክበብ ሳይሆኑ በግልፅ በሚያስቀምጡት ተገቢ መስፈርት መሰረት አባል ለመሆን የሚችለውን ሁሉ በአባልነት ለማሰባሰብ ዝግጁ የሆኑ በርግጥም የብዙሃን በርግጥም የሙያ ማህበሮች መሆን አለባቸው::

ማህበራቱ ግልፅና ለአዳዲስ አባላት ክፍት ከመሆን ባሻገር በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የሚሰሩ መሆን አለባቸው:: መሪዎቻቸውን በነፃና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን የሚመርጡና የሚሽሩ፣ ውሳኔዎቻቸውን በዴሞክራሲያዊ ውይይትና በድምፅ ብልጫ የሚወስኑ መሆን አለባቸው:: ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አሰራር ያላቸው የሙያና የብዙሃን ማህበራት የዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ መድረክ ሊሆኑ አይችሉም:: ውስጣዊ አሰራራቸው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ ማህበራት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ በጎ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ አይችሉም::

ማህበራቱ የጥቂቶች ክበብ ሳይሆን በግልፅ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ማንኛውንም የሚያሳትፉ፣ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ያላቸው የመሆናቸው ጉዳይ በዴሞክራሲያዊ ስርአቱ ውስጥ ገንቢ ሚና እንዲኖራቸው ለማድረግ መሟላት ያለበት ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ህገ-መንግስታዊ ግዴታን የማክበር ጉዳይም ጭምር ነው፡፡ ህገ-መንግስታችን በአንቀፅ 38 ንኡስ አንቀፅ 2፣ 3፣ ና 4 ላይ የሚከተለውን ያስቀምጣል፡፡

“1. በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሰራተኞች፣ በንግድ፣ በአሰሪዎችና ሙያ ማህበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት፡፡

“3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለሃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈፀማሉ፡፡

“4. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1ና 3 ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆኑ ድረስ በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡”

ከህገ-መንግስቱ አንቀፅ እንደሚታየው የሙያና የብዙሃን ማህበራት ዜጎችን በእኩልነት የሚያስተናግዱ ስለሆነም የአባልነት መስፈርቶቻቸውን በግልፅ አስቀምጠው መስፈርቱን ላሟላ ዜጋ ሁሉ በራቸውን ክፍት የሚያደርጉ እንጂ በራቸውን ቀርቅረው



የጥቂቶች ክበብ ወይም የቤተሰብ ሸንጎ መሆን የሚገባቸውና የሚችሉ አይደሉም፡፡ በራቸውን አለአግባብ የሚዘጉ ማህበሮች ካለባቸው ሌላ ጉድለት በተጨማሪ የአባልነት መስፈርቱን አሟልቶ በፈቃዱ አባል መሆን የሚፈልገውን ዜጋ መብት ይረግጣሉ፡፡ የውስጥ አሰራራቸው ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ማህበራትም በተመሳሳይ መልክ የሚታዩ ናቸው፡፡ ስለሆነም ህገ-መንግስቱ እነዚህ ድርጅቶች ከፖለቲካ -ርቲዎች ባልተለየ ሁኔታ ክፍትና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆኑ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ውጭ ሆነው ሲገኙም በፍርድ ቤት ሊጠየቁ የሚችሉ ይሆናሉ፡፡

የሙያና የብዙሃን ማህበራት የአባልነት መስፈርቱን የሚያሟላ ዜጋን በሰፊው ያሰባሰቡ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች መሆናቸው ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታው የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ የሚወስንና በህገ-መንግስቱም የተደነገገ ጉዳይ በመሆኑ መንግስት ይህንኑ መመሪያ በጥብቅ በማስፈፀም ማህበራቱ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል አለበት፡፡ በዚህ መሰረት የሙያና የብዙሃን ማህበራት የህግ እውቅና እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡ ህጋዊ ማህበራት በህገ-መንግስቱና ህገ-መንግስቱን መሰረት በማድረግ በወጡ ድንጋጌዎች መሰረት የአባልነት ምልመላ ስርአታቸውንና የውስጥ አሰራራቸውን የሚገልፅ ይፋ ሰነድ እንዲኖራቸው፣ ሰነዱም ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህንን ሳያረጋግጡ የህግ እውቅና መስጠት ለማህበራቱ መጠናከር የማይበጅ ከመሆኑም ባሻገር ህግን መጣስ ማለትም ይሆናል፡፡ ህጋዊ እውቅና ለመስጠትና በምዝገባ ሂደት ህጉን ለማስከበር

ከሚሰራው ስራ በተጨማሪ ከዚህ ውጭ የሆኑ ማህበራት ሲገኙ በአባላት ጥያቄ፣ ወይም በግለሰቦች ጥያቄ ሊቀርብ ከሚችል ክስ ባሻገር መንግስትም ህጋዊ ማስተካከያ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይገባዋል::

የሙያና የብዙሃን ማህበራት የሚደራጁት የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ነው:: በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ እነዚህ ማህበሮች የሚጠበቅባቸውን ሚና መጫወት የሚችሉትም በርግጥ በፅናት ለአባሎቻቸው መብትና ጥቅም መከበር ሲቆሙ ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንካራ እምነት የሌለውና ለዚሁ አላማ በፅናት የማይቆም ማህበር ተገቢ ሚናውን ሊጫወት አይችልም:: በርግጥ እነዚህ ማህበሮች የአባሎቻቸውን ጥቅምና መብት ማስከበር ያለባቸው በሰላማዊና ህጋዊ መንገድና ህጉ በሚፈቅደው አኳኋን ብቻ መሆን ይኖርበታል:: ከዚያም ባሻገር ማህበራቱ የኛ መብትና ጥቅም ብቻ ይከበር ሌላው ቢፈልግ ገደል ይግባ ሊሉ አይገባም:: ሌላው ገደል ቢገባ እነሱም አብረው ገደል መግባታቸው እንደማይቀርና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ጥቅሞችና መብቶችን በማጣጣምና በማቻቻል መርህ ካልሆነ በስተቀር በሌላ አኳኋን የሚሟላ ጥቅምና መብት ሊኖር እንደማይችል መገንዘብ አለባቸው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበራት ለአባሎቻቸው መብትና ጥቅም በብስለት፣ በፅናትና በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የሚቆሙ ማህበራት እንዲሆኑ ማድረግ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲጫወቱ ለማድረግ ወሳኝነት ያለው ጉዳይ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል::



ከላይ ከተቀመጠው መርህ የሚመነጨው መሰረታዊ የአሰራር ጉዳይ የማህበራቱን ነፃነት የማስጠበቅ ጉዳይ ነው:: ማህበራቱ የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም በማስጠበቅ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን እንዲንቀሳቀሱ ከተፈለገ ነፃነታቸው የተጠበቀና ከውጭ ከሚመጣ ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል:: በዚህ መሰረት ማህበራቱ ከመንግስት ነፃ መሆን አለባቸው:: መንግስት በማህበራቱ የውስጥ ጉዳይ በፍፁም ጣልቃ መግባት የለበትም:: የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት የሆኑ ዜጎች እንደሌላው ዜጋ ሁሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በአባልነት ለመሳተፍና የአባልነት መብትና ግዴታን ለመወጣት ይችላሉ:: ይሁንና ማህበራቱ ከፖለቲካ ድርጅቶችም ነፃነታቸው የተጠበቀ መሆን አለበት:: -ርቲዎች እንዳሻቸው የሚያሾርዋቸው፣ የሚያዝዋቸውና በውስጥ ጉዳያቸው ላይ ጣልቃ የሚገቡባቸው መሆን የለባቸውም:: መንግስት ህግና ስርአት በተከተለ አኳኋን የሙያና የብዙሃን ማህበራትን ነፃነት ለማስጠበቅ መንቀሳቀስ አለበት::

በፈቃደኝነቱ አባል መሆን የሚፈልግንና መስፈርቱን ያሟላ ዜጋ ሁሉ በእኩልነት የሚቀበሉና የሚያስተናግዱ፣ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ያላቸውና ነፃነታቸው የተጠበቀ የብዙሃንና የሙያ ማህበራት የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም ከማስከበር በተጨማሪ ከፍተኛ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ መድረኮችና መሳሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: በዚህ ረገድ ማህበራቱ ሊፈፅሟቸው የሚችሏቸውን ዋና ዋና ስራዎች እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል::

ማህበሮቹ በመሰረታዊ የአገሪቱ አቅጣጫዎች ላይ አንድ የጋራ አመለካከትና እምነት ለመፍጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ ተኪ የሌለው ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ ማህበራቱ ብዙሃኑን በሰፊው ያቀፉ ነፃና ዴሞክራሲያዊ መድረኮች ለመሆን የሚያስችል ባህሪ በሚይዙበት ወቅት አባሎቻቸው መብትና ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ስለሚችሉበት መንገድ ማወያየትና ማከራከር መቻል አለባቸው፡፡ የአባላቱ መብትና ጥቅም አገር በመገንባቱ የትግል ሂደት እንዴት በይበልጥ ሊጠበቅ እንደሚችል ማሰብ፣ መወያየትና አቋም መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚያም ባሻገር የሚወጡት ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች የአባላቱን መብትና ጥቅም በትክክለኛ አኳኋን የሚያስጠብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ማህበራቱና አባሎቻቸው ይህንን ማድረግ የሚችሉት በሚቀርቡት መሰረታዊ አቅጣጫዎች አማራጮች ዙሪያ በቂ ውይይት አካሂደው የተሟላ ግንዛቤ ሲይዙና ትክክለኛ የመሰላቸውን ደግፈው ትክክለኛ ያልመሰላቸውን መቃወም ሲችሉ ነው፡፡

ማህበሮቹ እንደዚህ አይነቱ በሳል ውይይት የሚካሄድባቸው፣ የዴሞክራሲ መድረኮች በሚሆኑበት ወቅት አባሎቹ ተደራጅቶ መብትና ጥቅምን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የማስጠበቅ ልምድ ያገኛሉ፡፡ የተለያዩ አማራጭ ሃሳቦችን ከአባላት መብትና ጥቅም አኳያ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የመተንተን፣ የመረዳት፣ የመደጋገፍና የመቃወም ልምድ ያገኛሉ፡፡ የዴሞክራሲ ባህል በህዝቡ ውስጥ ሰርፆ እንዲገባ ለማድረግ ልዩ ሚና የሚጫወቱ ታላላቅ ትምህርት ቤቶች ይሆናሉ፡፡ የአባላቱን



መብትና ጥቅም በተሻለ አኳኋን ያስጠብቃሉ የሚሏቸውን ጉዳዮች ደግፈው ከዚህ ውጭ ነው የሚሉትን በሚቃወሙበት ወቅት አንድ የጋራ አገራዊ እምነትና አመለካከት ለመፍጠር የሚያስችል ቁልፍ ርምጃ ይወሰዳል፡፡ ማህበራቱ ይጠቅመናል ብለው የሚደግፉት ሃሳብ በሂደት የጋራ አመለካከትና እምነት እርሾ እየሆነ፣ በይበልጥ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ በር ይከፍታል፡፡ የሚቃወሟቸውን ነገሮች ለይተው በመቃወማቸውም ለጋራ አመለካከት መዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የማይስማሙባቸው ነገሮች ተለይተው በመቀመጣቸው በቀጣይ ውይይትና ከልምድ ከሚገኝ ትምህርት በመነሳት በሂደት የጋራ አቋም ለመያዝ፣ የሚያግባቡና ትክክለኛ የሆኑ አማራጮችን ለመሻትና የጋራ እምነቶች እንዲሆኑ ለማድረግ የተመቸ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ከዚያም ባሻገር ልዩነቶችን በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ የመፍታት ልምድ ይዳብራል፡፡

የሙያና የብዙሃን ማህበራት ከላይ የተጠቀሰውን ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚፈለጉት ነገሮች ውሱንና በቀላሉም ሊሟሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ማህበራቱ በርግጥም ብዙሃኑን የሚያሳትፉና ለብዙሃኑ ክፍት የሆኑ ማህበራት መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ከማንኛውም ሰው ተፅእኖ ነፃ የሆኑ፣ ለአባሎቻቸው መብትና ጥቅም የቆሙ፣ በአባሎቻቸው ዴሞክራሲያዊ ውሳኔዎች የሚገዙና የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡ በመጨረሻም የተለያዩ አማራጭ ሃሳቦች ለአባላት እየቀረቡ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የሚፈተሹባቸው መድረኮች መሆን መቻል አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት በመሰረታዊ የአገር

ግንባታ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ የሚያወጣቸው ፅሁፎች በነዚህ መድረኮች እንዲፈተሹና ውይይት እንዲደረግባቸው ማድረግ በጣም ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በዚሁ ሂደት አባላቱ የሚደግፉትንና የሚቃወሙትን መለየት ይችላሉ፡፡ በፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ በሌሎች አካሎች የሚቀርቡ ሌሎች አማራጮች ካሉም በአባላቱ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ውይይት እንዲካሄድባቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ድርጅቶቹ የውይይት መድረኮች ብቻ አይደሉም፣ መሆንም አይገባቸውም፡፡ በሚይዙዋቸው የጋራ አቋሞች ዙሪያ የአባላትን መብትና ጥቅም ለማስከበር ተግባራዊ ርብርብ ማድረግም ይጠበቅባቸዋል፡፡ አባሎቻቸው በጋራና በተናጠል ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ ማነሳሳት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ ይህንን በሚያደርጉበት ወቅት በአንድ በኩል የልማት ትግላችንን ለማሳካት በሚደረገው ትግል ህዝቡ በሰፊውና በቀጥታ እንዲሳተፍ ለማድረግ በመድረክነት ያገለግላሉ፡፡ በሌላ በኩል ይኸው እንቅስቃሴ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን አቅጣጫ የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ ይችላሉ፡፡

መንግስት ድርጅቶቹ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ሃይሎች እንዲሆኑ በሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ድጋፍ መስጠት ይችላል፣ መስጠትም አለበት፡፡ ከሁሉም በፊት መንግስት እቅዶቹን የፖሊሲ አማራጮችን ለማህበራቱ መግለፅና ማስረዳት አለበት፡፡ ማህበራቱንና አባሎቻቸውን የሚነኩ መሰረታዊ ውሳኔዎች በሚወሰኑበትም ወቅት አስቀድሞ ማህበራቱን ማማከር፣



አስተያየታቸውን ማዳመጥና ጠቃሚ ነው ብሎ ያመነበትን መቀበል አለበት፡፡ ይህ በየደረጃው ባሉ የመንግስት አካላት በሰፊው መሰራት ያለበት ስራ ነው፡፡ በዚህ ላይ ተመስርቶ ማህበራቱና አባሎቻቸው ሊሰሯቸው ስለሚችሉ ተጨባጭ ስራዎችና ከመንግስት ስለሚጠበቅ አስተዋፅኦ የጋራ አቋም ለመያዝ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ ስምምነት በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ በጋራና በአጋርነት በቅንጅት የሚፈፀምበት፣ ስምምነት ባልተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ደግሞ ሁለቱም ወገኖች ህጋዊ በሆነ አኳኋን የየራሳቸውን አቅጣጫ ይዘው የሚሄዱበት አሰራር ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ በዚሁ መልኩ በጋራና በቅንጅት የሚሰሩ ስራዎች ላይም የስራ አፈፃፀም ግምገማ በጋራ የሚደረግበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

ይህ ስራ በጣም ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስቸግር ሊመስል ይችላል፡፡ ይሁንና ማህበራቱ የተለያየ ስፋትና ሚና ያላቸው በመሆናቸው ሰፊ የህብረተሰብ ክፍልን ላቀፉ ሰፊ ድርጅቶች ቅድሚያ በመስጠት በቅደም ተከተል መስራት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለማህበራቱ አባላት የሚሰጡ ማብራሪያዎች በአብዛኛው በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች እንዲሆኑ፣ በከፍተኛ የአስተዳደር እርከኖች የሚሰራው ስራ በአብዛኛው ከማህበራቱ መሪዎች ጋር በጉባኤዎችና በመሳሰሉት መድረኮች እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለፅ በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር እርከኖች መካከል ግልፅ የስራ ክፍፍል በማድረግ ችግሩን ማቃለል ይቻላል፡፡ በአንድ የአስተዳደር እርከንም የስራ ክፍፍል በማድረግ እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ

ቤት በስራ መስኩ አግባብነት ካላቸው ማህበራት ጋር እየተገናኘ የሚሰራበት ስርአት ማበጀት ይችላል፡፡ ግልፅ ቅደም ተከተል አውጥቶ፣ ሁሉም የመንግስት አካላት የስራ ክፍፍል በማድረግ በሰፊው እንዲንቀሳቀሱበት ከተደረገ ማህበራቱና መንግስት በብቃት በአጋርነት እንዲሰሩ ማህበራቱ በልማትና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታው ሂደት መጫወት የሚገባቸውን ሚና በተሟላ አኳኋን እንዲጫወቱ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሂደት ከሚገኘው ልምድ በመማርም አሰራሩን በይበልጥ እያሻሻሉ መሄድ ይቻላል፡፡

የሙያና የብዙሃን ማህበራት ከላይ የተዘረዘሩትን ተልእኮዎች በብቃት እንዲፈፅሙ ለማስቻል መንግስት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አኳያ የመጀመሪያውና ዋናው ርምጃ ማህበራቱ ሊጫወቱት ስለሚገባቸው ሚናና አጋርነቱ ተግባራዊ ስለሚሆንበት አሰራር በህዝቡና በመንግስት አካላት ዘንድ የተስተካከለ አመለካከት እንዲኖር የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት የሙያና የብዙሃን ማህበራትን በሰፊው ከማሳተፍ ውጭ የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ተልዕኳቸውን በብቃት መፈፀም እንደማይችሉ ተገንዝበው ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ በሙሉ ልብ እንዲነሳሱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

መንግስት በተጨማሪ የሙያና የብዙሃን ማህበራት የሚጠናከሩበትንና የሚበራከቱበትን ሁኔታ መፍጠርና ይህ የማህበራቱን ነፃነት በማይጋፋ አኳኋን እንዲፈፀም ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ መንግስት ማህበራቱ የሚደራጁበትና ህጋዊ



እውቅና የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡ ህገ-መንግስቱና በህገ-መንግስቱ ላይ ተመስርተው የወጡት ህጎች በሚያዙት መሰረት ማህበራቱ ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ብዙሃኑን የሚያሳትፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ በማህበራቱ ፍላጎትና ጥያቄ በስልጠናና በመሳሰሉት መንገዶች ቴክኒካዊ ድጋፍና እገዛ ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለበት፡፡ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት እነዚህን ማህበራት በአጋርነት አይተው ስለሚያሳትፉበት አሰራር ግልፅ መመሪያዎችን ማዘጋጀት አለበት፡፡

## 6. የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎና ያልተማከለ አስተዳደር፣

በአገር አስተዳደር ስርአት ውስጥ ያልተማከለ አስተዳደር ተግባራዊ የሚደረግባቸው የተለያዩ መልኮች አሉ፡፡ ያልተማከለ አስተዳደር ተፈላጊ የሚሆንባቸው በርካታ ምክንያቶችም አሉ፡፡ በኛ አገር ሁኔታ ያልተማከለ አስተዳደር ተፈላጊ የሚሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡

### 6.1. ያልተማከለ አስተዳደር አስፈላጊነት፣

አገራችን እጅግ በጣም የተለያየ የመልክአ-ምድር አቀማመጥ ያላት አገር ነች፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በየአካባቢው ያለው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ፣ የህዝቡ ባህልና አኗኗር የተለያየ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ልዩነት ባለበት አገር መንግስታዊ አገልግሎት ለህብረተሰቡ በብቃት መስጠት የሚቻለው

ከየአካባቢው ልዩ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ አኳኋን መቅረብ ሲችል ነው። አካባቢዎች ማምጣት የሚችሉትን የላቀ ልማት ማረጋገጥ የሚችሉት ከየአካባቢያቸው ልዩ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የልማት እቅድ ሲወጣና ተግባራዊ ሲሆን ነው። በአጭሩ የእያንዳንዱን አካባቢ ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የመንግስት አገልግሎትና የልማት እንቅስቃሴ መኖሩ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። በሁሉም ደረጃዎች መልካም አስተዳደር እንዲኖር ለማድረግ፣ በየደረጃው ከየአካባቢው ልዩ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ውሳኔ ለመወሰን የሚችል ያልተማከለ አስተዳደር ያስፈልጋል። በተማከለ አኳኋን የየራሳቸው የተለያየ ባህሪ ያላቸውን አካባቢዎች ለማስተዳደር መሞከር ከልማትና የመንግስትን አገልግሎት ከማፋጠን አኳያ በጣም ጎጂ ይሆናል።

አገራችን ሰፊ የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎት በበቂ አኳኋን ያልዳበረባት አገር ነች። ከተወሰኑ ማዕከሎች ለህብረተሰቡ መንግስታዊ አገልግሎት ለመስጠት ቢታሰብ ከአገሪቱ ስፋት አኳያ የሚመች አይሆንም፣ ህዝቡ የሚፈለገውን አገልግሎት በቀላሉና በሚፈለገው ፍጥነት ማግኘት የሚያዳግተው ይሆናል። የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት አለመስፋፋቱ ህብረተሰቡን ከተወሰኑ ማዕከሎች የማገልገሉን አማራጭ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከሞላ ጎደል ዝግ እንዲሆን ያደርገዋል። በመሆኑም ህብረተሰቡ መንግስታዊ አገልግሎቶችን በቀላሉና በቀልጣፋ አኳኋን እንዲያገኝ ለማድረግ ያልተማከለ የአስተዳደር ዘይቤን ተግባራዊ ማድረግ እጅግ ተመራጭ ይሆናል።



ህገ-መንግስታችን ብሄር/ብሄረሰቦች በየአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ያልተማከለ ፌዴራላዊ ስርአት ተቀርፆ ክልሎች ተቋቁመው ህዝቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ሁኔታ ተመቻችቷል። ያልተማከለ አስተዳደር ግን በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሚደረግ የስልጣን ክፍፍል ብቻ የታጠረ አይደለም፣ መሆንም አይገባውም። ያልተማከለ አስተዳደር ከላይ እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የሚከናወን የአስተዳደር ዘይቤ ነው። ብሄር/ብሄረሰቦች በጋራ አንድ ክልል መስርተው በሚተዳደሩበት ሁኔታ የብሄር/ብሄረሰቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እውን ለማድረግም ከክልል በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ያልተማከለ አስተዳደር ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ዴሞክራሲያችን በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ መመስረት እንዳለበት ተደጋግሞ የተገለፀ ጉዳይ ነው። ህዝቡ በተናጠልና፣ በብዙሃንና የሙያ ማህበራት አማካኝነት ከፌዴራል መንግስት ጀምሮ ባሉ የአስተዳደር እርከኖች መሳተፍ ይችላል፣ ይገባዋልም። ይሁንና ህዝቡ በይበልጥ በሰፊውና በቀጥታ ሊሳተፍ የሚችለው በየአቅራቢያው በሚገኙ ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ ነው። ያልተማከለ አስተዳደር ተግባራዊ ሆኖ በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ በቂ የመወሰን ስልጣን ሲኖራቸው የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ የላቀ ደረጃ ላይ ለማድረስ ይቻላል። በአገራችን ያልተማከለ አስተዳደር ተግባራዊ የሚሆንባቸው ከላይ የተጠቀሱት ተመሳሳይ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኛውና ያልተማከለ አስተዳደር

ስርአታችን መለያ ባህሪ የሚሆነው ለህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠሩ አላማ ነው:: ዋነኛ ባህሪውና መለያ አላማው ይህ በመሆኑ ያልተማከለ አስተዳደር ስርአታችን የስራ ክፍፍልን ብቻ ሳይሆን የስልጣን ክፍፍልን መሰረት ያደረገ፣ ስልጣንን በበቂ ደረጃ ለዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በሚሰጥ አኳኋን የሚፈፀም ነው::

ህገ-መንግስታችን ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ በመገንዘብ በአንቀፅ 50 ንኡስ አንቀፅ 4 ላይ እንደሚከተለው ይላል::

“4. ክልሎች፣ በክልልነትና ክልሎች አስፈላጊ ሆነው በሚያገኙዋቸው የአስተዳደር እርከኖች ይዋቀራሉ:: ህዝቡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ ይሳተፍ ዘንድ ለዝቅተኛ እርከኖች በቂ ስልጣን ይሰጣል::”

## 6.2. የዝቅተኛ አስተዳደር እርከኖች ብቃትና የህዝብ ተሳትፎ፣

በአገራችን ሁኔታ ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች የምንላቸው የገጠር ወረዳዎች፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤቶችና በስራቸው የተዋቀሩት የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች ናቸው:: የህዝቡን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚችል፣ በቂ ስልጣን ለዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች የሚሰጥ ያልተማከለ አሰራር ሊኖረን ይገባል ሲባል መሰረቱ ለክልሎች ሰፊ ስልጣን የሚሰጠው ፌዴራላዊ ስርአታችን ቢሆንም፣ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፣ ወረዳዎችን፣ ማዘጋጃ ቤቶችንና ቀበሌዎችን በሚያካትት መልኩ



ሲፈፀም ብቻ ነው:: በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ ያልተማከለ አስተዳደር ስንል በፌዴራል ስርአቱ ማዕቀፍ ውስጥ የዝቅተኛ አስተዳደር ስልጣን አሰራርን ማለታችን ነው::

ለህዝቡ መንግስታዊ አገልግሎት በቀላሉና በቅልጥፍና ለማቅረብ፣ ሁሉም አካባቢዎች ከሁኔታቸው ጋር አብሮ የሚሄድ የልማት እቅድ አዘጋጅተው በመተግበር ማግኘት የሚችሉትን የላቀ ልማት እንዲያገኙ ለማድረግ፣ ህዝቡ ለውሳኔ የሚያስፈልገው መረጃና የሙያተኛ ምክር በብቃት አግኝቶ ትክክለኛ ውሳኔ እንዲወስን፣ ውሳኔው በትክክል ተግባራዊ እንዲሆንለትና በአጠቃላይም ተሳትፎው እውን እንዲሆን ለማድረግ ስልጣን በበቂ መጠን ለዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ከማከፋፈል ጎን ለጎን በነዚህ ደረጃዎች ያሉ የመንግስት አካላት የማስፈፀም አቅምን በከፍተኛ ደረጃ ማጠናከር ያስፈልጋል:: የተስተካከለ አሰራርና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: በቂ ቁጥር ያለው ታታሪና ሙያተኛ የሰው ሃይል እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: ሙያተኞች በዚህ ደረጃ እንዲያገለግሉ ለማበረታታት ሰፊ የማስረዳትና የማሳመን ስራ መስራት አለበት:: የተለያዩ የማትጊያ ስልቶችም እየተቀየሱ ተግባራዊ መሆን አለባቸው::

ዞሮ ዞሮ ስልጣን በውል በተለየ ገንዘብና ንብረት ላይ የማዘዝ ስልጣን ማለት ነው:: ለነዚህ አካባቢዎች በቂ ስልጣን ተሰጥቷል ሊባል የሚችለውም በውል ተለይቶ የተቀመጠ የራሳቸው ገቢ ሲኖራቸውና ይህንኑ ይጠቅማል ላሉት ስራ

የመመደብ ስልጣን ሲኖራቸው ነው። በሌላ አነጋገር ባጀት የማውጣትና የማስፈፀም ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል። በዚህ ደረጃ ያሉ የአስተዳደር እርከኖች ራሳቸው ከአባቢያቸው የሚሰበስቡት ገቢ ሊኖራቸው ይገባል፣ ይህ ብቻ በአሁኑ ሰአት በቂ ስለማይሆን በውል ተለይቶ በተቀመጠ ቀመር መሰረት ከበላይ አካላት የበጀት ድጎማ ሊደረግላቸው ይገባል። ሁለቱን አጣምረው ይጠቅማል ባሉት መንገድ የራሳቸውን በጀት አዘጋጅተው፣ አፅድቀው፣ ተግባራዊ ማድረግ መቻል አለባቸው።

ህዝቡ በነዚህ የአስተዳደር እርከኖች በሰፊው እንዲሳተፍ ለማድረግ በነዚህ ደረጃዎች ያሉ ምክር ቤቶች ለዚሁ የሚያመች አሰራር ሊኖራቸው ይገባል። በዚሁ መሰረት ለምሳሌ በቀበሌ ደረጃ ያሉ ምክር ቤቶች ሰፋ ያለ ቁጥር ያላቸው እንዲሆን ከተደረገ በቀበሌው ኗሪ ከሆነው ህዝብ ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቁጥር የቀበሌ ምክር ቤት አባል ስለሚሆን የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ ከማረጋገጥ አኳያ ልዩ አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል። ከዚሁ በተጨማሪ በነዚህ ደረጃዎች ያሉ ምክር ቤቶች በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን ከመወሰናቸው በፊት ህዝቡን በቀጥታ በየቀበሌውና በየመንደሩም ይሁን በየማህበሩ እየሰበሰቡ ሊያማክሩና ሊያወያዩ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም። ይህ የቀበሌው ወይም የወረዳ አስተዳደሩ ነገሩን ለምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት ለነዋሪው ህዝብ በማቅረብ መልኩም ሊፈፀም ይችላል። የምክር ቤቶቹ አባላት ኑሯቸው ከህዝቡ ጋር በመሆኑ የህዝቡን ችግሮችና ጥያቄዎች እየተከታተሉ በምክር ቤት ሊነሱ የሚችሉትንና የሚገባቸውን እያነሱ መፍትሄ እንዲገኝላቸው ማድረግ ይችላሉ።



በነዚህና በመሳሰሉት መንገዶች በነዚህ ደረጃዎች ላይ ያሉ አስተዳደሮችና ምክር ቤቶች ህዝቡን በቀጥታና በሰፊው ማሳተፍ ይችላሉ፣ ማሳተፍም ይገባቸዋል።

## 6.3. ያልተማከለ አስተዳደርና አገራዊ መመሪያዎች፣

በአገራችን ያልተማከለ አስተዳደር መኖር አለበት፣ በየአካባቢው ያለው አስተዳደር የአካባቢውን ጉዳዮች በራሱ መጨረስ መቻል አለበት ሲባል እያንዳንዱ ወረዳና ቀበሌ ምንም አይነት የበላይ አካል መመሪያ አይኑረው፣ ወይንም ይህንን መመሪያ እየጣሰ እንዳሻው መሆን አለበት ማለት አይደለም። አላማችን አንድ የጋራ ኢኮኖሚና አንድ የጋራ አገር መገንባት ነው። ይህ ህገ-መንግስታዊ ግዴታም ጭምር ነው። ይህንኑ በመፃረር እያንዳንዱ አስተዳደር እንዳሻው በመሆን ሊሰራ አይችልም። ይህ በሚሆንበት ወቅት አንዱ ቀበሌ ወይም ወረዳ የሚሰራው በሌላው ቀበሌ ወይም ወረዳ ከሚሰራው ጋር የሚመጋገብና የሚደጋገፍ መሆኑ ቀርቶ የአስተዳደሮቹ ጥረት እርስ በራሱ የሚጣፋ ሊሆን ይችላል። እንደዚህ አይነቱ አሰራር የህዝቡን መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ፣ የህዝቡን መብትና ጥቅም የሚፃረር ይሆናል። ያልተማከለ አስተዳደር የመፍጠሩ ተግባርም ግቡን ሳይመታ ይቀራል።

በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ የወረዳ፣ ቀበሌ ወዘተ. አስተዳደር የአገሪቱን ህገ-መንግስትና በዚህ ላይ ተመስርተው የሚወጡትን መሰረታዊ አቅጣጫዎች ተከትሎ፣ እነዚህን መሰረት

በማድረግና ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር በማጣጣም የአካባቢውን ጉዳይ የሚመለከቱ ውሳኔዎችን በሚወስንበት ወቅት፣ በአንድ በኩል በየእርከኑ የሚወሰኑት ውሳኔዎች የተለያዩ ቢሆኑም ከአንድ መሰረታዊ መመሪያና አቅጣጫ የሚመነጩ በመሆናቸው እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና የህዝቡን መብትና ጥቅም የሚያረጋግጡ ይሆናሉ፡፡ አንድ የጋራ ኢኮኖሚንና አንድ የጋራ አገርን ለመፍጠር የሚያገለግሉ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ያሉ ሃላፊዎች በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በብቃት የተተነተኑ መመሪያዎች፣ አቅጣጫዎች ስለሚኖራቸው በነዚህ ላይ በመመስረት በሚቀይሷቸው ስራዎች ሁሉ ትክክለኛ መሰረታዊ አቅጣጫ፣ ድጋፍና መነሻ ያላቸው ስለሆነም ደግሞ የአካባቢውን ህዝብ በይበልጥ የሚጠቅሙ ይሆናሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት ያልተማከለ አስተዳደር ተግባራዊ ማድረግ ማለት በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ያሉ ባለስልጣኖች ምንም አይነት የአጠቃላይ መመሪያና አቅጣጫ ገደብ ሳይኖርባቸው እንዳሻቸው ይሆናሉ ማለት አይደለም፡፡ ይህ ያልተማከለ አስተዳደር መሰረታዊ አላማን የሚያናጋ እንጂ ያልተማከለ አስተዳደርን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አይሆንም፡፡ ያልተማከለ አስተዳደር ግቡን ሊመታ የሚችለው አጠቃላይ አገራዊ መመሪያዎችና አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግና እነዚህን በጥብቅ ተግባራዊ በማድረግ ብቻ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት እያንዳንዱ በዝቅተኛ እርከን ላይ



የሚገኘው አስተዳደርም እንደሌላው የመንግስት አካል ሁሉ ህገ-መንግስቱን መነሻ ማድረግና በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በህገ-መንግስቱ መሰረት ፌዴራል መንግስትና የክልል አስተዳደሮች የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ የሚቀይሷቸውን ስትራተጅዎችና ስልቶች፣ የሚያወጧቸውን መርሁ-ግብሮች በሚገባ ማወቅ፣ መረዳትና እነዚህን ከአካባቢው ልዩ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ማድረግ መቻል አለበት፡፡ በዚህ ደረጃ ያሉ የአስተዳደር እርከኖች በፌዴራልና በክልል መንግስታት የሚወጡ የፋይናንስ መመሪያዎችን፣ ህጎችንና ደንቦችን በተሟላ ሁኔታ መተግበርም አለባቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች በዚህ ደረጃ ላይ ባሉ አስተዳደሮች ላይ የተጫኑ ገደቦች ሳይሆኑ አስተዳደሮቹ ስራቸውን በብቃት ለመፈፀም፣ ከአካባቢያቸው ልዩ ሁኔታ ጋር የሚሄዱ ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚረዱዋቸው፣ አቅጣጫ የሚያስይዟቸው ድጋፎች መሆናቸውን ተገንዝበው በጥብቅ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው ይገባል፣ የበላይ አካላት ይህንን የማረጋገጥ መብትና ግዴታም ይኖራቸዋል፡፡

መንግስት ያልተማከለ አስተዳደርን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ለዴሞክራሲ ስርአት ማበብ ያለውን አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባትና ህገ-መንግስቱን መሰረት በማድረግ በአሁኑ ወቅት መርሁን ተግባራዊ ለማድረግ ሰፋ ያለ ስራ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳዎች ህገ-መንግስታዊ እውቅና ያለው ሰፊ ስልጣን እንዲሰጣቸውና በዚሁ መሰረት በብዙ አካባቢዎች ከሚቀጥለው አመት ጀምሮ የራሳቸውን በጀት እያፀደቁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ መብት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ማዘጋጃ

ቤቶችም ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል፣ ጥናቱን የሚያግዙ የተለያዩ ተግባራዊ ሙከራዎችም እየተደረጉ ነው፡፡ ይህንን አሰራር በተሟላ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ርብርብ መደረግ አለበት፣ በመደረግም ላይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የአስተዳደር እርከኖቹ ስራቸውን በአግባቡ ለመፈፀም የሚያስችላቸው ሰፊ የአቅም ግንባታ ስራ መሰራት አለበት፡፡ አደረጃጀትና አሰራራቸው በአገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለውን የአቅም ግንባታ ስራ መሰረት በማድረግ መሻሻል አለበት፡፡ በበቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል መጠናከር አለባቸው፡፡ መነሻ የሚሆን የሰው ሃይል አሰራርና አደረጃጀት ተሟልቶ ስልጣናቸውን ተግባራዊ ማድረግ እንዲጀምሩ በሂደትም የማስፈፀም አቅም ግንባታው ስራ ተጠናክሮ ስራቸውን ከጊዜ ጊዜ እያሻሻሉና ብቃታቸውን እየጨመሩ እንዲሄዱ መደረግ አለበት፡፡

በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ያሉ አስተዳደሮች ስራቸውን በትክክለኛ አኳኋን ለማስፈፀም የሚረዳቸው የተስተካከለ የፋይናንስና አስተዳደር መመሪያ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡ ይህንኑ መመሪያ የሚመለከተው ክፍል በሙሉ በሚገባ እንዲያውቀውና ለተግባራዊነቱም የበላይ አካላት ድጋፍና ቁጥጥር እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በበላይ አካላት የሚወጡ መሰረታዊ ፖሊሲዎችን ስትራተጅዎችን ስልቶችና መርሃ-ግብሮችን በዚህ ደረጃ ያሉ አስተዳዳሪዎች በጥልቀት እንዲያውቋቸው ሊደረግ



ይገባል፡፡ የበላይ አካል በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሃላፊዎች እነዚህን መሰረታዊ መመሪያዎች በሚገባ ጨብጠው ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር አጣጥመው ተግባራዊ ማድረግ ይችሉ ዘንድ የተሟላ ድጋፍ መስጠትና ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግም ይገባቸዋል፡፡

ያልተማከለ አስተዳደር አንድ ዋነኛ አላማ ለህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡ ስለሆነም በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ያሉ አስተዳደሮችና ምክር ቤቶች ከላይ የተጠቀሱትንና የመሳሰሉ ስልቶችን በመጠቀም ህዝቡን በቀጥታና በሰፊው ማሳተፍ መቻል አለባቸው፡፡ የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ዋነኛ መድረኮች እነዚህ መድረኮች መሆናቸውን በመገንዘብና የዴሞክራሲያችን አንድ መለያ ባህሪ በህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ መሆኑን በማስተዋል፣ በነዚህ ደረጃዎች ለሚኖረው የህዝብ ተሳትፎ ልዩ ግምት ሰጥቶ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

# የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና ዴሞክራሲ

## 1. የጋራ አላማዎች፣ የጋራ እሴቶችና የብሄር/ብሄረሰቦች መብት፣

የዴሞክራሲያችን መለያ ባህሪያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ የብሄሮች/ብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ የሚፈቅድ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡ ይህ መብት የህዝቦች ወንድማማችነትና በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አንድነት ለመፍጠር የታቀደ እንደሆነም ተገልጿል፡፡ አንድነቱ ሰፊ ግዛት በመያዝ አስፈላጊነት ላይ የተመሰረተ የተለያዩ ህዝቦች አስተዳደራዊ ትስስር ሳይሆን በጋራ አላማ፣ በጋራ እሴቶች ላይ የተመሰረተ አንድነት መሆን እንዳለበትም ተሰምሮበታል፡፡

የጋራ አላማችን ምን እንደሆነ በህገ-መንግስቱ መግቢያ ላይ በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚያስችለን አንድ የጋራ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ፣ አንድ የጋራ አገር መገንባት አንዱ መሰረታዊ አላማችን ነው፡፡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማታችንን ለማፋጠን፣ ሁላችንም ከዚሁ ተጠቃሚ እንድንሆን ለማድረግ አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብን፣ አንድ የጋራ አገራዊ ኢኮኖሚን መፍጠር ሁለተኛው መሰረታዊ አላማ ነው፡፡ የህዝቦቻችን ጠንካራ



አንድነት ተፈላጊ የሚሆንባቸው ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፡፡

ይሁንና የህዝቦቻችን ጠንካራ አንድነት በጋራ አላማዎቻችንና ለወደፊቱ ተግባራዊ በምናደርጋቸው የጋራ ራዕዮቻችን ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዳልሆነ ህገ-መንግስቱ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ አንድነታችን በጋራ እሴቶቻችን ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበትም ያስቀምጣል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች በታሪክ ሂደት ያፈሯቸው የጋራ እሴቶች የአንድነታችን መሰረቶች ናቸው፡፡ ይሁንና እነዚህ የጋራ እሴቶች በጎ ገፅታ እንዳላቸው ሁሉ በጎ ያልሆነ ገፅታም ስላላቸው ከታሪክ የወረስናቸውን ያልተስተካከሉ የህዝብ ግንኙነቶችን ማስተካከል፣ የህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰንና የእኩልነት መብትን ማረጋገጥ፣ የጋራ እሴቶቻችን የአንድነታችን መሰረት እንዲሆኑ ለማድረግ መሰራት ያለባቸው መሰረታዊ ስራዎች እንደሆኑ ህገ-መንግስቱ ያረጋግጣል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች ህገ-መንግስታችንን በነፃ ፍላጎታቸው ሲያፀድቁ የጋራ አላማዎቹንና ራዕዮቹን ደግፈው በነዚህና በጋራ እሴቶቻችን ላይ የተመሰረተ አንድ ጠንካራ የጋራ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ተስማምተው፣ ይህንን ለማድረግ የህዝቦች እኩልነትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መከበር እንዳለበት አምነው፣ እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸው የቃል-ኪዳናቸው መገለጫ የሆነውን ህገ-መንግስት መቀበላቸውን አረጋግጠዋል፡፡ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ተግባራዊ አፈፃፀም በነዚህ መሰረታዊ አላማዎችና መርሆዎች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

## 2. እኩልነት፣ እኩል ተጠቃሚነትና የብሄር/ብሄረሰቦች መብት፣

ህገ-መንግስታችን የኢትዮጵያ ህዝቦች ብሄር/ብሄረሰቦች እኩልነት ተከብሮ መቀጠል እንዳለበት በግልፅ ያስቀምጣል። የእኩልነት መብት በመሰረቱ የፖለቲካ መብት ነው። አንድ ብሄር/ብሄረሰብ ከሌላው ብሄር/ብሄረሰብ ጋር እኩል የሆነ መብት እንዳለው የሚያመለክት ነው። እኩል ተጠቃሚ የመሆን መብት በፖለቲካዊ እኩልነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከአገሪቱ ልማት እኩል መጠቀምን የሚያመለክት ነው። የህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መረጋገጡ በመፈቃቀድ ላይ ለተመሰረተው ጠንካራ የህዝቦች አንድነት፣ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ የሚፈጥረውን አላማ ለማሳካት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህን በተሟላ ሁኔታ ለማረጋገጥ ትርጉማቸውን በትክክል መረዳት፣ ለተግባራዊነታቸው እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ለይቶ ማወቅና ማስወገድ ያስፈልጋል።

### 2.1. የህዝቦች የእኩልነት መብት፣

በህገ-መንግስታችን የተረጋገጡ የብሄር/ብሄረሰቦች የእኩልነት መብቶች በአንቀፅ 39 በንኡስ አንቀፅ 2ና 3 ላይ የሰፈሩት ናቸው። ንኡስ አንቀፅ 2 ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በቋንቋቸው የመጠቀምና ቋንቋውን የማዳበር፣ ባህላቸውን የመግለፅ፣ የማዳበር፣ የማስፋፋትና ታሪካቸውን የመንከባከብ መብት እንዳላቸው ይገልፃል። ንኡስ አንቀፅ 3 ሁሉም ብሄር/



ብሄረሰቦች ራሳቸውን የማስተዳደር መብት እንዳላቸውና በጋራ ተቋሞች ሚዛናዊ በሆነ አኳኋን በእኩልነት መወከል እንዳለባቸው ያስቀምጣል። እያንዳንዱን ንኡስ አንቀፅ ዘርዝሮና ከህገ-መንግስታዊ መሰረታዊ አላማዎች ጋር አያይዞ ማየትም ያስፈልጋል።

ሁሉም ህዝቦች የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ የራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ አላቸው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ የነዚህ ብሄረሰባዊ እሴቶች ድምርና የጋራ ትስስራቸው ውጤት የሆኑ የጋራ እሴቶች ውጤት ነው። አንድ ህዝብ የሌላው ህዝብ የበላይ ወይም የበታች አይደለም፣ ሁሉም ህዝቦች እኩል ናቸው ከተባለ የህዝቦቹ መለያ የሆኑት ባህሪያትና እሴቶችም እኩል የህግ እውቅናና ጥበቃ ሊኖራቸው ይገባል። በመሆኑም ሁሉም ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀምና ቋንቋቸውን የማዳበር እኩል መብት ይኖራቸዋል። ሁሉም ህዝቦች ባህላቸውን የማስፋፋትና የማዳበር እኩል መብት ይኖራቸዋል። ሁሉም ህዝቦች ታሪካቸውን የመንከባከብና የማወቅ እኩል መብት ይኖራቸዋል።

እነዚህ የእኩልነት መብቶች መከበራቸው አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ የመፈጠሩን አላማ የሚያሳካ እንጂ ከዚሁ ጋር የሚጋጭ አይደለም። ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብት አላቸው ሲባል የሌላን ቋንቋ ማወቅና መማር የለባቸውም ማለት አይደለም። በአለም ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ

እየተጠናከረ በመምጣት ላይ ባለው የኢኮኖሚ ትስስር ምክንያት የአለም ህዝቦች የተለያዩ ቋንቋዎችን ለመማርና ለማወቅ እየተገደዱ ይገኛሉ። ከዚሁ ትስስር በይበልጥ ለመጠቀም እንደ እንግሊዘኛ ያሉ ሰፊ ታዋቂነት ያገኙ ቋንቋዎችን መማር እንዳለባቸው እየተገነዘቡ ማንም ሳያስገድዳቸው በገዛ ፈቃዳቸው እየተማሩ ይገኛሉ። በአለም ደረጃ እንደዚህ አይነቱ ክስተት እየተጠናከረ በመጣበት ሁኔታ በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ህዝቦች በሂደት እርስ በርሳቸው የሚገናኙባቸው የጋራ ቋንቋዎች ወይም ቋንቋ ማዳበራቸው አይቀርም። በተጨባጭም ተጎራባች ህዝቦች በገበያና በተለያዩ ማህበራዊ መድረኮች በሚገናኙበት ወቅት የጋራ ቋንቋ ስለሚያስፈልጋቸው አንዱ የሌላውን ቋንቋ የሚያውቅበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ህገ-መንግስታችን ይህንኑ በመገንዘብ በአንድ በኩል ሁሉም ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብት እንዳላቸው ሲያረጋግጥ በሌላ በኩል ደግሞ አማርኛን እንደአንድ የጋራ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ይቀበለዋል። ህገ-መንግስታችን ይህንን ያደረገው አንድን ቋንቋ የበላይ ሌላውን የበታች ለማድረግ አይደለም። በታሪክ አጋጣሚ አማርኛ ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከሆኑት ዜጎች በተጨማሪ ሌሎች ብዙ ኢትዮጵያውያንም የሚያውቁት ቋንቋ የመሆን ደረጃ ላይ ስለደረሰ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ መሆን እንደሚችል ስለታመነበት ብቻ ነው። ይህንን ውሳኔ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ መንግስታት እንዳደረጉት ሁሉ በኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ላይ የጫነ ሃይል



የለም። ሁሉም የአገራችን ብሄር/ብሄረሰቦች በጋራ መክረው በነፃ ፍላጎታቸው የወሰኑት ውሳኔ ነው።

ውሳኔው በህዝቦች ነፃ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ያለአንዳች ችግርና የህዝቦችን የእኩልነት መብት በማይፃረር መልኩ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል። የአማርኛ ቋንቋ የፌዴራል መግባቢያ ቋንቋ ከመሆን አልፎ እንደደቡብ ህዝቦች ክልል ያሉ በርካታ ብሄር/ብሄረሰቦችን ያቀፉ ክልሎችም የክልል መግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን አድርገውታል። ዜጎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ መብታቸው የተከበረ ቢሆንም አንዳንድ ብሄረሰቦች በነፃ ፍላጎታቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሳይሆን በአማርኛ ለመማር የወሰኑበት ሁኔታም ይታያል።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ዋናው ነገር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሚሆነው የትኛው ቋንቋ ነው የሚለው አይደለም። ይህ የጋራ ቋንቋ በሀይልና በተፅእኖ በህዝቦች ላይ የተጫነ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ነው። ህዝቦች በራሳቸው ነፃ ፍላጎት ሌላ ቋንቋን ለመማርና ለመጠቀም እስከወሰኑ ድረስ መብታቸውን የሚነካ ምንም ነገር የለም። የሌላውን ቋንቋ ሲማሩ በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀም መብታቸው በተከበረበት ሁኔታ እስከሆነ ድረስ የእኩልነት መብትን የሚያስከብር እንጂ የሚፃረር ነገር የለውም። ይልቁንም በቋንቋው የመጠቀም መብቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ የሌላ ቋንቋ መማሩና መጠቀሙ በህዝቦች የጋራ ኑሮ ሂደት ተገቢና የማይቀርም ጉዳይ ነው። ህገ-መንግስታችን ይህንን

የቋንቋዎች መወሳሰብ፣ ማደግና መክሰም ሂደት የሚያቋርጥና የሚገድብ ሳይሆን ይህ ሂደት በአስተዳደራዊ ተፅእኖና አድልዎ ሳይሆን የህዝቦች የእኩልነት መብት በተከበረበት ሁኔታ በኢኮኖሚያዊ ትስስር ሂደት፣ በተፈጥሯዊ የእድገት ሂደት የሚፈፀምበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው።

ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብት ሲረጋገጥላቸው የጋራ መግባቢያ ቋንቋን አስፈላጊነት በመገንዘብ በሙሉ ፈቃደኝነት የመግባቢያ ቋንቋቸውን የሚወስኑበትና የሚያዳብሩበትን ሁኔታ እንደሚፈጥሩ የራሳችን ልምድ በተጨባጭ ያረጋገጠው ነው። ቋንቋዎች ሁሉ በእኩልነት በሚታዩበት ወቅት አንዱ ህዝብ የበላይነት ሌላው ህዝብ የበታችነት ስሜት ሳይሰማው እርስ በርሳቸው ተማምነውና ተከባብረው በጋራ የሚሰሩበትን ቋንቋ ወስነው በጋራ እንደሚኖሩ ከራሳችን ልምድ በላይ ሌላ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም። የቋንቋዎች እኩልነት ብሎም የህዝቦች እኩልነት መከበሩ በመፈቃቀድ ላይ ለተመሰረተ አንድነት መሰረት እንደሚሆን፣ አንድ የጋራ -ለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማችንን እንደሚያሳካ ግልፅ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በቋንቋዎች እኩልነት ላይ የተስተካከለ አመለካከት በማይኖርበት ወቅት ቋንቋ ህዝቦችን የሚለያይ አጥር ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸው መከበር የለበትም የሚሉ ወገኖች፣ የህዝቦች



በቋንቋቸው የመጠቀም መብት ከተረጋገጠ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የማይኖርበት ሁኔታ ይፈጠራልና አንድ የጋራ ቋንቋ በህዝቡ ላይ በሃይል መጫን አለበት የሚሉ ወገኖች ህዝቦችን በቋንቋ አጥር ወደመነጣጠል እንደሚያመሩ ግሃድ ነው። በግድ የራስህን ቋንቋ ትተህ የሌላን ቋንቋ መማር አለብህ የተባለው ህዝብ ይህን ውሳኔ እንደጭቆና ርምጃ መውሰዱ የማይቀር ነው። የጭቆና ርምጃን ከልቡ ደግፎ የሚፈፅም ሰው ስለማይኖር ውሳኔው የተጫነበት ህዝብ በቻለው መንገድ ሁሉ ውሳኔውን ለመናድ፣ የቋንቋ አጥር ለማበጀት መሞከሩ አይቀርም። በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸው መከበር አለበት ሲባል በህዝቦች የማይታለፍ አጥር ለመፍጠር የተደረገ ነገር አድርገው በመረዳት የጋራ መግባቢያ ቋንቋን አስፈላጊነትና እድገት የሚሸረሽሩ፣ በዚሁ መብት ሽፋን ህዝቦችን ለማራራቅ የሚፈልጉ ወገኖች ይኖራሉ። እነዚህም ህዝቦችን የሚነጣጥሉ እንጂ የማንንም ህዝብ መብት የሚያስከብሩ ሊሆኑ አይችሉም። በአንድ በኩል ህዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብት እንዲረጋገጥላቸው፣ በሌላ በኩል በነፃ ፍላጎታቸው የጋራ መግባቢያ ቋንቋቸውን እንዲወስኑና በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር ሂደት የቋንቋዎችን ባህሪያዊ የእድገት ህግጋት ተከትሎ እንዲሄድ የማድረጉ አቅጣጫ የቋንቋዎችን አጥር በዘላቂና አስተማማኝ መንገድ ጥሶ የህዝቦችን ጠንካራ አንድነት ለመገንባት የሚያስችል ይሆናል።

ባለንበት አለም ህዝቦች ባህላቸውን በከፍተኛ ደረጃ

በመዋዋስ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሃይልና በተፅእኖ ሳይሆን በአለም ደረጃ እየተፈጠረ ባለው ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ምክንያት ማንም ሊያቆመው በማይችል አኳኋን የባህል ልውውጥና መዋዋስ ክስተት እየተፈፀመ ነው፡፡ ይህ በአንድ አገር ለምንኖር ህዝቦችም በላቀ ደረጃ የሚሰራ ጉዳይ ነው፡፡ በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስራችን ሂደት ህዝቦቻችን አንዱ የሌላውን ባህል እያወቀ፣ በጎ ገፅታውን እየወረሰና እየተዋሰ መሄዱና የጋራ የባህል እሴቶቻችን እየጎለበቱ መሄዳቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህ በተፋጠነ ገንቢ አኳኋን ሊከናወን የሚችለው የሃይልና የአድልዎ ርምጃ እስካልተጨመረበት ድረስ ነው፡፡ ህዝቦች ባህላቸውን የማዳበርና የማስፋፋት መብታቸው ሲከበር በነፃ ፍላጎታቸው የሌላውን ባህል ማወቃቸውና ከዚሁ ይጠቅማል የሚሉትን መዋሳቸው በፍፁም የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ በተፈጠረበት ሁኔታ ይህ የመዋዋስ ሂደት ይበልጥ እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ እንደሚሄድም በፍፁም አያጠራጥርም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የአንዱ ህዝብ ባህል የበላይ ሌላኛው የበታችና የተናቀ ተደርጎ በሚወሰድበት ወቅት፣ ህዝቦች ባህላቸውን የማዳበርና የማስፋፋት መብት በሚነፈጉበት ጊዜ የማንነታቸው መለያ የሆነን አንድ ነገር በሃይል እየተነጠቁ ናቸውና መቃወማቸው የማይቀር ነው፡፡ በሃይል የተጫነባቸውን ባህል ባገኙት መንገድ ሁሉ መቃወማቸውና ከዚሁ መማር የሚገባቸውንም ነገር ሳይማሩ መቅረታቸው የማያጠራጥር ነው፡፡



ባህላቸውን ከጥቃትና ከውርደት መከላከል ራሳቸውን ከመከላከል፣ ህልውናቸውን ከማረጋገጥ ጋር አያይዘው በማየት የባህላቸውን ጎጂ ገፅታዎች ሳይቀር ወደመጠበቅና መከላከል እንደሚያመሩ ገሀድ ነው፡፡ የባህሎች የእኩልነት መብት በህዝቦች መካከል ጠንካራ የባህል አጥር እንዲገነባና ተጠብቆ እንዳይኖር የሚያደርግ ነው፡፡

ህዝቦች ባህላቸው እንዲከበር፣ የባህል እኩልነት እንዲጠበቅ በሚደረግበት ወቅት የአገራችን ባህል በነዚህ የተለያዩ ባህሎች መጎልበትና ማበብ ላይ የተመሰረተ ሰፊ መሰረት ያለውና የበለፀገ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ አንድ የጋራ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር ሂደት ህዝቦች የባህል መዋዋስና መወራረስ እንዲፈጥሩ፣ የጋራ ባህላዊ እሴቶቻቸውን እያጎለበቱ እንዲመጡ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በነዚህ ምክንያቶች በህዝቦች መካከል የማይታለፍ የባህል አጥር መፈጠሩ ቀርቶ የጠንካራ ህዝባዊ አንድነታቸው መሰረት የሆነ ባህላዊ እሴት ይፈጠራል፡፡ በዚሁ መልኩ ሲታይም ህገ-መንግስታችን በሚደነግገው መልኩ የህዝቦች የባህል እኩልነትና መብት መከበሩ በመፈቃቀድ ላይ ለተመሰረተ ጠንካራ አንድነት መሰረት ነው፡፡

የአገራችን ህዝቦች በተለያየ ደረጃና መልክ ታሪካዊ ትስስር የነበራቸው ህዝቦች በመሆናቸው ይህንኑ ትስስር የሚገልፅ የጋራ ታሪክ አላቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ብሄር/ ብሄረሰብ የየራሱን አመጣጥ የሚገልፅ የራሱ ታሪክ አለው፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ ኢትዮጵያ ባህል ሁሉ የነዚህ ሁለት ገፅታዎች ድምር ውጤት ነው:: የተለያዩ ብሄር/ብሄረሰቦቻች ታሪክ ተደምሮ፣ ከጋራ ትስስር ታሪካቸው ጋር ተጣምሮ ነው የኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ የሚሆነው::

እያንዳንዱ ህዝብ የየራሱን ታሪክ የማወቅና የማክበር መብቱ ሲከበርለት፣ የሁሉም የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ታሪክ በተመሳሳይ መልኩ ሲታወቅና ሲከበር፣ የአንድ ወይም የሌላ ብሄር ጥቅም ብቻ ሳይሆን የመላ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጥቅም ይጠበቃል:: የሁሉም ህዝቦች ታሪክ ሲታወቅና ሲከበር ሁሉም ህዝቦች ታሪካቸው ይታወቃል፣ ይከበራልና:: ይህ በሆነበት ሁኔታ የጋራ ትስስር ታሪካቸውም በትክክል እንዲታወቅና እንዲከበር መሻታቸው በፍፁም የማይቀር ነው:: ይህ የትስስር ታሪክ የእያንዳንዱ ብሄር/ብሄረሰብ የተናጠል ታሪክም አካል ነውና የግሉን ታሪክ ለማወቅና ለማክበር የትስስሩንም ታሪክ ማወቅና ማክበር የግድ ይሆናል:: በሌላ በኩል ደግሞ የህዝቦች የተናጠል ታሪክ በሚታፈንበት፣ በሚጣጣልበት ወቅት ህዝቦች የግልና የጋራ ታሪካቸውን አጣምረው ከማወቅና ከማክበር አቅጣጫ ወጥተው፣ የተጣጣለውን የተናቀውን የግል ታሪካቸውን ለማወቅ በመጣር ላይ እንዲያተኩሩና የጋራ የታሪክ እሴቶቻችን እንዲዳከሙ ምክንያት ይሆናል::

በርግጥ በታሪክ ሂደት በህዝቦቻችን መካከል የበጎ ግንኙነትና ትስስር ገፅታዎች ብቻ ሳይሆኑ የቁርሾና የግጭት



ገፅታዎችም ነበሩ:: በነበረው ኋላ-ቀር ኢኮኖሚና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ምክንያት የመጡ አሉታዊ ገፅታዎችም ነበሩ:: የተናጠልና የጋራ ታሪካችን በትክክል እንዲታወቅ ሲደረግ በጎ ገፅታዎችን ብቻ ማወቅ አለብን ማለት አይደለም:: ይህ የታሪካችንን የተሟላ ስእል ስለማይሰጥ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ አሉታዊ ገፅታዎች እየተጋነኑና እየተውገረገሩ በህዝቡ ውስጥ ውስጡን እንዲሰራጩ በማድረግ የጋራ የታሪክ እሴቶቻችንን ከማዳከም በስተቀር የሚያስገኘው ጠቀሜታ የለም:: በጎና አሉታዊ ገፅታዎችን ሳያጋንኑ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ ታሪክ እንዲታወቅ በማድረግ፣ አሉታዊ ገፅታዎቹ እንዴት እንደተከሰቱ ተንትኖ በማስረዳት፣ በአሁኑ ወቅት እነኚህ አሉታዊ ገፅታዎች እንዳይደገሙ ማድረግ መሰረታዊ የህገ-መንግስታችን አላማ መሆኑን በማስረዳት፣ ትክክለኛውን ታሪክ በማቅረብ ነው ህዝቦች የጋራና የተናጠል ታሪካቸውን አጣምረው በማወቅና በማክበር ለአንድነታችን መሰረት የሚሆን አንድ እሴት እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው:: በዚህ መልክ የህዝቦችን የእኩልነት መብት በህገ-መንግስታችን ላይ በሰፈረው አኳኋን ተግባራዊ ማድረጉ ለጠንካራ ህዝባዊ አንድነት መሰረት ይሆናል::

የህዝቦች የእኩልነት መብት ቋንቋን፣ ባህልንና ታሪክን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ራስን በራስ የማስተዳደርን መብትንም የሚጨምር ነው:: ህዝቦች በየአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት አላቸው:: ህዝቡ በሰፊው ተሳታፊ የሚሆንበት የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባት ከዚህ ውጭ አማራጭ

የለም፡፡ ብሄር/ብሄረሰቦች በየአካባቢያቸው በትክክል ይመሩናል የሚሉዋቸውን ሰዎች በነፃና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን መርጠው መተዳደር መቻል አለባቸው፡፡ በዚሁ ክልል መተዳደሪያ ቋንቋቸውን የመወሰን፣ በቋንቋቸው የመጠቀም መብት ሊረጋገጥላቸው ይገባል፡፡ ህዝቦች የአካባቢያቸውን ጉዳይ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን በራሳቸውና በዴሞክራሲያዊ አግባብ መወሰን ሲችሉ በመካከላቸው አለመግባባት ሊፈጠር የሚችልበት አንድ መሰረታዊ ምንጭ ይደርቃል፣ ለጠንካራ ህዝባዊ አንድነታቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ሁሉም ህዝቦች ያለአንዳች አድልዎ ራሳቸውን ማስተዳደር ችለዋል፣ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ተወግዷልና በዕለት-ተዕለት ስራቸው እንቅፋት ሲያጋጥምም አንዱ ሌላውን የሚያማበት የሚቀየምበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ህዝቦች በህገ-መንግስቱ ላይ የሰፈሩትን መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በሚያደርግ አኳኋን ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ ችግር ቢያጋጥማቸው የዴሞክራሲ መብታቸውን በመጠቀም ያስተካክሉታል፡፡ የማንንም መብት ሳይጋፉ በህገ-መንግስቱ የተደነገጉ ሰብአዊና የዜግነት መብታቸው አክብረው ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ በህዝቦች መካከል መቃቃር የሚፈጠርበት በር ይዘጋል፡፡ በመሆኑም ህዝቦች በየአካባቢያቸው ራሳቸውን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዲያስተዳድሩ፣ በዚህ ረገድ ያላቸው የእኩልነት መብት እንዲከበር ሲደረግ ለጠንካራ ህዝባዊ አንድነት የተመቸ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡



ይሁንና ህዝቦች በግል ከሚመሰርቷቸው አስተዳደሮች በተጨማሪ የጋራ አስተዳደርም ይኖራቸዋል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች የተመሰረቱት አስተዳደሮች በርካታ ብሄር/ብሄረሰቦች በጋራ በመሆን የመሰረቷቸው ናቸው፡፡ ከዚያም ባሻገር ሁሉም የአገራችን ብሄር/ብሄረሰቦች በጋራ የመሰረቱት የፌዴራል መንግስት አለ፡፡ ሁሉም ህዝቦች በነዚህ መድረኮች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መወከል አለባቸው፡፡ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች በሚሆንበት አኳኋን ሳይሆን እኩልነታቸውን በሚያስከብር አኳኋን መወከል ይኖርባቸዋል፡፡ የህዝቦች የሉአላዊነት መገለጫ በሆኑ ምክር ቤቶች በእኩልነት መወከላቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ ደረጃ በእኩልነት በሚወከሉበት ወቅትና የዴሞክራሲ ስርአት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት በምክር ቤቶቹ የሚወሰኑት ውሳኔዎች የህዝቡ ሃቀኛ ተወካዮች በነፃና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወያይተውና ተከራክረው የሚወስኑዋቸው ስለሚሆኑ ህዝቡ አምኖ የሚቀበላቸው ይሆናል፡፡ በአንድ ወይም በሌላ ውሳኔ ላይ የተለየ ሃሳብ ያለውም ቢሆን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን የተወሰነ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ የጋራ መመሪያና ማሰሪያ ይሆናል ብለው ህዝቦች ባፀደቁት ህገ-መንግስት መሰረት የተወሰነ መሆኑን እስካረጋገጡ ድረስ የህዝቦችን እኩልነት የማይነካ እንደሆነ አምነው ይቀበሉታል፡፡

እነዚህ መሰረታዊ የህዝቦች የእኩልነት መብቶች ከተሟላ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ውጭ፣ ህገ-መንግስቱን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ከማድረግ ውጭ ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ

ሊሰመርበት ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ማሰርያና መተዳደሪያ ይሆነናል ብለው በነፃ ፍላጎታቸው ያፀደቁት መመሪያ ህገ-መንግስቱ ነው፡፡ ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ከማድረግ ውጭ የህዝቦችን ፍላጎት፣ የህዝቦችን ሃቀኛ እኩልነት ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፡፡ ከዚህም በላይ እኩልነት ስንል የህዝቦች እኩልነት፣ ህዝቦች ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት በእኩልነት የሚወከሉበት እኩልነት ማለታችን ነው፡፡ የተሟላ ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ በህዝቡ ስም የሚነግድ አስተዳደር እንጂ የህዝቡ የራሱ አስተዳደር ሊኖር አይችልም፡፡ የተሟላ ዴሞክራሲ ተግባራዊ ባልሆነበት ሁኔታ ህዝቡ ይሆኑኛል የሚላቸውን ሃቀኛ ወኪሎቹን ሊመርጥ ስለማይችል በእኩልነት ሊወከል አይችልም፡፡ ስለሆነም የእኩልነት መብት ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው የአስተዳደር እርከን የተሟላ ዴሞክራሲን ተግባራዊ ከማድረግ ውጭ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡

በአገራችን ታሪክ ይህንን ወይም ያኛውን ብሄር/ብሄረሰብ እንወክላለን የሚሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች በፖለቲካ መድረኮች ላይ ሲታዩ ኖረዋል፡፡ አሁንም በፖለቲካ መድረኮች ተዋናይ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ይሁንና ከነዚህ ውስጥ ቀላል ግምት የማይሰጣቸው ወገኖች ራሳቸውን በወኪልነት የሾሙ፣ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን የሚፃረር ተግባርና አሰራር ያላቸው ናቸው፡፡ የግለሰቦቹ ወይም የድርጅቶቹ ፍላጎት ሲሳካና በስልጣን ተካፋይ ሲሆኑ የህዝቦች እኩልነት የተረጋገጠ እንደሆነ አድርገው የሚወስዱ፣ ይህ ሳይሆን ሲቀር እኩልነት እንደተረገጠ አድርገው የሚወስዱ ናቸው፡፡



ከዚያም በላይ እንወክለዋለን የሚሉትን ህዝብ የዴሞክራሲ መብት እየረገጡ ለህዝቡ የእኩልነት መብት ቆመናል የሚሉ ናቸው፡፡ ህዝቡ በየደረጃው የራሱን መሪዎች በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ሲመርጥና ሲሽር፣ ተወካዮቹን ራሱ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ሲመርጥ የእኩልነት መብቱ ይረጋገጣል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ምንም ቢደረግ፣ ሺ ጊዜ ቢለፈፍ፣ ይህንን ወይም ያኛውን ብሄር/ብሄረሰብ እንወክላለን የሚሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሺ ጊዜ ቢቀያየሩ የህዝቡ የራሱ የእኩልነት መብት ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ ለህገ-መንግስቱና ለዴሞክራሲ የተሟላ ተግባራዊነት ያልቆመ ሰው ወይም ድርጅት ለህዝቦች የእኩልነት መብት መከበር ሊቆም አይችልም፡፡ በብሄር/ብሄረሰቡ ስም ለመነገድና ለመጠቀም ካልሆነ በስተቀር በርግጥ ለህዝቦች እኩልነት ሊቆም አይችልም፡፡ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ተግባር ያላቸው ጠባብና ትምክህተኛ ሃይሎች የህዝብን የእኩልነት መብት ሊያረጋግጡ የማይችሉትም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

ህገ-መንግስታችን የህዝቦችን እኩልነት በሚመለከት የሚያስቀምጣቸው ዋነኛ ድንጋጌዎች ከላይ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ የህዝቦችን የፖለቲካ እኩልነት መብት ለማረጋገጥ ወሳኝ የሆኑት ከላይ የተዘረዘሩት በመሆናቸው ህገ-መንግስቱ በነዚህ ላይ ማተኮሩም ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና ህገ-መንግስቱ የመከላከያ መርሆዎችን በሚያስቀምጥበት ወቅት የመከላከያ ሃይላችን የብሄር/ብሄረሰቦችን ሚዛናዊ ተዋፅኦ ማካተት እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በታሪካችን የመከላከያ ሃይል የህዝባችንን መብትና

እኩልነት ለማረጋገጥ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ማገልገሉ ከግምት ውስጥ ሲገባ በህዝብ ምርጫ ከሚቋቋሙት የዴሞክራሲ ተቋሞች ባሻገር የመከላከያ ሃይላችንም ሚዛናዊ ተዋፅኦ እንዲኖር መደረጉ ትክክለኛና ተገቢም ነው። የህዝቦቹ የእኩልነት መብት ዋስትናው ህገ-መንግስቱ በአጠቃላይ ቢሆንም የመከላከያ ሃይሉም ሚዛናዊ ተዋፅኦ እንዲኖር ማድረግ ተጨማሪ ዋስትና ሊሆን ይችላል።

## 2.2. የህዝቦች እኩል ተጠቃሚነት መብት፣

የህዝቦች የፖለቲካ እኩልነት መብት መረጋገጡ የህዝቦችን መብትና ጥቅም ለማረጋገጥ ዋነኛው ርምጃ ቢሆንም አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር የተፈለገው ህዝቦች ከሚገኘው ልማት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግም ጭምር ነው። ህገ-መንግስታችን ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከተሉትን ነገሮች ያስቀምጣል።

በአንቀፅ 43 የልማት መብትን አስመልክቶ ሲደነግግ በንኡስ አንቀፅ አንድ ላይ ‐የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ህዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።፡ ህዝቦች በዚህ ደረጃ እኩል አድል የማግኘት መብት እንዳላቸው በግልፅ ባይቀመጥም መንፈሱ ይኸው ለመሆኑ የሚያጠራጥር ነገር የለውም። ዞሮ ዞሮ የህዝቦቹ የልማት ዕድል እኩልነት በዜጎች የልማት ዕድል እኩልነት መገለፁ ስለማያቋርጥ ህገ-መንግስቱ ይህንን አስመልክቶ ይደነግጋል።



የኢኮኖሚ ነክ አላማዎችን አስመልክቶ ህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 39 ላይ ሲደነግግ በንኡስ አንቀፅ 1 2ና 4 ላይ የሚከተሉትን ያስቀምጣል።

“1. መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የአገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሃብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ሃላፊነት አለበት።

“2. መንግስት የኢትዮጵያዊያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል እድል እንዲኖራቸው የማድረግና ሃብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት።

“4. በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሄሮች ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች መንግስት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል።”

በአገራችን የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ አንዱ ተጠቃሚ ሌላው የበይ ተመልካች የሚሆንበት ከሆነ ሰላምን ማረጋገጥ አይችልም፣ የልማት እንቅስቃሴያችንም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው አይሆንም። የልማት እንቅስቃሴያችን ሁሉም ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት መሆን ይገባዋል። መንግስት የልማት እንቅስቃሴያችን ይህንን ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን እንዲፈፀም የማድረግ ህገ-መንግስታዊ ግዴታ አለበት። ይሁንና ሁሉም ዜጋ በልማቱ ተግባር ላይ እኩል ለመሳተፍ የሚያስችለው እኩል ሃብትና ንብረት፣ እኩል ጉልበትና እውቀት የለውም። ስለሆነም መንግስት የነፃ ገበያን ኢኮኖሚያዊ ስርአት

በመገንባት ሂደት እኩል ሃብትና እውቀት የሌላቸውን ዜጎች ከልማቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊያደርግ አይችልም።

መንግስት ከዚህ አኳያ ሊያደርግ የሚችለው ሁሉም ዜጋ ባለው ገንዘብ፣ ጉልበትና እውቀት ለመጠቀም እኩል መብት እንዲኖረው ማድረግ ነው። ሁሉም ዜጋ ያለውን የልማት አቅም ለመጠቀም የሚችልበት እኩል ዕድል እንዲኖር ማድረግ ነው። የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 89 ንኡስ አንቀፅ 2 የሚለውም ይህንኑ ነው። ድንጋጌው ዜጎች ኑሯቸውን ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲሰጣቸው ማድረግ እንደሚገባ ያሳያል። ስለሆነም መንግስት ህዝቡ ኑሮውን ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲያገኝ፣ ሁሉም ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ እንዲቀየስ ማድረግ ይኖርበታል። ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች ይህንን እኩል ዕድል ሲያገኙና በየደረጃቸው ተጠቃሚ ሲሆኑ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በዚሁ ደረጃ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ እነዚህ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች የብሄር ብሄረሰቦችን እኩል ተጠቃሚነትም የሚመለከቱ ይሆናል።

እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ የመልማት መብት ብቻ ሳይሆን የመልማት እኩል ዕድልና መብትም ሊኖረው ይገባል። የሚቀየሰው የልማት አቅጣጫ ህዝቦቹ ከልማቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚፈጥር መሆን ይኖርበታል። እንደዜጎቹ ሁሉ ብሄር ብሄረሰቦችም እኩል የሰለጠነ የሰው ሃይል፣ እኩል የተመቻቸ የመልክዐ-ምድር አቀማመጥ ወዘተ. ያላቸው



አይደሉም። ስለሆነም በልማቱ መቶ በመቶ እኩል እንዲሆኑ ማድረግ አይቻልም። በተለይም በምንገነባው የኢኮኖሚ ስርአት ቁልፍ የልማት ተዋናይ የሚሆነው የግል ባለሃብት በመሆኑና ባለሃብቱ የተሻለ ትርፍ በሚያስገኝለት አኳኋንና ቦታ የሚሰማራ እንጂ ብሄር/ብሄረሰቦች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚሰማራ ስላልሆነ ሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች ከልማቱ እኩል ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም። ባላቸው አቅምና ሁኔታ ማግኘት የሚችሉትን የላቀ ልማት ለማግኘት እኩል ዕድልና መብት ሊሰጣቸው ግን ይገባል፣ ይችላልም።

የክልሎች እኩል የመልማት ዕድል ተግባራዊ የሚሆነው አንድ አገራዊ ኢኮኖሚ በመፍጠር ሂደትና በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ ነው። የጋራና የተናጠል ጥቅማችን የሚጠበቀው አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ስንፈጥር መሆኑን በመገንዘብ ህገ-መንግስቱ ይህንኑ እንደ አንድ መሰረታዊ አላማው ወስዶታል። ባለንበት አለም ከኢትዮጵያ የላቀ ልማትና የበዛ ህዝብ ያላቸው አገሮች ይህንኑ ተገንዝበው የአገሮችን ድንበር ተሻግረው በተለያዩ አገሮች መካከል አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር በመረባረብ ላይ ናቸው። ከዚህ አኳያ የአውሮ- ማህበረሰብ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። በዚህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ይፈጠራል መባሉ፣ ከዚህ ውጭ የጋራና የተናጠል ጥቅማችንን ማስጠበቅ፣ ልማታችንን ማፋጠን አይቻልም መባሉ በፍፁም አማራጭ የለውም። ይልቁንም ይህ የነገሩ መጨረሻ እንዳልሆነ በሂደት ከኢትዮጵያም ባሻገር በአፍሪካ ደረጃ አንድ የኢኮኖሚ

ማህበረሰብ ለመፍጠር መታገል እንደሚያስፈልግ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የጋራና የተናጠል ጥቅማችን የሚጠበቀውና ልማታችን የሚፋጠነው አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመፍጠር በመሆኑ ክልሎችም እኩል የመልማት ዕድል ሊያገኙ የሚችሉት በዚሁ ማዕቀፍ ነው፡፡ እያንዳንዱ ክልል ራሱን በኬላ አጥሮ፣ የተበጣጠሰ ኢኮኖሚ በሚፈጥርበት ማዕቀፍ ውስጥ የሚረጋገጥ የእኩል ተጠቃሚነት ዕድልና መብት አይኖርም፡፡ በመሆኑም አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን በመፍጠር ሂደት ሁሉም ክልሎች ባላቸው አቅም የላቀ ልማት የሚያገኙበት እኩል ዕድል የሚሰጥ የልማት አቅጣጫ መቀየስ አለበት፡፡ ሁሉም ዜጎች ብሎም ሁሉም ህዝቦች ከልማቱ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበት አቅጣጫ መቀየስ አለበት፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ክልሎች ያላቸውን የልማት አቅም የላቀ ፍጥነትና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን ተጠቅመውበት መገኘት የሚችለው የላቀ ልማት ካልተገኘ በስተቀር፣ ሁሉም ክልሎች ያላቸውን እምቅ የልማት አቅም በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ካላደረጉ የአገሪቱ አጠቃላይ ልማት በሚፈለገውና ሊሆን በሚችለው ደረጃ በፍጥነት ሊያድግ አይችልም፡፡ ስለሆነም አንድ አገር አቀፍ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠሩ አላማና ሁሉም ክልሎች እኩል የልማት ዕድል እንዲያገኙ የማድረጉ አላማ ተደጋግፈውና ተመጋግበው የሚሄዱ



እንጂ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም፡፡

ይህንን እኩል ዕድልና መብት የማረጋገጥ ስራ ለመስራት በመንግስት መከናወን ያለባቸው በርካታ ስራዎች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የአገሪቱ የልማት አቅጣጫ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ የህዝቦች የጋራና የተናጠል ጥቅም የሚጠበቀው እንደዚህ አይነቱ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ሲፈጠር በመሆኑ ይህንኑ በተፋጠነ ሁኔታ ለመገንባት የማያስችል የልማት ስትራቴጅ የህዝቦችን የልማት እኩል መብትና ዕድል ሊያረጋግጥ አይችልም፡፡ የሚቀየሰው የአገራዊ ልማት ስትራቴጅ ሁሉም ዜጎች ብሎም ሁሉም ህዝቦች ያላቸውን የልማት አቅም አሟጠው ሊጠቀሙ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱ የልማት አቅጣጫ ካልተቀየሰ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሳይውሉ የሚቀሩ የልማት አቅሞች ስለሚኖሩ ልማታችን ፈጣን ሊሆን፣ ሁሉም ክልሎች ማረጋገጥ የሚችሉትን የላቀ ልማት ማረጋገጥ የሚቻል አይሆንም፡፡ በአጠቃላይ ሁሉም ክልሎች ማስመዝገብ የሚችሉትን የላቀ ልማት የማስመዝገብ እኩል መብትና ዕድል ለማረጋገጥ፣ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን በአፋጣኝ ለመፍጠርና ሁሉንም የልማት አቅሞች አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል አገራዊ የልማት አቅጣጫ መቀየስ አለበት፡፡ መንግስት ይህንን ለማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ በመቀየሱ ይህ ቅድመ ሁኔታ ተሟልቷል ሊባል ይችላል፡፡

ብሄር/ብሄረሰቦች የልማት እኩል ዕድል እንዲያገኙ አካባቢያቸውን የማስተዳደር እኩል ዕድል ማግኘት አለባቸው:: አንዱ አካባቢውን ለማስተዳደር፣ በዚሁ መብት ተጠቅሞ ያለውን አቅም ሁሉ አረባርቦ ልማት ለማምጣት ዕድል የሚያገኝበት ሌላው ግን አካባቢውን በራሱ የማስተዳደር መብት ተነፍጎ የሚኖርበት ሁኔታ ከተፈጠረ የልማት እኩል ዕድል ሊኖር አይችልም:: ይህም ቅድመ ሁኔታ በህገ-መንግስቱ የተደነገገና ሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች በየአካባቢያቸው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ስለተፈጠረ ተሟልቷል ሊባል ይችላል::

ባለንበት ወቅት ዋናው የልማት ሃይላችን ሰራተኛው ህዝባችን ነው:: እያንዳንዱ አካባቢ ይህን ሃይል የልማት አቅሙን እንዲያጎለብትና አቅሙን አሟጦ እንዲጠቀም ለማድረግ ከቻለ ለማስመዝገብ የሚችለውን የላቀ ልማት ማስመዝገብ እንደሚችል ጥርጥር የለውም:: ከዚያ ቀጥሎ ባለሃብቱ ዋነኛ ተዋናይ በመሆኑ እያንዳንዱ አካባቢ ልማታዊ አስተዋፅኦ ያለውን ባለሀብት በሰፊው ለማሳተፍ የሚያስችል ሁኔታን ከፈጠረ ሊያስመዘግብ የሚችለውን የላቀ ልማት እንደሚያስመዘግብ ምንም ጥርጥር የለውም:: እነዚህን ሁለት ዋነኛ የልማት ሃይሎች በአግባቡ ማንቀሳቀስ ያልቻለ አካባቢ ምንም ነገር ቢደረግ የሚረባ ልማት ሊኖረው አይችልም:: እነዚህን ሁለት የልማት አቅሞች ለማንቀሳቀስ የሚያስችል አገር አቀፍ የልማት አቅጣጫ መነደፉና ሁሉም አካባቢዎች ይህንኑ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ያለው አመራር ማግኘታቸው ወሳኝ ይሆናል:: ይህ



እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስትና የመንግስት በጀትም በልማቱ ላይ ሚና አላቸው::

ዋናው የመንግስት ሚና ዋነኛ የልማት ሃይሎች የሆኑትን ህዝቡንና የግል ባለሀብቶችን ማንቀሳቀስ ሲሆን በነሱ ሊሸፈን ያልተቻለውን ክፍተት የመሸፈን ሚናም ይጫወታል:: ይህንን ለማድረግ ገንዘብ ያስፈልገዋል:: በአገሪቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ በእኩልነት ስራ ላይ መዋሉ እኩል የልማት ዕድልና መብት እንዲኖር ለማድረግ ተፈላጊ ነው:: የፌዴራል መንግስት ለሁሉም ክልሎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የበጀት ድጎማ መስጠቱ ለዚሁ ስራ መሳካት በጣም አስፈላጊ ነው:: የፌዴራል መንግስት የልማት እንቅስቃሴ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን በአፋጣኝ ለመፍጠር የሚያስችል እንዲሆን ማድረጉም ለአላማው መሳካት አስፈላጊ ነው::

ፌዴራል መንግስት ለክልሎች የሚሰጠው ድጎማ የብሄር/ብሄረሰቦች ተወካዮች ባቋቋሙት የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚያወጣው ቀመር ላይ የተመሰረተ እንዲሆንና በግልፅ በሚታወቅ መስፈርት እንዲሆን መደረጉ የልማት እኩል ዕድልን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው:: በርግጥ ቀመሩ በየጊዜው እየተፈተሸ መዳበርና መሻሻል ያለበት ነው:: ይሁንና ዋናው ጉዳይ ቀመሩ በግልፅና ፍትሃዊ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ነው:: ይህ በመሰረቱ በተረጋገጠበት ወቅት ቀመሩን በየጊዜው የመፈተሽና የማስተካከል ጉዳይ እኩል ዕድል የማግኘቱን

መሰረታዊ ጉዳይ የሚነካ አይሆንም፡፡

የፌዴራል መንግስት ለሁሉም ክልሎች እኩል ዕድል ከመስጠት አኳያ ሌላው መሰራት ያለበት ጉዳይ የራሱን የልማት በጀት በተቻለ ፍጥነት በአገራችን አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር አላማ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡ ይህንኑ አላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች የትም ቢሰሩ ተጠቃሚ የሚሆነው ፕሮጀክቶቹ የተሰሩበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱ ህዝብ በአጠቃላይ ነው፡፡ የልማት እኩል ዕድል በአንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ ስለሚረጋገጥ ፌዴራል መንግስት ይህንኑ መርህ በመከተል የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተወካዮች ተወያይተው በሚያፀድቁት በጀት የሚመራ መሆኑ ይህንኑ የእኩልነት ዕድል የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ህገ-መንግስቱ ወደኋላ ለቀሩ ብሄር/ብሄረሰቦች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል ብሎ መደንገጉ ሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች የልማት እኩል ዕድል ይኖራቸዋል ከሚለው ጋር የሚጋጭ ቢመስልም የሚጋጭ አይደለም፡፡ ወደኋላ ለቀሩት ብሄር/ብሄረሰቦች ልዩ ድጋፍ የሚሰጠው እነሱም በሌሎች ጫንቃ ላይ ታዝለው እንዲኖሩ ሳይሆን የልማት አቅማቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ ለማስቻል ነው፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት የነሱ ልማትም ተፈጥሮ የአገሪቱ ልማት በአጠቃላይ ስለሚፋጠን ሁሉም ህዝቦች ተጠቃሚ መሆናቸው በፍፁም የማይቀር ነው፡፡ ወደኋላ የቀሩ ክልሎች ልማታቸውን ለማፋጠን የሚያስችላቸው ዋናው ነገር የአካባቢውን



ህዝብና የግል ባለሃብቶችን በሰፊው ለማንቀሳቀስ የመቻል ጉዳይ ነው፡፡ ብቃት ያለው የመንግስት አስተዳደር የመገንባት፣ ህዝቡን የማስተማር፣ ቀልጣፋ የሆነ የመንግስት አሰራርና አደረጃጀት እንዲኖራቸው የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ የሚሰጣቸው ልዩ ድጋፍ በዋነኛነት በማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራ ላይ ያተኮረ ነው መሆን ያለበት፡፡ በዚህ መስክ ደከም ያለ የማስፈፀም አቅም ላላቸው ብሄር/ብሄረሰቦች የማስፈፀም አቅማቸውን ለማጎልበት ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት ለሁሉም ህዝቦች እኩል ዕድል የመስጠቱን መርህ ተግባራዊ የሚያደርግ እንጂ ይህንኑ የሚፃረር አይደለም፡፡

እነዚህ ብሄር/ብሄረሰቦች ልማታቸውን ለማፋጠን የሚያስፈልጋቸው ሌላው ጉዳይ የመሰረተ-ልማት አገልግሎት ነው፡፡ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ክልሎች እኩል የመሰረተ-ልማት ዝርጋታ የነበራቸው ስላልሆኑ ይህንኑ ለማስተካከል ወደኋላ ለቀሩት ተጨማሪ ድጋፍ መስጠትና ይህንኑ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመፍጠር ማዕቀፍ ውስጥ መፈፀም ለሁሉም ብሄር/ ብሄረሰቦች እኩል ዕድል መስጠት እንጂ ይህንኑ መርህ የሚፃረር አይደለም፡፡ በመሆኑም በፌዴራል መንግስት የሚከናወኑ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታ ስራዎች በዋነኛነት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመፍጠር አላማ ማለትም በኢኮኖሚያዊ አዋጭነት መርህ የሚዘጋጁ እንዲሆኑ፣ ከዚሁ ጋር በማጣጣም የመሰረተ-ልማት አገልግሎቶች በአገሪቱ በአጠቃላይ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲሰራጩ መደረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ፌዴራል መንግስት እነዚህን

መርሆዎች በመከተል መስራቱ ለህዝቦች የልማት እኩል ዕድል ማረጋገጡን የሚያመለክት ነው::

## 2.3. የህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያጋጥሙ ችግሮች፣

የህዝቦች እኩልነት መብት በህገ-መንግስት መረጋገጡ፣ ህዝቦች በልማቱ የመጠቀም እኩል ዕድል የሚያገኙበት መርህ መቀየሱ አንድ ትልቅ ርምጃ ነው:: ይህንኑ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ ቀጥሎ የሚመጣው ቁልፍ ርምጃ ነው:: እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ በሚካሄደው ርብርብ ሁለት መሰረታዊ ችግሮች ያጋጥማሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ የሚታየው የአመለካከት ችግር ሲሆን ቀጥሎ የሚታየው የማስፈፀም አቅም ችግር ነው::

የዴሞክራሲ ስርአትን በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ለማድረግ በመሰረታዊ የስርአቱ አቅጣጫዎች ላይ አንድ የጋራ አገራዊ አመለካከትና እምነት መያዝ እንደሚያስፈልግ በተደጋጋሚ ተገልጿል:: ይህ በብሄር/ብሄረሰብ ጥያቄ ላይም በይበልጥ የሚሰራ ነው:: በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስራዎቻችን ውስጥ ጥልቀት ያለው የጋራ አመለካከት በመፍጠር ረገድ ሰፊ ስራ የሚጠይቀው ይኸው ጉዳይ ነው:: የአመለካከት ችግሩ ራሱ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ በጉዳዩ ላይ ሊኖር የሚገባው ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት በብቃት



ተተንትኖ በሰፊው አለመቅረቡ በነገሩ ላይ የተስተካከለ ግንዛቤ ለመያዝ ችግር መሆኑ ነው:: ከዚያም በተጨማሪ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አመለካከትና ጥቅም ያላቸው ወገኖች፣ ጠባቦችና ትምክህተኞች አበክረው የሚረባረቡበት ጉዳይ መሆኑ ነው::

የእኩልነት መብቶችን በሚመለከት በዋነኛነት የሚታዩት የአመለካከት ችግሮች እነዚህ መብቶች በህዝብ ስም ለሚነግዱ፣ ለመጠቀም ለሚሹ ቡድኖችና ግለሰቦች የተሰጡ ሳይሆኑ ለህዝብ የተሰጡ መብቶች መሆናቸውና ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ጀምሮ የህዝቡን የዴሞክራሲ መብትና ውክልና የማረጋገጥ ጉዳይ መሆኑን በሚገባ አለመገንዘብ ነው:: የእኩልነት መብት ማረጋገጥ፣ የዴሞክራሲ ስርአትና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚከናወን ውክልናን ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተነጣጥለው እንደማይሄዱ፣ ስለዚህም የህዝቡን የዴሞክራሲ መብት የማያከብሩ ሃይሎች በምንም አይነት መንገድ ለህዝቡ የእኩልነት መብት ሊቆሙ እንደማይችሉ በመገንዘብ ላይ ያለ ችግር ነው::

የእኩልነት መብቶችን በተመለከተ ያለው ሌላው ችግር በአንድ በኩል ትምክህተኞች የእኩልነት መብቶችን ተግባራዊ ማድረግ ማለት በህዝቦች መካከል የቋንቋ የባህል፣ የታሪክና የክልላዊ አስተዳደር አጥር በማበጀት የህዝቡን አንድነትና ኢትዮጵያዊ ስሜት ማላሸቅን ያመጣል በማለት የእኩልነት መብቶችን የሚፃረር አመለካከት ሲያራምዱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጠባቦች እነዚህን መብቶች እንደ እኩልነት መብት ሳይሆን

በህዝቦች መካከል የማይዘለል አጥር ለመፍጠር እንደተቀረፁ ነገሮች አድርጎ የመውሰድና በነዚህ ሽፋን የህዝቦችን ወንድማማችነትንና አንድነት የሚሸረሽር አመለካከት ያራምዳሉ፡፡ ሁለቱም አመለካከቶች ዞሮ ዞሮ እኩልነቱን የሚፃረሩ በህዝቦች መካከል በተግባር የቋንቋ፣ የባህል፣ የታሪክና የክልላዊ አስተዳደር አጥር እንዲጠናከር የሚያደርጉ ናቸው፡፡

እኩል የመጠቀም ዕድልን በተመለከተ በአመለካከት ደረጃ ጎልቶ የሚታየው ችግር የነገሩን ምንነት በመገንዘብ ላይ ነው፡፡ እኩል የመጠቀም ዕድል ሁሉም ክልሎች በሁሉም ነገር እኩል እንዲሆኑ የማድረግ ጉዳይ ሳይሆን ሁሉም ክልሎች ያላቸውን አቅም አሟጠው ሊያስመዘግቡ የሚችሉትን የላቀ ልማት የማምጣት እኩል ዕድል እንዲያገኙ የማድረግ ጉዳይ እንደሆነ፣ በዚህም ረገድ ወሳኙ ጉዳይ በፌዴራል ደረጃ ሁሉንም የልማት አቅሞች አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል፣ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት የልማት አቅጣጫ መቀየስና በተቻለ ፍጥነት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር እንደሆነ አለመገንዘብ ነው፡፡ በክልል ደረጃ ዋናው ነገር የተረጋገጠውን የራስን በራስ ማስተዳደር መብት በመጠቀም ዋናዎቹን የልማት ሃይሎች ማለትም ህዝቡንና የግል ባለሀብቶችን በብቃት የማንቀሳቀስ ጉዳይ እንደሆነ አለመገንዘብ ነው፡፡ በፌዴራል ደረጃ የሚሰጠው የበጀት ድጎማ አስፈላጊ ቢሆንም ልማትን ከማፋጠን አንፃር ዋናው ጉዳይ እሱው ሊሆን እንደማይችል አለመገንዘብ ነው፡፡ የፌዴራል መንግስት ድጎማ በግልፅ በተቀመጠ መስፈርት



ላይ ተመስርቶ እስከተሰጠ ድረስ በሂደት የሚሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩትም በመሰረታዊ ይዘቱ ፍትሃዊ እንደሆነ፣ የፌዴራል መንግስት በጀት አንድ የጋራ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመፍጠር ላይ ስለሆነም ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ላይ ባተኮሩ ፕሮጀክቶች ላይ ማተኮር እንዳለበት አለመገንዘብ ነው፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን በጥገኞች፣ በትምክህተኞችና በጠባቦች የሚቀነቀኑ የተሳሳቱ አመለካከቶችም አሉ፡፡ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን በመጠቀም ዋናዎቹን የልማት ሃይሎች ሳያንቀሳቅሱ ይልቁንም እነዚህን የሚያመክን አመለካከትና ተግባር ይዞ ልማትን በድጎማ ለማረጋገጥ አንጋጦ የመጠበቅ አመለካከት ይራመዳል፡፡ ይህ አመለካከት የመንግስትን ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የራስን ኑሮ ለማመቻቸት ከመጠቀም ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ቅስቀሳቸውና ውዥንብራቸው ዋነኛ ማዕከል ይኸው እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ሌላው በነዚህ ወገኖች የሚቀነቀነው የተሳሳተ አመለካከት የክልል ልማት ሲባል ይህን ጉዳይ አንድም አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከመፍጠር መሰረታዊ አላማ ነጥሎ፣ የተበጣጠሱ የክልል ኢኮኖሚዎችን ከመፍጠር ጋር የማያያዝ፣ አለያም አንድ አገራዊ ኢኮኖሚ በመፍጠር መፈክር ሽፋን ሁሉም ክልሎች ማምጣት የሚችሉትን የላቀ ልማት ለማምጣት ከመሞከር ይልቅ የልማት እንቅስቃሴው በውሱን ከተሞችና አካባቢዎች የታጠረ እንዲሆን የመፈለግ አዝማሚያ ነው፡፡

የእኩልነት መብትና ከልማቱ የመጠቀም እኩል ዕድልን ለመተግበር በክልሎችና በየብሄር/ብሄረሰቡ ሰፊና ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያስፈልጋል፡፡ በቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል፣ ጠንካራ አደረጃጀትና አሰራር፣ ብቃት ያለው አመራር በሚኖርበት ወቅት በእኩልነት መብቶች በሰፊው ለመጠቀም፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ተጠቅሞ፣ ዋናዎቹን የልማት ሃይሎች በብቃት አንቀሳቅሶ ልማትን ለማፋጠንና ተጠቃሚ ለመሆን ይቻላል፡፡ ይህ ባልሆነበት አካባቢ በመብቶቹ በተሟላ ለመገልገልና ተጠቃሚ ለመሆን አይቻልም፡፡ ይልቁንም በአመራር ብቃትና በማስፈፀም አቅም ጥንካሬ ላይ ሰፊ ልዩነት የሚታይ በመሆኑ መብቶቹን ተግባራዊ በማድረግ ረገድና ህዝቦች በመብቶቹ የመጠቀም እኩል ዕድል እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ያለው ዋናው ችግር ይህ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህ መሰረታዊ ጉዳይ በቂ ግንዛቤ አግኝቶ ካልተፈታ በስተቀር በህገ-መንግስቱ የተቀመጡ የእኩልነት ድንጋጌዎች በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

ከዚህ በመነሳት መንግስት በየደረጃው ያለውን አመራር ለማጠናከር፣ በየደረጃው ያለውን የማስፈፀም አቅም ለማሻሻል በዚህ ጉዳይ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች ያለውን ሰፊ ልዩነት ለማጥበብ ወደኋላ ለቀሩት ልዩ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በአሁኑ ወቅት መንግስት በዚሁ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመረባረብ ላይ ያለ በመሆኑ ሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች የጉዳዩን ምንነትና ወሳኝነት ተገንዝበው ለስኬታማነቱ አበክረው



እንዲታገሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የዴሞክራሲ ስርአታችን ስር እንዲሰድ ከማድረግ አኳያ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሟላ የጋራ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት እንዲኖር ማድረግ ቁልፍ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በሚነሱት ጥያቄዎች ላይ ሰፊና ቀጣይ ውይይት እንዲካሄድ የተሳሳቱ አመለካከቶች እንዲስተካከሉ ማድረግም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 3. የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ፣

ህገ-መንግስታችን በማያሻማ አኳኋን እንደሚያስቀምጠው የብሄር/ብሄረሰቦችን መብት ማክበር የሚፈለግበት ዋነኛ ምክንያት በህዝቦች እኩልነትና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብን ለመፍጠር ነው፡፡ ይህ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፈጠር እንዳለበት ብቻ ሳይሆን ምን አይነት ይዘት ያለው ማህበረሰብ እንደሚሆንም በህገ-መንግስቱ ተደንግጓል፡፡ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚያስችል ህዝቦች የጋራ መተዳደሪያችንና ማሰሪያ ቃል ኪዳናችን ነው ብለው መክረው በነፃ ፍላጎታቸው ባፀደቁት ህገ-መንግስት መሰረት መፈፀም ያለበት ነው፡፡

### 3.1. አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣

ህገ-መንግስታችን በአንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 19.2 ላይ

የሚከተለውን ይደነግጋል፡፡

1. ህገ-መንግስቱ የአገሪቱ የበላይ ህግ ነው፡፡ ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ-መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2. ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው፣ ህገ-መንግስትን የማስከበርና ለህገ-መንግስቱ ተገዥ የመሆን ሃላፊነት አለባቸው፡፡

የአንድነታችን መሰረታዊ አላማ፣ አንድነታችን የህዝብን ጥቅም በማስጠበቅ ላይ የተመሰረተ የራሱ ይዘትና ባህሪ ያለው እንዲሆን የሚያደርገው አንድ መሰረታዊ ጉዳይ በህገ-መንግስት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱን በአገሪቱ በመላ በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ በማድረግ ነው አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የምንሆነው፡፡ አንድ የጋራ መተዳደሪያ ቃል ኪዳን አንድ የጋራ መመሪያ ሰነድ ከሌለ ወይም በሁሉም የአገሪቱ ጫፎች በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ካልሆነ፣ አስተዳደራዊ ትስስር ሊኖር ይችል ይሆናል፣ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ሊኖር ግን አይችልም፡፡

በየክልሉ በየደረጃው ከአካባቢው ጋር የሚጣጣሙ አደረጃጀቶች አሰራሮች ህጎች ወዘተ. ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የፌዴራል



ስርአት አንድ መሰረታዊ ተፈላጊነትም እንደዚህ አይነት ልዩነቶችን ማስተናገድ ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ የተለያዩ አሰራሮች ህጎች ወዘተ. በአንድ ጠንካራ መሰረት ላይ መመስረት አለባቸው፡፡ በየክልሉና በየደረጃው ያለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ አገሪቱ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ እንድትሆን የሚያደርጋት ነገር መኖር አለበት፡፡ ያ መሰረት ህገ-መንግስቱ ነው፡፡ በየትኛውም የአገሪቱ ጫፍ ያለ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም የመንግስት አካል ህገ-መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡ አግባብ ባለው የመንግስት አካል የሚወጡ ህጎች፣ የሚሰጡ ውሳኔዎች ከህገ-መንግስቱ ጋር የሚጋጩ ከሆኑ በምንም አይነት መንገድ ተፈፃሚነት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ የህዝቦች የጋራ ቃልኪዳን መገለጫ የሆነው ህገ-መንግስት ከቀበሌ እስከ ፌዴራል መንግስት ድረስ በሁሉም ክልሎች በጥብቅ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ ሁሉም ዜጋና አካል ህገ-መንግስቱን በጥንቃቄ ተረድቶ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

ህገ-መንግስቱ የአገራችን ብሄር/ብሄረሰቦች በጋራ መክረው አምነውበት ያፀደቁት በመሆኑ ሁሉም ክልሎች ህገ-መንግስቱን በጥብቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የፌዴራል መንግስትና የክልል መንግስታት ህገ-መንግስቱን የማስከበር መብትና ግዴታ እንዳለባቸው በህገ-መንግስቱ የተደነገገውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ይሁንና በተለያዩ አጋጣሚዎች ህገ-መንግስቱ በተሳሳተ አቅጣጫ እየተተረጎመ ወይም ተግባራዊ እየተደረገ ከሆነ፣ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ

ለመፍጠር መሰረት የሚሆነን መሰረታዊ ነገር እየተናደ ነውና የፌዴራል መንግስት እንደአስፈላጊነቱ ጣልቃ ገብቶ ማስተካከል እንዳለበት ህገ-መንግስቱ ራሱ ይደነግጋል፡፡ ህገ-መንግስቱን ያፀደቁት የተለያዩ ብሄር/ብሄረሰቦች ተወካዮች ህገ-መንግስቱ በሁሉም ክልሎች መረጋገጡ እጅግ ወሳኝ መሆኑን በማመን ፌዴራል መንግስት በክልሎች ላይ ጣልቃ ከሚገባባቸው በጣም ጥቂት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ይኸው እንዲሆን ወስነው በህገ-መንግስቱ በራሱ እንዲደነገግ አድርገዋል፡፡

ህገ-መንግስቱ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ሁለት የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል፡፡ አንደኛው ድንጋጌ ክልሎች ህገ-መንግስቱን ጥሰው ስርአቱን ለአደጋ በሚያጋልጡበት ወቅት የሚወሰድ ርምጃን የሚመለከት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 82 ንኡስ አንቀፅ 9 ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤቱን ስልጣንና ተግባር ሲዘረዝር ማንኛውም ክልል ይህን ህገ-መንግስት በመጣስ ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራል መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፡ ይላል፡፡ የአንድነታችን ማሰሪያ የሆነው ህገ-መንግስት በሆነ ክልል እየተጣሰ ህገ-መንግስታዊ ስርአቱ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ ህገ-መንግስቱ በተጣሰበት ክልል ያለው ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ለአደጋ ይጋለጣሉ፡፡ ይህ በሚሆንበትም ወቅት እጅና እግራቸውን አጣጥፈው ሊቀመጡ አይችሉም፡፡ ጣልቃ ገብተው ህገ-መንግስቱ እንዲከበር ማድረግና አደጋውን ማስወገድ አለባቸው፡፡ ይህ ውሳኔ የሚወሰነው ግን



ብሄር/ብሄረሰቦቹ እንደ ብሄር/ብሄረሰቦች በተወከሉበት ምክር ቤት ማለትም በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ይሆናል፡፡ እነዚህ የብሄር/ብሄረሰቦች ተወካዮች ጉዳዩን መርምርው የጋራ ጥቅማችንን ለአደጋ አጋልጧል ብለው ባመኑበት ወቅት ፌዴራል መንግስቱን በየትኛውም ክልል ጣልቃ እንዲገባ አዘው ያስፈፅማሉ፡፡

ህገ-መንግስቱን በአጠቃላይ በመጣስ ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን ለአደጋ ከሚያጋልጥ ጉዳይ በመለስ በክልሎች ሰብአዊ መብቶች ሲጣሱም የፌዴራል መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ሊታዘዝ ይችላል፡፡ በህገ-መንግስቱ ላይ የተደነገጉት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የህገ-መንግስቱ ቁልፍ አካሎች ናቸው፡፡ የምንገነባው አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ከሚቆምባቸው መሰረታዊ ምሰሶዎች አንዱ የነዚህ መብቶች መከበር ነው፡፡ ሁሉም ክልሎችና የመንግስት አካላት እነዚህን መብቶች ያስከብራሉ፣ መብቶቹ በሚጣሱበት ወቅት አፋጣኝ የማስተካከያ ርምጃ ይወስዳሉ ተብሎም ይጠበቃል፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ምን መደረግ እንዳለበት ህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 55 ንኡስ አንቀፅ 16 ላይ ፦በማንኛውም ክልል ሰብአዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም ሳይችል ሲቀር በራሱ አነሳሽነትና ያለ ክልሉ ፈቃድ ተገቢው ርምጃ እንዲወሰድ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ ያቀርባል፣ በተደረሰበት ውሳኔ መሰረት ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ይሰጣል፡፡፡ ይላል፡፡ ይህ ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡

በአጠቃላይ ህገ-መንግስቱ የአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመፍጠሩ አላማ መሰረትና የአንድነታችን መሰረታዊ ይዘት በመሆኑ፣ ሁሉም የአገራችን ብሄር/ብሄረሰቦች መከረው በነፃ ፍላጎታቸው የደነገጉት በመሆኑ በሁሉም አካባቢዎች በጥብቅ መከበር አለበት፡፡ የህገ-መንግስቱ በጥብቅ መከበር የብሄር/ ብሄረሰቦችን መብትና ጥቅም ለመጠበቅ፣ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብን ለመፍጠር እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ህገ-መንግስቱን ያፀደቁት የአገራችን ብሄር/ብሄረሰቦች እነዚህ ሲጣሱ የፌዴራል መንግስት ጣልቃ የሚገባበትን ድንጋጌዎች እስከማስቀመጥ ድረስ ሄደዋል፡፡

## 3.2. አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና ሲቪል ሰርቪስ፣

በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የፖለቲካ አመራሩ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች በብቃት የሚያስፈፅምና የሙያ ምክር የሚሰጥ በሙያተኞች የተዋቀረ ሲቪል ሰርቪስ መኖሩ ምን ያህል ተፈላጊ እንደሆነ ተደጋግሞ የተገለፀ ጉዳይ ነው፡፡ አገራችን በፌዴራል ስርአት የምትተዳደር እንደመሆንዋ መጠን ራሱን የቻለ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስና ራሳቸውን የቻሉ የክልል ሲቪል ሰርቪሶች መኖራቸውም ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ ሁለት ሲቪል ሰርቪሶች የየራሳቸው ባህሪ ቢኖራቸውም በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የሚኖር ሲቪል ሰርቪስ ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርአትና መልካም



አስተዳደር ሊኖር አይችልም፡፡ ህገ-መንግስቱ የዚህ ጉዳይ በአግባቡ ተግባራዊ መሆን በመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያለውን ትርጉም በመረዳት አስፈላጊውን ድንጋጌ ደንግጓል፡፡

ህገ-መንግስቱ የክልል ስልጣንና ተግባርን በሚደነግግበት አንቀፅ 32 ላይ በንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ላይ ፡የክልሉን መስተዳድር ሰራተኞች አስተዳደርና የስራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል፣ ያስፈፅማል፣ ሆኖም ለአንድ የስራ መደብ የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የስልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ከአጠቃላይ የአገሪቱ መመዘኛዎች ጋር የተቀራረቡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡፡ ይላል፡፡ ህገ-መንግስቱ በዚሁ ድንጋጌ ገደብ ያለው ስልጣን ለክልሎች ይሰጣል፡፡ በአንድ በኩል ክልሎች የየራሳቸውን ሲቪል ሰርቪስ የመፍጠር፣ የማዋቀርና ይህንኑ ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር አጣጥመው የመፈፀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ሲቪል ሰርቪሱ በሙያተኞች የሚዋቀር አካል እንደመሆኑ መጠን የፌዴራልም፣ የክልልም ሲቪል ሰርቪሶች በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚወጣው መመዘኛ ጋር ተቀራራቢ የሆነ መስፈርት ማስቀመጥና መተግበር እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

ህገ-መንግስቱን ያፀደቁት የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ተወካዮች ይህንን ድንጋጌ በሚደነግጉበት ወቅት በበርካታ አካባቢዎች መስፈርቶቹን የሚያሟላ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት

እንደሚኖር ይገነዘቡ ነበር፡፡ ይሁንና በሁሉም አካባቢ አንድም ባይሆን ተቀራራቢ መሆን አለበት ከማለት አልፈው ብቃት ያለው ሙያተኛ የሌለው ሲቪል ሰርቪስ በየትኛውም አካባቢ እንዲደራጅ አልፈቀዱም፡፡ ሲቪል ሰርቪሱ ተቀራራቢ መስፈርት ባላቸው ሙያተኞች መሞላት አለበት ሲሉ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ሰው በአካባቢው ከሌለ ሲቪል ሰርቪሱ ባዶ ይሁን ማለታቸው እንዳልሆነ መገመት በፍፁም አያስቸግርም፡፡ ባዶ በሆነ ሲቪል ሰርቪስ መንግስታዊ አስተዳደር ማከናወን እንደማይቻል ማንም ሊገነዘበው የሚችል ጉዳይ ነውና መስፈርቱን የሚያሟላ የሰው ሃይል በአካባቢው ከሌለ ከሌላ አካባቢ መስፈርቱን የሚያሟላ ሰው መልምሎ ማሟላት እንጂ መስፈርቱን የማያሟላ የአካባቢው ሰው መመደብ እንደማይቻል ማስቀመጣቸው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እንዳላቸውና ይህ መብት በጥብቅ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት የደነገጉ ሰዎች ሲቪል ሰርቪሱ ተቀራራቢ በሆነ መስፈርት የሚመለመል ለሙያተኞች የተዋቀረ አካል መሆን አለበት ብለው መደንገጋቸው፣ በአካባቢው መስፈርቱን የሚያሟላ ሰው ሲጠፋ ከሌላ አካባቢ መመልመል እንዳለበት የሚጠቁም ድንጋጌ ማስቀመጣቸው የህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በአንድ እጅ ሰጥቶ ይህንን መብት በሌላ እጅ መውሰድ አይሆንም ወይ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ አንዳንድ ሙያውና የስራ ታታሪነቱ ሳይኖራቸው የብሄረሰብ ታርጋ ለጥፈው በሲቪል ሰርቪሱ



በመቀጠር ስራውን የግል መጠቀሚያ ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎችም ስራው በነሱ መያዙን የብሄር/ብሄረሰቦች እኩልነትን ከማስከበር አኳያ እንደ ወሳኝ መመዘኛ አድርገው የሚያቀርቡም አሉ፡፡ ከዚያም አልፈው በአንድ ብሄር/ብሄረሰብ ውስጥ የሲቪል ሰርቪሱ የምልመላ መመዘኛ የዞን፣ የወረዳ የቀበሌ እኩልነትን የሚያረጋግጥ እንደሆነ አድርገው እስከማቅረብ የሚሄዱ አሉ፡፡ ይህን አስተሳሰብ የህገ-መንግስቱ አፅዳቂዎች የተጋሩት አልነበረም፡፡ ለምን?

የህገ-መንግስቱ አፅዳቂዎች ከምንም በላይ ትኩረት የሰጡት ለህዝቦች መብትና ጥቅም፣ ለህዝቦች እኩልነት ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ አኳኋን በህዝቡ በራሱ ነፃ ምርጫ ለሚከናወን እኩልነት ነው፡፡ በመሆኑም በምርጫ በሚቋቋሙት ተቋሞች ላይ ተቀራራቢ መስፈርት ማስቀመጥ ምንም አይነት ገደብ አላስቀመጡም፡፡ ህዝቡ የተማረም ይሁን ያልተማረ ሰው ይጠቅመኛል፣ በብቃት ይወክለኛል እስካለ ድረስ መምረጥ ይችላል፡፡ የህገ-መንግስቱ  አርቃቂዎች ከዚህም አልፈው አካባቢውን የሚመለከቱ መሰረታዊ ውሳኔዎች ህዝቡ በመረጣቸው ተወካዮችና በተወካዮች በሚሾሙ የፖለቲካ ሃላፊዎች መወሰን እንዳለባቸው በግልፅ አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች እስከተሟሉ ድረስ የህዝቡ የዴሞክራሲና የእኩልነት መብት በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚረጋገጥ ያውቃሉ፡፡

በዚሁ ክልል የሲቪል ሰርቪሱ ሚና የህዝቡ ተወካዮችና

የፖለቲካ ተሿሚዎች የወሰኑዋቸውን ውሳኔዎችና እቅዶች በብቃት መፈፀም፣ ብቃት ያለው የሙያ ምክር መስጠት እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡ የህዝቡ መብትና ጥቅም በይበልጥ የሚረጋገጠው የሚወስናቸው ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው እቅዶች ተልፈስፍሰው በወረቀት ላይ ሳይቀሩ በብቃት ሲፈፀሙ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ የህዝቡ መብትና ጥቅም የሚረጋገጠው ለፖሊሲና እቅድ ቀረፃ የሚረዳ ብቃት ያለው የምክር አገልግሎት ሲገኝ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ስለሆነም የህዝቡ መብትና ጥቅም የሚጠበቀው የሙያ ብቃትና የስራ ትጋት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሲኖር እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ የሙያ ብቃትና የስራ ትጋት የሌለው ሲቪል ሰርቪስ ሲኖር የህዝቡ ዴሞክራሲያዊ ውሳኔዎችና እቅዶች ከንቱ የወረቀት ነብሮች ሆነው ይቀራሉ፣ በሙያዊ ምክር የተደገፉ ውሳኔዎችም አይሆኑም፡፡ በመሆኑም የህዝቡን መብትና ጥቅም ለማስከበር ሲቪል ሰርቪሱ ከምንም ነገር በላይ የሙያ ብቃትና የስራ ትጋት ባላቸው ሰዎች መዋቀር አለበት፡፡

የሙያ ብቃትና የስራ ትጋት ያለው ሲቪል ሰርቪስን በመፍጠር ክልል የአካባቢውን ህዝብ ባህልና ቋንቋ ለሚያውቁ ሰዎች ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግም ሰፊ የአቅም ግንባታና የስልጠና ስራ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይሁንና ለአካባቢው ሰዎች ቅድሚያ የሚሰጠው ተቀራራቢ የሆነውን የሙያና የስራ ትጋት መስፈርት እስካሟሉ ድረስ ነው፡፡ ይህንን የሚያሟሉ የአካባቢው ሰዎች ከሌሉ የህዝቡን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚቻለው በአንድ በኩል ሙያውና የስራ ትጋቱ



ያላቸው የአካባቢው ሰዎች ለመፍጠር እየተረባረቡ በሌላ በኩል ደግሞ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎች ከሌሎች አካባቢዎች በመመልመል ነው፡፡ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከሌሉ የህዝብ መብትና ጥቅም በይበልጥ የሚረጋገጠው መስፈርቱን የሚያሟሉ የውጭ አገር ዜጎችን በመመልመል ነው፡፡ የሙያ ብቃትና የስራ ትጋት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ሲኖር ብቻ ነውና የህዝቡ መብትና ጥቅም የሚጠበቀው፡፡ ይህን ለማድረግ በቅድሚያ መስፈርቱን ለሚያሟሉ የአካባቢው ሰዎች፣ ቀጥሎ ለሌሎች ኢትዮጵያውያን፣ ቀጥሎ ለውጭ ዜጎች መስጠት እንጂ መስፈርቱን የማያሟላን ማንኛውም ሰው በምንም አይነት ምክንያት በመመልመል አይደለም፡፡ የህገ-መንግስቱ አፅዳቂዎች ይህንኑ በማወቅ ነው በሁሉም አካባቢዎች ተቀራራቢ የሆነ የሲቪል ሰርቪስ መስፈርት መኖር አለበት ብለው የደነገጉት፡፡

ሙያውና የስራ ብቃቱ ሳይኖራቸው በመንግስት ስራ ላይ ተኮፍሰው ራሳቸውን ለመጥቀም የሚሹ ወገኖች «እኛ እያለን የሌላ አካባቢ ሰው እየተቀጠረ ነው፣ የእኩልነት መብታችን እየተጣሰ ነው» ብለው በብሄረሰብ ታርጋ ከዚያም አልፈው በመንደርና በቆዬ ታርጋ ለመነገድ እንደሚሞክሩ የታወቀ ነው፡፡ ይህ ግን በህዝቡ ስም ያለአግባብ ጥቅም የማግኘት ጥገኛ አመለካከት እንጂ የህዝብ መብት፣ ጥቅምና እኩልነትን የማረጋገጥ አላማ ያለው አመለካከት አይደለም፡፡ በብሄረሰቦች መካከል የማይጣሱ የተለያዩ አጥሮችን ማበጀት ከማንም በላይ

የሚጠቅመው በጥገኛ አመለካከትና ጥቅም የታወሩትን እነዚህን ሰዎች በመሆኑ የጠባብነትና የትምክህተኛነት ዋነኛ አራማጆችም በሙያቸውና በስራ ብቃታቸው የሚተማመኑ ሰዎች ሳይሆኑ የመንግስትን ስራ ለግል መጠቀሚያ ለማዋል የሚፈልጉ ሰዎች ሆነው ይገኛሉ::

ይህ ጉዳይ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስም የሚሰራ ነው:: ሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች በምርጫ በሚቋቋሙ የህዝቡ ሉአላዊነትና እኩልነት መገለጫ በሆኑ ምክር ቤቶች ላይ ያለአንዳች ሌላ መስፈረት ህዝቡ በመረጣቸው ሰዎች መሳተፍ ይኖርባቸዋል:: የሁሉንም ህዝቦች መብትና እኩልነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ ሲቪል ሰርቪስ የሚዋቀረው ግን የሙያ ብቃቱና የስራ ታታሪነቱ ባላቸው ሰዎች ነው:: በዚሁ ክልል ፌዴራል ሲቪል ሰርቪሱ የአገሪቱን ህዝብ መምሰሉ፣ የተመጣጠነ ብሄራዊ ተዋፅኦ ያለው መሆኑ ጠቃሚና አስፈላጊም ነው:: በመሆኑም የሚቀመጡትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ በሲቪል ሰርቪሱ በቂ ተሳትፎ ለሌላቸው አካባቢዎችና ያታ ቅድሚያ መስጠት አለበት:: መስፈርቱን የሚያሟሉ በቂ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ካልተገኙ በቂ ተሳትፎ የሌላቸውን በትምህርትና ስልጠና ለማብቃት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መደገፍ ያስፈልጋል:: ከዚህ ውጭ ግን መስፈርቱን የማያሟላ ሰው በሲቪል ሰርቪሱ ማጎር ጥገኝነትን ማስፋፋት እንጂ የህዝቦችን እኩልነት ማረጋገጥ፣ መብትና ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ሊሆን አይችልም::



በዚህ መሰረት በአገራችን አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብን የመፍጠሩ ስራ፣ ተቀራራቢ የሙያና የስራ ትጋት መስፈርት በሚያሟሉ ሰዎች የተዋቀሩ የፌዴራልና የክልል ሲቪል ሰርቪሶችን መፍጠር፣ በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ስርአት ውስጥ ሲቪል ሰርቪሱ ማሟላት የሚገባውን ነገር ሁሉ በመላው አገራችን ተግባራዊ ማድረግን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት:: የክልል መንግስታትና ፌዴራል መንግስት ይህንን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል:: በዚህ ረገድ ባለፉት ጊዜያት ይህ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ በተለያየ መልክ ሲጣስ ወይም በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር የነበረ በመሆኑ በአፋጣኝ ተስተካክሎ ህገ-መንግስቱ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው::

### 3.3. አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና የህግ-አስከባሪ ሃይሎች፣

በአገራችን የህግ የበላይነት የሰፈነበትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን ለማድረግ ለህገ-መንግስቱ ታማኝ የሆኑ፣ ህገ-መንግስቱን የሚያከብሩና የሚያስከብሩ የህግ አስከባሪ ሃይሎች መኖር አለባቸው:: የህግ አስከባሪዎቹ ከሌላው የሲቪል ሰርቪስ አካል ባልተለየ ሁኔታ ስራቸውን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችላቸው ሙያና የስራ ትጋት ሊኖራቸው ይገባል:: እነዚህ ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ የህግ አስከባሪ ሃይሎች የተመጣጠነ ተዋፅኦ ሊኖራቸው ይገባል:: እነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች

የሚታወቁና በተደጋጋሚ የተገለፁ መሆናቸው በዚህ ፅሁፍ ላይ የሚተኮርባቸው አይደሉም። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች መብታቸው ተከብሮ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብን ለመመስረት በወሰኑበት ማዕቀፍ ውስጥ ክልሎችና የፌዴራል መንግስት ህግን በማስከበር ረገድ ያላቸው ሚና ምን እንደሆነ በዝርዝር ማየቱ ግን አስፈላጊ ነው።

ክልሎችም ሆኑ የፌዴራል መንግስቱ ህገ-መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። ህገ-መንግስቱ በህግ የበላይነት መርህ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ክልሎችና የፌዴራል መንግስት ህገ-መንግስቱን በማስከበር ግዴታቸው የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ መብትና ግዴታ አላቸው። በመሆኑም በአገራችን ህግ የማስከበሩ ስራ ለክልሎች ወይም ለፌዴራል መንግስት ብቻ የተሰጠ አይደለም። ሁሉም በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የየራሳቸው ህግን የማስከበር ሃላፊነት አለባቸው። ሁሉም ይህንን ሃላፊነት በቅንጅትና በትብብር መፈፀም ይጠበቅባቸዋል። ህገ-መንግስታችን ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ደንግጓል።

ከላይ እንደተገለፀው ሁሉ በየትኛውም ክልል ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር ሲኖር ፌዴራል መንግስት በፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ውሳኔ ጣልቃ ገብቶ የማስተካከል መብትና ግዴታ አለው። በተመሳሳይ መልክ ሰብአዊ መብቶች በየትኛውም ክልል በሚጣሱበት ወቅትና ክልሉ ይህንኑ ለማስተካከል አቅሙ ወይም ፍላጎቱ ከሌለው በፌዴራል ተወካዮች



ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የጋራ ውሳኔ ፌዴራል መንግስቱ የማስተካከያ ርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ይቻላል። እነዚህ ስራዎች ዞረው ዞረው ህግን የማስከበር ስራዎች መሆናቸው የማይቀር ነው። ስለሆነም በፌዴራል መንግስት ህግን የማስከበር ስልጣን ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ይሁንና ህገ-መንግስቱንና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር ሁሉም የክልል መንግስታት አምነው በቁርጠኝነት ያስፈፅሙታል ተብሎ የሚጠበቅ ስለሆነ ፌዴራል መንግስት በዚሁ ክልል ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ይከሰታል ተብሎ አይጠበቅም። የፌዴራል መንግስት ህግን የማስከበር ዋነኛው ስልጣንም ይህ ነው ተብሎ አይታሰብም።

ህገ-መንግስቱ የፌዴራል መንግስትን ስልጣንና ተግባር በሚዘረዝርበት አንቀፅ 51 ላይ በንኡስ አንቀፅ 6 ፦ የአገርና የህዝብ የመከላከያና የደህንነት እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የፖሊሲ ሃይል ያደራጃል፣ ይመራል፡ ይላል። በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 14 ላይ ደግሞ ፦ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሰረት የአገሪቱን የመከላከያ ሃይል ያሰማራል፡ ይላል። የክልልን ስልጣንና ተግባር የሚደነግገው የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 52 በንኡስ አንቀፅ 2-ሰ ላይ ፦የክልሉን የፖሊስ ሃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ያስጠብቃል፡ ይላል። የእያንዳንዱን ክፍል ስራና ሃላፊነትና በሁለቱም መካከል መኖር የሚገባውን ቅንጅት ከነዚህ መሰረታዊ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች በመነሳት መረዳት ይቻላል።

የአገሪቱን አጠቃላይ ሰላምና ደህንነት የማስከበር ስልጣን የፌዴራል መንግስት ነው። አንድን ክልል ሳይሆን የአገሪቱን አጠቃላይ ሰላምና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን የመከታተል መብት የፌዴራል መንግስት በመሆኑ ስራቸውን በአገሪቱ በመላ የሚያከናውኑ የፌዴራል መንግስት ተቋሞቸ ይኖራሉ። የመከላከያና የደህንነት እንዲሁም የፌዴራል ፖሊስ ተቋም ይህንኑ የአገሪቱን አጠቃላይ ሰላምና ደህንነት የማረጋገጥ ተልእኮ ይዘው ስራቸውን በመላ አገሪቱ የሚያከናውኑ ናቸው። እነዚህ ተቋሞች ይህንን ስራ የሚፈፅሙት መላውን የአገራችን ህዝብ በመወከልና ሰላምና ደህንነትን ለመጠበቅ ስለሆነ ማንኛውም ዜጋ ይሁን በየትኛው ደረጃ ያለ የመንግስት አካል በስራቸው የመተባበር ግዴታ አለበት።

በአንድ ክልል ውስጥ የታጠረ፣ ክልሉን ብቻ የሚመለከት ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ ስራ የተሰጠው ለክልሎች ሲሆን ክልሎች ይህንን ስራ ለመስራት የራሳቸው የፖሊስ ሃይል ያቋቁሟሉ። በመሆኑም በአገራችን አንድ የመከላከያና አንድ የደህንነት ተቋም ብቻ ሲኖር ሁለት የፖሊስ ተቋሞች ማለትም የፌዴራል ፖሊስ ተቋምና የክልል ፖሊስ ተቋም ይኖራሉ። ክልሉ የክልሉን የፖሊስ ሃይል በመጠቀም ሰላምና ደህንነትን የማስጠበቅ ግዴታ ያለበት ቢሆንም ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመው ፌዴራል መንግስት በክልሉ ጥያቄ መሰረት ክልሉን የመርዳት ግዴታም አለበት። የክልሉን ፀጥታ በማስጠበቅ ረገድ በክልል ፖሊስና በፌዴራል ህግ አስከባሪ ሃይሎች መካከል



ቅንጅትና መደጋገፍ መኖር አለበት።

በክልልና በፌዴራል ደረጃ ህግን በማስከበር ስራ ላይ ቅንጅትና መደጋገፍ እንዲኖር በማድረግ ረገድ የስራ ክፍፍላቸውን በትክክል ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ አኳያ ህገ-መንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎቹን አስቀምጧል። የአገሪቱን ፀጥታና ደህንነት በአጠቃላይ የሚነካን ጉዳይ ተከታትሎ የማስወገድ ስራ የፌዴራል መንግስት ተቋሞች ስራ ነው። የክልሉን ፀጥታና ደህንነት ብቻ የሚነካ ጉዳይን ተከታትሎ የማስወገድ ስራ የክልል ፖሊስ ስራ ነው። የስራ ክፍፍሉን በዚሁ መልኩ ለይቶ ማስቀመጡ ተገቢ ቢሆንም በሁለቱ ስራዎች መካከል መወሳሰብ መኖሩ አይቀርም። ይህንኑ በህግ በይበልጥ መዘርዘሩ ተገቢ ቢሆንም መዘርዘሩ ብቻውን ግን በቂ መፍትሄ ሊሆን አይችልም። ሁለቱ የህግ አስከባሪ አካላት በስልጣንና ተግባራቸው ክልል በቅርብ በመቀናጀት መስራት መቻል አለባቸው።

የፌዴራል መንግስት ተቋሞች የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ በሚሰሩት ስራ ክልሎች የመተግበር ግዴታ አለባቸው። አገር ማለት የሁሉም ክልሎች ድምር ውጤት ነውና ይህ ካልሆነ የአገር ፀጥታ ሊጠበቅ አይችልም። በተመሳሳይ መልኩ ክልሎች የክልላቸውን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ከአቅማቸው በላይ የሆነ ችግር ሲገጥማቸው የፌዴራል መንግስት የህግ አስከባሪ ሃይሎች ሊደግፉዋቸው ይገባል። ይህ ካልሆነ አንድ የጋራ ፖለቲካዊ

ማህበረሰብ የመፍጠሩ ተፈላጊነት ራሱ በጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገባ ነው።

ስለሆነም ሁለቱ የህግ አስከባሪ ሃይሎች የየራሳቸው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የየራሳቸውን ስራ ለመስራትም አንዱ የሌላውን ድጋፍ የሚያስፈልገው በመሆኑ፣ የየራሳቸው ስራ ምን እንደሆነ በህግ መዘርዘሩ ተገቢ ቢሆንም በዚህ ብቻ ሙሉ በሙሉ የማይፈታ በመሆኑና የአገር ደህንነትን በአጠቃላይ አገሪቱን የሚነኩ ጉዳዮችና የክልሉን ደህንነት ብቻ የሚነኩ ጉዳዮች የመወሳሰብ ባህሪ ስለሚኖራቸው፣ መወሳሰቡም በቅንጅትና በትብብር ካልሆነ በሌላ አኳኋን ሊፈታ ስለማይችል የቅንጅትና ትብብር ጉዳይ ልዩ ግምት ሊሰጠው ይገባል። የሁለቱን አካላትን የስራ ክፍፍል በዝርዝር በህግ ከመወሰን በተጨማሪ የቅንጅቱና የትብብሩ ስራ በምን መልክ መፈፀም እንዳለበትና በምን ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዳለበት በውል ተለይቶ ሊቀመጥ ይገባል። ይህ በተለይም የፌዴራልና የክልል ፖሊስን በሚመለከት ልዩ ግምት ተሰጥቶት መፈፀም ያለበት ይሆናል።

የክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋመው የፖሊስ ሃይል የሲቪል ሰርቪሱን መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ የሚቋቋም መሆን አለበት። የፖሊስ ስራ የሙያ ስራም ነውና የፖሊስ ሃይል ምልመላና እድገት በሙያ ብቃትና በስራ ትጋት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። የሙያ ብቃቱና የስራ ትጋቱ የሌለው ማንም ሰው በምንም ምክንያት የፖሊስ ሃይሉ አባል



መሆን የለበትም። በሌላ በኩል ደግሞ የፖሊስ ሃይል ቁልፍ የህግ አስከባሪ ሃይል ነውና ለህገ-መንግስቱ ታማኝ የሆነና ህገ-መንግስቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ማንኛውንም ህገ-መንግስቱን የሚጥስና የህግ የበላይነትን የሚፃረር ዜጋ ወይም አካል አድኖና ተከታትሎ ለፍርድ የሚያቀርብ መሆን አለበት። እንደዚህ አይነቱ ጠንካራ እምነት በህገ-መንግስትና በህግ የበላይነት ላይ የሌለው ማንኛውም ሰው በፖሊስ ሃይል መታቀፍ የለበትም።

የሙያ ብቃቱ፣ የስራ ትጋቱና ለህገ-መንግስት ታማኝነቱ የተረጋገጠ ፖሊስ ሲኖር የህዝቦች ሰላምና ደህንነት ይረጋገጣል፣ መብትና ጥቅማቸው ይጠበቃል። ከተጠቀሱት ዋነኛ መስፈርቶች አንዳቸውንም ያጓደለ የፖሊስ ሃይል በሚኖርበት ወቅት የህዝቡ ሰላም ይታወካል፣ የህዝቡ መብትና ጥቅም በአንድ ወይም በሌላ መልክ መረጋገጡ በፍፁም የማይቀር ይሆናል። ስለዚህ መስፈርቶቹን የማሟላት ጉዳይ በምንም ምክንያት ሊታለፍ የሚገባው ጉዳይ አይደለም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የፖሊስ ሃይል በየደረጃው ህዝቡን መምሰል አለበት። ስለሆነም መስፈርቱን ካሟሉት ሰዎች ውስጥ ቅድሚያ በፖሊስ ሃይሉ ውስጥ በቂ ተሳትፎ ለሌላቸው ክፍሎች መሰጠት አለበት። በዚህ ደረጃ መስፈርቱን የሚያሟሉ በቂ ሰዎች ከሌሉ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎች ለማፍራት ለየት ያለ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ይህ መርህ ለፌዴራል የደህንነት ሀይልና ለመከላከያ ሃይልም የሚሰራ ነው።

የዴሞክራሲ ስርአትን በብቃት የሚያገለግል የፖሊስ

ሃይል ወንጀለኞችን አድኖ ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል የሙያ ብቃትና ትጋት ያለው መሆን አለበት፡፡ ስርአቱን በብቃት የሚያገለግል የፖሊስ ሃይል ለህገ-መንግስቱ የማያወላዳ ታማኝነት ያለውና የዜጎች መብትን በጥብቅ የሚያከብር መሆን አለበት፡፡ እንደዚህ አይነቱን የፖሊስ ሃይል ለመፍጠር መስፈርቶቹን ያሚሉ ዜጎች ብቻ ሃይሉን እንዲቀላቀሉ ማድረግ፣ ከዚህ ውጭ የሆነ ማንኛውም ሰው እንዳይመለመል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በግልፅ በተቀመጡ ትክክለኛ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ ምልመላን በማካሄድ ብቻ የሚፈታ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንኑ ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ የሙያ ስልጠና፣ ጠንካራ የህገ-መንግስትና የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ ትምህርትም መሰጠት አለበት፡፡ የፖሊስ ሃይል የዕለት-ተዕለት አሰራርም እነዚህን የሚያጠናክር፣ መስፈርቶቹን በላቀ ደረጃ ያሚሉትን የሚያሳድግ፣ መስፈርቶቹን የማያሚሉትን የሚያገል መሆን አለበት፡፡

ዴሞክራሲያችን በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ መሆን ስላለበት የፖሊስ ስራም የህዝቡን ተሳትፎ በሚያካትትና በሚጋብዝ መልክ መፈፀም ያለበት ነው፡፡ ህዝቡ የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥና ወንጀለኞችን ለፍርድ በማቅረብ ስራ ላይ በፖሊስ ሃይል አስተባባሪነት በሰፊው የሚሳተፍበት ስርአት መዘርጋት አለበት፡፡ ህዝቡ የፖሊስ ሃይሉ ስራውን በትክክል እየፈፀመ መሆኑን የሚከታተልበት፣ ከዚህ ውጭ የሆነ ስራ በሚሰራበት ወቅት የማስተካከያ ርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ



የሚያስችልና ተጠያቂነትን የሚያሰፈን ስርአት መኖር አለበት፡፡

በመላው አገሪቱ የሚገነባው የክልልም ሆነ የፖሊስ ሃይል ከላይ የተጠቀሱትን ባህሪያት የተላበሰ እንዲሆን ለማድረግ ክልሎችና ፌዴራል መንግስት በየፊናቸው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፌዴራል መንግስት የፖሊስ ሙያተኞችን በማሰልጠን የፖሊስ አሰራርና አደረጃጀት ህገ-መንግስቱን ለማስከበር የሚያስችል እንዲሆን ለማድረግ የጥናትና የምክር አገልግሎት ለክልሎች መሰጠት አለበት፡፡ ወጥነት ያለው የህግ ማስከበር ስራ እንዲሰራ ማድረግ የፌዴራል መንግስት ሃላፊነትም ስለሆነ በዚህ ረገድ ጠንካራ እንቅስቃሴ መደረግ አለበት፡፡ ይህ ስራ ዴሞክራሲያችን ስር እንዲሰድ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ጉዳይ ስለሆነ ባለፈው ጊዜ በዚህ ረገድ የነበሩ ጉድለቶችን አስተካክሎ ወደሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ የተቀናጀ ጠንካራ ርብርብ ይደረጋል፡፡ የመከላከያ ሃይሉ ህግ በማስከበር ረገድ ሚና ቢኖረውም በዋናነት የውጭ ጥቃትን በመመከት ላይ ስለሚያተኩር በዚህ ፅሁፍ ላይ በዝርዝር የሚታይ ጉዳይ አይሆንም፡፡

## 4. የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ፣

የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራና የተናጠል ጥቅም የሚረጋገጠው፣ የሁላችንም እድገት የሚፋጠነው በአገራችን አንድ የኢኮኖሚ

ማህበረሰብ ሲፈጠር መሆኑን ህገ-መንግስቱን ያፀደቁት የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች ተወካዮች በጥብቅ ያመኑበት ጉዳይ ነው። በመሆኑም የህዝቦችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠርን አላማ የህገ-መንግስቱ አንድ መሰረታዊ አላማ እንዲሆን አድርገውታል። ህገ-መንግስቱ የህዝቦች የጋራ ቃልኪዳን መገለጫ ነውና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማም የመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች አላማ፣ የቃል ኪዳናቸው መገለጫ ነው። ህገ-መንግስቱ የዚሁ አላማ ማስፈፀሚያ መሳሪያ ነው።

## 4.1. አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማና መሰረታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣

አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያ ማህበረሰብ በመሰረተ-ልማት አውታሮች በጥብቅ የተሳሰረና የተቆራኘ መሆን አለበት። አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያ ኢኮኖሚ አንድ ገንዘብና የገንዘብ ፖሊሲ፣ አንድ አይነት መሰረታዊ የኢኮኖሚ ህጎችና አንድ አይነት መሰረታዊ የልማት ሰትራተጅዎች ያለው መሆን አለበት። አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እንዲኖር ያ ማህበረሰብ ከሌሎች የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች ጋር እንደ አንድ አካል ሆኖ መገናኘት አለበት። አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እንዲኖር የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄሰቦች እነዚህን ስራዎች በተናጠል ሳይሆን የጋራቸው በሆነው የፌዴራል መንግስት በጋራ አማካኝነት መፈፀም መቻል አለባቸው።



ህገ-መንግስቱ ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ በሚገባ በመገንዘብ አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለመፈጠር መሰረታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ህጎች ያላቸውን ፋይዳ በመረዳት እነዚህን የመቀየስና የማስፈፀም ስልጣን በፌዴራል መንግስት ነው የሚሰጠው። በመሆኑም የፌዴራል መንግስት ስልጣንና ተግባርን በሚደነግገው አንቀፅ 51 ውስጥ ካሉት 21 ንኡስ አንቀፆች ውስጥ ከ12 የማያንሱት ማለትም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ንኡስ አንቀፆች የሚደነግጉት ፌዴራል መንግስት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስፈልጉትን ስልጣኖች ዘርዝረው የሚሰጥ ድንጋጌዎችን ነው።

ይህ መሆኑ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ያላቸውን መብት የሚፃረር አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ የክልሎች ልማት የሚረጋገጠው አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በሚፈጠርበት ማዕቀፍ ውስጥ ስለሆነ ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎች ሁሉ የክልሎችን ጥቅም የሚያስጠብቁ እንጅ የሚፃረሩ አይደሉም። ከዚሁ በተጨማሪ ሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች በፌዴራል መንግስት የፖለቲካ ስልጣን በእኩልነት ስለሚወከሉና በጋራም ስለሚወስኑ የብሄር/ብሄረሰቦች መብትና ጥቅምን የሚያስጠብቅ እንጂ የሚፃረር አይደለም። ክልሎች በነዚህ አጠቃላይ የፖሊሲ ማዕቀፎች ውስጥ ሆነው የየራሳቸውን የልማት እቅድ እያወጡ ስለሚያስፈፅሙ፣ በነዚህ አጠቃላይ የፖሊሲ ማዕቀፎች ውስጥ ሆነው ከየአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ ዝርዝር ፖሊሲዎችን ስለሚያወጡ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደሩ

መብት በዚህም ረገድ የተረጋገጠ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የብሄር-ብሄረሰቦችን መብት የማስከበሩና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠሩ አላማ ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ተደጋጋፊ አላማዎች እንጂ የሚጋጩ አላማዎች አይደሉም፡፡

አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚያስፈልጉ ስልጣኖች የብሄር/ብሄረሰቦች የጋራ ስልጣን ማለትም የፌዴራል መንግስት ስልጣን እንዲሆኑ መደረጉ ልማታችንን ለማፋጠን የሚያስችል የፖለቲካ ማዕቀፍን ይፈጥራል፡፡ ይህ ብቻውን ግን ልማትን ሊያመጣ፣ ልማትን የተፋጠነ እንዲሆን ለማድረግ አይችልም፡፡ ይህንኑ ስልጣን ተጠቅሞ ልማትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ ትክክለኛ የልማት አቅጣጫዎችን መቀየስና መተግበርም ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ ቁልፍ ሚና የሚኖራቸው የሁሉም የአገራችን አካባቢዎች የልማት አቅምን አሟጦ የሚጠቀም የልማት ስትራተጅ ቀይሶ ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይም በአገሪቱ ውስጥ ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር የመፍጠሩን ስራ የሚያቀላጥፍ ነው፡፡

በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ የአገሪቱን አጠቃላይ ልማት ከማፋጠን አኳያ ሁለት መሰረታዊ አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አንደኛው አማራጭ የልማት ርብርቡ ለልማት የተመቻ ሁኔታ ባላቸው አካባቢዎች ላይ እንዲያተኩር በማድረግ በሌሎቹ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች በሂደት ወደነዚህ አካባቢዎች እየተሰባሰቡና ካሉበትም ሆነው ከዚሁ ልማት በመጠቀም አገሪቱ



እንድትለማ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው አማራጭ ሁሉም አካባቢዎች ማምጣት የሚችሉትን የላቀ ልማት እንዲያመጡ በማድረግ የአገሪቱ አጠቃላይ ልማት እንዲቀላጠፍ ሁሉም ከጋራና ከተናጠል ልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ዋናው የልማት ሃይል የህዝቡ ጉልበት በሆነባት አገራችን ያለንን የልማት አቅም አሟጠን በመጠቀም ልማታችንን ለማፋጠን የሚያስችለን ብቸኛው አማራጭ ሁለተኛው አማራጭ ነው፡፡ ህዝቦች ከጋራና ከተናጠል ልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችለን አማራጭ ሁለተኛው አማራጭ ነው፡፡ የህገ-መንግስቱን አንድ መሰረታዊ አላማ ለማሳካት የሚያስችለውም አማራጭ ይኸው ነው፡፡ በመሆኑም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ የልማት ስትራተጅዎችንና ስልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር በአንድ ሳምባ የሚተነፍስ አንድ ኢኮኖሚ በአገራችን እንዲኖር ለማድረግ አገሪቱን በሞላ በመሰረተ-ልማት ማስተሳሰር፣ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ሰፊ የሸቀጥና የአገልግሎት ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የመሰረተ-ልማት አውታሮች የመዘርጋት ስራ የተቀላጠፈ እንዲሆን ለማድረግ በዋነኛነት በኢኮኖሚያዊ አዋጭነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሰረተ-ልማት የመዘርጋት ስራ መሰራት አለበት፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የመሰረተ-ልማቱ አለመኖር ልማቱን ሊዘጋ በሚችልባቸው ሁኔታዎች አገሪቱን በመሰረተ-ልማት ለማስተሳሰሩ አላማ ቅድሚያ ሰጥቶ

በኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ቅድሚያ የማይሰጣቸው የመሰረተ-ልማት ስራዎችም መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ዞሮ ዞሮ በተቻለ ፍጥነት አገሪቱን በመሰረተ-ልማት አውታሮች የማቆራኘት አላማን ለመተግበር የሚያገለግሉና ተጣጥመው ሊፈፀሙ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች መካከል ሰፊ የስራ ክፍፍል እንዲኖር የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ነፃ ዝውውር የሚያደናቅፉ ነገሮች ሁሉ እንዲወገዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአገራችንን ልማት የሚያፋጥንና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን የሚፈጥር አቅጣጫ የመቀየስ ስራ የፌዴራል መንግስት ቢሆንም በፌደራል መንግስት ብቻ ተግባራዊ የሚሆን አይደለም፡፡ ክልሎችና በአጠቃላይም መላው ህዝብ አቅጣጫውን ተግባራዊ የማድረግ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም የሚቀየሰው አቅጣጫ መላው ህዝብ እንዲያውቀው በጥልቀት እንዲገነዘበውና እንዲያምንበት መደረግ አለበት፡፡ በዚህ ላይ ተመስርተው ክልሎችና ፌዴራል መንግስት የየበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡና ይህንኑ በቅርብ በመተጋገዝና በመቀናጀት እንዲፈፅሙት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አቅጣጫው በፌዴራል መንግስት አማካኝነት የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረሰቦች በጋራ የሚቀይሱት ሲሆን አፈፃፀሙም በፌዴራል መንግስት በጋራና በክልሎች በተናጠል በትብብርና በቅንጅት የሚፈፀም መሆን ይኖርበታል፡፡



## 4.2. የካፒታል ነፃ ዝውውርና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ፣

በአገራችን ፈጣን እድገት ለማምጣትና ህዝቡም ከልማቱ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የልማት ሃይሎችን በሰፊው ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ አንዱ ዋነኛ የልማት ሃይል ካፒታል ሲሆን ሌላው የህዝቡ ጉልበት ነው፡፡ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን እያመረቱ ትርፍ በማግኘት ራሳቸውን ጠቅመው ህዝቡንና አገሪቱን የሚጠቅሙ ልማታዊ ባለሃብቶችን በሰፊው ማንቀሳቀስ መቻል አለብን፡፡ የግል ባለሃብቶችን በአገሪቱ በሞላ በሰፊው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ሊያስመዘግቡ የሚችሉትን የላቀ ልማት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አይቻልም፡፡ ሁሉም የአገራችን አካባቢዎች የግል ባለሃብቱን በብቃት ለማስተናገድ፣ ለመደገፍና በሰፊው በስራ ላይ ለማሰማራት የሚያስችላቸው ሁኔታን መፍጠር አለብን፡፡

በልማት ስራ ላይ የሚሰማራውን የግል ባለሀብት በሰፊው ከማንቀሳቀስ ውጭ ፈጣን ልማት ማረጋገጥና ሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ከልማቱ የመጠቀም እኩል እድል እንዲኖራቸው ማድረግ በፍፁም የማይታሰብ የመሆኑን ያህል በጥገኝነት የተሰማሩትን መቆጣጠርም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት ሲያቀርቡ በመንግስትና ህዝብ ጫንቃ ላይ በመታዘል፣ በማጭበርበርና

በመሳሰሉት ህገ-ወጥ መንገዶች ለመክበር የሚሹ ወገኖች ከልማት ይልቅ ድህነትና ጥፋትን የሚያስፋፉ በመሆናቸው መገታት ይኖርባቸዋል፡፡ የግል ባለሃብቶች በሰፊው እንዲሰማሩ ማትጋት፣ መደገፍና ማስተናገድ ያስፈልጋል ሲባል ልማታዊ ባለሃብቱን እንጂ ጥገኛውን አይደለም፡፡

ልማታዊ ባለሃብቱ በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች በሰፊው ሊሰማራ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ጋር ተያይዞ የሚታየው በነፃ ለመዘዋወር የመቻሉ ጉዳይ ነው፡፡ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ያለምንም ውጣ ውረድና አድልዎ ካፒታሉን አሰማርቶ መስራት መቻል አለበት፡፡ ካፒታል ከአንዱ አካባቢ ወደሌላው አካባቢ እንደልብ መንቀሳቀስ ካልቻለ፣ ሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ማምጣት የሚችሉትን የላቀ ልማት ማምጣት የሚቻላቸው አይሆንም፡፡ ካፒታል እንደልብ መንቀሳቀስና መዘዋወር ካልቻለ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መኖር አይችልም፡፡ ፈጣን ልማትን ለማረጋገጥና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ካፒታል በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ያለአድልዎና ውጣ ውረድ፣ በነፃ እንደልብ የመዘዋወርና የመስራት መብት ሊረጋገጥለት ይገባል፡፡ ይህ ካፒታልን ብቻ ሳይሆን የሰራተኛ ጉልበትንም የሚመለከት መሆን ይኖርበታል፡፡

ህገ-መንግስታችን ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በተለያዩ አንቀፆች ትክክለኛ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ በአንቀፅ 41 ንኡስ አንቀፅ 1 ላይ “ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሪቱ ውስጥ



በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያ የመረጠውን ስራ የመስራት መብት አለው፡፡” ይላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአንቀፅ 32 ንኡስ አንቀፅ 1 ላይ “ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በህጋዊ መንገድ አገሪቱ ውስጥ የሚገኝ ያለው ዜጋ በመረጠው የአገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከአገር የመውጣት ነፃነት አለው፡፡” ይላል፡፡ ይህንኑ መርህ የሚያብራሩ ሌሎች በርካታ ድንጋጌዎችም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከተያዘው ርዕስ አኳያ ዋናው ጉዳይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ፣ በየትኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት መብት ያለው መሆኑ ነው፡፡

ካፒታል በአገሪቱ ውስጥ በነፃና ያለአድልዎ እንዲቀሳቀስ በማድረግ ጉዳይ ላይ የሚነሱ በርካታ የተሳሳቱ አመለካከቶች አሉ፡፡ ብሄሩ ምንም ይሁን ምን ማንኛውም ባለሃብት በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት መብቱ በእኩልነት ይረጋገጥ ከተባለ በልማት ወደኋላ የቀሩ ብሄር/ብሄረሰቦች የራሳቸው ጠንካራ ባለሃብት ስለሌላቸው ይደፈቃሉ፣ ጠንካራ የግል ባለሃብት የመፍጠር ዕድላቸው ይቀጭጫል፣ በሚል መልክ የሚቀርብ አስተያየት አንዱ የተሳሳተ አስተያየት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህን የመሰለ አስተሳሰብ ያላቸው ክፍሎች ብሄር/ብሄረሰቦች የኛ ለሚሏቸው ባለሀብቶች ልዩ ዕድል ሰጥተው ልዩ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፣ ሁሉንም ባለሃብት እኩል ማስተናገድ የለባቸውም ይላሉ፡፡

የህገ-መንግስታችን መሰረታዊ መነሻ የህዝቦችን፣ የሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች ህዝቦችን ጥቅም ማስጠበቅ ነው:: በየትኛውም አካባቢ ያለ ህዝብ በአካባቢው የልማታዊ ባለሃብት እንቅስቀሴ ሲኖር ይጠቀማል:: በልማት ስራው ምክንያት የስራ ዕድል ያገኛል:: በአካባቢው በሚፈጠር ተጨማሪ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ተጨማሪ የገበያ ዕድል ያገኛል:: ህዝቡ እነዚህን ጥቅሞች ሊያገኝ የሚችለው በገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት የሚያመርት ባለሃብት እስከተሰማራ ድረስ ነው:: እንደዚህ አይነቱ ባለሃብት በአካባቢው ከተሰማሩ ባለሃብቱ የየትኛውም ብሄር/ብሄረሰብ ቢሆን ህዝቡ ጥቅሞችን ያገኛል:: እንደዚህ አይነቱ ባለሀብት በሌለበት ይልቁንም በልማት ስራ ላይ ፋይዳ ያለው ሚና የሌለውና በአቋራጭ ለመክበር የሚጥር ባለሀብት በሚርመሰመስበት ሁኔታ ህዝቡ ጥቅሞቹን ሊያገኝ አይችልም::

የህዝቡን ጥቅምና የአካባቢውን ልማት ከማረጋገጥ አኳያ ሲታይ ወሳኙ ነገር የባለሃብቱ ብሄር/ብሄረሰባዊ ምንጭ አይደለም:: ዋናው ነገር በልማት ላይ የሚሳተፍ ባለሀብት መሆኑና እንደዚህ አይነቱ ባለሃብት በአካባቢው በሰፊው መሰማራቱ ነው:: የየትም ብሄር ጥገኛ ህዝቡን ያደኸያል እንጅ አካባቢውን አያለማም:: የየትኛውም ብሄር ልማታዊ ባለሀብት አካባቢውን ያለማል፣ ከዚህም ህዝቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ዕድል ይፈጥራል:: የህዝቡን ጥቅምና የአካባቢውን ልማት ለማረጋገጥ በአካባቢው መሰማራት የሚፈልገውን ልማታዊ ባለሃብት ሁሉ ብሄራዊ ገደብ ወይም ልዩነት ሳይደረግበት በሰፊው ማሳተፍ፣ ማበረታታት፣ በአካባቢው



ሊርመሰመስ የሚፈልገውን ጥገኛ ደግሞ ምንም አይነት የብሄር ልዩነት ሳይደረግበት መግታትና ማክሰም ያስፈልጋል:: ልዩነት የሚያስፈልገው በብሄር/ብሄረሰብ ሳይሆን በልማታዊ ባለሃብትና/በጥገኛ መካከል ብቻ ነው::

የአካባቢው ተወላጅ የሆነ ባለሃብትም እንደሌላው ባለሃብት ሁሉ መደገፍና መበረታታት አለበት:: የአካባቢው ባለሃብት ልማታዊ ባለሃብት እስከሆነ ድረስ የተሟላ ድጋፍና እገዛ ያገኛል:: መንግስት ሊሰጥ የሚችለውን ድጋፍና ማበረታቻ ሁሉ ያለአድልዎ ስለሚሰጥ ተጠቃሚ ይሆናል፣ አካባቢውን ያለማል:: ጥገኛ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ፀረ-ልማት በመሆኑ የህዝቡን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል መገታት ይኖርበታል:: የአካባቢው ባለሀብትና በልዩ ሁኔታ ለመጠቀም ተብሎ በገበያ ተወዳዳሪ መሆን የማይችሉትን በመንግስትና ህዝብ ወጭ መደገፍ ማለት ህዝቡን አስርቦ ጥገኞችን መቀለብ ማለት ስለሆነ የሚደገፍ አይደለም:: በገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉት ደግሞ የመወዳደር አቅሙ አላቸውና የሚያስፈልጋቸው ነገር ልዩነት ሳይሆን እኩልነት ነው:: ለሁሉም እኩል ድጋፍና ዕድል ተሰጥቶ በገበያ ተወዳድሮ ያሸነፈው ያሸንፋል:: በገበያ ተወዳድሮ የሚያሸንፍ ግን አካባቢውን ለማልማት ይሁን ህዝቡን ለመጥቀም የማይችል ስለሆነ ልዩ ድጋፍ ቢደረግለትም ህዝቡን ከማቆርቆዝ አልፎ የሚያስገኘው ጥቅም የለም:: ስለሆነም ለብሄሬ ባለሀብት ልዩ ጥቅምና ድጋፍ መስጠት የሚል አባባል የአካባቢውን ልማታዊ ባለሀብቶች ለማጠናከር ምንም ፋይዳ የሌለው፣ ጥገኞችን

በማበራከት የአካባቢውን ልማትና የህዝቡን ተጠቃሚነት የሚጎዳ የጥገኝነት አመለካከት ከመሆን የማይዘል ጉዳይ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በአንድ አካባቢ አስር ወይም መቶ ልማታዊ ባለሀብቶች በሚሰማሩበት ጊዜ ለሌሎች ልማታዊ ባለሃብቶች ዕድሉ የተዘጋ ኊቦታው፡ የተያዘ ይመስላቸዋል። ይህ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ባህሪን በሚገባ ባለመገንዘብ የሚመጣ ችግር ነው። በአለም ውስጥ እጅግ የዳበረ ኢኮኖሚ ያላትን በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ከሚልዮን ዶላር በላይ ካፒታል ያላቸው ባለሃብቶች በላይ በላዩ የተነባበሩባት አገር አሜሪካ ነች። ይህም ሆኖ ከመላው አለም የውጭ ባለሃብት ወደአሜሪካ በሰፊው ይጎርፋል። በአለም የውጭ ኢንቬስትመንትን በመሳብና ወደአገርዋ በማስገባት ከአሜሪካ ጋር የሚወዳደር ማንም አገር የለም። ሳለው ይጨመርለታል እንዲሉ የራስዋ ባለሃብቶች በላይ በላይ በተነባበሩባት አገር ከመላው አለምም ተጨማሪ ቢልዮኖችን በኢንቨስትመንት መልክ ታስገባለች።

ይህ ክስተት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ በርግጥም ሳለው የሚጨምር በመሆኑ የሚመጣ እንጂ በአጋጣሚ የሆነ ጉዳይ አይደለም። የግል ባለሃብቶች ልማታዊ እንቅስቃሴ በሚበራከትበት ወቅት፣ ከጥገኛነት ነፃ በሆነና በገበያ ውድድር በሚመራበት ወቅት ለሌሎች ባለሃብቶች ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ዕድል ይከፍታል። በገበያ ውድድር መርህ የሚሰሩ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ባለሚሊዮኖች በአሜሪካ በመኖራቸው በመላው አለም ያሉ ባለሀብቶች ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድል ስለፈጠረላቸው እየጎረፉ ነው። በኛ አገር ሁኔታ ችግራችን የኢንቨስተሮች አለመኖር እንጂ የስራ ዕድል መጣበብ ወይም ኊየቦታ መያዝ፡ አይደለም። እንኳንስና እኛ አሜሪካኖችም በላይ በላዩ ላይ የተነባበረ የግል ባለሃብት ተከማችቶ የስራ ዕድል መጣበብ ሳይሆን ቀጣይ የልማት ዕድልን ነው ያገኙት። የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ አንድ ተሰርቶ ያለቀለት ዳቦን እንደመጋራት መወሰድ የለበትም። ተሰርቶ ያለቀለት ዳቦ ሲሆን አንዱ ግማሹን ከወሰደ ለሌላው የሚቀረው ግማሽ ዳቦ ብቻ ነው። በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ልማታዊ ባለሀብት በስራ ላይ በሚሰማራበት ወቅት የነበረውን ዳቦ የሚጋራ ሳይሆን አዲስ ሃብት ነው የሚፈጥረው። ሊፈጠር የሚችለው ሃብት ገደብ ያለው አይደለም። ለዚህ ነው ስርአቱ ሳለው የሚጨምረው። በመሆኑም በአንድ አካባቢ ልማታዊ ባለሃብቶች በሰፊው ሲሰማሩ ለአካባቢው ልማታዊ ባለሀብቶች መጠናከር ዕድል ከመፍጠር በስተቀር በባለ ሃብቶቹ ላይ የሚያስከትለው ምንም ጉዳት የለም።

በየአካባቢው ልማታዊ የግል ባለሃብቶች ብሄራቸው ምንም ይሁን ምን በሰፊው እንዲሰማሩና ሁሉም በእኩልነት እንዲደገፉ ማድረግ በቅድሚያ ለአካባቢው ህዝብ ከዚያም ቀጥሎ ለአካባቢው ባለሃብቶች የሚጠቅም በመሆኑ በጥብቅ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል። በዚህ መርህ የሚጎዱ ሰዎች የሉም ማለት ግን አይደለም። በገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርትና ሸቀጥ ማምረት የማይችሉ የብሄር ታርጋቸውን ለጥፈው በህዝቡ ጫንቃ ላይ

ሆነው ለመክበር የሚፈልጉ ጥገኞች በዚህ ሂደት እንደሚከስሙ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በመሆኑም በአገራችን ነፃ የካፒታል ዝውውር እንዳይኖር፣ የብሄራቸውን ህዝብ ስም በመጠቀም አጥር አበጅተው በጥገኝነት ለመመዝበር መራወጣቸው አልቀረም፡፡ በህዝቦች መካከል አጥር ማበጀት፣ ቁርሾ እንዲፈጠር መጣር ከጥገኛ አመለካከታቸውና ጥቅማቸው የሚመነጭ ነው፡፡ ጠባብነትና ትምክህተኝነት ዋነኛ መነሻቸው ጥገኝነት ነው የምንለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ዋናዎቹ የጠባብነትና የትምክህተኝነት አቀንቀኞች በገበያ በነፃ ተወዳድረው መክበር የማይችሉ ጥገኛ ባለሃብቶች በሙያቸውና በስራ ትጋታቸው ተማምነው ከመጠቀም ይልቅ ከዚህ ውጭ ለመጠቀም የሚሹ ጥገኝነት የተጠናወታቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም በአገራችን ልማትን በማፋጠን፣ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ፈጥሮ ህዝቡና ልማታዊ ባለሃብቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ህገ-መንግስቱ በሚደነግገው መሰረት ካፒታል በአገራችን በነፃ እንዲንቀሳቀስና በእኩልነት እንዲስተናገድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ በማድረግ ህዝቡ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ አመለካከት እንዲይዝ መጣር፣ ጠባብነትና ትምክህተኝነትን ምንጩ ከሆነው ጥገኛነት ጋር አያይዞ መታገል ያስፈልጋል፡፡

## 4.3. የጉልበት ነፃ ዝውውርና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማ፣

ህገ-መንግስቱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም



የአገሪቱ አካባቢ ተዘዋውሮ ስራ የመስራት መብት እንዳለው በማያሻማ አኳኋን ግልፅ አድርጓል፡፡ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ ተዋናይ የሆኑት ካፒታልና የሰው ጉልበት እንዲሁም ሸቀጦችና አገልግሎቶች በነፃ የሚዘዋወሩበት ሁኔታ በሌለበት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ብሎ ነገር ሊታሰብ አይችልም፡፡ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር አላማችንን ለማሳካት የጉልበት ነፃ ዝውውርን መፍቀድ ይኖርብናል፡፡

የአገራችን አካባቢዎች ሁሉ ማስመዝገብ የሚችሉትን የላቀ ልማት እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ ዋነኛው ሃይላችን የህዝቡ ጉልበት ነው፡፡ ህዝቡ በየአካባቢው በልማት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ማድረግ ይኖብርናል፡፡ ዋነኛው አቅጣጫችንም ህዝቡ በየአካባቢው በልማት ስራ ላይ ተሳትፎ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይሁንና በተለያዩ አጋጣሚዎች በአንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ የሙያተኛ ወይም የሰራተኛ ጉልበት እጥረት፣ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ትርፍ ወይም ሻል ባለ መጠን የሚገኝ ሙያተኛና ሰራተኛ ጉልበት መኖሩ የማይቀር ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት እጥረት በታየበት አካባቢ ፈጣን ልማት ሊመጣና ህዝቡ ሊጠቀም የሚችለው በቂ የሰው ሃይል ካለበት እጥረት ወዳለበት የሰው ጉልበት በነፃ እንዲዘዋወር ሲደረግ ነው፡፡ በሙያተኛ ወይም በሰራተኛ ጉልበት እጥረት በሚገባ ሳይሰራ ሊቀር ይችል የነበረው የልማት ስራ ተከናውኖ አካባቢውም አገሪቱም ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡ ትርፍ ጉልበት ያለበት አካባቢም በሚገባ ሳይሰራ ሊቀር ይችል የነበረው

የሰው ሃይል በሙሉ አቅሙ ወደሚሰራበት አካባቢ በመዞሩ ተጠቃሚ ይሆናል:: ሁሉንም አካባቢዎችና አገሪቱን በአጠቃላይ የሚጠቅም ርምጃ ይሆናል::

ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ወገኖች ከሌላ አካባቢ የሚመጣውን ሙያተኛና ሰራተኛ ጉልበት አካባቢውን በማልማት የአካባቢውንም ህዝብ እንደሚጠቅም የልማት አቅም ሳይሆን ስራን እንደሚሻማ ቀበኛ አድርገው በማየት የጉልበት ነፃ ዝውውር በብሄር/ብሄረሰብ አጥር መገታት አለበት ይላሉ:: በልማታዊ አስተዋፅኦው የሚተማመን ባለሃብት፣ በሙያውና በስራ ትጋቱ የሚተማመን ዜጋ ሁሉም ዜጎች በእኩልነት በሚስተናገዱበት ሁኔታ የካፒታልና የጉልበት ነፃ ዝውውር መኖር እንደሚጠቅማቸው፣ አካባቢያቸውም እንደሚለማ ስለሚያውቁ ይህንን ነፃ እንቅስቃሴ የሚገድብና በብሄር/ብሄረሰቦች መካከል መነጣጠልና ቁርሾን የሚፈጥር ነገር አይቀበሉም:: የሚጠይቁት ሁሉም ያለአድልዎ በእኩልነት እንዲስተናገዱ ነው:: በጥገኝነት ለመክበር የሚፈልጉት፣ በሙያቸውና በስራ ታታሪነታቸው ለመጠቀም ዝግጁ ያልሆኑት ግን ብሄር/ብሄረሰባቸውን ከሌላው ነጥለው በጫንቃው ላይ ለመኖርና ለመጠቀም ስለሚፈልጉ የሚመኙት እኩልነት የተረጋገጠበት ነፃ የጉልበት ዝውውር አይደለም:: የሚፈልጉት መነጣጠልና አድልዎን ነው:: ለጥገኛ ጥቅማቸው ሲሉ አድልዎንና ህዝቦችን በተለያዩ አጥሮች መበጣጠሳቸውን ይመኛሉ::



በአጠቃላይም ህገ-መንግስታችን የብሄር/ብሄረሰቦች መብት ተከብሮ፣ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስቀመጠው አቅጣጫ በአገራችን ብቸኛ የሰላም ዋስትና ነው:: የፈነጠቀው የዴሞክራሲ ጮራ ደምቆ እንዲያበራና ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሚያስችል ብቸኛ አቅጣጫ ነው:: የህዝቦችን አስተማማኝ አንድነት ሊፈጥር የሚችል ትክክለኛ አቅጣጫ ነው:: ህዝቦች በጋራና በተናጠል በይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ፈጣን ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ትክክለኛ የመፍትሄ አቅጣጫ ነው:: ይሁንና ይህም በትግል ካልሆነ በስተቀር እጅና እግርን አጣጥፎ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል ነገር አይደለም::

ይህንኑ የህልውናችን፣ የዴሞክራሲያችንና የልማታችን ብቸኛ ማረጋገጫ የሆነውን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ ሁለት የተሳሰሩ ስራዎች መሰራት ይኖርባቸዋል:: በመጀመሪያ ደረጃ ስለአቅጣጫው ምንነትና ይዘት ህብረተሰቡና አስፈፃሚ አካላት የተሟላና ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መደረግ ይኖርበታል:: አቅጣጫውን በትክክልና በጥልቀት ባለመገንዘብ የሚሰሩ የተሳሳቱ ስራዎች ወይም መሰራት ሲገባቸው ሳይሰሩ የሚቀሩ ስራዎች አላማውን በከፍተኛ ደረጃ ሊያሰናክሉ ይችላሉ:: ይህንኑ ተገንዝቦ በጉዳዩ ላይ የጠራ የጋራ እምነትና አመለካከት እንዲኖር፣ በዚህ ላይ ተመስርቶም ድንጋጌዎቹ በትክክልና በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆኑ መረባረብ ያስፈልጋል:: ይህ ፅሁፍ ይህንኑ ለማድረግ አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል::

በሌላ በኩል ደግሞ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚፈታተኑ የጠባብነትና የትምክህተኛነት አመለካከቶች ካልተወገዱ በስተቀር በጉዳዩ ላይ ህብረተሰቡ አንድ ጠንካራ የጋራ አመለካከትና እምነት መያዝ አይችልም፡፡ የጠባብነትና የትምክህተኝነት አመለካከቶችን ከግንዛቤ እጥረት በመነሳት የሚይዛቸው ሰው በርካታ ቢሆንም የሃሳቦቹ ዋነኛ አቀንቃኞችና ከዚሁ ተጠቃሚ የሚሆኑት ጥገኞችና በጥገኝነት መንገድ ለመጠቀም የሚሹ ወገኖች ናቸው፡፡ በመሆኑም ጠባብነትና ትምክህተኝነት ፀረ-ዴሞክራሲ፣ ፀረ-ህዝባዊ አንድነት ብቻ ሳይሆን ፀረ-ልማትም ጭምር ናቸው፡፡ ጠባብነትንና ትምክህተኝነትን በአመለካከት ደረጃ መታገሉ ያለማሰለስ መከናወን ያለበት ቢሆንም ከስረ መሰረታቸው የሚደርቁት ይህ ትግል ጥገኝነትን ከማክሰም ትግል ጋር ተያይዞ ሲፈፀም ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል ህብረተሰቡ ትክክለኛ አመለካከቱን እንዲጨብጠው ለማድረግ ሰፊ የማብራሪያ ስራ መስራት በዚሁ ላይ ተመስርቶ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ ጠባብነትና ትምክህተኝነት በአመለካከት ደረጃ ያለማሰለስ መታገል፣ ጥገኝነትን በማክሰም አስተሳሰቦቹን ከምንጫቸው ማድረቅ ያስፈልጋል፡፡